አርነት መውጣት

ጽሑፍ፡ - በዋረን ደብልዩ ዊርዝቢ

ትርጉም፡ - ጌቱ ግዛው

እርማት፡ - ፈቃዱ ገብሬ እና ተስፋዬ መስፍን

Copyright ©1996 by SIM, Addis Ababa, Ethiopia: originally published in English under the title of BE FREE, copyright © 1975 by SP Publications, Inc., Wheaton, Illinois, U.S.A. All rights reserved.

ማውጫ

መግቢያ ገጽ

ክፍል 1 በግል ሕይወት ልምምድ ላይ የተሰጠ ገለጻ ክፍል፡-
ጸጋና ወንጌል 1

1. በየምሥራቹ ቃል ላይ የተንዙ የሐሰት
ወሬዎች 2

2. ነፃ ሆኖ መወለድ 16

3. የነፃነት ተጋዳይ፥ ክፍል 1 27

4. የነፃነት ተጋዳይ፥ ክፍል 2 38

ክፍል 2 የመሠረታዊ እምነት ትምህርት ገለጻ ክፍል፡-
ጸጋና ሕግ 48

5. አዚም የተደረገባቸውና የደነዘዙ 49

6. የሕግ የማስተዋል ጥበብ 61

7. ለማደግ ጊዜው አሁን ነው! 73

8. ወላጅ እናትህን አግኝ 84

ክፍል 3 የተግባራዊ ኑሮ ገለጻ ክፍል፡- ጸጋና የክርስቲያን ሕይወት
. 95

9. ቁም! ሌባ! 96

10. አምስተኛው ነፃነት 108

11. የፍቅር ነፃነት 121

12. የነፃነት መለያዎች 132

መግቢያ

የገላትያ መልእክት መግቢያ አደገኛ መጽሐፍ ነው።

ይህ መጽሐፍ በዘመናችን ባሉት አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ እውነተኛውን መንፈሳዊ ሕይወት በመተካት ላይ የሚገኘውን የሕግ አክራሪነት ዝንባሌ የሚያጋልጥ ነው። «በሐሰተኛ ትምህርቶች መካከል ያለ» ከማለት ይልቅ «በአብያተ ክርስቲያናት ዘንድ» ውስጥ ያልኩበት ዋናው ምክንያት በዚህ ዘመን ሕግ አክራሪነት የበለጠ የሰፈነው በቤተክርስቲያን ውስጥ ስለሆነ ነው።

በሚሊየን የሚቆጠሩ አማኞች አንዳንድ ድርጊቶችን ከመፈጸም በመቆጠባቸው ወይም አንድ የሃይማኖት መሪ በመከተላቸው ወይም የአንድ ቡድን አባል በመሆናቸው ብቻ «መንፈሳዊ» እንደሆኑ ያስባሉ። ዳሩ ግን ይህ ስሕተት መሆኑንና ወደ ትክክለኛው ሕይወት መምጣት የምንችለው ራሳችንን መንፈስ ቅዱስ እንዲቆጣጠረን በፈቀድንለት መጠን መሆኑን ጌታ በገላትያ መልእክት ውስጥ በግልፅ አሳይቶናል።

መንፈስ ቅዱስ የበላይ ተቆጣጣሪ ሲሆን ባርነት ሳይሆን አርነት፥ ውድድር ሳይሆን ትብብር፥ ሰውን ማሞካሸትና ማመስገን ሳይሆን እግዚአብሔርን ማክበር ይሰፍናል። ዓለም እውነተኛውን የክርስትና ሕይወት ታያለች፤ ኃጢአተኞችም አዳኙን ወደ ማወቅ ይደርሳሉ። መንፈሳዊ እንቅስቃሴ (ሪቫይቫል) የሚለው ቃል ከጥንት ጀምሮ እንደዚህ ዓይነቱን ተግባር ለመግለጥ የተሰጠ ስያሜ ነው።

የገላትያን መልእክት ለብዙ ወራት በማጥናቴ በአንድ በኩል ትሑት (መንፈሰ ሰባራ) ሲያደርገኝ በሌላ በኩል ግን ለለውጥ የምጥር ሆኛለሁ። ይኸውም የቱንም ያህል በአገልግሎታችን ሌሎችን ሰዎች ለመማረክ የቻልን ብንሆንም፥ እግዚአብሔር ግን በዚህ አገልግሎታችን በተመሳሳይ ሁኔታ አለመርካቱን መረዳቴ ትሑት አድርጎኛል። ለለውጥ ለመታገል መነሣሣቴ ደግሞ በቅድሚያ እኔው ራሴ መንፈሳዊ ጥልቀት ያለውን ሕይወት መኖር እንደሚገባኝ በመገንዘቤና ብሎም መንፈሳዊ ጥልቀት ያለውን አገልግሎት መስጠት እንዳለብኝ በመረዳቴ ነው። ሕይወቴ ወይም አገልግሎቴ ከጊዜው ሁኔታ ጋር የሚስማማ ቢሆንም ባይሆንም መንፈስ ቅዱስ በራሱ መንገድ በሕይወቴ እንዲሠራ ደፍሬ መጋበዝ ያስፈልገኛል።

የገላትያ መልእክት አደገኛ መጽሐፍ ነው ያልኩት ለዚህ ነው። ለጳውሎስ ይህን መልእክት መጻፉ አደገኛ ነበር። ለገላትያም ሰዎች መልእክቱን ማንበብ አደገኛ ነበር። ምናልባትም የእኔም ይህን የገላትያ መልእክት ጥናት መጻፍ አደገኛ ሊሆን ይችላል። (ከወዳጆቼ አንዳንዶቹ ሊርቁኝ፥ በአንዳንድ ስፍራ እንድሰብክ ይቀርብልኝ የነበረውን ጥሪ ላጣ እችል ይሆናል።) ምንም ይምጣ ምንም የእኔ ጸሎት በክርስቶስ ውስጥ ያለንን ነጻነት በማወቅና በደስታ በመለማመድ የክርስቶስ ሞት ለሕይወታችን ዋጋ የሌለው ከንቱ ነገር አለመሆኑን እንድንመሰክር ነው። «እንግዲህ ልጁ አርነት ቢያወጣችሁ በእውነት አርነት ትወጣላችሁ» (ዮሐንስ 8፡36)።

ወዳጄ ሆይ፥ አርነት ውጣ!

ዋርን ደብልዩ ዊርዝቢ

ክፍል 1

በግል ሕይወት ልምምድ ላይ የተሰጠ ገለጻ ክፍል፡-

ጸጋና ወንጌል

ምዕራፍ 1-2

ገላትያ 1፡1-10

በኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታንም ባነሣው በእግዚአብሔር አብ ሐዋርያ የሆነ እንጂ ከሰዎች ወይም በሰው ያልሆነ ጳውሎስ ከእኔም ጋር ያሉት ወንድሞች ሁሉ፥ ወደ ገላትያ አብያተ ክርስቲያናት፤

ከእግዚአብሔር ከአባታችን ከጌታችንም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን። ክፉ ከሆነ ከአሁኑ ዓለም ያድነን ዘንድ እንደ አምላካችንና እንደ አባታችን ፈቃድ ስለ ኃጢአታችን ራሱን ሰጠ። ለአብ ከዘላለም እስከ ዘላለም ክብር ይሁን አሜን።

በክርስቶስ ጸጋ እናንተን ከጠራችሁ ከእርሱ ወደ ልዩ ወንጌል እንዲህ ፈጥናችሁ እንዴት እንዳለፋችሁ እደነቃለሁ፤ እርሱ ግን ሌላ ወንጌል አይደለም፤ የሚያናውጧችሁ የክርስቶስንም ወንጌል ሊያጣምሙ የሚወዱ አንዳንዶች አሉ እንጂ። ነገር ግን እኛ ብንሆን ወይም ከሰማይ መልአክ፥ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌል ቢሰብክላችሁ፥ የተረገመ ይሁን። አስቀድመን እንዳልን እንዲሁ አሁን ሁለተኛ እላለሁ፥ ከተቀበላችሁት የተለየውን ማንም ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን።

ሰውን ወይስ እግዚአብሔርን አሁን እሺ አሰኛለሁን? ወይም ሰውን ደስ ላሰኝ እፈልጋለሁን? አሁን ሰውን ደስ ባሰኝ የክርስቶስ ባሪያ ባልሆንሁም።

-1-

በየምሥራቹ ቃል ላይ የተነዙ የሐሰት ወሬዎች

በቤቴ በራፍ የቆመ የሚኖር አንድ ጉብል እጅግ አሳማኝ በሆነ አቀራረብ በየሳምንቱ ለሚወጣ አንድ ጋዜጣ የገንዘ ደንበኛ ሊያደርገኝ ብዙ ይጥር ነበር። «ብዙ ገንዘብ ማውጣት አይኖርብህም፤ በሳምንት ከ25 ሳንቲም የማይበልጥ ገንዘብ ነው የሚያስከፍለው፤ በጣም ደስ የሚለው ነገር ደግሞ ጋዜጣችን ደግ ደጉን ነገር ብቻ ነው የሚያወጣው» በማለት ብዙ ጎተጎተኝ።

በመከራ በተሞላው በዚህ ዓለም ውስጥ ማንኛውንም ዓይነት «መልካም ዜና» መስማት የሚናፍቅ እየሆነ መጥቷል። ስለዚህም ከላይ የተጠቀሰውን ጋዜጣ መግዛት ወጪውን የሚያካክስ ሊሆን ይችላል። ክርስቶስን የግል አዳኙ አድርጎ ለተቀበለ ሰው እውነተኛው «የምሥራች ቃል» ወንጌል ነው። «መጽሐፍ እንደሚል ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ሞተ፥ ተቀበረም፥ በሦስተኛው ቀን ተነሣ» (1ኛ ቆሮ. 15፡3-4)። ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ በፈጸመው ተግባር ምክንያት ኃጢአተኞች ይቅርታን ሊያገኙና ወደ መንግሥተ ሰማያት ሊሄዱ ይችላሉ። ይህም በክርስቶስ በማመን ስለሚገኘው ደህንነት የሚያበስረው ዜና በዓለም ላይ ከሁሉም የላቀና እጅግ አስፈላጊ የምሥራች ነው።

የጳውሎስንና በእርሱም በኩል ደግሞ የሌሎችን ሕይወት ለመለወጥ ያስቻለው መልእክት ይህ ነው። ስለዚህ በዚህ መልእክት ላይ ጥቃት በተከፈተ ጊዜ ጳውሎስ የወንጌልን እውነት ሊከላከል ተነሣ። አንዳንድ ሐሰተኛ አስተማሪዎች ጳውሎስ ወደ ቆረቆረው የገላትያ ቤተ ክርስቲያናት በመግባት እርሱ ካስተማረው የተለየ መልእክትን እያስተማሩ ነበር።

ጳውሎስ ለገላትያ ክርስቲያኖች የጻፈውን መልእክት ማንበብ ስትጀምር በሌሎች መልእክቶቹ እንደሚያደርገው ሁሉ እግዚአብሔርን በማመስገንና ለቅዱሳን ጸሎት በማድረግ ስለማይጀምር እንግዳ ነገር እንደ ገጠመው ትገምት ይሆናል። ጳውሎስ ለወንጌል እውነትና ለክርስትና ሕይወት ነጻነት ለመዋጋት ተዘጋጅቶ ስለነበር ለሌላ ጉዳይ ጊዜ አልነበረውም። ሐሰተኛ አስተማሪዎች የሕግና የጸጋ ድብልቅ የሆነ ሐሰተኛ «ወንጌል» እያስፋፉ ስለነበር በዝምታ የሚያልፈው ጉዳይ አልነበረም።

ጳውሎስ የወንጌልን እውነት ለገላትያ ክርስቲያኖች ለማስተማር ያደረገው አቀራረብ እንዴት ነበር? ሐዋርያው ይህንን ፍልሚያ ለመፋለም የመንደርደሪያ ንግግሩን ባደረገበት በእነዚህ የመክፈቻ ጥቅሶች ሦስት ግልጽ እርምጃዎችን ወስዷል።

1. ስለ ሥልጣኑ ማብራሪያ ይሰጣል (1፡1-5)

ጳውሎስ በመልእክቱ የኋለኛ ክፍል የፍቅሩና የርህራሄው መሠረት ስለሆኑት ጉዳዮች ለገላትያ ክርስቲያኖች ይነግራቸዋል (4፡12-20)። በመጀመሪያ ግን ከጌታ ስለ ተሰጠው ሥልጣን እንዲያውቁ ሊገልጥላቸው ይፈልጋል።

ሦስት የሥልጣን ምንጮች ነበሩት፡-

አገልግሎቱ (1፡1-2)። «ሐዋርያ የሆነ...ጳውሎስ»። በቤተክርስቲያን ታሪክ የመጀመሪያዎቹ ጊዜያት እግዚአብሔር አንዳንድ የተለያዩ ሰዎችን ለልዩ ተግባራት ይጠራ ነበር። ከእነዚህ መካከል ሐዋርያት ይገኙበታል። የቃሉ ትርጉም «አንድን ተግባር ለመፈጸም ከሥልጣን ጋር የተላከ» ማለት ነው። ኢየሱስ በምድር ላይ ባገለገለባቸው ዓመታት በርካታ ደቀ መዛሙርት («ተማሪዎች») ነበሩት። ከእነዚህ መካከል 12 ሐዋርያትን መርጦ ነበር (ማር.3፡13-19)። ኋላም ሐዋርያ የመሆን አንዱ መመዘኛ የትንሣኤው ምስክር ሆኖ መገኘት ነበር (የሐዋ.1፡21-22፤ 2፡32፤ 3፡15)። ጳውሎስ በክርስቶስ ምድራዊ አገልግሎት ወቅት ደቀ መዝሙር ወይም ሐዋርያ እንዳልነበር እርግጥ ነው። ነገር ግን ከሞት የተነሣውን ጌታን አይቷል፤ ተልዕኮውንም ከእርሱ ተቀብሏል (የሐዋ. 9፡1-18፤ 1ኛ ቆሮ. 9፡1)።

በተአምራዊ መንገድ የተፈጸመው የጳውሎስ መለወጥና ለሐዋርያነት መጠራት አንዳንድ ችግሮችን ፈጥሮ ነበር። በቅድሚያ ከመጀመሪያዎቹ ሐዋርያት መካከል አልነበረም። በዚህ ምክንያት እውነተኛ ሐዋርያ አይደለም በማለት ጠላቶቹ ይናገሩ ነበር። ጳውሎስ ግን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ መጀመሪያዎቹ አሥራ ሁለት ሐዋርያት ሁሉ እርሱንም ሐዋርያ እንዳደረገው በጥንቃቄ ይገልጻል። ሐዋርያነቱ በመለኮታዊ ሹመት እንጂ በሰዎች ምርጫ ወይም ማረጋገጫ አልነበረም። ስለዚህ በገላትያ አብያተ ክርስቲያናት ለተፈጠረው ችግር የመፍትሔ ሃሳብ ለማቅረብ ሥልጣን ነበረው።

ጳውሎስ ለሥልጣኑ መሠረት የሆነ ሁለተኛ ምክንያት ነበረው። በገላትያ የነበሩ አብያተ ክርስቲያናትን የመሠረተው እርሱ ነበር። መልእክቱን የሚጽፍላቸው ከመጀመሪያው የሕይወትን መልእክት እንዳመጣላቸው ሰው ሆኖ እንጂ እንደማይታወቅ እንግዳ ሰው አልነበረም። ይህ መልእክት ጳውሎስ ለእነዚህ አማኞች የነበረውን ፍቅር ይገልጣል (4፡12-19 ተመልከት)። ይሁን እንጂ ላቀረበላቸው ፍቅር ተገቢውን ምላሽ አላገኘም።

የገላትያ አብያተ ክርስቲያናትን ማን እንደ መሠረታቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች በጥንቃቄ ሲያጠኑትና ሲመረምሩት የነበረ ጉዳይ ነው። ገላትያ የሚለው ቃል ራሱ ለዚህ ችግር አስተዋፅዖ አለው። ክርስቶስ ከመወለዱ ከበርካታ መቶ ዓመታት በፊት ጨካኝና ኃይለኛ የነበሩት የጎል ነገዶች ዛሬ የፈረንሳይ ምድር እየተባለ ከሚጠራው ስፍራ ተሰደው ወደ ትንሿ እስያ በመምጣት ገላትያን መሠረቱ። ስለዚህ የቃሉ ትርጉም «የጎሎች አገር» ማለት ነው። ሮማውያን የጥንቱን ዓለም እንደገና በሚያደራጁበት ወቅት ገላትያን አንድ ትልቅ ክፍለ አገር በማድረግና ሌሎች በርካታ ክፍሎችን በመጨመር ክፍለ አገሩን በአጠቃላይ ገላትያ ብለው ጠሩት። ጳውሎስ ወደ ነበረበት ጊዜ ስንመለስ፥ አንድ ሰው ስለ ገላትያ ሲናገር ትንሿን የገላትያ አገር ማለቱን ይሆን ወይም ትልቁን የሮም ክፍለ ሃገር እርግጠኛ መሆን አንችልም።

ጳውሎስ መልእክቱን የጻፈው ገላትያ ለተባለችው ትንሿ አገር ወይም ገላትያ ለተባለው የሮም ክፍለ አገር የመሆኑ ጉዳይ ላይ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን በሐሳብ ይለያያሉ። የመጀመሪያውን አመለካከት «የሰሜን ገላትያ ንድፈ አሳብ» ሲባል የኋለኛው ደግሞ «የደቡብ ገላትያ ንድፈ አሳብ» ይባላል። በእነዚህ ሁለት የተለያዩ አመለካከቶች ላይ ወደ ስምምነት ባይደረስም ጳውሎስ መልእክቱን የጻፈው በመጀመሪያው ሐዋርያዊ ጉዞው ለመሠረታቸው በገላትያ ክፍለ አገር ደቡብ ክፍል ለሚገኙ ለአንጾኪያ፥ ለኢቆንዮን፥ ለልስጥራና ለደርቤ አብያተ ክርስቲያናት መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ (የሐዋ. 13-14)።

ጳውሎስ ወንጌልን አስተምሮአቸው የተለወጡ ሰዎችን ጉዳይ በፍቅር ይከታተል ነበር። የመሠረታቸው አብያተ ክርስቲያናት ክርስቶስን ሲያከብሩ የማየት ጥልቅ ፍላጎት ነበረው (የሐዋ. 15፡36፤ 2ኛ ቆሮ. 11፡28 ተመልከት)። ወደ ክርስቶስ የመራቸውን አማኞች ያለ አንዳች እንክብካቤ

ችላ ሊላቸው አልፈለገም። (እንደ ሞግዚት ያደርገው ለነበረው እንክብካቤ ምሳሌ ይሆን ዘንድ 1ኛ ተሰ. 2 አንብብ።)

ወንጌልን ያስተማራቸው ምዕመናን በሐሠት መምህራን ትምህርት መሳሳታቸው በጣም አሳስቦት ነበር። አዳዲስ አማኞች ለክርስቶስ እንዴት መኖር እንዳለባቸው የማስተማር ኃላፊነት እነርሱን ወደ ክርስቶስ ከማምጣት ተልዕኮ ተነጥሎ ሊታይ የማይገባው ጉዳይ ነው (ማቴ. 28፡19-20)። ብዙዎቹ የገላትያ ክርስቲያኖች በጌታ «መንፈሳዊ አባታቸው» ከነበረው ከጳውሎስ ሥር በማፈንገጥ የብሉይ ኪዳን ሕግን ከእግዚአብሔር ጸጋ ወንጌል ጋር በመቀየጥ የሚያስተምሩትን የሕግ መምህራንን መከተላቸው የሚያሳዝን ነው። (እነዚህ ሐሰተኛ መምህራን ክርስቲያኖችን በማታለል ወደ አይሁድ ሃይማኖት መንገድ ይመሩ ስለነበር «የይሁዲነት አቀንቃኞች» በማለት እንጠራቸዋለን።)

ስለዚህ ጳውሎስ የሐዋርያነትና በተለይ ደግሞ የገላትያ አብያተ ክርስቲያናት መሥራችነት አገልግሎት ነበረው። ስለዚህ በየአብያተ ክርስቲያናቱ ለነበሩ ችግሮች መፍትሔ የመስጠት ሥልጣን ነበረው። ከዚህም በተጨማሪ ለሥልጣኑ ምንጭ የሚሆነው ሌላ ሁለተኛ ምክንያት አለው።

ይህም ሁለተኛ ምክንያት መልእክቱ ነው (1፡3-4)። ገና ከመጀመሪያውኑ አንሥቶ ጳውሎስ የወንጌልን መልእክት እንደሚገባ ሲያብራራ እንመለከተዋለን። የይሁዲነት አቀንቃኞችም ሊለውጡት የሞከሩት ይህንኑ መልእክቱን ነበር። ለወንጌል ማዕከሉ፥ ሰው የሆነው የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ስብዕና ነው። ኢየሱስ ራሱን ለመስቀል ሞት አሳልፎ በመስጠት የኃጢአትን ዋጋ ከፈለ። (በገላትያ መልእክት ውስጥ መስቀሉ ዋና ነገር እንደሆነ ትገነዘባለህ (2፡19-21፤ 3፡1፥ 13፤ 4፡5፤ 5፡11፥ 24፤ 6፡12-14 ተመልከት)። ክርስቶስ ዋጋ የከፈለው አንድ ዓላማን ከግቡ ለማድረስ ነበር፤ ይህ ዓላማ ደግሞ ኃጢአተኞችን ከባርነት ነጻ ማውጣት ነው።

የገላትያ መልእክት በይዘቱ ደጋግሞ የሚያነሣው ርዕስ «በክርስቶስ የሚገኝ ነጻነት» የሚለውን ነው። (በ2፡4፤ 4፡3፥ 9፥ 24-25፤ 5፡1 ላይ «ባርነት» የሚለውን ቃል ተመልከት)። የይሁዲነት አቀንቃኞች ክርስቲያኖችን ከጸጋ ነጻነት ወደ ሕግ ባርነት ሊመሯቸው ፈልገው ነበር። ክርስቶስ የሞተው ሰዎችን ነፃ ለማውጣት ስለሆነ ባርነት የወንጌል መልእክት አካል እንዳልሆነ ጳውሎስ ያውቅ ነበር።

አገልግሎቱና መልእክቱ የመንፈሳዊ ሥልጣኑ ምንጮች ነበሩ። ከእነዚህ ሌላ ውስጣዊ አሳቡ (ዓላማው) የሥልጣኑ ምክንያት ነበር።

ውስጣዊ ዓላማው (1:5):- «ለአብ ከዘላለም እስከዘላለም ክብር ይሁን!» ሐሰተኛ መምህራን የሚያገለግሉት ለክርስቶስ ክብር ሳይሆን ለራሳቸው ክብር ነበር (6:12-14 ተመልከት)። እንደዛሬዎቹ ሐሰተኛ መምህራን የይሁዲነት አቀንቃኞችም ሰዎችን ለክርስቶስ የመማረክ ጉዳይ ጉዳያቸው አልነበረም። በዚህ ፈንታ ሌሎች ወደ ክርስቶስ ያመጧቸውን ሰዎች በመስረቅና የራሳቸው አባል በማድረግ ስለ አባላቶቻቸው ብዛት ይመካሉ። የጳውሎስ ውስጣዊ ዓላማ ግን ንጹህና ፈሪሃ እግዚአብሔር የሞላበት ነበር። ይህም ኢየሱስ ክርስቶስን ማክበር ነበር (1ኛ ቆሮ. 6:19-20፤ 10:31-33 ተመልከት)።

ጳውሎስ ስለመንፈሳዊ ሥልጣኑ እንደሚገባ ገለፃ ከሰጠ በኋላ ሌላም ገለፃ ስለሚያስፈልገው ለሁለተኛ ጉዳይ ሲዘጋጅ እንመለከተዋለን፤ ይህም የክርስቲያንን ነፃነት የሚመለከተው ነው።

2. የተሰማውን ሥጋትና ጭንቀት ገለጸ (1:6-7)

«...ወደ ልዩ ወንጌል እንዲህ ፈጥናችሁ እንዴት እንዳለፋችሁ እደነቃለሁ!» የገላትያ ሰዎች የእግዚአብሔርን ጸጋ ገሸሽ እያደረጉ መሄዳቸው ለጳውሎስ የመጀመሪያው ምክንያት ነበር። የእግዚአብሔርን ጸጋ እየተጋፉ ነበር። (ሙሉ በሙሉ ወደ ኋላ ባይመለሱም እንኳ በሂደት ላይ እንደሆኑ ከሁኔታው መረዳት ይቻላል።)

ጳውሎስ ብረቱን በግለቱ ይቀጠቅጠዋል። እነዚህን ሰዎች እግዚአብሔር በጸጋው ጠርቶ ከኃጢአታቸው አድኖአቸው ነበር። አሁን ግን ከጸጋ ወደ ሕግ መመለስ ጀመሩ። ነፃነትን ትተው ወደ ባርነት አመሩ። ይህንንም ያደረጉት «መንፈሳዊ አባታቸው» የሆነውን ጳውሎስን ሳያማክሩ ወይም መንፈስ ቅዱስ እንዲያስተምራቸው ጊዜ ሳይሰጡ ነበር። ትናንሽ ልጆች ከረሜላ ስለ ሰጣቸው ብቻ እንግዳን ሰው እንደሚከተሉ ሁሉ እነርሱም በይሁዲነት አቀንቃኞች ሃይማኖት የማይረባ ፍቅር ተዘናግተው ነበር።

«የእግዚአብሔር ጸጋ» የዚህ መልእክት መሠረታዊ ርዕስ አሳብ ነው (1:3፥ 6፥ 15፤ 2:9፥ 21፤ 5:4፤ 6:18)። ጸጋ የሚለውን ቃል ቀለል ባለ አማርኛ ብናስቀምጠው ለማይገባቸው ኃጢአተኞች የተሰጠ ነፃ የእግዚአብሔር ችሮታ ማለት ነው። «ጸጋ» ና «ስጦታ» የሚሉት ቃሎች

በአንድነት የሚሄዱ ናቸው፤ ምክንያቱም ደህንነት በጸጋው የሚገኝ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው (ኤፌሶን 2፡8-10)። የገላትያ አማኞች ያደረጉት ነገር ከነበሩበት ሃይማኖት ወደ ሌላ ሃይማኖት ወይም ከነበሩበት «ቤተ ክርስቲያን» ወደ ሌላ ቤተ ክርስቲያን መሄድ ብቻ አልነበረም፤ ነገር ግን ከእግዚአብሔር ጸጋ ውጭ መሆንንም የሚጨምር ነበር። የጸጋውን ባለቤት እግዚአብሔርን ጨርሰው መካዳቸው የነገሩን ክፋት አጉልቶ ያሳያል። የጠራቸውና ያዳናቸው እግዚአብሔር ነበር፤ አሁን ግን ባርነትን በሚያመጡ ሰብዓዊ መሪዎች አማካይነት እግዚአብሔርን ካዱት።

የክርስትና ሕይወት በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ከእግዚአብሔር ጋር የሚደረግ ሕያው ግንኙነት መሆኑን መዘንጋት የለብንም። አንድ ሰው ራሱን ለክርስቶስ በመስጠትና በእርሱ በመታመን እንጂ (ሮሜ 11፡6) ሥርዓትን በማሟላት ክርስቲያን አይሆንም። አንዱ ሌላውን የሚቃረን ስለሆነ ጸጋንና ሥራን መቀላቀል አይቻልም። ደህንነት በኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ የተገዛልን የእግዚአብሔር ጸጋ ስጦታ ነው። ከጸጋ ወደ ሕግ መመለስ ያዳነንን እግዚአብሔርን መካድ ማለት ነው።

የገላትያ ሰዎች ጳውሎስን ለታላቅ ጭንቀትና ሥጋት የዳረገ ሌላ ኃጢአትም ፈጽመው ተገኝተዋል። ይህም ደግሞ የእግዚአብሔርን ወንጌል ማጣመም ወይም ማዛባት ነበር። ምንም እንኳ የይሁዲነት አቀንቃኞች «ወንጌል» እንሰብካለን ቢሉም፥ በሰው መልካም ሥራና በሌላ በኩል ደግሞ በእግዚአብሔር ጸጋ ላይ የተመሠረተ ሁለት ዓይነት ወንጌል ሊኖር አይችልም። ጳውሎስ ሲጽፍ «የሚሰብኩት ሌላ ወንጌል አይደለም፤ በፍጽም ወንጌል ሊሆን የማይችል ከእውነተኛ ወንጌል ጨርሶ የተለየ መልእክት ነው» ይላል። እነዚህ ሰዎች የሚሰብኩት ወንጌል ከእውነተኛው የክርስቶስ ወንጌል የተለየ ባይሆንም፥ በአሁኑ ዘመን ያሉ መናፍቃን እንደሚያደርጉት ሁሉ የይሁዲነት አቀንቃኞችም «በኢየሱስ ክርስቶስ እናምናለን፤ ሆኖም እስካሁን ባመናችሁት ላይ የምንጨምረው ነገር አለን» ይሉ ነበር። ከእግዚአብሔር ጸጋ የተሻላ ነገር ያላቸው ይመስል ነበር የሚናገሩት!

በቁጥር 7ላይ «ማጣመም» ተብሎ የተተረጎመውን ቃል በአዲስ ኪዳን የምናገኘው ሦስት ጊዜ ብቻ ነው (የሐዋ. 2፡20፤ ያዕ. 4፡9፤ ገላ. 1፡7)። የቃሉ ትርጉም «መዞር» «ወደ ተቃራኒ ባሕርይ መለወጥ» ማለት ነው። ቃሉ «መቀልበስ» ተብሎ ሊተረጎምም ይችላል። በሌላ አባባል የይሁዲነት አቀንቃኞች ወንጌልን ቀልብሰው ወደ ሕግ አከራሪነት መልሰውት ነበር ማለት

ነው። ጳውሎስ በዚህ መልእክት የጎለኛው ክፍል ላይ ሕግ ለክርስቶስ መምጣት እንዴት ቅድመ ዝግጅት እንደ ነበር ይገልጻል። የይሁዲነት አቀንቃኞች ግን ከዚህ የተለየ ትርጉም ነበራቸው፤ በእነርሱ አመለካከት ሕግና ወንጌል በአንድነት የሚሄዱ ናቸው። «እንደ ሙሴ ሥርዓት ካልተገረዛችሁ ትድኑ ዘንድ አትችሉም» (የሐዋ. 15፡1) የሚል አቋም ነበራቸው።

ይህ «እምነትን መተውና እውነትን ማጣመም» በገላትያ ክርስቲያኖች ምን ውጤት አስከተለ? በእርግጥም አናውጦአቸው ወይም አውኮአቸው ነበር (ገላ. 1፡7)። ይህ ማናወጥ ወይም ማወክ የሚለው ቃል ግራ መጋባትንና እረፍት ማጣትን የሚያመለክት ነው። ይህ ቃል በሌሎች ስፍራዎች በተግባር ላይ የዋለበትን መንገድ ስትመለከት የቃሉን ጠንካራነት ትገነዘባለህ። ደቀ መዛሙርት በባሕር ላይ በሚጓዙበት ጊዜ ጀልባዋን ማዕበል ሲያናውጣት የተሰማቸው ስሜት ይህን ይመስል ነበር (ማቴ. 14፡26)። ንጉሥ ሄሮድስ አዲስ ንጉሥ እንደ ተወለደ በሰማ ጊዜ ስለተሰማው ስሜት ለመግለጥ ማቴዎስ የተጠቀመው በዚህ ቃል ነበር (ማቴ. 2፡3)። ጳውሎስ ወደ ክርስቶስ ስላመጣቸው ሰዎች ሥጋትና ጭንቀት ቢያድርበት የሚያስደንቅ ሊሆን አይችልም፤ ምክንያቱም ወደ ገላትያ አብያተ ክርስቲያናት በመጡት ሐሰተኛ ትምህርቶች እየተናወጡ ነበር። ጸጋ ሁልጊዜ የሚመራው ወደ ሰላም ነው (ገላትያ 1፡3 ተመልከት)። እነዚህ አማኞች ግን ጸጋን ስለ ተዉ በልባቸው ሰላም አልነበራቸውም።

የእግዚአብሔር ጸጋ ከሰው ደኅንነት የላቀ ነገርን እንደሚያካትት ማስታወስ ያስፈልጋል። በጸጋ መዳን ብቻ ሳይሆን በዚሁ ጸጋ መኖርም ያስፈልጋል (1ኛ ቆሮ. 15፡10)። ጸጋ የክርስትና ሕይወት መሠረት ስለሆነ በጸጋ እንቆማለን (ሮሜ 5፡1-2)። አሸናፊ የምንሆንበትንም ብርታት የምናገኘው በጸጋ ነው (2ኛ ጢሞ. 2፡1-4)። ጸጋ ያለአንዳች ማጉረምረም መከራን እንድንቀበልና የምንቀበለውንም መከራ ለእግዚአብሔር ክብር እንድናውለው ያስችለናል (2ኛ ቆሮ. 12፡1-10)። አንድ ክርስቲያን በእግዚአብሔር ጸጋ ከመኖር ዘወር ሲል በራሱ ኃይል ለመደገፍ ይገደዳል። ይህም ወደ ውድቀትና ተስፋ መቁረጥ ያመራል። ጳውሎስ «ከጸጋ መውደቅ» የሚለው ይህንኑ ነው (ገላ. 5፡4)። ከዚህም በላይ ከጸጋ ክልል መውጣትና ወደ ሕግ ክልል መግባት ማለት ነው፤ ከእግዚአብሔር ኃይል ይልቅ በራሳችን ኃይል መታመን ማለት ነው።

ጳውሎስ አንድ ቀን ወዳጆቹ የነበሩ ሰዎች ዛሬ የእግዚአብሔርን ጸጋ እያጥላሉ ሲመለከት፥ የወንጌልን እውነት በማጣመም በሥጋ ጥረትና በራሳቸው ብርታት ለመኖር ሲሞክሩ አይቶ ሥጋት ቢያድርበት አያስገርምም። የክርስትና ሕይወታቸውን በመንፈስ ጀምረው ነበር። በኋላ ግን በሥጋ ኃይል ለመቀጠል ሞከሩ (ገላ. 3፡3)።

ጳውሎስ የሐዋርያነት ሥልጣኑን አስረድቶ ያደረበትንም ሥጋት ከገለጠ በኋላ ወደ ሦስተኛው ደረጃ ይሸጋገራል፡-

3. ባላንጣዎቹን አጋለጠ (1፡8-10)

«ፍቅርን እንጂ ጦርነትን አታድርጉ!» የሚለው መፈክር ታዋቂ ቢሆንም ሁልጊዜ ተግባር ላይ ሲውል አይታይም። ሐኪሞች በበሽታና በሞት ላይ ጦርነት ማካሄድ አለባቸው፤ የጤና ባለሙያዎች በቆሻሻና በአካባቢ ብክለት ላይ ጦርነት ማወጅ አለባቸው። የፍትሕ ሰዎች በተዛባ ፍርድና በወንጀል ላይ ጦርነት ማካሄድ አለባቸው። እነዚህ ሁሉ ውጊያን የሚያካሂዱት ለሚወዱት ነገር ብለው ነው።

«እግዚአብሔርን የምትወድዱ ክፋትን ጥሉ» [መዝ. (97)፡10]። «ክፉውን ነገር ተጸየፉት፤ ከበጎ ነገር ጋር ተባበሩ» (ሮሜ 12፡9)። ጳውሎስ እውነትንና ወደ ክርስቶስ የመራቸውን ሰዎች ያፈቅር ስለ ነበር በሐሰተኛ አስተማሪዎች ላይ ጦርነትን አወጀ። ባል እስክታገባ ድረስ ሴት ልጁን እንደሚጠብቅ አፍቃሪ አባት እርሱም ወደ ክርስቶስ የመራቸውን ሰዎች በኃጢአት ተታለው እንዳይወድቁ ይጠብቃቸው ነበር (2ኛ ቆሮ. 11፡1-4)።

የይሁዲነት አቀንቃኞች የሚታወቁት በሚሰብኩት የሐሰት ወንጌል ነበር። የአንድ ሰው የአገልግሎት መፈተኛ ለእግዚአብሔር ቃል ያለው ታማኝነት እንጂ ታዋቂነት (ማቴ. 24፡11) ወይም ደግሞ ተአምራዊ ምልክቶችና ድንቆች ማድረግ (ማቴ. 24፡23-24) አይደለም። (ኢሳ. 8፡20፤ 1ኛ ጢሞ.4፤ 1ኛ ዮሐ. 4፡1-6 ተመልከት። 2ኛ ዮሐ. 5፡11 ሐሰተኛ ትምህርት የሚያስተምሩ ሰዎችን እንዳናበረታታ የሚያስጠነቅቅ መሆኑን አስተውል።) ጳውሎስ ወንጌልን ከክርስቶስ እንደ ተቀበለ (1ኛ ቆሮ።15፡1-8) እርሱ ደግሞ ለሌሎች ለታመኑ ሰዎች ሰጠ (1ኛ ጢሞ. 1፡11ና 6፡20፤ 2ኛ ጢሞ. 1፡13ና 2፡2)። የይሁዲነት አቀንቃኞች ግን እውነተኛውን ወንጌል በራሳቸው ሐሰተኛ ወንጌል ተክተው ነበር። ጳውሎስም

ለዚህ ኃጢአታቸው የተረገሙ እንዲሆኑ አወጀ። የተጠቀመበት ቃል አናቴማ የሚል ሲሆን፥ ትርጉሙም «ለጥፋት የተመደበ» ማለት ነው። (የዚህን ቃል ጠንካራ ትርጉም ለማግኘት የሐዋ. 23፡14 ተመልከት።) ከእውነተኛው ወንጌል የተለዩ የትኛውንም ወንጌል የሚሰብክ ማንኛውም ሰው መልአክም ቢሆን፥ ወይም ጳውሎስ ራሱ እንኳ ቢሆን የተረገመ ነው።

የጳውሎስ ባላንጣዎች ሌላም ሁለተኛ ባሕርይ ነበራቸው። ይኸውም፡- የሚያደርጉትን ሁሉ በተሳሳተ ወይም ደግሞ በሐሰተኛ ዓላማ ተነሣሥተው የሚፈጽሙ መሆናቸው ነው። ጳውሎስ ወንጌልን ለአሕዛብ በሚሰማማ መንገድ ለማቅረብ ሲል በራርዞታል በማለት ተቀናቃኞቹ ይከሰሱት ነበር። ምናልባትም ይህን ያሉት፥ «በሁሉ መንገድ አንዳንዶችን አድን ዘንድ ከሁሉ ጋር በሁሉ ነገር እንደ እነርሱ ሆንሁ» (1ኛ ቆሮ. 9፡22) በማለት ጳውሎስ የተናገረውን በትክክለኛው መንገድ ባለመረዳታቸው ሊሆን ይችላል። ጳውሎስ ከአይሁድ፥ ጋር ሲሆን እንደ አይሁድ፥ ከአሕዛብ ጋር ሲሆን ደግሞ እንደ አሕዛብ በመኖር ሰውን ደስ ለማሰኘት የሚጥር፥ አቋም የለሽ ሰው ነው ይሉ ነበር።

እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ሰውን ደስ ለማሰኘት ሲሉ ጠባያቸውን የሚለዋውጡ ሐሰተኛ አስተማሪዎች ነበሩ። ይህንንም አስመልክቶ ጳውሎስ «በብርቱ ይፈልጉአችኋል፥ ለመልካም አይደለም» (4፡17) በማለት ጽፏል። «እናንተን ከእኔ ፈጽሞ ለመለየትና ለእነርሱ የተለየ ትኩረት እንድትሰጡ ይፈልጋሉ።» ሐሰተኛ አስተማሪዎቹ የአይሁድ ሕዝብ ስደት እንዳያስነሡባቸው ስለ ፈሩ ወደ ብሉይ ኪዳን ሕጎች በመመለስ እውነተኛውን የወንጌልን አቋም እንደ ሸቀጥ ሲለዋውጡ መቆየታቸውን ያጋልጣቸዋል (6፡12-15)። ጳውሎስ ሰውን ደስ ለማሰኘት ሲል የሚኖር ሰው እንዳልነበር ግልጽ ነው። አገልግሎቱም (1፡1) ሆነ መልእክቱ (1፡12) የተገኘው ከሰው አልነበረም፤ ስለዚህ ሰውን ለምን ይፍራ? ሰውን ለማስደሰትስ ለምን ይድከም? ጳውሎስ ከልቡ የሚፈልገው ክርስቶስን ደስ ማሰኘት ነበር።

የሙዚቃ ደራሲው ቨርዲ የመጀመሪያውን ኦፔራ በፍሎረንስ ከተማ ባቀረበበት ወቅት፥ ከአንድ ከለላ ሥር በመሸሸግ፥ ከተመልካቾች መካከል የነበረውን ታላቁን የሙዚቃ ሰው ሮዚኒን አተኩሮ ይመለከት ነበር። ቨርዲ በዚያ በአዳራሹ ውስጥ የነበሩት ሰዎች ሁሉ በደስታ ቢያጨበጭቡለት ወይም ቢያፈዙበት ግድ አልነበረውም። እርሱ የሚፈልገው ዋናው ነገር ከዚህ ዋናና

ታላቅ የሙዚቃ ሰው የማረጋገጫ ፈገግታ ነበር። ጳውሎስም እንደዚሁ ነበር። ለወንጌል መከራን መቀበል ምን እንደ ሆነ አውቆአል፤ የሰዎች አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ማረጋገጫ ከአቋሙ አላንቀሳቀሰውም፤ «ስለዚህ ደግሞ... እርሱን ደስ የምናሰኝ ልንሆን እንቀናለን» አለ (2ኛ ቆሮ. 5:9)። የጳውሎስ ዋናው ፍላጎት ክርስቶስን ደስ ማሰኘት ብቻ ነበር።

የእግዚአብሔር አገልጋይ ሰዎችን የሚማርክና ደስ ማሰኘት የሚችል ይሆን ዘንድ፥ ብዙ ጊዜ አቋሙን እንዲያለሳልስ ይፈተናል። ዲ.ኤል.ሙዲ የተባለው ሰባኪ አንድ ቀን በእንግሊዝ አገር በሚሰብክበት ወቅት፥ አንድ ሠራተኛ ወደ መድረኩ በመውጣት በጣም የተከበሩ ታዋቂ ሰው ወደ አዳራሹ ስለ መግባታቸው ይነግረዋል። «ስብሰባው የበረከት ይሁንላቸው» የሚል ምላሽ ብቻ በመስጠት በማንም ሰው ላይ የተለየ ተጽዕኖ ሳያሳድር በጀመረው መንገድ ስብከቱን ቀጠለ።

ጳውሎስ መልእክተኛ (አምባሳደር) እንጂ ፖለቲከኛ አልነበረም። ተግባሩ መልእክቱን ማወጅ እንጂ «ፖለቲካን ማቀንቀን» አልነበረም። በሌላ በኩል ግን እነዚህ የይሁዲነት አቀንቃኞች ከፍርሃታቸው የተነሣ አይሁዳውያንና አሕዛብን ሁሉ ደስ ለማሰኘት ሕግንና ጸጋን በመቀየጥ አስተማሩ። ይሁን እንጂ፥ አድራጎታቸው እግዚአብሔርን የሚያስደስት ወይም የሚያሳዝን ስለመሆኑ አልተጨነቁም ነበር።

ጳውሎስ ሐሰተኛ አስተማሪዎችን ለመቋቋም የወሰደውን ሦስት እርምጃዎች ተመልከተናል፦ እነዚህም ሥልጣኑን መግለጥ፥ ያደረበትን ሥጋት ማስረዳትና ባላንጣዎቹን ማጋለጥ ነበሩ። ለመሆኑ ባላንጣዎቹን የሚያጠቃው እንዴት ነበር? የገላትያ ክርስቲያኖች የሚያስፈልጋቸው ብቸኛ ነገር በእግዚአብሔር ጸጋ ማመን እንደ ሆነ ለማስረዳት የተጠቀመበት አቀራረብ ምን ዓይነት ነበር? መልእክቱን እንዲሁ ላይ ላዩን ብንመለከት እንኳ ጳውሎስ እውነተኛ የወንጌል ጠበቃ እንደ ሆነ መገንዘብ ይቻላል። መልእክቱን በአንድ ጊዜ አንብብ። በምታነብበትም ጊዜ ጳውሎስ የተጠቀመባቸውን ሦስት አቀራረቦች አስተውል።

የመጀመሪያው አቀራረቡ ግላዊ ነበር(ምዕ.1-2)። በዚህም ከኢየሱስ ክርስቶስና ከወንጌል መልእክት ጋር የነበረውን የግል ልምምዱን ይገልጣል። ወንጌልን የተቀበለው ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ሳይሆን፥ በግሉ ከጌታ እንደነበረና (1:11-24) ሐዋርያት ግን መልእክቱንና አገልግሎቱን እንዳረጋገጡለት ይናገራል (2:1-10)። ከዚህም በላይ መሪ ሐዋርያ

የነበረው ጴጥሮስ እንኳ የቀድሞ አቋሙን ባለሰለሰ ጊዜ ጳውሎስ ለወንጌል ጠበቃ በመሆን በአቋሙ ጸንቶ ነበር (2፡11-21)። ጳውሎስ የግል ሕይወት ታሪኩን ባጭሩ ያቀረበበት ይህ ክፍል የሚያረጋግጠው የጳውሎስ መልእክትና አገልግሎት ለእምነቱ ሐቀኛ መሆኑን እንጂ «አስመሳይ ሐዋርያ» እንዳልነበረ ነው።

ምዕራፍ 3 እና 4 መሠረታዊ ክርስትና ትምህርትን የያዙ ሲሆኑ፥ በእነዚህ ምዕራፎች ኃጢአተኞች የሚድኑት በእምነትና በጸጋ እንጂ በሥራና በሕግ እንዳይደለ ለማሳየት በርካታ የመከራከሪያ አሳቦችን ያቀርባል። በመጀመሪያ በራሳቸው ልምምዶች ላይ ያተኩራል (3፡1-5)። ቀጥሎ በምዕራፍ 3፡6-14 ላይ ወደ ብሉይ ኪዳን ሕግ በመመለስ አብርሃምና ነቢያት እንኳ ደህንነት በእምነት በሚገኝ ጸጋ ብቻ እንደሆነ ተገንዝበው እንደ ነበር ያሳየናል። ስለ ሕግ ከተናገረ በኋላ ደግሞ ከመጀመሪያውኑ ሕጉ ለምን እንደ ተሰጠ ያመለክታል (3፡15-4፡18)። በሕግና በጸጋ መካከል ያለውን ግንኙነት ለመግለጽ የሣራንና አጋርን ታሪክ እንደ ምሳሌ ያቀርበዋል (4፡19-31)።

የመጨረሻዎቹ ሁለት ምዕራፎች ጳውሎስ የመከራከሪያ አሳብ ከማቅረብ አልፎ ከሕይወት ጋር ወደ ማዛመድ ያመራባቸው ናቸው። የይሁዲነት አቀንቃኞች ጳውሎስ የእግዚአብሔርን የጸጋ ወንጌል ይሰብክ ስለ ነበር ሥርዓት አልበኝነትን ያስፋፋል በማለት ይከሱት ነበር። ስለዚህ ጳውሎስ በእግዚአብሔር ጸጋና በተግባራዊ ክርስቲያናዊ ሕይወት መካከል ያለውን ግንኙነት በዚህ ክፍል ያስረዳል። በጸጋ መኖር ማለት በባርነት ሳይሆን በነጻነት፥ (5፡1-12) በሥጋ ሳይሆን በመንፈስ በመደገፍ፥ ለራስ ሳይሆን ለሌሎች፥ ከሰው ማረጋገጫ ለማግኘት ሳይሆን ለእግዚአብሔር ክብር መኖር መሆኑን ያሳያል (6፡11-18)። ከሁለቱ በአንዱ ማለትም በሕግ ወይም በጸጋ እንጂ በሁለቱም መኖር አይቻልም።

የገላትያ መልእክት በቀላሉ የሚታይ መጽሐፍ አይደለም። በተሐድሶ እንቅስቃሴ ወቅት ማርቲን ሉተር ያነገበው የነፃነት ቻርተር የገላትያ መልእክትን ነበር። የሉተር ጽሑፎች በለንደን አልደርስጌት መንገድ ግንቦት 24 ቀን 1738 እ.ኤ.አ. በተደረገ ትንሽ ስብሰባ ላይ ለጆን ዌስሊ ደኅንነት በእምነት መሆኑን አስረዱት። ዌስሊ እግዚአብሔር በብሪታኒያ ደሴቶች በአስደናቂ መንገድ መንፈሳዊ እንቅስቃሴን ለማምጣት የተጠቀመበት ሰው ነበር። በመጨረሻም ለሜቶዲስት ቤተ ክርስቲያን መመሥረት ምክንያት

የሆነው ይህ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ነበር። ከዚህም ሌላ እንግሊዝኛ ተናጋሪ በሆነው ዓለም ሁሉ ላይ በጎ ተጽዕኖ አሳድሮአል። የገላትያን መጽሐፍ በምናጠናበት ጊዜ ዛሬም ቢሆን ሌላ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ሊያስነሣ በሚችል ታላቅ መንፈሳዊ ሥራ ውስጥ ተሳታፊ እንሆናለን።

ለገላትያ መልእክት የቀረበ አስተዋጽኦ

መሪ አሳብ፡- በእግዚአብሔር ጸጋ ውስጥ የሚገኝ ክርስቲያናዊ ነፃነትም ከጳውሎስ የግል ሕይወት ጋር የተያያዘ

ክፍል 1. በግል ሕይወት ላይ የተሰጠ ገለጻ ክፍል፡- ጸጋና ወንጌል - ምዕራፍ1፡1-2

1. በጳውሎስ መልዕክት የታወጀ ጸጋ 1፡1-10
2. በጳውሎስ ሕይወት በተግባር የታየ ጸጋ 1፡11-24
3. ጳውሎስ በአገልግሎቱ የተሟገተለት ጸጋ 2፡1-21
   (1) በቤተ ክርስቲያን ጎብረት ውስጥ 2፡1-10
   (2) በግሉ ከጴጥሮስ ጋር 2፡11-21

ክፍል 2. የመሠረተ እምነት ትምህርት ገለጻ ክፍል፡- ጸጋና ሕግ - ምዕራፍ 3-4

1. ከግል ሕይወቱ ያቀረበው የመከራከሪያ አሳብ 3፡1-5
2. መጽሐፍ ቅዱሳዊ የመከራከሪያ አሳብ 3፡6-14
3. አእምሮአዊ የመከራከሪያ አሳብ 3፡15-29
4. ታሪካዊ የመከራከሪያ አሳብ 4፡12-18
5. ስሜታዊ የመከራከሪያ አሳብ 4፡12-18
6. ተምሳሌታዊ የመከራከሪያ አሳብ 4፡19-31

ክፍል 3. የተግባራዊ ኑሮ ገለጻ ክፍል፡- ጸጋና የክርስቲያን ሕይወት - ምዕራፍ 5-6

1. ነጻነት እንጂ ባርነት አይደለም 5፡11-12
2. በመንፈስ እንጂ በሥጋ አይደለም 5፡13-26
3. ለሌሎች እንጂ ለራስ መኖር አይደለም 6፡1-10
4. ለእግዚአብሔር ክብር እንጂ ለሰው ምስጋና መኖር አይደለም 6፡11-18

ገላትያ 1፡11-24

ወንድሞች ሆይ፥ በእኔ የተሰበከ ወንጌል እንደ ሰው እንዳይደለ አስታውቃችኋለሁ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ገልጦልኛል እንጂ እኔ ከሰው አልተቀበልሁትም አልተማርሁትምም። በአይሁድ ሥርዓት በፊት እንዴት እንደ ኖርሁ ሰምታችኋልና፤ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ያለ ልክ አሳድድና አጠፋ ነበር፥ ለአባቶችም ወግ ከመጠን ይልቅ እየቀናሁ በወገኔ ዘንድ በዘመኔ ካሉት ብዙዎችን በአይሁድ ሥርዓት እበልጥ ነበር። ነገር ግን በእናቴ ማኅፀን ሳለሁ የለየኝ በጸጋውም የጠራኝ እግዚአብሔር በአሕዛብ መካከል ስለ እርሱ ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ልጁን በእኔ ሁኔታ ሊገልጥ በወደደ ጊዜ፥ ወዲያው ከሥጋና ከደም ጋር አልተማከርሁም፥ ከእኔም በፊት ሐዋርያት ወደ ነበሩት ወደ ኢየሩሳሌም አልወጣሁም፥ ነገር ግን ወደ ዓረብ አገር ሄድሁ፤ እንደ ገናም ወደ ደማስቆ ተመለስሁ።

ከዚህ ወዲያ ከሦስት ዓመት በኋላ ኬፋን ልጠይቅ ወደ ኢየሩሳሌም ወጥቼ ከእርሱ ጋር አሥራ አምስት ቀን ሰነበትሁ፤ ነገር ግን ከጌታ ወንድም ከያዕቆብ በቀር ከሐዋርያት ሌላ አላየሁም። ስለምጽፍላችሁም ነገር፥ እነሆ በእግዚአብሔር ፊት ሐሰት አልናገርም። ከዚያ ወዲያ ወደ ሶርያና ወደ ኪልቅያ አገር መጣሁ። በክርስቶስም ያሉት የይሁዳ ማኅበሮች ፊቴን አያውቁም ነበር፤ ነገር ግን፡- ቀድሞ እኛን ያሳድድ የነበረ፥ እርሱ በፊት ያጠፋው የነበረውን ሃይማኖት አሁን ይሰብካል ተብሎ ሲነገር ይሰሙ ነበር፤ ስለ እኔም እግዚአብሔርን ያከብሩ ነበር።

ነፃ ሆኖ መወለድ

ኤመርሰን «ማንኛውም ሰው ታላቅ መሆን ከፈለገ ሌላውን መምሰል የለበትም» በማለት በጻፈው አባባል ብዙዎች ይስማማሉ።

እንግሊዛዊው የሥነ ጥበብ ሃያሲ ጆን ሩስኪን፥ ከሌሎች ሰዎች ጋር ተመሳሳይ እንዳልሆን እፈራለሁ። ወርቅን መፈብረክ የማይቻለውን ያህል ታላላቅ ሰዎችን መፈብረክም አይቻልም» ብሏል።

ጀርመናዊ ፈላስፋ ሾፐንሃወር « ሌሎችን ለመምሰል በምናደርገው ጥረት ከእውነተኛ ማንነታቸው ሦስት አራተኛውን እናጣለን» ብሎአል።

በአሜሪካ የሚገኘው የሜቶዲስት ቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያ ጳጳስ የነበረው ፍራንሲስ አሸበሪ ዲያቆናት ክህነት በሚቀበሉት ፕሮግራም ላይ «ጌታ ሆይ፥ እነዚህን ወንድሞች ሌላውን ሰው ያለመምሰልን ፍላጎት አሳድርባቸው» በማለት ጸልዮ ነበር።

በእርግጥ ከግልግት ይልቅ ግጥፋትን የሚመርጥ የተሳሳተ ግለኝነት አለ። ነገር ግን አንዱ ሌላውን እየመሰለ በሚኖርበት ህብረተሰብ፥ በእግዚአብሔር ፈቃድ ራሱን ሆኖ ለመኖር የሚደፍር ጳውሎስን የመሰለ ሰው ግግኝት መልካም ነው። ይህ በክርስቶስ የነበረው ነጻነት ግን ተመሳስሎ መኖርን ለለመዱ ሁሉ ትልቅ ፍራቻ አሳድሮባቸዋል።

ጳውሎስ ሌላውን ባለመምሰል የራሱን አቋም በጽናት በመያዙ፥ ጠላቶቹ መልእክቱና አገልግሎቱ በእርግጥ ከእግዚአብሔር ላለመሆኑ ማረጋገጫ አድርገው አቅርበውበት ነበር። «ሐዋርያ ነኝ እያለ በሐዋርያነት ልማድ አይኖርም» ብለው ይከራከሩ ነበር። ጳውሎስ በገላትያ መልእክት ምላሽ የሚሰጠው ለዚህ የተሳሳተ ግንዛቤ ነበር። ሌሎችን ያለመምሰሉ በመለኮታዊ እውቀት ሆን ተብሎ የተደረገ ነበር። እግዚአብሔር ራሱ ለጳውሎስ በተለየ መንገድ ለመግለጥ ፈቀደ።

ጳውሎስ በቁጥር 11ና 12 ላይ የመልእክቱን ዋና አሳብ ያቀርባል። መልእክቱና አገልግሎቱ ከመለኮት የተሰጡ ናቸው። የሚሰብከውን ወንጌል ከኢየሱስ ክርስቶስ የተቀበለው እንጂ እርሱ የፈጠረው ወይም ከሰው የተቀበለው አልነበረም። መልእክቱና ሐዋርያዊ አገልግሎቱ ከአምላክ

የተሰጠ ነበር። ወንጌል የተሰጠው ከሰማይ በኢየሱስ ክርስቶስ ስለሆነ (1ኛ ቆሮ. 15፡1-11) በዚህ በጳውሎስ ወንጌል ላይ ምንም ነገር የሚጨምር መለኮታዊ ፍርድን ይቀበላል።

ይህንን አሳቡን ለማረጋገጥ ጳውሎስ ከሁሉ የተሻለው ሆኖ ያገኘው መንገድ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር እንዴት እንደ ተገናኘና ለሕይወቱ ያደረገውን ጉዳይ ካለፈው ታሪኩ ጋር በማያያዝ ማቅረብ ነበር። መልእክቱን የሚያነቡት ሰዎች የቀድሞ ሕይወቱን የሚያውቁ ቢሆኑም እንኳ (ገላ. 1፡13) የሕይወት ልምምዶቹን ትርጉም በሙላት እንዳልተረዱ ግልጽ ነው (ገላ.1፡13)። ስለዚህ ጳውሎስ ከቀድሞ ልምምዱ ሦስቱን በማቅረብ ሐዋርያነቱና የሚሰብከው ወንጌል በእውነት ከእግዚአብሔር የተሰጠ እንደሆነ ያረጋግጣል።

1. አሳዳጁ ጳውሎስ (1፡13-14)

ጳውሎስ ስለ ቀድሞ ሕይወቱ መግለጽ የጀመረው ያልተለወጠ የአይሁድ ሃይማኖት መምህር ከነበረበት ጊዜ አንሥቶ ነው። (ጳውሎስ ስለ ሕይወቱ በግልጽ የተናገረበት ታሪክ በሐዋ. 22ና 26 ደግሞ 9 ላይ በተጨማሪ ተመልከት።) ጳውሎስ ይህንን የቀድሞ ታሪኩን በመናገር ከቤተ ክርስቲያንና (ቁ. 13) ከአይሁድ ሃይማኖት (ቁ. 14) ጋር የነበረውን ግንኙነት አመለከተ። ቤተ ክርስቲያንን እያሳደደ በአይሁድ ሃይማኖት ጥቅምና እድገት ያገኝ ነበር። ሁሉም ነገር እርሱ በሚፈልገው መንገድ ይሄድ ነበር። ስለዚህ በፍጥነት እንደ አንድ እስራኤላዊ መሪ እየታወቀ መጣ።

ገና «የጠርሴሱ ሳውል» ተብሎ ቤተ ክርስቲያንን ያሳድድ በነበረበት ወቅት ጳውሎስ የፈጸማቸውን ተግባራት ለመግለጥ የተጠቀመባቸውን ቃላት ልብ ብሎ መመልከት በጣም ጠቃሚ ነው። በእስጢፋኖስ መገደል«ተስማምቶ ነበር» (የሐዋ. 8፡1 ተመልከት)። ቤተሰብን በመለያየትና አማኞችን በማሰር «ቤተ ክርስቲያንን ማወኩን» ቀጥሎ ነበር (የሐዋ. 8፡3)። የሚናገረው ሁሉ «ዛቻና ግድያ» ነበር (የሐዋ.9፡1)። ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያንን ለማፍረስ በጽኑ ስለ ተነሣሣ አማኞች እንዲገደሉ ተስማማ (የሐዋ. 22፡4-5፤ 26፡9-11)። እግዚአብሔር ግን እንደ እርሱ ያለ ኃጢአተኛን ለማዳን ፈቃዱ የመሆኑን እውነታ በመልእክቶቹ ላይ ጠቅሶታል (1ኛ ቆሮ. 15፡9፤ ፊልጵ. 3፡6፤ 1ኛ ጢሞ. 1፡13)።

ጳውሎስ ኢየሱስ አስመሳይ እንደ ሆነና የደጎንነት መልእክቱም ውሸት እንደ ሆነ ነበር የገመተው። እግዚአብሔር በሙሴ በኩል እንደ ተናገረ እርግጠኛ ነበር። ግን በናዝሬቱ ኢየሱስ በኩል እንደ ተናገረ ግን እንዴት እርግጠኛ መሆን ይችላል? በአይሁድ ወግ ጠልቆ ያደገው ወጣቱ የጠርሴሱ ሳአል ለእምነቱ ይጋደል ነበር። «የናዝራውያንን የእምነት ክፍል» ቀናተኛ አሳዳጅ መሆኑ በሰፊው ታውቆ ነበር (የሐዋ. 9፡13-14 ተመልከት)። የመምህር ገማልያል ታዋቂ ጎበዝ ተማሪ የነበረው ጳውሎስ የአይሁድ እምነት ውስጥ ታላቅ መሪ እንደሚሆን ሁሉም ሰው ይገምት ነበር (የሐዋ. 22፡3)። የግሉ ሃይማኖታዊ ሕይወቱ፥ የነበረው ከፍተኛ ትምህርት (የሐዋ. 26፡24)፥ ባዕድ ሃይማኖቶችን ለመቃወም የነበረው ቅንዓት ሁሉ በአንድነት ተደማምረው በዘመኑ የተከበረ ሃይማኖታዊ መምህር አደረጉት።

ከዚያም በድንገት ቤተ ክርስቲያንን አሳዳጅ የነበረው የጠርሴሱ ሳአል የወንጌል ሰባኪው ሐዋርያው ጳውሎስ ሆነ። ይህ ለውጥ ቀስ በቀስ የተከሰተ አልነበረም፥ በቅጽበት፥ ያለአንዳች ማስጠንቀቂያ ወይም መልእክት የተፈጸመ እንጂ (የሐዋ. 9፡1-9)። ሳአል ክርስቲያኖችን ለማሳደድ ወደ ደማስቆ ይሄድ ነበር። ከጥቂት ቀናት በኋላ ግን በደማስቆ ላሉ አይሁዶች«ክርስቲያኖች ትክክል» ናቸው ብሎ ይሰብክ ጀመር። አይሁዶች ይህን ቅጽበታዊ ለውጥ እንዴት አድርገው ሊገልጹት ይችላሉ?

ለጳውሎስ ቅጽበታዊ ለውጥ ምክንያቱ የገዛ ሕዝቡ አይሁዳውያን ሊሆኑ ይችላሉን? ጨርሶ የማይታሰብ ነው! አይሁዳውያን የጳውሎስን ክርስቲያኖችን የማሳደድ ዘመቻ ይደግፉና ያበረታቱ ስለነበር ለውጡ ታላቅ ሃፍረት ሆኖባቸው ነበር።

ለጳውሎስ ድንገተኛ ለውጥ ምክንያቱ የሚያሳድዳቸው ክርስቲያኖች ነበሩን? በእርግጥ ክርስቲያኖች ይጸልዩለት ነበር፤ የእስጢፋኖስ ሞት በተለይ ደግሞ በዚያን ዕለት ያቀረበው አስደናቂ ምስክርነት በጳውሎስ ላይ ጥልቅ ተጽዕኖ ማድረጉ የማያጠራጥር ነው (የሐዋ. 22፡19-20)። ነገር ግን ክርስቲያኖች ከእርሱ ይሸሹ ነበር (የሐዋ. 8፡1፥4፤ 9፡10-16)፤ እኛ እስከምናውቀው ድረስ ይህ ወጣት የሃይማኖት መምህር ክርስቲያን ይሆናል የሚል አሳብ ጨርሶ አልነበራቸውም።

አስደናቂ የሆነው የጳውሎስ ለውጥ ምክንያት አይሁዳውያን ወይም ክርስቲያኖች ካልሆኑ ታዲያ፥ ማን ሊሆን ይችላል? ከእግዚአብሔር የመጣ መሆን አለበት!

የጳውሎስን መለወጥ በማንኛውም መንገድ ብንመለከተውም ተአምራዊ ለመሆኑ ግን ምንም አማራጭ ሊኖረን አይችልም። እግዚአብሔር በጌጋው ተአምር ካልሠራ በስተቀር የቀድሞው ሳኦል ሐዋርያው ጳውሎስ ይሆናል ብሎ ማሰብ በፍጹም የማይሆን ነበር። ለጳውሎስ ደህንነትን የሰጠው አምላክ እንደጋና በሐዋርያነት እንዲያገለግል የወንጌልን መልእክት ሰጠው። ለይሁዲነት አቀንቃኞች የጳውሎስን ሐዋርያነትና ወንጌል መካድ መልዕክታቸው መካድ ነበር። ጳውሎስ ይሰብከው የነበረው መልእክት እርሱ ራሱ ያመነበትንና የለወጠውን እውነት ነበር። የሰው መልእክት ብቻ ግን እንዲህ ዓይነቱን ለውጥ ሊያመጣ አይችልም። የጳውሎስ መከራከሪያ አሳብ መደምደሚያ ግልጽ ነበር፡- የአሳዳጅነት ሕይወቱና የተለማመደው አስደናቂ ለውጥ፥ መልእክቱና አገልግሎቱ ከእግዚአብሔር ለመሆኑ ብቁ ማረጋገጫዎች ናቸው።

2. አማኙ ጳውሎስ (1፡15-16፥ 24)

ጳውሎስ የቀድሞ ባሕርዩንና አካሄዱን ከተረከ በኋላ እንዴት እንደ ተለወጠ ይገልጻል። ምክንያቱም ይህ በሕይወቱ ላይ ወሳኝ ጉዳይ ነው። ለክሳሾቹ እንዲህ ይላቸዋል፥ «ለሌሎች የምሰብከውን ወንጌል እኔው ራሴው ተለማምጄዋለሁ። ይህ እውነተኛ ወንጌል ነው፤ ከዚህ የተለየ ወንጌል ትክክለኛ አይደለም።» በእነዚህ ከላይ በተመለከትናቸው ቁጥሮች ውስጥ ጳውሎስ እንዴት እንደ ተለወጠ ይገልጻል።

የጳውሎስን ሕይወት በአስደናቂ መንገድ የለወጠ እግዚአብሔር ነበር (1፡15-16)። «... ልጁን በእኔ ሁኔታ ሊገልጥ በወደደ ጊዜ...»። ጳውሎስ በሕይወቱ ስለ ተፈጸመው ለውጥ በሚናገርበት በማንኛውም ጊዜ ትኩረቱ ይህን ያደረገው እግዚአብሔር እንደ ነበር በመግለጥ ላይ ነበር። «ደህንነት ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው» (ዮናስ 2፡10)።

ጳውሎስን እግዚአብሔር የጠራው በጸጋው ነበር (1፡15)። ይህ የጳውሎስ ልምምድ ወጣቱ ኤርምያስንና መጥምቁ ዮሐንስን ያስታውሰናል (ኤር. 1፡4-10ና ሉቃስ 1፡5-17)። ደኅንነት የሚገኘው በሰው ጥረት ወይም መልካም ጠባይ ሳይሆን በእግዚአብሔር ጸጋ ነው። እግዚአብሔር በጸጋው የመረጠውን ሁሉ በቃሉ ይጠራል (1ኛ ተሰ. 1፡4-5)። ስለዚህ ጸጋና ጥሪ የማይነጣጠሉ ናቸው (ገላ. 1፡15)። በእግዚአብሔር ልውላዊ ፈቃድና በሰው የመታዘዝ ኃላፊነት መካከል ያለው ምስጢር ለእኛ በሙላት

አልተገለጠልንም። እግዚአብሔር «ማንም እንዳይጠፋ» እንደሚወድና በክርስቶስ ያመኑ ሁሉ «ዓለም ሳይፈጠር በፊት... » እንደተመረጡ (ኤፌ. 1:4) ግን እናውቃለን።

እግዚአብሔር ይህንን ያደረገው በክርስቶስ በኩል ነው (1:16)። ጳውሎስ ከመለወጡ በፊት የሚመካበት በርካታ ነገር እንደነበረው በሌላ መልእክቱ ግልጽ አድርጎታል (ፊልጵ. 3)። ሃይማኖት፥ ግላዊ ጽድቅ፥ መልካም ምስክርነትና ታዋቂነት ነበረው። ክርስቶስ ግን አልነበረውም። በደማስቆ መንገድ ላይ እያለ ግን ከክርስቶስ ጽድቅ ጋር ሲወዳደር ልክ እንደ አዳፋ ጨርቅ የቆሸሸውን የራሱን ጽድቅ ሲመለከት በሕይወቱ ምን እንደ ጎደለው ተገነዘበ። «ለእኔ ረብ የነበረውን ሁሉ ስለ ክርስቶስ እንደ ጉዳት እቆጥራለሁ» (ፊል. 3:7)።

እግዚአብሔር ክርስቶስን ለጳውሎስ፥ በጳውሎስ ውስጥ፥ በጳውሎስ አማካይነት ገለጠለት። «የአይሁድ ሃይማኖት» የውጫዊ ሥርዓታት አምልኮ ልምምድ ነበር (ገላ፡14)። በክርስቶስ ማመን ግን ከጌታ ጋር እውን የሆነ ውስጣዊ ልምምድን አምጥቷል። በጳውሎስ ዘንድ የነበረው አብይ እውነት ክርስቶስ በሰው ሕይወት ውስጥ የመኖሩ ጉዳይ ነበር (ገላ. 2:20፤ 4:19)።

እግዚአብሔር ይህንን ያደረገው ለሌሎች ጥቅም ነው (1:16)። እግዚአብሔር ጳውሎስን የመረጠው ሊያድነው ብቻ ሳይሆን ሌሎችን ለመማረክ መሳሪያ እንዲሆነውም ነበር። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የመመረጥ መሠረታዊ ትምህርት ኩራትን ወይም ራስ ወዳድነትን እንዲፈጥር የተነገረበት ክፍል ጨርሶ የለም። መመረጥ ኃላፊነትን የሚያካትት ነው። እግዚአብሔር ጳውሎስን የመረጠው እርሱ የተለማመደውን ጸጋ በአሕዛብ መካከል እንዲሰብክ ነበር። የጳውሎስ መለወጥ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደ ነበር ይህ ራሱ ማረጋገጫ ነበር። ምክንያቱም በአሕዛብ ላይ ንቀት የነበረው አይሁዳዊ መምህር እነርሱን ለማገልገል በግሉ መወሰን በፍጹም የማይሆንለት ነውና! (የሐዋ. 9:15፤ 15:12፤ 22:21-22፤ ኤፌ. 3:1፥8 ተመልከት)።

እግዚአብሔር ይህንን ያደረገው ለክብሩ ነበር (1:24)። ሃይማኖታዊ ግትርነት የነበረው ጳውሎስ በሰዎች ዘንድ ክብር ቢኖረውም፥ የሚያደርገው ሁሉ ግን እግዚአብሔርን አላስከበረም። ሰው የተፈጠረው እግዚአብሔርን ለማክበር ሲሆን (ኢሳ. 43:7)፥ ደግሞም ሰው የሚድነው እግዚአብሔርን ለማክበር ነው (1ኛ ቆሮ. 6:19-20)። በጳውሎስ ሕይወትና አገልግሎት

ውስጥ እግዚአብሔርን ማስከበር የሁልጊዜ ቋሚና ውስጣዊ ዓላማ ነበር (ሮሜ 11፡36፥16፤ 16፡27፤ አፌ. 1፡6፤ 3፡20-21፤ ፊልጵ. 4፡20፤ 1ኛ ቆሮ. 10፡31)። የይሁዲነት አቀንቃኞች ፍላጎት ግን ራሳቸውን ማክበር ነበር (ገላ. 6፡11-18)። በጳውሎስ አገልግሎት የተለወጡትን የሚሰርቁትና ወደ ክህደት የሚመሩት ለዚሁ ዓላማቸው ነበር። ጳውሎስ ለራሱ የሚሆን ክብርን ፈልጎ ቢሆን ኖሮ አይሁዳዊ መምህር መሆኑን በቀጠለና ምናልባትም በገማልያል እግር ሊተካ በቻለም ነበር። ነገር ግን ጳውሎስን ያነሣሣውና ያነቃቃው የእግዚአብሔር ክብር እንደ መሆኑ ይህም የእኛንም ሕይወት ሊያነቃቃ የሚያስፈልገን ነው።

ቻርልስ ሐዶን ስፐርጀን ወጣት ሰባኪ በነበረበት ጊዜ፥ ተቀዳሚ ተዋቂነት እንዲያገኝ በማሰብ ወደ ኮሌጅ እንዲገባ አባቱ ጆን ስፐርጀን አሳብ አቅርቦለት ነበር። በለንደን የሚገኘው እስቴፕኒ ኮሌጅ ኃላፊ ከነበረው ዶክተር ጆሴፍ አንጉስ ጋር እንዲገናኝም ሁኔታዎችን አመቻችቶለት ነበር። በካምብሪጅ በሚገኘው ሚስተር ማክሚላን ቤት በተደረገው ቀጠሮ መሠረት ስፐርጀን በሰዓቱ በመገኘት ለሁለት ሰዓት ሙሉ ቢጠባበቅም ምሁሩ ዶክተር ግን ሳይመጣ ቀረ። በኋላ ከአንድ ሰው እንደ ተረዳው ግን፥ ዶክተር አንጉስ በሌላ ክፍል ውስጥ ሲጠብቀው እንደ ነበረና አሁን ግን ወደ ሌላ ቀጠሮ ስፍራ መሄዱን አወቀ። ስፐርጀን በሁኔታው አዝኖ የሰብከት አገልግሎት ወደሚሰጥበት ቦታ አመራ። በመንገድም ሲሄድ ጥርት ባለ ሁኔታ እንዲህ የሚል ድምጽ ሰማ፡- «ለራስህ ታላቅን ነገር ትፈልጋለህን? አትፈልገው!» (ኤር. 45፡5 ተመልከት)። ከዚያን ቅጽበት ጀምሮ ስፐርጀን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለእግዚአብሔር ክብር ለማድረግ ወሰነ። እግዚአብሔርም ፈጽሞ ልዩ በሆነ መንገድ ባረከው።

ጳውሎስ ራሱን ያቀረበው አሳዳጅ እንደ ነበር ነው፤ ስለ ፀባዩና ማንነቱም ማብራሪያ ሰጥቶአል። ከዚህም ጋር በማያያዝ እንዴት አማኝ ለመሆን እንደ በቃና ለማመን የቻለበትንም መንገድ ገልጾአል። አሁን ደግሞ ሦስተኛውን የሕይወት ገጽታውን ያቀርባል።

3. ወንጌል ሰባኪው ጳውሎስ (1፡16-23)

ጳውሎስ ከተለወጠ በኋላ ከአማኞች ጋር የነበረው ግንኙነት ምን ነበር? ይህ የሐዋርያነት ሥልጣኑን ለመከላከል ላቀረበው ንግግር በጣም ጠቃሚ ጥያቄ ነው። ጳውሎስ በደማስቆ መንገድ የደህንነትን ልምምድ ካገኘ በኋላ

ወዲያውኑ ከሐዋርያት ጋር ግንኙነት አላደረገም። «ወዲያው ከሥጋና ከደም ጋር አልተማከርኩም» (ገላ. 1፡16)። እንደ እውነቱ ጳውሎስ ከተለወጠ በኋላ ሊያደርገው የሚገባው ትክክለኛ ነገር፥ ለኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን ራሱን ማስተዋወቅና ከእርሱ በፊት በክርስቶስ ከነበሩት ሰዎች መንፈሳዊ መመሪያ በመቀበል ለሕይወቱ የሚጠቅመውን ማድረግ ነበር። ዳሩ ግን ጳውሎስ ይህንን አላደርግም። ይህ ውሳኔውም ከጌታ ነበር። ከዚህ ውጪ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ ቢሆን ኖሮ ሁሉም አይሁዳውያን ከነበሩት ከሐዋርያት ጋር ተዳምሮ በአሕዛብ መካከል ለሚፈጽመው አገልግሎቱ እንቅፋት ይሆንበት ነበር።

እዚህ ነጥብ ላይ ግን የወንጌል መልእክት «አስቀድሞ ለአይሁዳውያን» እንደተሰጠ ማስታወስ ያስፈልጋል (የሐዋ. 3፡26፤ ሮሜ 1፡16)። የጌታ አገልግሎት ለእስራኤል ሕዝብ እንደ ነበር ሁሉ የሐዋርያትም የመጀመሪያዎቹ ጥቂት ዓመታት አገልግሎት ለእስራኤል ሕዝብ ነበር (የሐዋ. 1-7 ተመልከት)። ይህንን አሠራር የለወጠው የእስጢፋኖስ ሞት ነበር። አማኞች በተበተኑበት ስፍራ ሁሉ ወንጌልን እየሰበኩ ዞሩ (የሐዋ. 8፡4፤ 11፡19-30)። ፊልጶስ የወንጌልን መልእክት ይዞ ወደ ሳምራውያን ሄደ (የሐዋ. 8)፤ ቀጥሎም እግዚአብሔር ይህን መልእክት ወደ አሕዛብ እንዲያደርስ ጴጥሮስን መራው (የሐዋ. 10)። ሆኖም የወንጌልን መልእክት ለአብዛኛው የአሕዛብ ወገን የማድረስ ሥራ የተሰጠው ለጳውሎስ ነበር (የሐዋ. 22፡21-22፤ ኤፌ. 3፡1፥8)። በዚህም ምክንያት በኢየሩሳሌም አብዛኛውን አገልግሎታቸውን ለአይሁዳውያን ከሰጡ ሐዋርያት እግዚአብሔር ጳውሎስን ለየው።

ጳውሎስ ወዲያውኑ ወደ ኢየሩሳሌም አልሄደም። ታዲያ፥ የሄደው ወደ የት ነበር? ያደረጋቸውን ግንኙነቶች እንደገና በማንሣት መልእክቱንም ሆነ ሐዋርያዊ ጥሪውን ከየትኞቹም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንዳልተቀበለ ያረጋግጣል። (ይህን ክፍል ከሐዋ. 9፡10-31 ጋር አወዳድር፤ ከፍተኛ የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች እንኳ በጳውሎስ ሕይወት ቅደም ተከተል እንዳልተስማሙ አስተውል። ደግነቱ የታሪኩ ዝርዝር ሁኔታ በጳውሎስ መልእክት ላይ የሚያሳድረው ተጽእኖ ያለመኖሩ ነው። በጊዜ ቅደም ተከተሉ አንድ ዓይነት አሳብ ባይኖረንም እንኳ በሥነ መለኮት ትምህርቱ ግን እንስማማለን።)

ወደ ዓረብ አገር ሄዶ ነበር (1፡17)። ይህ የሆነው የመጀመሪያ አገልግሎቱን በደማስቆ ከፈጸመ በኋላ ነበር (የሐዋ. 9፡19-20)። ጳውሎስ «ከሥጋና ከደም ጋር ከመማከር» ይልቅ ራሱን ለጸሎትና ለጥናት በማዘጋጀትና ደግሞም የጥሞና ጊዜ በመውሰድ ከጌታ ጋር አሳለፈ። ከሦስቱ ዓመታት አብዛኛውን ጊዜ በዓረብ አገር ማሳለፉ ቢታወቅም ለግል መንፈሳዊ እድገት ብቻ ሳይሆን ከዚሁ ጊዜ ከፊሉን ለውነጌል ሥራ እንዳዋለው አያጠራጥርም (ገላትያ 1፡18)። ሐዋርያት ለሦስት ዓመታት ከጌታ ጋር በመቆየት እንደ ተማሩ ሁሉ ጳውሎስም በፈንታው ከጌታ ለመማር ጊዜ አስፈልጎታል።

ቀጥሎም ወደ ደማስቆ ተመልሶ ነበር (1፡17)። በዚህ ጊዜ ኢየሩሳሌምን ለመጎብኘት ሁኔታው ቢያመቻውም ጌታ ግን በተለየ መንገድ መራው። የክርስትና እምነትን እንደ ተቀበለ ወደ ታወቀበት ከተማ ተመልሶ መሄዱ አደገኛ ነበር። ከርስትናን ያጠፋልናል ብለው የጠበቁት ሰው ራሱ ክርስትናን እንደ ተቀበለ ስለሚያውቁ ሊገድሉት ይፈልጋሉ። በሐዋ. 9፡23-25 የተጠቀሰው ጳውሎስን በቅርጫት አድርጎ በቅጥር ላይ የማሳለፍ ተግባር የተፈጸመው በዚህ ጊዜ ነበር (2ኛ ቆሮ. 11፡32-33 ተመልከት)። ወደ ደማስቆ መመለሱና በዚያ የገጠመው አደጋ የአይሁድ መሪዎች ጳውሎስን እንደ ጠላት እንደ ተመለከቱት ተጨማሪ ማስረጃ ሲሆን፥ ይህም በክርስቶስ የተለማመደው ነገር እውነት መሆኑን ያሳያል።

በመጨረሻ ኢየሩሳሌምን ጎብኝቶ ነበር (1፡18-20)። ይህ የሆነው ከተለወጠ ከሦስት ዓመት በኋላ ሲሆን ዋና አላማው ጴጥሮስን ለመጎብኘት ነበር። ይሁን እንጂ ጳውሎስ ከምዕመናን ጎብረት ጋር ለመቀላቀል ብዙ ችግር ገጥሞታል! (የሐዋ. 9፡26-28)። ጳውሎስ መልእክቱንና አገልግሎቱን የተቀበለው ከሐዋርያት ዘንድ ቢሆን ኖሮ ግን ይህ ጨርሶ ባልሆነ ነበረ። የእርሱ ልምምድ ከጌታ ኢየሱስ ዘንድ ብቻ በመሆኑ ሐዋርያት ጠርጥረውት ነበር። በኢየሩሳሌም የቆየው ለ15 ቀናት ብቻ ሲሆን በዚያም ከጴጥሮስና ከጌታ ወንድም ያዕቆብ ጋር ብቻ ነበር የተገናኘው። ስለዚህ መልእክቱንም ሆነ የሐዋርያነት ሥልጣኑን የተቀበለው ከኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን አልነበረም ማለት ነው። ይህን ለማድረግ ጊዜውም እድሉም አልነበረውም። ነገር ግን መልእክቱንም ሆነ ሐዋርያነቱን በቀጥታ ከክርስቶስ ዘንድ ተቀብሎ ነበር።

ወደ ትውልድ ስፍራው ጠርሴስ ተመለሰ (1፡21-23)። በደማስቆ እንደ ሆነው ሁሉ በኢየሩሳሌምም ችግር የገጠመው ለምን እንደ ሆነ በሐዋርያት ሥራ ላይ ያለው ጽሑፍ እንደገና ያብራራዋል (የሐዋ. 9፡28-30)። ጳውሎስ በሶርያ ባለፈ ጊዜ ቃሉን ሰብኮ ነበር። የትውልድ አገሩ ግዛት ወደ ሆነችው ወደ ኪልቅያ በደረሰ ጊዜ (የሐዋ. 21፡39፤ 22፡3) ወንጌልን ማስፋፋት ጀመረ (የሐዋ. 15፡23 ተመልከት)። ጳውሎስ በአንጾኪያ ለነበረው አገልግሎት በርናባስ እስከታጨ ድረስ ለሰባት ዓመታት ያህል በኪልቅያ እንደ ቆየ የታሪክ አዋቂዎች ይስማማሉ (የሐዋ. 11፡19-26)። በኢየሩሳሌም ይኖሩ የነበሩ ጥቂት አማኞች ጳውሎስን ያውቁት ነበር፤ ይሁን እንጂ በፊት ያጠፋው የነበረውን እምነት አሁን ግን እርሱ ራሱ እየሰበከው ነው የሚለውን ወሬ ከመስማታቸው በቀር በይሁዳ የነበሩ አብያተ ክርስቲያናት አያውቁትም ነበር።

የጳውሎስን የቀድሞ ሕይወት፥ የተለማመደውን ለውጥና ከሌሎች ጋር የነበረውን ግንኙነት በትክክል የተገነዘበ ማንኛውም ሰው መልእክቱን ወይም አገልግሎቱን ተውሶ ወይም ራሱ ፈልስፎ ነው ብሎ እንዴት ሊከሰው ይችላል? የወንጌልን መልእክት የተቀበለው በእርግጥ ከኢየሱስ ክርስቶስ በተሰጠ መገለጥ መሆኑ የማያጠራጥር ነው። ስለዚህ የእግዚአብሔር መሠረታዊ እውነት እንጂ የሰው ፍልስፍና ያልሆነውን ወንጌልን እንዴት እንደምንጠቀምበት እጅግ መጠንቀቅ አለብን።

አንዳንድ ተቺ (ሐያሲ) ምሁራን «ወንጌሉን አጣመውታል» በማለት ጳውሎስን ይከሱታል። የምናየው ማስረጃ ግን የክሱን ተቃራኒ ነው። በምድር ላይ ሲያስተምር የነበረው ክርስቶስ ከሰማይ ሆኖ በጳውሎስ በኩል አስተምሯል። ጳውሎስ ትምህርቱን «ተቀበለው» እንጂ አልፈለሰፈውም (ሮሜ 1፡5፤ 1ኛ ቆሮ. 11፡23፤ 15፡3)። ጳውሎስ በተለወጠ ጊዜ እግዚአብሔር ወደፊት እንደሚገለጥለት ተናግሮታል (የሐዋ. 26፡16) ይህም እውነቱን ሊያሳውቅ እንደ ነበር ግልጽ ነው። ይህ ማለት በአራቱ ወንጌላትና በመልእክቶች ውስጥ የተገለጠው ክርስቶስ አንድ በመሆኑ በክርስቶስና በጳውሎስ መካከል ግጭት አልነበረም። ጳውሎስ መልእክቶቹን ለአብያተ ክርስቲያናት በሚጽፍበት ጊዜ ትምህርቶቹን ከኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርቶች ጋር በአንድ ደረጃ አስቀምጦአል (2ኛ ተሰ. 3፡3-15)። ሐዋርያው ጴጥሮስ እንኳ የጳውሎስን መልእክቶች «ቅዱሳት መጻሕፍት» ብሎ ጠርቶአቸዋል (2 ጴጥ. 3፡15-16)።

የአሁኑም ዘመን «የይሁዲነት አቀንቃኞችም» ቢሆኑ፥ እንደ ቀድሞዎቹ አቻዎቻቸው ሁሉ የጳውሎስን ሥልጣን ይቃወማሉ፤ የሚሰብከውንም ወንጌል እውነት ለማፍረስ ይሞክራሉ። በጳውሎስ ዘመን መልእክታቸው ወንጌልን ከሙሴ ሕግ ጋር መደባለቅ ነበር። በዘመናችን ደግሞ መልእክታቸው ወንጌልን ከሃይማኖታዊ መሪዎች፥ ከሃይማኖታዊ መጻሕፍትና ከሃይማኖታዊ ድርጅቶች ጋር በማያያዝ «እንደዚህ ካላደረግክ... ለመዳን አትችልም» የሚል ነው(የሐዋ. 15፡1)። ብዙውን ጊዜ የቡድናቸው አባል መሆንና ሕጎቻቸውን መጠበቅ ለደህንነት የሚያቀርቧቸው ቅድመ ሁኔታዎች ናቸው። በኢየሱስ፥ በጳውሎስና በሌሎች ሐዋርያት የተሰበከው የጸጋ ወንጌል ቢነገራቸው እንኳ እነርሱ «እግዚአብሔር አዲስ መገለጥን ሰጥቶናል» በማለት ይመልሳሉ።

ጳውሎስ ለእነዚህ ሰዎች የሚሰጠው መልስ አለ፤ «ከተቀበላችሁት የተለየውን ወንጌል ማንም ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን» (ገላ. 1፡9)። አንድ ኃጢአተኛ ክርስቶስን በማመን ዳግም በሚወለድበት ጊዜ (ዮሐ. 3፡1-18) «የሚወለደው ነፃ ሆኖ ነው»። ያዳነው ክርስቶስ ነፃ አውጥቶታል። ከዚያ በኋላ የኃጢአት ወይም የሰይጣን ባሪያ አይደለም፤ ለሰው ሃይማኖታዊ መመሪያም ባሪያ መሆን የለበትም (ገላ. 4፡1-11፤ 5፡1) «እንግዲህ ልጁ አርነት ቢያወጣችሁ በእውነት አርነት ትወጣላችሁ» (ዮሐ. 8፡36)።

ገላትያ 2፡1-10

ከዚያ ወዲያ ከአሥራ አራት ዓመት በኋላ ከበርናባስ ጋር ቲቶን ደግሞ ይዤ ወደ ኢየሩሳሌም ሁለተኛ ወጣሁ፤ እንደ ተገለጠልኝም ወጣሁ፤ ምናልባትም በከንቱ እንዳልሮጥ ወይም በከንቱ ሮጬ እንዳልሆን በአሕዛብ መካከል የምሰብከውን ወንጌል አስታወቅኋቸው፤ ዋኖች ግን መስለው ለሚታዩ ለብቻቸው አስታወቅኋቸው፤ ዋኖች ግን ከእኔ ጋር የነበረ ቲቶ እንኳ የግሪክ ሰው ሲሆን ይገረዝ ዘንድ ግድ አላሉትም፤ ነገር ግን ባሪያዎች ሊያደርጉን በክርስቶስ ኢየሱስ ያለንን አርነታችንን ይሰልሉ ዘንድ ሾልከው በስውር ስለ ገቡ ስለ ሐሰተኞች ወንድሞች ነበረ። የወንጌልም እውነት በእናንተ ዘንድ ጸንቶ እንዲኖር ለአንድ ሰዓት እንኳ ለቅቀን አልተገዛንላቸውም። አለቆች የመሰሉት ግን፥ በፊት ማን እንደነበሩ አይገደኝም፤ እግዚአብሔር የሰውን ፊት አይቶ አያደላም፤ አለቆች የመሰሉት አንዳች እንኳ አልጨመሩልኝምና፥ ተመልሰው ግን ጴጥሮስ ለተገረዙት የሆነው ወንጌል አደራ እንደ ተሰጠው፤ እንዲሁ ለእኔ ላልተገረዙት የሆነው ወንጌል አደራ እንደ ተሰጠኝ አዩ፤ ለተገረዙት ሐዋርያ እንዲሆን ለጴጥሮስ የሠራለት፥ ለእኔ ደግሞ ለአሕዛብ ሐዋርያ እንድሆን ሠርቶአልና። ደግሞ የተሰጠኝን ጸጋ አውቀው፥ አዕማድ መስለው የሚታዩ ያዕቆብና ኬፋ ዮሐንስም እኛ ወደ አሕዛብ እነርሱም ወደ ተገረዙት ይሄዱ ዘንድ ለእኔና ለበርናባስ ቀኝ እጃቸውን ሰጡን፤ ድሆችን እናስብ ዘንድ ብቻ ለመኑን፤ ይህንም ደግሞ ላደርግ ተጋሁ።

- 3 -

የነፃነት ተጋዳይ፥ ክፍል 1

«ይህ አገር ነፃ አገር ሆኖ የሚቆየው ጠንካራ ዜጎች እስከ ኖሩበት ድረስ ብቻ ነው»።

ይህን አባባል የጻፈው የረጅም ጊዜ የዜና ገምጋሚ የሆነው አልመር ዴቪስ ሀዊ ቄር ቦርን ፍሪሀ በሚለው መጽሐፉ ነበር። ይህን አባባል ሐዋርያው ጳውሎስም ሲያስተጋባ እንመለከታለን። ለጳውሎስ በክርስቶስ ያለው ነጻነት ከታዋቂነት ወይም ከራሱ ሕይወት እንኳ እጅግ የላቀ ዋጋ ነበረው። ለዚህ ነፃነት ለመጋደል ፈቃደኛ ነበር።

ጳውሎስ ለክርስትና ነጻነት የመጀመሪያውን ገድል ያደረገው በኢየሩሳሌም ጉባኤ ላይ ሲሆን (ገላ. 2፡1-10፤ የሐዋ. 15፡1-35)፥ ሁለተኛውን ገድል ያደረገው ደግሞ ከጴጥሮስ ጋር በግል ባደረገው ግንኙነት ወቅት ነበር (ገላ. 2፡11-21)። ጳውሎስ ይህንን መንፈሳዊ ጦርነት ለማካሄድ ፈቃደኛ ባይሆን ኖሮ የመጀመሪያው ምዕተ ዓመት ቤተ ክርስቲያን ከአይሁድ ወገን ብቻ የሆነችና ሕግንና ጸጋን ቀይጣ የምትሰብክ ትሆን ነበር። ነገር ግን ጳውሎስ ደፍሮ በወሰደው ጽኑ አቋም ወንጌል ከሕግ አጥባቂነት ነፃ ሆኖ በታላቅ በረከት ለአሕዛብ ደረሰ።

በኢየሩሳሌም ጉባኤ የተካሄደውን ሦስት ገቢራዊ ትርኢት ከመመልከታችን በፊት ከተሳታፊዎቹ ጋር በሚገባ መተዋወቅ አለብን። በእርግጥ ጳውሎስን የምናውቀው ታላቅ የአሕዛብ ሐዋርያ እንደ ሆነ ነው።

ከጳውሎስ የቅርብ ጓደኞች አንዱ በርናባስ ነበር። ጳውሎስ ከኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን ጋር ኅብረት ለማድረግ በሞከረ ጊዜ መንገዱን የከፈተለት በርናባስ ነበር (የሐዋ. 9፡26-28)። በርናባስ ማለት «የመጽናናት ልጅ» ማለት ሲሆን ይህን ሰው ሁልጊዜ የምናገኘው አንድን ሰው ሲያጽናና ነው። በአንጾኪያ ለነበሩ አሕዛብ ወንጌል በደረሰ ጊዜ በእምነታቸው እንዲያበረታታቸው የተላከላቸው በርናባስ ነበር (የሐዋ. 11፡19-24)።

ስለዚህ ከመጀመሪያው ጀምሮ በርናባስ ከአሕዛብ አማኞች ጋር የተያያዘ ነበር። በአንጾኪያ ቤተክርስቲያንን በአገልግሎት እንዲረዳ ጳውሎስን ወደዚያ ያመጣው በርናባስ ነበር (የሐዋ. 11፡25-26)። ጳውሎስና በርናባስ

በማስተማር ብቻ ሳይሆን ድሆችንም በመርዳት በአንድነት አገልግለዋል (የሐዋ. 11:27-30)

በመጀመሪያ ሐዋርያዊ ጉዞው በርናባስ ከጳውሎስ ጋር ነበረ (የሐዋ. 13:1-14:28)፤ በሚሰብኩት ወንጌል የእግዚአብሔርን በረከት አይቷል። ወጣቱ ዮሐንስ ማርቆስ አገልግሎቱን ሲወጣ ከጳውሎስ ጋር አለመግባባት ቢፈጥሩም፥ በኋላ ግን ይህን ወጣት ያበረታታውና ያጽናናው በርናባስ ነበር (የሐዋ. 3:13፤ 15:36-41)። የኋላ ኋላ ጳውሎስ ማርቆስን ለማመስገንና ከወዳጅነቱ ተጠቃሚ ለመሆን ችሎ ነበር (ቆላ. 4:10፤ 2ኛ ጢሞ. 4:11)።

ቲቶ ከጳውሎስ ጋር አብሮ የሚሠራ ከአሕዛብ ወገን የሆነ አማኝ ነው፥ እንደሚታወቀው ቲቶ ጌታን የተቀበለው በጳውሎስ አገልግሎት ነበር (ቲቶ 1:4)። ቲቶ ጳውሎስ በአሕዛብ መካከል ባካሄደው አገልግሎት የተገኘ ፍሬ ሲሆን ወደ ኢየሩሳሌሙም ጉባኤ የተወሰደውም ለአሕዛብ ክርስቲያኖች «ማስረጃ» እንዲሆን ነበር። ቲቶ እጅግ አስቸጋሪ ወደ ነበሩት አብያተ ክርስቲያናት በመሄድና ለችግራቸው መፍትሔ በመስጠት ለጳውሎስ አገልግሎት ከፍተኛ አስተዋፅዖ አድርጓል (2ኛ ቆሮ. 7፤ ቲቶ 1:5)።

የኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን አዕማድ የነበሩት ሦስቱ ሰዎች ጴጥሮስ፥ ዮሐንስና ያዕቆብ ነበሩ። ይህ ያዕቆብ የጌታ ወንድም እንጂ በሄሮድስ የተገደለው ሐዋርያው ያዕቆብ አይደለም (የሐዋ. 12:1-2)። ጴጥሮስን ደግሞ በወንጌላትና በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍት የመጀመሪያ ግማሽ ክፍል ውስጥ ባለው ተቀዳሚነት እናውቀዋለን። ኢየሱስ «ቁልፎቹን» የሰጠውና የእምነትን በር ለአይሁዶች (የሐዋ. 2) ለሳምራውያንና (የሐዋ. 8) ለአሕዛብ (የሐዋ. 10) የከፈተ ጴጥሮስ ነበር። ዮሐንስንም ቢሆን የኢየሱስ የቅርብ ደቀ መዛሙርት ከነበሩት ሦስት ሐዋርያት አንዱ በመሆኑና ቃሉን ለማገልገል ከጴጥሮስ ጋር ተያይዞ በመቅረቡ የምናውቀው ሐዋርያ ነው (የሐዋ. 3:1፥11፤ 4:13)።

ምናልባት ሰፋ ባለ መንገድ ልናስተዋውቀው የሚያስፈልገው ያዕቆብን ሊሆን ይችላል። በወንጌላት በተመዘገበው ታሪክ እንደምናየው ማርያምና ዮሴፍ ሌሎች ልጆች ነበሯቸው፤ ከእነርሱም አንዱ ያዕቆብ ነበር (ማቴ. 13:55፤ ማር. 6:3) (ኢየሱስ የተወለደው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንጂ በተፈጥሮአዊ ልደት እንዳልሆነ የተረጋገጠ ነው ማቴ. 1:18-25፤ ሉቃስ 1:26-28)። የጌታ ወንድሞችና እህቶች ኢየሱስ በምድር ላይ እያገለገለ

ሳለ በእርሱ አላመኑም ነበር (ዮሐ. 7፡1-5)። ይሁን እንጂ፥ «ወንድሞቹ» ከመጀመሪያይቱ ቤተ ክርስቲያን ጋር ኅብረት እንደ ነበራቸው እንመለከታለን (የሐዋ. 1፡13-14)። ከሞት የተነሣው ክርስቶስ ለያዕቆብ እንደ ተገለጠለትና የያዕቆብ ሕይወት አቅጣጫ የተለወጠው በዚህ ምክንያት እንደ ነበር ጳውሎስ ይናገራል (1ኛ ቆሮ. 15፡5-7)። ያዕቆብ በኢየሩሳሌም የነበረችው የመጀመሪያይቱ ቤተክርስቲያን መሪ ነበር (የሐዋ. 15ን እና 21፡18 ተመልከት)። የያዕቆብን መልእክት የጻፈው እርሱ ሲሆን ይህ መልእክትና የሐዋ. 21፡18 በአስተሳሰብ ዝንባሌው አይሁዳዊ እንደ ነበር ያመለክቱናል።

ከላይ ከጠቀስናቸው ሰዎች ሌላ «ሐዋርያትና ሽማግሌዎች» (የሐዋ. 15፡4፥6)፥ እንዲሁም ወደ ስብሰባው ሾልከው በመግባት አማኞች በክርስቶስ ያላቸውን ነፃነት ለመግፈፍ የሞከሩ ሐሰተኛ ወንድሞች በዚህ ጉባዔ ውስጥ ነበሩ (ገላ. 2፡4)። እነዚህ ያለጥርጥር የይሁዲነት አቀንቃኞች ሲሆኑ የጳውሎስን እግር በየቤተክርስቲያኑ እየተከተሉ በእርሱ ትምህርት የተለወጡ ሰዎችን ያጠምዱ ነበር። ጳውሎስ እነዚህን ሰዎች «ሐሰተኛ ወንድሞች» ብሎ መጥራቱ የሚያመለክተው በጉባዔው ለመጠቀም የሚሞክሩ እንጂ እውነተኛ ክርስቲያኖች እንዳልነበሩ ነው።

እንግዲህ በጉባዔው ላይ የተገኙት የተለያዩ ገጸ ባሕርያት ይህን የሚመስሉ ነበሩ፤ ስለ ድርጊቱ በሙላት ለመረዳት የሐዋ. 15ን ከገላትያ 2፡1-10 ጋር በማያያዝ ማንበቡ ብዙ ሊረዳን ይችላል።

ገቢር 1. የግል ምክክር (2፡1-2)

ጳውሎስና በርናባስ ከመጀመሪያው ሐዋርያዊ ጉዞአቸው ወደ አንጾኪያ የተመለሱት እግዚአብሔር «ለአሕዛብም የሃይማኖትን ደጅ እንደ ከፈተላቸው» (የሐዋ. 14፡27) በማየታቸው እጅግ በመደነቅና በመደሰት ነበር። በኢየሩሳሌም የሚገኙት ሕግ አክራሪ አይሁዳውያን ግን ጳውሎስና በርናባስ ባቀረቡት መግለጫ ተበሳጭተው ወደ አንጾኪያ መጡና አንድ አሕዛብ ክርስቲያን ከመሆኑ በፊት የአይሁድን እምነት መቀበል አለበት በማለት ያስተምሩ ጀመር (የሐዋ. 15፡1)።

አሕዛብ እንዲቀበሉት የተጠየቁት ግርዘት ከአብርሃም ጊዜ ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ በጣም አስፈላጊ አይሁዳዊ ሥርዓት ነበር (ዘፍጥረት 17)። ግርዘትን መቀበል ማለት ደግሞ ጠቅላላውን የአይሁድ ሕግ መቀበልና

መፈጸም ማለት ነበር። አንዳንድ የዘመናችን አብያተ ክርስቲያናት የጥምቀትን መንፈሳዊ ትርጉም በመዘንጋት ውጫዊ ሥነ-ሥርዓት እንዳደረጉት ሁሉ አይሁዳውያንም የግርዘትን ውስጣዊና መንፈሳዊ ትርጉም ባለመረዳት እንዲሁ ሥርዓቱን ብቻ ነበር የያዙት (ዘዳ. 10፡16፤ ኤር. 4፡1-4፤ ሮሜ 2፡25-29)። እውነተኛ ክርስቲያን ውስጣዊ የልብ ግርዘትን ስለ ተለማመደ (ቆላ. 2፡10-11) ምንም ዓይነት የሥጋ ግርዘት አያስፈልገውም (ፊልጵ. 3፡1-3)።

ጳውሎስና በርናባስ በወንጌል እውነት እነዚህን ሰዎች ባፋጠጡዋቸው ጊዜ የጋለ ክርክር ተፈጥሮ ነበር (የሐዋ. 15፡2)። ለዚህ ጥያቄ መልስ ለማግኘትና ክርክሩን ለማርገብ መሪዎች የሚገኙበት ስብሰባ በኢየሩሳሌም ማካሄድ ከሁሉ የተሻለ እንደሚሆን ውሳኔ ላይ ተደረሰ። ይህ «የኢየሩሳሌም ጉባኤ» ከሁሉም አብያተ ክርስቲያናት የተውጣጡ ተወካዮች የተገኙበት የአንዳንድ እምነት ክፍል አጠቃላይ ስብሰባ ዓይነት ሊሆን እንደሚችል ልናስብ አይገባም። የኢየሩሳሌሙ ስብሰባ ይህ ዓይነት አልነበረም። ጳውሎስ፥ በርናባስ፥ ቲቶና ሌሎች ከአንጾኪያ የመጡ ሰዎች ከአይሁድ ሕግ ፍጹም ነፃ በሆነ መንገድ የዳኑትን አሕዛብ ክርስቲያኖች ወክለው ተገኙ። ይሁን እንጂ፥ ጳውሎስ በአሕዛብ ግዛት የመሠረታቸው አብያተ ክርስቲያናት ተወካዮቻቸውን መርጠው አልላኩም ነበር።

ከአንጾኪያ የተላከው ቡድን አባላት ወደ ኢየሩሳሌም በደረሱ ጊዜ ከቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጋር የግል ስብሰባ አደረጉ። ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም የሄደው «በመገለጥ» ማለትም ጌታ ስለ ላከው እንጂ ቤተክርስቲያን ስለ ላከችው አልነበረም (ገላ. 2፡1 እና 1፡12ን አነጻጽር)። ወደ ዋናው ጉባዔ የተባበረ የአንድነት ውሳኔ ይዘው መቅረብ ይችሉ ዘንድ ከመሪዎቹ ጋር በቅድሚያ እንዲነጋገር እግዚአብሔር ለጳውሎስ ጥበብን ሰጠው።

ጳውሎስ «ምናልባት በከንቱ እንዳልሮጥ ወይም በከንቱ ሮጬ እንዳልሆን» (ቁ. 2) ማለቱ፥ ለመልእክቱ ወይም ለአገልግሎቱ እርግጠኝነት አልነበረውም ማለት አይደለም። ወደ ጉባኤው በሚሄድበት ወቅት የነበረው የመንፈስ ጥንካሬ አንዳችም ጥርጣሬ እንደሌለው የሚያሳይ ነበር (የሐዋ. 15፡3)። ጳውሎስን ያሳሰበው ጉዳይ ቢኖር ወደፊት ወንጌል በአሕዛብ ሕይወት ውስጥ የሚኖረው ስፍራ ነበር። ግልጽ በሆነ ሁኔታ ከክርስቶስ የተቀበለው አገልግሎትም ወንጌልን ለአሕዛብ ማዳረስ ነበረበት። ምናልባት የቤተክርስቲያን «አዕማድ» የነበሩት ሰዎች አቋም ከአይሁዲነት አቀንቃኞች

ጋር ቢስማማ ወይም ደግሞ የአቋም መለሳለስ ቢደረግ የጳውሎስ አገልግሎት ሥጋት ላይ በወደቀም ነበር። ጳውሎስ ከአጠቃላይ ጉባኤው ጋር ከመነጋገሩ በፊት የመሪዎችን ማረጋገጫ አስቀድሞ ባያገኝ ኖሮ በጉባዔው ውስጥ ሦስት ቦታ መከፋፈል ሊከሰት በቻለ ነበር።

የዚህ ግላዊ ምክክር ውጤት ምን ነበር? ሐዋርያትና ሽማግሌዎች የጳውሎስን ወንጌል ትክክለኛነት አረጋገጡ። በእርሱ ወንጌል ላይ አንዳችም ነገር አልጨመሩም (ገላ. 2:6)። ይህንንም በማድረጋቸው የይሁዲነት አቀንቃኞች አቋም ስህተት እንደሆነ ግልጽ አደረጉ። ሆኖም ይህ ግላዊ ምክክር የጉዳዩ መጀመሪያ ብቻ ነበር።

ገቢር 2. ዋናው የመሪዎች ጉባኤ (2:3-5)

ሉቃስ የኢየሩሳሌምን ጉባኤ ታሪካዊ ዘገባ ጽፏል (የሐዋ. 15:6-21)። በዚህ ጉባዔ ላይ ከጴጥሮስ ጀምሮ በርካታ ምስክሮች የእግዚአብሔርን የጸጋ ወንጌል ጉዳይ አቀረቡ (የሐዋ. 1:7-11)። በመጀመሪያ የእግዚአብሔርን ወንጌል ለአሕዛብ እንዲያደርስ የተመረጠ ጴጥሮስ ነበር (የሐዋ. 10)። ስለዚህ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን ለአይሁዶች እንደ ሰጠ ሁሉ ለሚያምኑበት አሕዛብም እንደ ሰጣቸው ለጉባኤው አስገነዘበ። በሁለቱም መካከል «ልዩነት የለም» ሲል አረጋገጠ።

ይሁን እንጂ በአይሁድና በአሕዛብ መካከል ለበርካታ ምእተ ዓመታት የቆየ ልዩነት ስለ ነበር ለመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ይህን መቀበል አስቸጋሪ ነበር (ዘሌ. 11:43-47፤ 20:22-27)። ኢየሱስ በመስቀል ላይ በመሞት በአይሁድና በአሕዛብ መካከል የነበረውን ልዩነት በማስወገዱ (ኤፌ. 2:11-12) በክርስቶስ ውስጥ የዘር ልዩነት አልነበረም (ገላ. 3:28)። ጴጥሮስ በዚህ ጉባዔ ባደረገው ንግግር የደህንነት መንገድ አንድ ብቻ፥ ይህም በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ብቻ እንደ ሆነ ግልጽ አደረገ።

ከዚያም በኋላ ጳውሎስና በርናባስ እግዚአብሔር በአሕዛብ መካከል ስላደረገው ነገር ለጉባኤው ተናገሩ (የሐዋ. 15:12)። ምን አይነት ግሩም «የወንጌል አገልግሎት ዜና» ነበር! በዚያ የነበሩ «ሐሰተኛ ወንድሞች» ከጳውሎስና በርናባስ ጋር ቢከራከሩም እንኳ ሁለቱ የመስቀል ወታደሮች እጃቸውን አልሰጡም። ጳውሎስ «የወንጌል እውነት» በአሕዛብ መካከል እንዲሰፋፋ ፍላጎት ነበረው (ገላ. 2:5)።

እዚህ ላይ ቲቶ «መፈተኛ» የተደረገ ይመስላል። ቲቶ ከአሕዛብ ወገን ጌታን የተቀበለ ሰው ሲሆን፥ የግርዘትን ሥርዓት ግን አልፈጸመም። ይህም ሆኖ ደህንነትን ማግኘቱ ለሁሉም ግልጽ ነበር። እንግዲያስ የይሁዲነት አቀንቃኞች «እንደ ሙሴ ሥርዓት ካልተገረዛችሁ ትድኑ ዘንድ አትችሉም» (የሐዋ. 15፡1) ማለታቸው ትክክል ቢሆን ኖሮ ቲቶ ደህንነትን ሊያገኝ አይችልም ነበር ማለት ነው። እርሱ ግን የዳነና መንፈስ ቅዱስ እንዳለው በሕይወቱ ማረጋገጫ ያለው ሰው ነበር። ስለዚህ የይሁዲነት አቀንቃኞች ተሳስተዋል ማለት ነው።

እዚህ ላይ ሌላው የጳውሎስ ረዳት የነበረውን ጢሞቴዎስን መመልከት ሊረዳን ይችላል (የሐዋ. 16፡1-3 ተመልከት)። ጳውሎስ ቲቶ እንዲገረዝ ፈቃደኛ ባለመሆኑና በጢሞቴዎስ መገረዝ ግን መስማማቱ የአሳብ ያለ መረጋጋት እንደ ነበረበት የሚያመለክት አይደለም። ምክንያቱም ከሁለቱም ጋር ሁለት የተለያዩ ጉዳዮች በመያያዛቸው ነው። የጢሞቴዎስን ጉዳይ ስንመለከት፥ ጳውሎስ እርሱን ወደ ክርስቶስ ለማምጣት ሲል ለአይሁድ ሕግ አልተገዛም ነበር። ጢሞቴዎስ ከፊል አይሁዳዊ ከፊል ደግሞ አሕዛብ ስለ ነበር ምናልባትም የእርሱ ያለመገረዝ በእስራኤል ሕዝብ መካከል ለነበረው አገልግሎቱ እንቅፋት ሊሆንበት በቻለም ነበር። ቲቶ ግን ሙሉ በሙሉ አሕዛብ ነበር። ስለዚህ ለአይሁድ ሕግ ቢገዛ ኖሮ በክርስትና ልምምዱ ውስጥ የጎደለው ነገር እንዳለ ባመለከተም ነበር። ቲቶን መግረዝ ፍርሃትንና የአቋም መለሳለስ ሲሆን፥ ጢሞቴዎስን ያለመገረዝ ማለት ግን በአገልግሎቱ ላይ የማያስፈልግ ችግር መፍጠር ማለት ነበር።

የቤተ ክርስቲያን መሪ የነበረው ያዕቆብ የቀረቡትን የመከራከሪያ አሳቦችና የተሰጣቸውን እልባት በማስመልከት ማጠቃለያ ንግግር አቀረበ (የሐዋ. 15፡13-21)። ራሱ አይሁዳዊ ቢሆንም አንድ አሕዛብ ክርስቲያን እንዲሆን ከተፈለገ አስቀድሞ አይሁዳዊ መሆን እንደማያስፈልገው ግልጽ አደረገ። እግዚአብሔር ለዚህ ዘመን ያለው ዕቅድ «ለስሙ የሚሆን ወገንን ከአሕዛብ ይወስድ ዘንድ...» ነው። አይሁዳውያንና አሕዛብ የሚድኑት በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ብቻ ነው። ደህንነትን እንዳይቀበሉ እንቅፋት እንዳይሆናቸው በማለት ያዕቆብ በጉባኤው የተገኙት ክርስቲያን አሕዛብን አይሁዳውያንን ለማሰናከል ምንም ነገር እንዳያደርጉ ጠየቃቸው። ጳውሎስ በዚህ ጉባኤ የነበረውን ድርሻ በአሸናፊነት ተወጣ።

በቅድሚያ መሪዎች የጳውሎስን ወንጌል በመቀበላቸው የእርሱ አመለካከት የበላይነትን አግኝቶ ነበር። እንደዚሁም ጉባኤው ከጳውሎስ ጋር በመስማማት የአይሁድ እምነት አቀንቃኞችን በተቃወመበት ጊዜ ጳውሎስ በድጋሚ አሸነፈ።

ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች በጻፈው መልእክት ውስጥ የኢየሩሳሌምን ጉባኤ ውጤት በተደጋጋሚ አንጸባርቋል። ጳውሎስ፥ ጴጥሮስ በጠቀሰው አይነት (የሐዋ. 15፡10) ተመሳሳይ ማስጠንቀቂያ በመጠቀም «የባርነት ቀንበር» (የሐዋ. 5፡1) ሲል ጽፏል። በተለይም ግርዘትና (2፡3፤ 5፡3-4፤ 6፡12-13) እንደዚሁም እንደ ነፃነትና ባርነት የመሳሰሉት ነጥቦች በተደጋጋሚ ተጠቅሰዋል (ገላ. 2፡4፤ 4፡3፥9፥ 21-31፤ 5፡1)።

ጳውሎስና ጓደኞቹ ለወንጌል ነፃነት በድፍረት የወሰዱትን ጽኑ አቋም፥ ከብዙ መቶ ዓመታት በኋላ በዚህ ዘመን የምንገኝ ክርስቲያኖችም ልናደንቀው ይገባል። የጳውሎስ ትልቁ አትኩሮት «የቤተክርስቲያን ሰላም» ሳይሆን «የወንጌል እውነት» ነበር (2፡5፥14)። እግዚአብሔር ከላይ የላከው ጥበብ «በመጀመሪያ ንጽሕት ናት በኋላም ታራቂ...» (ያዕቆብ 3፡17) የሚል ነው። «የሚጠይቀውን ዋጋ ሁሉ ከፍሎ ሰላምን ማውረድ» የሚለው አባባል ግን የጳውሎስ አገልግሎት ፍልስፍና እንዳልነበር ሁሉ የእኛም ሊሆን አይገባም።

የጸጋ ጠላቶች ከጳውሎስ ጊዜ ጀምሮ ግልጽና ቀጥተኛ በሆነው በእግዚአብሔር የጸጋ ወንጌል ላይ የተለያዩ ነገሮችን ለመጨመር ይጥራሉ። ሰው ደህንነትን የሚያገኘው በክርስቶስ በማመንና በተለያዩ ተጨማሪ ነገሮች ነው ይላሉ። እነዚህም ተጨማሪ ነገሮች መልካም ሥራ፥ አሥርቱ ሕግጋት፥ ጥምቀት፥ የቤተ ክርስቲያን አባልነት፥ ሃይማኖታዊ ሥርዓትና የመሳሰሉት ሲሆኑ፥ ጳውሎስ ይህንን የሚያስተምሩ አስተማሪዎች የተሳሳቱ እንደ ሆኑ ግልጽ አድርጓል። ጳውሎስ ኢየሱስ ክርስቶስን ማዕከል ከሚያደርገው ከእግዚአብሔር የጸጋ ወንጌል የተለየ ወንጌል የሚሰብከውን ማንኛውንም ፍጡር (ሰው ወይም መልአክ) የተረገመ እንዲሆን አውጇል (ገላ. 1፡6-9፤ በተጨማሪም ወንጌል የሚለውን ቃል ትርጉም ለመረዳት 1ኛ ቆሮ. 15፡1-7 ተመልከት)። ወንጌልን ማጣመም እንደ ቀላል የሚታለፍ ነገር አይደለም።

ገቢር 3. ግለሰባዊ ማረጋገጫ (2:6-10)

የይሁዲነት አቀንቃኞች ተስፋ ያደረጉት የኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን መሪዎች ከጳውሎስ ጋር አይስማሙም ብለው ነበር። ከዚህ በተጻራሪ ግን ጳውሎስ በግለሰቦችም ሆነ በቤተክርስቲያን መሪዎች አቋም ብዙም እንዳልተነካ ግልጽ አደረገ። በእርግጥ ያከብራቸው ነበር፤ ባያከብራቸው ኖሮ ከእነርሱ ጋር በግል ምክክር ባላደረገም ነበር። የሚያደርጉትን ተጽዕኖ በመፍራት ግን ከአቋሙ ለመለሳለስ ወይም የእርሱ ደጋፊ ሊያደርጋቸውም አልሞከረም ነበር። ዋናው ፍላጎቱ በሕይወቱና በአገልግሎቱ በመሥራት ላይ የነበረውን «የእግዚአብሔርን ጸጋ» እንዲያውቁለት ነበር (ገላ. 2:7)። እነርሱም ይህን አድርገዋል።

ጉባኤው የጳውሎስን ወንጌል እውነተኛነት በማረጋገጥና የእርሱን ጠላቶች በመቃወም ብቻ አልተወሰነም። የጳውሎስን አገልግሎት በማበረታታት እግዚአብሔር በአሕዛብ መካከል ሊሠራ ያለውን የወንጌል ሥራ በተለይ ለጳውሎስ እንደ ሰጠ ይፋ አደረገ። በጳውሎስ መልእክት ወይም አገልግሎት ላይ ምንም ለመጨመር አልፈለገም፤ አንዳችም ነገር ላለመቀነስም ደግሞ ተጠንቅቋል። ለአይሁድና ለአሕዛብ አንዱ ወንጌል ብቻ እንዲሰበክ ተስማምቷል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ እግዚአብሔር የተለያዩ የአገልግሎት መስኮችን ለተለያዩ ሰዎች እንደ ሰጠ መሪዎች ተገንዝበው ነበር። የቆርኔሌዎስን ቤተሰብ (የሐዋ. 10) እና እንዲሁም ሳምራውያንን (የሐዋ. 8) በአንድ ጊዜ ጉብኝት ከማገልገሉ በቀር የጴጥሮስ አገልግሎት የሚያተኩረው በአይሁዳውያን ላይ ብቻ ነበር። ጳውሎስ ደግሞ በአሕዛብ መካከል የእግዚአብሔር ልዩ አምባሳደር እንዲሆን የተጠራ ነበር። በዚህ እውነታ መሠረት እያንዳንዱ ሰው እግዚአብሔር በመደበው ክልል እንዲያገለግል ስምምነት ላይ ተደረሰ።

«ለተገረዙት የሆነው ወንጌል» ና «ላልተገረዙት የሆነው ወንጌል» ሁለቱ የተለያዩ መልእክቶች አይደሉም። እውነተኛው ወንጌል አንድ ብቻ እንደ ሆነ ቀደም ብሎ ስምምነት ላይ ተደርሷል። በአገልግሎት ክልል አንጻር ግን አንድ ለአይሁድ አንድ ደግሞ ለአሕዛብ የሆነ ሁለት የተለያዩ የአገልግሎት ክልሎች ነበሩ። ጴጥሮስና ጳውሎስ የሚሰብኩት ወንጌል አንድ ነበር። አንዱ ጌታ በሁለቱም በመጠቀም ይሥራ እንጂ (ገላ. 2:8) የሚያገለግሉት ግን የተለያዩ ሕዝቦችን ነበር።

ይህም ማለት ጳውሎስ አይሁዶችን ወደ ክርስቶስ ለማምጣት ጥረት እንዳያደርግ ማለት አይደለም። ይልቁኑ የሥጋ ወገኖቹ ለሆኑት አይሁድ ከፍተኛ ሸክም በልቡ ይሰማው ነበር (ሮሜ 9፡1-3)። ጳውሎስ ወደ አንድ ከተማ በሚደርስበት ጊዜ በዚያ ከተማ የአይሁድ ምኩራብ ካለ በቅድሚያ በመሄድ አገልግሎቱን በገዛ ሕዝቡ መካከል ይጀምር ነበር። ጴጥሮስም ቢሆን አሕዛብን ጨርሶ እንዳያገለግል ማለት አይደለም፤ ነገር ግን እያንዳንዱ ሰው በመንፈስ ቅዱስ በተመደበለት የአገልግሎት ክልል ላይ ያተኩር ነበር ማለት ነው። ያዕቆብ፥ ጴጥሮስና ዮሐንስ ወደ አይሁዳውያን ሲሄዱ ጳውሎስ ደግሞ አሕዛብን ለማገልገል ሄደ (ገላ. 2፡9 ላይ «አሕዛብ» የሚለው ቃል ከአይሁድ ሕዝብ በስተቀር የቀረውን ዓለም ሕዝብ የሚያካትት ነው)።

የኢየሩሳሌም ጉባኤ ሲጀመር ለመከፋፈልና ለጸብ ሰፊ በር ቢኖርም የተፈጸመው ግን ትብብርና ስምምነት ጎልቶ በታየበት ሁኔታ ነበር። «ወንድሞች በኅብረት ቢቀመጡ እነሆ መልካም ነው፤ እነሆም ያማረ ነው» [መዝ. (133)፡ 1]። ይህ ዓይነት ሕብረት በዘመናችን አብያተ ክርስቲያናት መካከል መኖሩ በጣም ጠቃሚ ነው።

ሁላችንም የምንሰብከው አንዱን ወንጌል ነው። በዚህም የክርስቶስን ቤተክርስቲያን ለመገንባት በአንድነት ለመሥራት እንጥራለን። ሆኖም እግዚአብሔር ለተለያዩ ስፍራዎችና የተለያዩ አገልግሎቶች የተለያዩ ሰዎችን የመጥራቱን እውነት ልንገነዘብ ያስፈልጋል። ክርስቶስን በሚያውቁና በሚወዱ ሰዎች መካከል «ውድድር» የሚባል ነገር በፍጹም ሊኖር አይገባም። ጴጥሮስ ታላቅ ሰው ነበር፤ ምናልባትም ዋናው መሪ ሐዋርያ ነው፤ አዲስ መጥ የሆነው ጳውሎስ በጌታ ምሪት ወደ አገልግሎቱ በመጣ ጊዜ ግን አገልግሎቱን የተቀበለው በታላቅ ደስታ ነበር። በምዕራፍ 1 ላይ ጳውሎስ ከሌሎች ሐዋርያት በተለየ ሁኔታ ራሱን ችሎ እንዴት እንደሚያገለግል ተናግሮ ነበር፤ አሁን ደግሞ በምዕራፍ 2 ከሐዋርያት ጋር በመደጋገፍ እንዴት እንደሚሠሩ ይናገራል። ጳውሎስ እንደ ፈለገው ለመሆን ነፃነት ቢኖረውም በወንጌል አገልግሎት ውስጥ ግን ከሐዋርያት ጋር በፈቃደኝነትና በኅብረት ይሠራ ነበር።

ቀጥለን ከሥነ መለኮት ትምህርት ወደ ተግባራዊ ልምምድ እናልፋለን። ይህም ድሆችን ስለመርዳት የተመለከተ ይሆናል (ቁ. 10)። እነዚህ ነገሮች በአንድነት የሚሄዱ መሆናቸው የማያጠራጥር ነው። ትክክለኛ የእምነት ትምህርትም ቢሆን የክርስቲያናዊ ተግባር ምትክ ጨርሶ ሊሆን አይችልም

(ያዕ. 2፡14-26)። ብዙ ጊዜ አብያተ ክርስቲያናት በስብሰባቸው ላይ ስለ ተለያዩ ነገሮች ውይይት ያደርጋሉ፤ ይህን በችግር ማጥ የወደቀውን ዓለም ለመርዳት ግን ምንም እርምጃ ሲወስዱ አይታዩም። ጳውሎስ ግን ለድሆች ሁልጊዜ ትኩረት በመስጠት (የሐዋ. 11፡27-30) የሚያቀርቡትን አሳብ ለመከተል ደስተኛ ነበር።

ምንም እንኳ ይህ ጉባኤ የተጠናቀቀው ጳውሎስና ሌሎች መሪዎች ስምምነት ላይ ከደረሱ በኋላ ቢሆንም ለችግሩ ዘላቂ መፍትሔ አስገኝቶአል ማለት አይደለም። ነገር ግን የይሁዲነት አቀንቃኞች ጳውሎስ ሥራ ውስጥ ጣልቃ በመግባት የቆረቆራቸውን አብያተ ክርስቲያናት መውረራቸውን ቀጠሉ። ጳውሎስ የዚህን ጉባኤ ውጤት መልካም የምሥራች በአንጾኪያ፥ ሶርያና ኪልቅያ ለሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት (የሐዋ. 16፡4)ና እንዲሁም በሌሎችም አካባቢዎች ለሚገኙ ላገለገለባቸው አብያተ ክርስቲያናት አበሰረ (የሐዋ. 16፡4)። የይሁዲነት አቀንቃኞች ግን ከአንጾኪያ ጀምረው ጳውሎስን እግር በእግር መከተል አልተዉም። (ተደብድቦ እንደሚጮህ ውሻ ሆነውበት ነበር። ፊልጵ. 3፡1-3 ተመልከት)። እንዲያውም በአንጾኪያ ጴጥሮስን እንኳ ወደ ዓላማቸው እንዲያዘነብል ለማድረግ ችለው ነበር (ገላ. 2፡11-21 ተመልከት)።

እነዚህ የይሁዲነት አቀንቃኞች ወደ ገላትያ አብያተ ክርስቲያናት የሄዱት የሐሰት ትምህርት እንከርዳዳቸውን ለመዝራት ነበር፤ ከዚህም የተነሣ ጳውሎስ ይህን የምናጠናውን የገላትያ መልእክት ጻፈ። አንዳንድ ሊቃውንት መልእክቱን የላከው ከኤፌሶን ወይም ከቆሮንቶስ ሆኖ ነው ቢሉም፥ ጳውሎስ ግን የጻፈው ከኢየሩሳሌሙ ጉባኤ በኋላ ብዙም ጊዜ ሳይቆይ ከአንጾኪያ ይሆናል። እነዚህ ታሪካዊ ዝርዝር ሁኔታዎች ጠቃሚ ቢሆኑም የመልእክቱን ጭብጥ አሳብ ለመረዳት ግን የግድ አስፈላጊ አይደሉም። በተጨማሪም የገላትያ መልእክት ጥንታዊ መልእክት ነው ለማለት እንችላለን፤ ያመነውን፥ የሰበከውንና በቀጣይ አገልግሎቱ የጻፈበትን ዋና ዋና የእምነት ትምህርቶች ሁሉ እናገኝበታለን።

እነሆ የትዕይንቱ ገቢር መጋረጃ በዚህ የተዘጋ ቢሆንም፥ የሚቀጥለውን ገቢር እንመለከት ዘንድ መጋረጃው እንደገና ይከፈታል። አሁን ደግሞ የእግዚአብሔር «የነጻነት ተጋዳይ» የሆነው ጳውሎስ ስለ ወንጌል እውነት ሲከራከር እንመለከታለን፤ በዚህ ወቅት ግን ከጴጥሮስ ጋር ነው።

ገላትያ 2፡11-21

ነገር ግን ኬፋ ወደ አንጾኪያ በመጣ ጊዜ ፊት ለፊት ተቃወምሁት፥ ይፈረድበት ዘንድ ይገባ ነበርና። አንዳንድ ከያዕቆብ ዘንድ ሳይመጡ ከአሕዛብ ጋር አብሮ ይበላ ነበርና፤ በመጡ ጊዜ ግን ከተገረዙት ወገን ያሉትን ፈርቶ ያፈገፍግ ነበርና ከእነርሱ ተለየ። የቀሩትም አይሁድ ደግሞ፥ በርናባስ ስንኳ በግብዝነታቸው እስከ ተሳበ ድረስ፥ ከእርሱ ጋር አብረው ግብዞች ሆኑ። ነገር ግን እንደ ወንጌል እውነት በቅንነት እንዳልሄዱ ባየሁ ጊዜ በሁሉ ፊት ኬፋን፡- አንተ አይሁዳዊ ሳለህ በአይሁድ ኑሮ ያይደለ በአሕዛብ ኑሮ ብትኖር፥ አሕዛብ በአይሁድ ኑሮ ሊኖሩ እንዴት ግድ አልሃቸው? አልሁት። እኛ በፍጥረት አይሁድ ነን ኃጢአተኞችም የሆኑ አሕዛብ አይደለንም፤ ነገር ግን ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን እንዲጸድቅ እንጂ በሕግ ሥራ እንዳይሆን አውቀን፥ ሥጋን የለበሰ ሁሉ በሕግ ሥራ ስለማይጸድቅ፥ እኛ ራሳችን በሕግ ሥራ ሳይሆን በክርስቶስ እምነት እንጸድቅ ዘንድ በክርስቶስ ኢየሱስ አምነናል። ነገር ግን በክርስቶስ ልንጸድቅ የምንፈልግ ስንሆን ራሳችን ደግሞ ኃጢአተኞች ሆነን ከተገኘን፥ እንግዲያስ ክርስቶስ የኃጢአት አገልጋይ ነዋ? አይደለም። ያፈረስሁትን ይህን እንደ ገና የማንጽ ከሆንሁ ራሴ ሕግ ተላላፊ እንድሆን አስረዳለሁና። እኔ ለእግዚአብሔር ሕያው ሆኜ እኖር ዘንድ በሕግ በኩል በሕግ ሞቼ ነበርና። ከክርስቶስ ጋር ተሰቅዬአለሁ፤ እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም፤ ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል፤ አሁንም በሥጋ የምኖርበት ኑሮ በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው ነው። የእግዚአብሔርን ጸጋ አልጥልም፤ ጽድቅስ በሕግ በኩል ከሆነ እንኪያስ ክርስቶስ በከንቱ ሞተ።

የነፃነት ታጋዳይ፥ ክፍል ሁለት

«ነፃነት ያላሰለሰ ተጋድሎን ትጠይቃለች!» ይህን የተናገረው ዌንዴል ፊልፕስ የተባለው ሰው በ1852 እ.አ.አ. በማሳቹሴትስ ከተማ በተደረገው ጸረ ባርያ ፍንገላ ስብሰባ ላይ ነበር። አባባሉ በፖለቲካው መስክ ብቻ ሳይሆን በመንፈሳዊውም ዓለም ውስጥ እውነትነት አለው። ጳውሎስ የእግዚአብሔርን የጸጋ ወንጌል ከሚኖርበት ክልል ውጭ ወደ ተለያዩ ግዛቶች ለማዳረስ ሕይወቱን ጭምር ለአደጋ በማጋለጥ እንኳ አገልግሏል። እርሱም ሆነ የቆረቆራቸው አብያተ ክርስቲያናት በክርስቶስ ያላቸው ነጻነት በጠላት እንዲገፈፍ ፈቃዱ አልነበረም። የወንጌልን እውነት በተመለከተ ከሐዋርያው ጴጥሮስ፥ ከበርናባስና ከአንዳንድ የያዕቆብ ጓደኞች ጋር ፊት ለፊት እንዲጋፈጥ ያደረገውም ይህ ውስጣዊ «መንፈሳዊ ጽናት» ነበር። የአሁኑ ድራማ ደግሞ ሦስት ክፍሎችን ያካትታል።

1. የጴጥሮስ ግርሻ (2፡11-13)

በሐዋርያት ሥራ 15 ከተገለጸው እጅግ ጠቃሚ ጉባኤ ጥቂት ቆይቶ ጴጥሮስ ከኢየሩሳሌም ወደ አንጾኪያ መጣ። በመጀመሪያ የምናስተውለው ነገር ጴጥሮስ ያን ጊዜ ስለ ነበረው ነፃነት ነው። ያለአንዳች ልዩነት ከአይሁድና ከአሕዛብ አማኞች ሁሉ ጋር ኅብረት ያደርግ ነበር። «ከአሕዛብ ጋር መብላት» ማለት እነርሱን መቀበል ማለት ነው፤ በክርስቶስ እንዳለ አንድ ቤተሰብ አሕዛብን ከአይሁድ ጋር በእኩልነት መመልከት ማለት ነው።

ጴጥሮስ ወግ አጥባቂ አይሁዳዊ ሆኖ ያደገ ሰው ስለ ነበር ለእርሱ ይህን ትምህርት ለመቀበል ቀላል አልነበረም። ኢየሱስ በመስቀል ላይ ከመሞቱ በፊት ከጴጥሮስ ጋር ባሳለፈው ጊዜ ይህን ትምህርት አስተምሮት ነበር (ማቴ. 15፡1-20)። መንፈስ ቅዱስ ደግሞ ጴጥሮስን የሮማ መቶ አለቃ ወደ ነበረው ወደ ቆርኔሌዎስ ቤት በላከው ጊዜ ይህን ጉዳይ እንደገና አረጋግጦለት ነበር (የሐዋ. 10)። በተጨማሪም ይህ እውነት በኢየሩሳሌም የመሪዎች ጉባኤ ላይ ጸንቶአል (የሐዋ. 15)። በዚህ ጉባኤ ከነበሩ ዋነኛ ምስክሮች አንዱ ጴጥሮስ ነበር።

ጴጥሮስን በዚህ ተግባሩ ከመንቀፋችን በፊት ከምናውቃቸው የመጽሐፍ ቅዱስ መሠረታዊ ትምህርቶች ለስንቱ ታዛዥ እንደሆንን የራሳችንን ሕይወት መመርመር የተሻለ ነው። የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ በምንመረምርበት ጊዜ የምናጤነው ሙሉው መጽሐፍ ቅዱስ በእጃቸው የገባና በየዘመናቱ የኖሩ አማኞች እንኳ፥ የክርስትናን እምነት እውነትና ተግባር ለመለማመዱ እጅግ ዳተኞች እንደ ነበሩ ነው። በክርስቶስ ስም የተፈጸሙትን ስደቶችና ልዩነቶችን ስንመለከት ያሳፍሩናል። ለመሠረታዊ የእምነት ትምህርቶች በቤተክርስቲያን ስብሰባዎች ላይ ሽንጥን ገትሮ መከራከር አንድ ነገር ሲሆን፥ በሌላ በኩል ደግሞ በዕለታዊ ሕይወት ውስጥ ተግባራዊ ማድረግ ጨርሶ የተለየ ነገር ነው።

የጴጥሮስ ነፃነት ፈተና የገጠመው በገዛ ራሱ ፍርሃት ነበር። እርሱ አንጾኪያ በነበረ ጊዜ የያዕቆብ ባልደረቦች የነበሩ አንዳንድ ሰዎች ቤተክርስቲያኑን ጎብኝተው ነበር። (ያዕቆብ የክርስትና አማኝ ቢሆንም እንኳ አክራሪ አይሁዳዊ እንደ ነበር ታስታውሳለህ።) ያዕቆብ እነዚህን ሰዎች የላከው ጴጥሮስን በምሥጢር ለመከታተል ነበር የሚል ግምት በጳውሎስ ዘንድ ካለማደሩም በላይ፥ የኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን ባለሥልጣናት ስለ መሆናቸውም አላመለከተም። እርግጥ እነዚህ ሰዎች «ከተገረዙት ቡድን» መካከል እንደ ነበሩ አንዳችም ጥርጥር የለውም (የሐዋ. 15፡1፥5)። አመጣጣቸውም የአንጾኪያን ቤተክርስቲያን ለሃይማኖት ሕጎች ተገዢ ለማድረግ ነበር።

ጴጥሮስ ወደ ቆርኔሌዎስ ቤት ሄዶ ካገለገለ በኋላ ለዚህ ድርጊቱ መከላከያ እንዲያቀርብ ተጠይቆ ጉዳዩን በሚገባ አስረድቷል (የሐዋ. 11)። አሁን ግን ፈራ። መንፈስ ቅዱስ ወደ ቆርኔሌዎስ ቤት እንዲሄድ በላከው ጊዜ ወደዚያ ለመሄድም ሆነ በኢየሩሳሌም ጉባኤ ለመገኘት አልፈራም ነበር። አሁን ግን የተቃዋሚዎች ደጋፊ የሆኑ ሰዎች ሲመጡ፥ ጴጥሮስ ቀድሞ የነበረውን ድፍረት አጣ። «ሰውን መፍራት ወጥመድ ያመጣል» (ምሳሌ 29፡25)።

ይህን ፍርሃት እንዴት ልንገልጸው እንችላለን? ጴጥሮስ በስሜት የሚነዳ ሰው እንደነበር እናውቃለን። አሁን አስደናቂ የሆነ እምነትና ድፍረት እናይበትና ወዲያውኑ ደግሞ ሙሉ በሙሉ ወድቆ እናገኘዋለን። ማዕበል በሚያናውጠው ባሕር ላይ እየተራመደ ወደ ኢየሱስ ለመምጣት ያልሞከረውን ያህል፥ ወዲያውኑ ግን ፈራና መስጠም ጀመረ። ኢየሱስን እስከ ሕይወቱ ፍጻሜ ድረስ እንደሚከተለው ተናግሮ ነበር፤ ቆይቶ ግን ጌታውን ሦስት ጊዜ ካደ። በሐዋርያት ሥራ የምናየው ጴጥሮስ በአራቱ

መንጌላት ከምናየው የበለጠ ጽኑ አቋም ያለው ቢሆንም፥ እኛም ፍጹማን እንዳልሆንን ሁሉ እርሱም ፍጹም አልነበረም። የገዛ ፍርሃቱ ወደ ውድቀት መራው። ከአሕዛብ አማኞች ጋር የፍቅር ግብጥ ማድረጉን ትቶ ተለያቸው ።

የጴጥሮስ ውድቀት ሁለት አሳዛኝ ገጽታዎች አሉት። በመጀመሪያ ደረጃ ግብዝ ሆነ ለማስመሰል መሞከር የሚል ትርጉም የያዘ ቃል ነው። ጴጥሮስን ለዚህ ያደረሰው እውነተኛው ምክንያት ፍርሃት ሆኖ ሳለ እርሱ ግን ታማኝነት እንደ ሆነ ለማስመሰል ሞክሯል። ያለመታዘዛችንን ለመሸፈን «በመሠረታዊ የእምነት ትምህርቶች» ምክንያት አድርጎ ማቅረብ እንዴት ቀላል ነው።

ሁለተኛው አሳዛኝ ነገር ደግሞ ጴጥሮስ ከእርሱ ጋር ሌሎችን ወደ ስሕተት መምራቱ ነበር። በርናባስም እንኳ በዚሁ ስሕተት ተጠልፎ ነበር። በአንጾኪያ ከሚገኙ መንፈሳዊ መሪዎች አንዱ ስለ ነበር (የሐዋ. 11፡19-26)፥ የእርሱ ያለመታዘዝ በንብረቱ ውስጥ በሚገኙ ሌሎች ሰዎች ላይ የሚያደርሰው ተጽዕኖ ቀላል አልነበረም።

እስኪ ጴጥሮስና በርናባስ በዚያን ዘመን አሸንፈው ቤተክርስቲያንን ወደ ሕግ አክራሪነት መሯት ብለን እናስብ። ውጤቱ ምን ሊሆን ይችል ነበር? ጳውሎስንና በርናባስን ያሰግራቸው የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ታላቅ አገልጋዩ ቤተ ክርስቲያን በመሆን ትቀጥል ነበርን? (የሐዋ. 13) ወይስ ከተገረዙት ቡድን የሆኑ አገልጋዮች በመላክ ጳውሎስ የመሠረታቸውን አብያተ ክርስቲያናት ይግርኩ ወይም ይከፋፍሉ ነበርን? ይህ ችግር የግል ወይም የቡድን አልነበረም። ጥያቄው «የወንጌል እውነት» ጥያቄ ስለነበር ጳውሎስ ለጉዳዩ በጽናት ለመጋደል ቆርጦ ተነሣ።

2. የጳውሎስ ግሣጼ (2፡14-21)

ጳውሎስ ከጴጥሮስ ጋር ያደረገው ንግግር የተጠቃለለው የት ላይ እንደ ሆነ በግልጽ ካለመታወቁም በላይ፥ በምንባቡም ውስጥ ለገላትያ ሰዎች የጻፈው መልእክት ከየት እንደሚቀጥል የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎችን ግራ ያጋባ ጉዳይ ነው። ሆኖም መልእክቱ ከየትኛውም ክፍል የቀጠለ ቢሆንም በሙሉ የሚናገረው በክርስቶስ ስላለን ነፃነት ስለ ሆነ ምንም ለውጥ አያመጣም። እንደዚሁም ምንም እንኳ በአጭሩ የቀረበ ቢመስልም፥ ይህ ክፍል ጳውሎስ ጴጥሮስን ስለመገሠጹ የሚናገረውን ክፍል ሙሉ በሙሉ ያቀፈ ነው እንበል። ግሣጼውም በሙሉ በመሠረታዊ እምነት ትምህርት ላይ

የተመሠረተ ነበር። ጴጥሮስ ከአሕዛብ በመለየቱ ምክንያት የካደው አምስት መሠረታዊ የክርስትና ትምህርቶችን ነበር።

(1) የቤተ ክርስቲያንን አንድነት (2፡14)። ጴጥሮስ አይሁዳዊ ነበር፤ በክርስቶስ በማመኑ ግን ክርስቲያን ሆነ። ክርስቲያን ስለሆነ የዘር ልዩነት የሌለባት ቤተክርስቲያን አካል ነው (ገላ. 3፡28)። እግዚአብሔር ለጴጥሮስ መጀመሪያ በቆርኔሌዎስ ቤትና ከዚያም በኢየሩሳሌም ጉባኤ ይህን ትምህርት እንዴት እንዳስተማረው ተመልከተናል።

የጳውሎስ ንግግር የጴጥሮስን ልብ እንደነካው ማሰብ እንችላለን። «አንተ አይሁዳዊ ሳለህ በአይሁድ ኑሮ ያይደለ በአሕዛብ ኑሮ ብትኖር አሕዛብ በአይሁድ ኑሮ ሊኖሩ እንዴት ግድ አልሃቸው?»

ጴጥሮስ ራሱ በኢየሩሳሌም ጉባኤ እንዲህ ብሎ ነበር፡- «በእኛና በእነርሱ መካከል አንዳችም አልለየም» (የሐዋ. 15፡9)። አሁን ግን ጴጥሮስ ራሱ ልዩነት አደረገ። የእግዚአብሔር ሰዎች በተለያዩ ቡድኖች ቢከፋፈሉም እንኳ አንድ ሕዝብ ናቸው። ከዚህ ውጪ ቅዱሳት መጻሕፍትን የሚጥስና ወንድምን ከወንድም የሚለይ ማንኛውም ተግባር የክርስቶስን አካል አንድነት መካድ ነው።

(2) በእምነት መጽደቅ (2፡15-16)። በዚህ መልዕክት ውስጥ መጽደቅ የሚለው ቃል ለመጀመሪያ የተጠቀሰው በዚህ ስፍራ ነው። (ገላትያ የጳውሎስ የመጀመሪያው መልእክት ነው ብለን የምናምን ከሆነ ከጠቅላላው መልእክቱ ውስጥ ጽድቅ የሚለውን ቃል ለመጀመሪያ የተጠቀመበት በዚህ ክፍል ነው ማለት እንችላለን።) «በእምነት የሚገኝ ጽድቅ» የሚለው ጥቅስ ለዘመነ ተሐድሶ መሪ ቃል ሆኖ ከማገልገሉም በላይ፥ ለእኛም ይህን ትምህርት መረዳት እጅግ አስፈላጊ ነው።

«ሰውስ በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ መሆን እንዴት ይችላል?» (ኢዮብ 9፡2) የሚለው ጥያቄ መልስ ዘላለማዊ ይዞታችንን የሚወስን ስለ ሆነ በጣም አስፈላጊ ጥያቄ ነበር። እግዚአብሔር ለዚህ ጥያቄ የሰጠው መልስ «ጻድቅ በእምነት ይኖራል» (ዕብ. 2፡4) የሚል ሲሆን ማርቲን ሉተርን ከሃይማኖታዊ ባርነትና ፍርሃት ነፃ ያደረገውም ይኸው መመሪያ ነበር። ይህ ጽንስ አሳብ እጅግ አስፈላጊ ስለ ሆነ ሦስት የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ስለዚህ ጉዳይ ያብራሩልናል። እነርሱም፡- ሮሜ (1፡17)፥ ገላትያ (3፡11) እና ዕብራውያን (10፡38) ናቸው። የሮሜ መልእክት «ጻድቅ» የሚለውን ቃል

ትርጉም ሲያብራራ፥ «ይኖራል» የሚለውን ቃል ገላትያ፥ «በእምነት» የሚለውን ቃል ዕብራውያን በቅደም ተከተል ያብራራልናል።

ለመሆኑ «ጽድቅ» ማለት ምን ማለት ነው? ጽድቅ እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ ያመነውን ኃጢአተኛ ጻድቅ ነህ የሚልበት የተግባር መግለጫ ነው። ይህንን ቃል ለማስረዳት የተጠቀምንባቸውን እያንዳንዱን ቃል ማስተዋል በጣም ጠቃሚ ነው። መጽደቅ የአንድ ጊዜ ተግባር እንጂ ሂደት አይደለም። አንድ ክርስቲያን ከሌላ ክርስቲያን የበለጠ መጽደቅ አይችልም። የሮሜ 5፡1 ቀጥተኛ ትርጉም እንዲህ የሚል ነው፡- «እንግዲህ አንድ ጊዜ ለዘላለም በእምነት ከጸደቅን ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም አለን»። በእምነት ከጸደቅን የሚለው ቃል ይህ ተግባር በእግዚአብሔርና ኃጢአተኛ በሆነው አማኝ መካከል በቅጽበት ወዲያውኑ የሚፈጸም እንደሆነ ያሳየናል። በሥራ ቢሆን ኖሮ ይህ ተግባር ቀስ በቀስ በሂደት የሚፈጸም ይሆን ነበር።

በተጨማሪ መጽደቅ የሰው ባሕርይ ወይም መልካም ሥራ ውጤት ሳይሆን የእግዚአብሔር ተግባር ነው። «የሚያጸድቅ እግዚአብሔር ነው...» (ሮሜ 8፡33)። አንድ ኃጢአተኛ በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ የሚሆነው «የሕግ ሥራዎችን» በመፈጸም ሳይሆን፥ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ብቻ ነው። ጳውሎስ በዚህ መልእክት የኋለኛ ክፍል እንደሚገልጠው፥ ሕግ የተሰጠው ኃጢአትን ለመግለጥ እንጂ ከኃጢአት ነጻ ለማውጣት አይደለም (ሮሜ 3፡20 ተመልከት)። እግዚአብሔር በጸጋው ኃጢአታችንን በክርስቶስ ላይ አኖረው፤ የክርስቶስ ጽድቅ ደግሞ ለእኛ ተቆረጠልን (2ኛ ቆሮ. 5፡21 ተመልከት)።

እግዚአብሔር ኃጢአተኛውን አማኝ ወዲያውኑ «ጻድቅ» ብሎ ይጠራዋል እንጂ ቀስ በቀስ ጻድቅ አያደርገውም። (በእርግጥ ያዕቆብ ምዕራፍ 2 ውስጥ እንደሚናገረው እውነተኛ ጽድቅ ወደ ተለወጠ ሕይወት ይመራል።) አንድ ሰው በክርስቶስ ከማመኑ በፊት በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአተኛ ነው። በክርስቶስ ባመነበት ቅጽበት ግን ኃጢአተኛ አይደለህም ተብሎ ይታወጅለታል። ከዚያ በኋላ እንደገና ጥፋተኛ ነህ አይባልም።

መጽደቅ ማለት እንዲሁ «ይቅርታን ማግኘት» ማለት ብቻ አይደለም። ምክንያቱም አንድ ሰው ይቅርታን ካገኘ በኋላ እንደገና ኃጢአትን አድርጎ ጥፋተኛ መሆን ይችላል። አንድ ጊዜ በእምነት ከጸደቀ በኋላ በእግዚአብሔር ፊት እንደገና ኃጢአተኛ ሊባል ፈጽሞ አይችልም።

እንደዚሁም ጽድቅ «ምህረት ከማግኘት» የተለየ ነው። ምክንያቱም ምህረት ያገኘ ወንጀለኛ ጥፋቱ በወንጀል ማጎደር (ሪኮርድ) ተመዝግቦ ስለሚያዝበት ነው። አንድ ኃጢአተኛ በእምነት ከጸደቀ ግን የቀድሞ ኃጢአቱ አንደገና ጨርሶ ሊታሰብበት አይችልም። እግዚአብሔር ጨርሶ የኃጢአት መዝገብን አይዝበትም [መዝ. (32)፡ 1-2፤ ሮሜ 4፡ 1-8] ተመልከት)።

በመጨረሻም እግዚአብሔር የሚያጸድቀው ኃጢአተኞችን እንጂ «መልካም ሰዎችን» አይደለም። ጳውሎስ እግዚአብሔር ኃጢአተኛውን አጸደቀ ብሏል (ሮሜ 4፡ 5)። ብዙ ኃጢአተኞች የማይጸድቁት ኃጢአተኞች መሆናቸውን ስለማያምኑ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ የሚያድነው ኃጢአተኞችን ብቻ ነው (ማቴ. 9፡ 9-13፤ ሉቃ. 18፡ 9-14)።

ጴጥሮስ፥ ራሱን ከአሕዛብ ባገለለ ጊዜ ጽድቅ በእምነት የሚገኝ የመሆኑን እውነታ እየካደ ነበር። በሌላ አባባል «እኛ አይሁዶች ከአሕዛብ የተለየንና የተሻልን ነን» ማለቱ ነበር። ሆኖም አይሁዶችም ሆኑ አሕዛብ ኃጢአተኞች ናቸው (ሮሜ 3፡ 22-23)። ሊድኑ የሚችሉትም በክርስቶስ በማመን ብቻ ነው።

(3) ከሕግ ነፃ መሆንን (2፡ 17-18)። ጴጥሮስ በኢየሩሳሌም ጉባኤ የሙሴን ሕግ ከከባድ ቀንበር ጋር አወዳድሮት ነበር (የሐዋ. 15፡ 10ና ገላ. 5፡ 1 ተመልከት)። አሁን ግን ራሱን በዚህ ከባድ ቀንበር ሥር አደረገ።

ጳውሎስ ለጴጥሮስ ያቀረበው የመከራከሪያ አሳብ እንዲህ የሚል ነበር፡- «እኔና አንተ ደህንነትን ያገኘነው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን እንጂ በሕግ አይደለም። አሁን ግን ደኅንነትን ካገኘህ በኋላ እንደገና ወደ ሕግ ተመለስክ። ይህን ማድረግ ደግሞ ያዳነህ ክርስቶስ ብቻ አይደለም እንደማለት ነው፤ ክርስቶስ ብቻ እንዳዳነህ ብትቀበል ኖሮ ግን ሕግን አትፈልግም ነበር። ስለዚህ በአንተ አመለካከት ኃጢአተኛ ያደረገህ ክርስቶስ ነው ማለት ነው።

«በተጨማሪም የእግዚአብሔር የጸጋ ወንጌል ለአይሁድና ለአሕዛብ ሰብከህ ነበር፤ የዳኑት በእምነት እንጂ በሕግ ሥራ እንዳይደለ ነግረሃቸው ነበር። ወደ ሕግ አከራሪነት በመመለስ ያፈረስኸውን እንደገና እየገነባህ ነው ማለት ነው። ስለዚህ ከመጀመሪያውኑ በማፍረስህ በደል አድርገህ ነበር ማለት ነው!»

በሌላ አባባል የጳውሎስ የመከራከሪያ ነጥብ ራሱ ጴጥሮስ የእግዚአብሔርን ጸጋ ከተካፈለበት ልምምድ በመነሣት ነበር። ወደ ሙሴ ሕግ

መመለስ ግለት እግዚአብሔር ለእርሱ ያደረገለትንና በእርሱ ውስጥ ያደረገውን ሁሉ መካድ ግለት ነው።

(4) ራሱን ወንጌልን (2፡19-20)። ሰው የሚጸድቀው በሕግ ሥራዎች ከሆነ ታዲያ ኢየሱስ ክርስቶስ ለምን ሞተ? የክርስቶስ ሞት፥ መቀበርና ትንሣኤ የወንጌል መሠረታዊ እውነቶች ናቸው (1ኛ ቆሮ. 15፡1-8)። በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን ድነናል (እርሱ ለእኛ ሞተ)። በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ባለ እምነት እንኖራለን (እርሱ በእኛ ውስጥ ይኖራል)። በተጨማሪ ከእርሱ ጋር በመንፈስ አንድ በመሆናችን ከእርሱ ጋር ሞትን (ሮሜ 6 ተመልከት)። ይህም ለሕግ የሞትን ነን ማለት አይደለም። ወደ ሙሴ መመለስ ግለት ተመልሶ ወደ መቃብር ጉድጓድ መግባት ግለት ነው። እኛ ግን «በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ» ከእርሱ ጋር ተነሥተናል (ሮሜ 6፡4)። የምንኖረውም በትንሣኤው ኃይል ስለ ሆነ የሕግ «እርዳታ» አያስፈልገንም።

(5) የእግዚአብሔርን ጸጋ (2፡21)። የይሁዲነት አቀንቃኞች ሕግንና ጸጋን ለመደባለቅ ሞክሩ፤ ጳውሎስ ግን ይህ ጨርሶ የማይቻል እንደሆነ ይናገራል። ወደ ሕግ መመለስ ግለት የእግዚአብሔርን ጸጋ «መጣል» ግለት ነው።

ጴጥሮስ ደህንነትን ያገኘ በመሆኑ የእግዚአብሔርን ጸጋ ተለማምዶአል። በአገልግሎቱም ይህን ጸጋ ያውጅ ነበር። ከአሕዛብ ክርስቲያኖች ጎብረት ራሱን ሲለይ ግን የእግዚአብሔርን ጸጋ በግልጽ ክዶአል።

ጸጋ እንዲህ ይላል፡- «ልዩነት የለም! ሁሉም ኃጢአትን ሠርተዋልና፥ ሁሉም ለመዳን የሚችሉት በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ነው!»

የጴጥሮስ ተግባር ግን «ልዩነት አለ! የእግዚአብሔር ጸጋ በቂ ባለመሆኑ ተጨማሪ ሕግ ያስፈልገናል» የሚል ነበር።

ወደ ሕግ መመለስ በመስቀል ላይ የተፈጸመውን ሥራ ከንቱ ማድረግ ነበር። «ጽድቅስ በሕግ በኩል ከሆነ እንኪያስ ክርስቶስ በከንቱ ሞተ» (ቁ. 21)። ሕግ «አድርግ» ሲል ጸጋ ግን «ተደርጓል» ይላል። የክርስቶስ የድል ጩኸት «ተፈጸመ!» የሚል ነበር (ዮሐ. 19፡30)። «ጸጋው በእምነት አድናአችኋል» (ኤፌ. 2፡8)።

ለጳውሎስ ግማጹ ጴጥሮስ መልስ ስለመስጠቱ የተዘገበ አንዳችም ነገር ባይኖርም ቅዱሳት መጻሕፍት የሚያመለክቱት ኃጢአቱን አምኖ በመቀበል

ጎብረቱን እንደገና እንዳደሰ ነው። ሁለቱን መልእክቶቹን (1ኛና 2ኛ ጴጥሮስ) ስንመለከት ከእግዚአብሔር ጸጋ ዞር የማለት አንዳችም ምልክት አናይበትም። እንዲያውም የ1ኛ ጴጥሮስ መልእክት ዋና ዓላማ «እውነተኛ የእግዚአብሔር ጸጋ» (5፡12) የሚል ነው። በዚህ መልእክት በእያንዳንዱ ምዕራፍ ውስጥ «ጸጋ» የሚለውን ቃል እንመለከታለን። እርሱና ጳውሎስ በፍጹም ስምምነት ላይ እንደ ነበሩ ለማመልከት ጴጥሮስ ከፍተኛ ጥንቃቄ አድርጓል። «ከጴጥሮስ ዘርፎ ለጳውሎስ መክፈል» አይቻልም (2ኛ ጴጥ. 3፡15-16)።

የዚህ አስደናቂ ድራማ ገቢር ሁለት ክፍሎች በዚህ መልክ ተጠናቅቀዋል። መጋረጃው ግን ገና አልተዘጋም፤ እኔና እናንተን የሚጨምር ሦስተኛ ክፍል አለ።

3. የአማኞች ምላሽ

ጴጥሮስ የወንጌልን እውነት በተግባር ለመመስከር ፈተና በገጠመው ጊዜ ምን እንደ ደረሰበት እናውቃለን፡- ፍርሃትና ውድቀት ነበር የደረሰበት። ጳውሎስ የወንጌል እውነት ተበርዞ ባየ ጊዜ ምን እንዳደረገ አይተናል፡- በከፍተኛ ድፍረት ለወንጌል እውነት ተከራከረ። በዛሬ ጊዜ በጣም አስፈላጊ የሆነው ጥያቄ ግን «ለወንጌል እውነት እኔ ያለኝ ምላሽ ምንድን ነው?» የሚል መሆን አለበት። ወደዚህ መጽሐፍ መሠረታዊ የክርስትና ትምህርት ክፍል ከማለፋችን በፊት ራሳችንን መመርመር ያለብን ከዚህ በመነሣት ሊሆን ይገባል። ስለዚህ እያንዳንዳችን ልንመልሳቸው የሚገባን አንዳንድ ጥያቄዎች አቅርቤአለሁ።

(1) በእግዚአብሔር ጸጋ ድኛለሁን? ማዳን የሚችለው ብቸኛው ወንጌል በኢየሱስ ክርስቶስ የተገለጠው የእግዚአብሔር ጸጋ ወንጌል ነው። ከዚህ የተለየ ማንኛውም ወንጌል የሐሰት ወንጌል በመሆኑ የተረገመ ነው (ገላ. 1፡6-9)። አንድ ሰው ጸጋን እንዲህ ብሎ ተረጎመው፡-«ክርስቶስ በከፈለው ዋጋ የሚገኝ የእግዚአብሔር ብልጥግና»። ይህ በጣም ጥሩ ትርጉም ነው። ለደህንነቴ የታመንኩት በራሴ ነውን? (በመልካም ሥነ ምግባሬ፥ በደግ ሥራዬ ወይም በሃይማኖቴ ወዘተ።) እንዲህ ከሆነ ክርስቲያን አይደለሁም ማለት ነው፤ ምክንያቱም እውነተኛ ክርስቲያን በክርስቶስ ብቻ የሚታመን ነው። «ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለምና» (ኤፌ. 2፡8-9)።

(2) ሕግንና ጸጋን ለመደባለቅ እሞክራለሁን? ሕግ እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት አንድ ነገር ግድረግ አለብኝ ሲል፥ ጸጋ ግን እግዚአብሔር የእኔን ሥራ ጨርሶልኛል፤ ለእኔም የሚያስፈልገኝ በክርስቶስ ማመን ብቻ ነው ይላል። ደህንነትን ለማግኘት ክርስቶስን ከማመን በስተቀር ምንም ተጨማሪ ነገር አያስፈልገንም። የቤተ ክርስቲያን አባልነትና ሃይማኖታዊ ተግባራት በክርስቶስ ላለን እምነት መልካም መግለጫ ቢሆኑም፥ የዘላለምን ሕይወት ላማግኘት ግን በክርስቶስ በማመናችን ላይ ግን ምንም የሚጨምሩት ነገር የለም። «በጸጋ ከሆነ ግን ከሥራ መሆኑ ቀርቶአል፤ ጸጋ ያለዚያ ጸጋ መሆኑ ቀርቶአል (ሮሜ 11፡6)። ነገር ግን ከሥራ ከሆነ ከጸጋ መሆኑ ቀርቶአል። ያለዚያ ሥራ ሥራ መሆኑ ቀርቶአል።

(3) በክርስቶስ በማመኔ ባገኘሁት ጽድቅ ሐሤት አደርጋለሁን? ብዙውን ጊዜ «መጽደቅ» ማለት «ከዚህ በፊት ጨርሶ ኃጢአትን ያላደረግሁ የመሆን ያህል ነው» ተብሎአል። ይህም ትክክል ነው። አንድ ሰው በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ መሆኑን መረዳቱ ለልቡ ታላቅ ሰላምን ይሰጠዋል (ሮሜ 5፡1)። እስቲ የክርስቶስ ጽድቅ ያንተ ጽድቅ ሆኖ እንደ ተቆጠረልህ አስብ። እግዚአብሔር በክርስቶስ ጻድቃን መሆናችንን ማወጅ ብቻ ሳይሆን የሚመለከተን ከዚህ በፊት ጨርሶ ኃጢአት ያላደረግን ያህል አድርጎ ነው። ኃጢአታችን በሙሉ በክርስቶስ መስቀል ላይ ስለ ተፈረደበት ፍርድን ጨርሶ ልንፈራ አይገባም (ሮሜ 8፡1)።

(4) በጸጋ ባገኘሁት ነጻነት እየተራመድኩ ነውን? ነጻነት ማለት በክርስቶስ ውስጥ ሐሴት ግድረግና እርሱ እንድንሆን የወሰነውን ወደ መሆን መምጣት ማለት ነው እንጂ (ኤፌ. 2፡10)፥ የባለመብትነት ጉዳይ አይደለም። ነፃነት ማለት «የማድረግን ነፃነት» ብቻ ሳይሆን «ያለማድረግንም ነፃነት» ያቀፈ ነው። በኃጢአትና በሕግ ባርነት ሥር አይደለንም። ጳውሎስ በዚህ መልእክት ተግባራዊ ክፍል (ምዕራፍ 5ና 6) ውስጥ እንደሚገልጸው፥ እግዚአብሔርን የምንታዘዘው በፍቅር እንጂ በሕግ ስለ ተገደድን አይደለም። ክርስቲያኖች በክርስቶስ ውስጥ ባለው አስደናቂ ነፃነት ሐሴት ያደርጋሉ። እኔስ በዚህ ነፃነት ሐሴት እያደረግሁ ነውን?

(5) የወንጌልን እውነት ለመከላከል ፈቃደኛ ነኝን? ይህ ማለት በከተማው ውስጥ ካሉት ከእያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያንና የእሑድ ትምህርት ቤት

መምህራን ጋር መከራከር አለብን ማለት አይደለም። ነገር ግን በክርስቶስ የዘላለም ሕይወትን ያስገኙልንን እውነቶች ሰዎች በሚክዱበት ጊዜ ያለአንዳች ፍርሃት በድፍረት እንጋፈጣቸዋለን ማለት ነው። «ሰውን ደስ ላሰኝ እፈልጋለሁን? አሁን ሰውን ደስ ባሰኝ የክርስቶስ ባሪያ ባልሆንሁም» (ገላ. 1፡10)።

በተለያየ ጊዜ የምንገናኛቸው ብዙዎች ሰዎች ደህንነት የሚገኘው በክርስቶስ በማመንና በተጨማሪም «መልካም ተግባሮችን በማድረግ፥ አሥርቱ ሕግጋትን በመጠበቅ፥ ለተራራው ስብከት በመታዘዝ» እና ሌሎች ሃይማኖታዊ ነገሮችን በመፈጸም እንደ ሆነ ያስባሉ። እኛ ግን ጳውሎስ የተለማመደው አይነት ሐዋርያዊ ሥልጣን ባይኖረንም እንኳ የምንሰብከው የእግዚአብሔር ቃል አለን። እውነትን ለሌሎች ማካፈል ደግሞ ግዴታችን ነው።

(6) «እንደ ወንጌል እውነት በቅንነት» እየኖርሁ ነውን? (ገላ. 2፡14) ለእውነት ለመታገል ከሁሉ የበለጠ ትክክለኛው መንገድ በእውነት መኖር ነው። በሕይወቴ የምኖረው ኑሮ ከምናገረው ተጻራሪ ከሆነ ግን፥ በቃል ብቻ ለወንጌል ለመከላከል የማደርገው ጥረት ውጤት እጅግ አነስተኛ ነው። ስለዚህ ጳውሎስ በእግዚአብሔር ጸጋ በነፃነት መኖር እንዴት እንደሚቻል ሊገልጽልን ስለ ሆነ ለሚነግረን መታዘዝ በጣም ጠቃሚ ነው።

ከዚያ በፊት ግን የሚከተለውን ምሳሌ እንመልከት፡- አንድ ታላቅ ባለጸጋ ሰው ያመረተውን እህል እንዲሸጥለት ለአንድ ነጋዴ ከሰጠ በኋላ ወደ ሩቅ አገር ሄደ። እህሉን ሰፍሮ የሚሸጥበትንም መለኪያ (መስፈሪያ) ጭምር ሰጥቶት ነበር የሄደው። ይሁን እንጂ በተሰጠው መስፈሪያ ማንም የሚገዛው ሰው አልተገኘም። በዚህ ጊዜ ነጋዴው ገበያተኛ ለማግኘት መፍትሔው መስፈሪያውን መለወጥ እንደ ሆነ ስላሰበ፥ መስፈሪያውን ለወጠ፤ ወዲያውኑ ብዙ ገዢ ስላገኘ እህሉን በመሉ ሸጠ ጨረሰ። የእህሉ ባለቤት ሲመጣ የሰጠውን እህል ሽያጭ እንዲያስረክበው ጠየቀው፤ ነጋዴው ግን መስፈሪያውን ለውጦ ስለ ሸጠ የተጠበቀውን ገንዘብ ሊያስረክበው አልቻለም።

ትክክለኛውን መመዘኛ መቀየር በማምረት ተግባርም ሆነ በአገልግሎት ውጤታማ አያደርግም። ጳውሎስ «የወንጌል እውነትን» መመዘኛ በትክክል ጠብቆ እንደ ቆየ እኛም ይህንኑ ማድረግ አለብን።

ክፍል 2

የመሠረታዊ እምነት ትምህርት ገለጽ ክፍል፡-

ጸጋና ሕግ

ምዕራፍ 3-4

ገላትያ 3፡1-14

የማታስተውሉ የገላትያ ሰዎች ሆይ፥ በዓይናችሁ ፊት ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ተሰቀለ ሆኖ ተሥሎ ነበር፤ ለእውነት እንዳትታዘዙ አዚም ያደረገባችሁ ማን ነው? ይህን ብቻ ከእናንተ እንድማር እወዳለሁ፤ በሕግ ሥራ ወይስ ከእምነት ጋር በሆነ መስማት መንፈስን ተቀበላችሁን? እንዲህን የማታስተውሉ ናችሁ? በመንፈስ ጀምራችሁ አሁን በሥጋ ትፈጽማላችሁን? በውኑ ከንቱ እንደ ሆነስ እንደዚህ ያለ መከራ በከንቱ ተቀበላችሁን? እንግዲህ መንፈስን የሚሰጣችሁ በእናንተም ዘንድ ተአምራት የሚያደርግ፥ በሕግ ሥራ ነውን ወይስ ከእምነት ጋር በሆነ መስማት ነው?

እንዲሁ አብርሃም በእግዚአብሔር አመነና ጽድቅ ሆኖ ተቆጠረለት። እንኪያስ ከእምነት የሆኑት እነዚህ የአብርሃም ልጆች እንደ ሆኑ አወቁ። መጽሐፍም እግዚአብሔር አሕዛብን በእምነት እንዲያጸድቅ አስቀድሞ አይቶ፡- በአንተ አሕዛብ ሁሉ ይባረካሉ ብሎ ወንጌልን ለአብርሃም አስቀድሞ ሰበከ። እንደዚህ ከእምነት የሆኑት ካመነው ከአብርሃም ጋር ይባረካሉ።

ከሕግ ሥራ የሆኑት ሁሉ በእርግማን በታች ናቸውና፤ በሕግ መጽሐፍ በተጻፉት ሁሉ ጸንቶ የማይኖር የማያደርግም ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ ተጽፎአልና። ጻድቅ በእምነት ይኖራል ተብሎአልና፤ ማንም በእግዚአብሔር ፊት በሕግ እንዳይጸድቅ ግልጽ ነው። ሕግም ከእምነት አይደለም፤ ነገር ግን፡- የሚያደርገው ይኖርበታል ተብሎአል። በእንጨት የሚሰቀል ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ ተጽፎአልና ክርስቶስ ስለ እኛ እርግማን ሆኖ ከሕግ እርግማን ዋጀን፤ የመንፈስን ተስፋ በእምነት እንድንቀበል፥ የአብርሃም በረከት ወደ አሕዛብ በኢየሱስ ክርስቶስ ይደርስላቸው ዘንድ።

-5-

አዚም የተደረገባቸውና የደነዘዙ

ከየትኞቹም ጳውሎስ ካስተላለፋቸው ጠንካራ ጽሑፎች መካከል በገላትያ 3 እና 4 የምናገኛቸው 60 ቁጥሮች ቀደምትነቱን ይይዛሉ። ጳውሎስ ለወንጌል እውነት እየተዋጋ ነበር። ደህንነት በጸጋ እንጂ በሕግ ሥራዎች እንዳይደለ ማስረገጥ ነበረበት። ተቃዋሚዎቹ በሙሉ የገላትያን አብያተ ክርስቲያናት ለማሳሳት የሚቻላቸውን ሁሉ ያደርጉ ስለ ነበር ጳውሎስ እነርሱን የሚዋጋው በግማሽ ልብ መሆን አልነበረበትም። ጳውሎስ ብቁ የመከራከር ችሎታ ነበረው። በእነዚህ ሁለት ምዕራፎች ችሎታውን በሚገባ አሳይቷል። የመከራከርና የማሳመን ችሎታው የዋዛ አልነበረም።

ጳውሎስ እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን በሕግ ሥራዎች ሳይሆን በክርስቶስ በማመን እንደሚያድናቸው ለማስረገጥ ስድስት የተለያዩ መከራከሪያ አሳቦችን ያቀርባል። የሚጀምረው የገላትያ ሰዎች ደህንነትን ባገኙበት ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ያደረጉትን ግላዊ ልምምድ እንዲያስቡ በማድረግ ነው (3፡1-5)። የመከራከሪያ ነጥቦቹን ትክክለኛነት ለማሳየት ስድስት የብሉይ ኪዳን ጥቅሶችን በመጥቅስ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክርክርን ያቀርባል (3፡6-14)። ቃል ኪዳን ምን እንደ ሆነና እንዴትስ ተግባራዊ እንደሚሆን በምክንያታዊነት (ሎጂክ) የተመሠረቱ አስተሳሰቦችን ይደረድራል (3፡15-29)። በመቀጠል ደግሞ በእስራኤል ታሪክ ውስጥ ሕግ የነበረውን ስፍራ ለማሳየት ታሪክ-ነክ የመከራከሪያ ነጥቦችን ያሰፍራል (4፡1-11)።

ጳውሎስ በክርስቶስ ለማረካቸው ሰዎች ያለው ፍቅር እዚህ ነጥብ ላይ ጎልቶ ይታያል። ይህም የተንጸባረቀው በርህራሄ በተሞላው የክርክር አቀራረቡ ነው (4፡12-18)። ጳውሎስ ፍቅሩንና ከዚህ ቀደም ባለፉት ዓመታት ከእርሱ ጋር ያሳለፉትን ደስታ የተሞላ ግንኙነት እንዲያስታውሱ ይለምናቸዋል። ከዚህ በኋላ ደግሞ በአብርሃም ሕይወት ላይ በማተኮርና ከሣራና ከአጋር ጋር የነበረውን ግንኙነት በማስመልከት ተምሣሌታዊ (አሊጎሪካል) ማስረጃዎችን ያቀርባል (14፡19-31)። በመጨረሻም በሁለቱ

ምዕራፎች መደምደሚያ ላይ ክርስቲያናዊ ትምህርት ላይ የተመሠረቱትን ተግባራዊ መከራከሪያ ነጥቦቹን አስፍሯል።

1. ግላዊ የመከራከሪያ አሳብ (3፡1-5)

የዚህ ክፍል ዋናው አሳብ «መከራ መቀበል» (በቁ. 4) በሚለው ቃል የሚጠቃለል ሲሆን፥ ቃሉም «መለማመድ» ተብሎ ሊተረጎም እንደሚችል እንመለከታለን። «እንደዚህ ያሉ በርካታ ነገሮችን በከንቱ ተለማመዳችሁን?» በማለት ጳውሎስ ይጠይቃቸዋል። በክርስቶስ ባመኑበት ጊዜ ጳውሎስ አብሮአቸው ነበር፤ ስለ ሆነም ክርክሩን ከክርስቲያናዊ ልምምድ አንጻር መጀመሩ ብልህነት ነበር። በልምምድ ላይ የተመሠረተ ክርክርን ማቅረብ አደገኛ መሆኑ የማያጠራጥር ነው፤ እውነተኛ ያልሆነ ልምምድ አለ፤ ከዚህም በላይ ልምምዶችን በተሳሳተ ሁኔታ ልንጠቀምባቸው እንችላለን። ልምምዶቻችን በእግዚአብሔር ቃል መፈተን አለባቸው፤ ልምምዶቻችን ሊለዋወጡ ይችላሉ፤ የእግዚአብሔር ቃል ግን አይለወጥም። ሚዛን መጠበቅ አለብን። ጳውሎስ የገላትያ ክርስቲያኖችን ልምምድ ከግይለወጠው የእግዚአብሔር ቃል አንጻር ይፈትነዋል (ቁ. 6-14)።

ጳውሎስ እነዚህን ሰዎች በመጀመሪያ በነበኛቸው ወቅት በሕይወታቸው አንድ ነገር እንደ ተለማመዱ የታወቀ ነው። የይሁዲነት አቀንቃኞች ግን ወደ እነርሱ መጡና ልምምዳቸው የተሟላ እንዳልሆነ አሳመኗቸው። በልምምዳቸው ላይ «አንድ ነገር መጨመር» እንደሚያስፈልጋቸው ነግሯቸው። ይህ «ጎደላቸው» የተባለው አንድ ነገር ለሙሴ ሕግ መታዘዝ ነበር። እነዚህ ሐሰተኛ አስተማሪዎች አዚም አደረጉባቸው፤ አቄሉአቸው። ጳውሎስ የገላትያ ሰዎችን «የማያስተውሉ» (ሞኞች) ብሎ በመጥራቱ ክርስቶስ በተራራው ስብከት በማቴ. 5፡22 ላይ የተናገረውን ቃል መጣሱ አልነበረም። ምክንያቱም ሁለት የተለያዩ አሳቦችን በሚገልጹ ሁለት የተለያዩ ቃሎች በመጠቀሙ ነው። በገላ. 3፡1 የተጠቀሰው «ሞኞች» የሚለው ቃል «መንፈሳዊ ደደብነትን» የሚያመለክት ሲሆን (ሉቃ. 24፡25 ተመልከት)፥ ኢየሱስ የተጠቀመበት ቃል ግን «ፈሪሃ እግዚአብሔር የለሽነትን» ለማመልከት ነበር። ጳውሎስ የሚናገረው ስለ ሐቅ ነው። ኢየሱስ የሚያስጠነቅቀው ግን በአንደበታችን ያለ አግባብ የመጠቀምን ጉዳይ ነው።

ጳውሎስ ከእግዚአብሔር ጋር እውነተኛ ግንኙነት አድርገው እንደ ነበር ያስታውሳቸዋል።

እግዚአብሔር ወልድን አይተው ነበር (3፡ 1)። ጳውሎስ ስለ «ክርስቶስና ስለመስቀል ላይ ሞቱ» ለገላቲያ ሰዎች ሥዕላዊ በሆነ ቋንቋ ገልጾላቸው ስለነበረ፥ የኢየሱስ የመስቀል ላይ ሞት ለዓይነ ሕሊናቸው ወለል ብሎ ይታያቸው ነበር። «እንደ ተሰቀለ ሆኖ ተሥሎ ነበር» የሚለው ሐረግ «ሕዝብ በሚያየው ስፍራ የተሣለ ወይም የግስታወቂያ ሰሌዳ ላይ በግልጽ የተለጠፈ» የሚል ትርጉም ከሚሰጥ የግሪክ ቃል የተገኘ ነው። ጠቃሚ የሆነ ማስታወቂያን ሕዝብ በግልጽ ሊያይ በሚችልበት ስፍራ እንደምናደርገው ሁሉ፥ ጳውሎስም ክርስቶስ ለኃጢአተኞች በመስቀል ላይ መሰቀሉንና መሞቱን ለገላትያ ሰዎች ለማሳየት ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ነበር። የገላትያ ሰዎች ይህን እውነት ሰምተውና አምነው በመታዘዝ በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ ተወልደው ነበር።

የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው ነበር (3፡2-3)። በዚህ መልእክት መንፈስ ቅዱስ 18 ጊዜ ተጠቅሶአል፤ ለእግዚአብሔር ጸጋ ወንጌል በሚያደርገው ክርክር ሁሉ መንፈስ ቅዱስ ከፍተኛ ድርሻ ነበረው። እውነተኛውና ብቸኛው ማስረጃ መንፈስ ቅዱስ በአማኝ ሕይወት ውስጥ ለውጥ ማምጣቱ ነው (ሮሜ 8፡9 ተመልከት)። ጳውሎስ «እንግዲህ መንፈስን የሚሰጣችሁ በእናንተም ዘንድ ተአምራት የሚያደርግ በሕግ ሥራ ነውን ወይስ ከእምነት ጋር በሆነ መስማት ነው?» የሚል እጅግ ጠቃሚ ጥያቄ ይጠይቃል። ለዚህ ጥያቄ የሚኖረው መልስ አንድ ብቻ መሆኑ እርግጥ ነው። መንፈስ ቅዱስ ወደ ሕይወታቸው የመጣው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመናቸው ብቻ ነበር።

መንፈስ ቅዱስ በደህንነትና በክርስቲያናዊ ሕይወት ውስጥ ያለውን ተግባር መረዳት ለእኛም ቢሆን በጣም አስፈላጊ ነው። መንፈስ ቅዱስ የጠፋውን ኃጢአተኛ በመውቀስ ክርስቶስን ይገልጥለታል (ዮሐ. 16፡7-11)። ከዚህ በኋላ ኃጢአተኛው ለመንፈስ ቅዱስ በመታዘዝ በክርስቶስ ሊያምን ወይም «አልቀበልም» ማለት ይችላል (የሐዋ. 7፡51)። አንድ ኃጢአተኛ በክርስቶስ በሚያምንበት ጊዜ ከመንፈስ ቅዱስ ይወለዳል (ዮሐ. 3፡1-8)፤ አዲስ ሕይወትንም ይቀበላል። ደግሞም የክርስቶስ መንፈሳዊ አካል ከፍል ይሆን ዘንድ በመንፈስ ቅዱስ ይጠመቃል (1ኛ ቆሮ. 12፡12-14)። አንድ ቀን የክርስቶስ ክብር ተካፋይ እንዲሆንም በመንፈስ ቅዱስ ይታተማል (ኤፌ. 1፡13-14)።

መንፈስ ቅዱስ ለአማኙ በርካታ ነገሮችን ስለሚያደርግ ማንኛውም አማኝ በውስጡ ለሚኖረው መንፈስ ቅዱስ የመታዘዝ ኃላፊነት አለበት ማለት ነው

(1ኛ ቆሮ. 6፡19-20)። ክርስቲያን ቃሉን በማንበብ፥ በመጸለይና ለእግዚአብሔር ፈቃድ በመታዘዝ በመንፈስ መመላለስ አለበት (ገላትያ 5፡16፥ 25)። ለእግዚአብሔር ካልታዘዘ መንፈስ ቅዱስን ያሳዝናል (ኤፌ. 4፡30)። ይህን በማድረግ ከቀጠለ ግን መንፈስ ቅዱስን ያጠፋል (1ኛ ተሰ. 5፡19)። ይህ ማለት መንፈስ ቅዱስ ትቶት ይሄዳል ማለት አይደለም፤ ምክንያቱም ኢየሱስ መንፈስ ቅዱስ ከአማኙ ጋር የሚኖረው ለዘለዓለም እንደሆነ ተናግሯል (ዮሐ. 14፡16)። ነገር ግን ለእለታዊ የክርስትና ኑሮ የሚያስፈልገውን ደስታና ኃይል መንፈስ ቅዱስ አይሰጠውም ማለት ነው። አማኞች በመንፈስ ቅዱስ መሞላት አለባቸው (ኤፌ. 5፡18-21)። ይህም በቀላል አባባል «በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ሥር መሆን አለባቸው» ማለት ነው። ይህ ከንጹህ ምንጭ ውኃ የመጠጣትን ያህል የማያቋርጥ ልምምድ ነው (ዮሐ. 7፡37-39)።

ስለዚህ የገላትያ ክርስቲያኖች በክርስቶስ ባመኑበት ወቅት መንፈስ ቅዱስን የተቀበሉት በእምነት እንጂ በሕግ ሥራዎች አማካይነት አልነበረም። ይህም ጳውሎስን ወደ ሌላ ጥያቄ ይመራዋል፡- ጥያቄው ይህን ይመስላል፡- «በሕግ ካልጀመራችሁ አሁን ስለ ሕግ ለምን ታነሣላችሁ፤ በመንፈስ ከመጀመራችሁ ያለመንፈስ ቅዱስ ዕርዳታ በሥጋ ብቻ በመታመን ወደ ብስለት መምጣት ትችላላችሁን?» «ሥጋ» የሚለው ቃል እዚህ የሚያመለክተው የአማኙን አሮጌ ባሕርይ (ተፈጥሮ) እንጂ የሰውን አካል አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ «ሥጋ» የሚለውን ቃል በየትኛውም ስፍራ የተጠቀመበት ስሜት አሉታዊ ነው (ዘፍ. 6፡1-7፤ ሮሜ 7፡18፤ ዮሐ. 6፡63፤ ፊልጵ. 3፡3)። ደህንነትን ያገኘነው በሥጋ ሳይሆን በመንፈስ፥ በሕግ ሳይሆን በእምነት ስለ ሆነ በዚያው መንገድ መቀጠል ትክክለኛ ነገር ነው።

በዚህ ስፍራ ሰብዓዊ ልደትን በመግለጫነት መጠቀም ይቻላል። ሕፃን እንዲረገዝና እንዲወለድ ሁለት ወላጆች (አባትና እናት) እንደሚያስፈልጉት ሁሉ፥ አንድ ሰው በእግዚአብሔር ቤተሰብ እንዲወለድ ሁለት መንፈሳዊ ወላጆች ያስፈልጉታል። እነርሱም የእግዚአብሔር መንፈስና የእግዚአብሔር ቃል ናቸው (ዮሐ. 3፡1-8፤ 1ኛ ጴጥ. 1፡22-25)። አንድ ጤነኛ ሕፃን በሚወለድበት ጊዜ ለሕይወት የሚያስፈልጉት ነገሮች በሙሉ አሉት፤ ምንም ተጨማሪ ነገር አያስፈልገውም። የእግዚአብሔርም ልጅ ሆኖ የሚወለደው እንደዚሁ በመንፈስ የተሞላ ሆኖ ስለሚወለድ ሌላ ተጨማሪ ነገር

አያስፈልገውም። ሕፃኑ እያደገ እንዲሄድ የሚያስፈልገው ምግብ፥ የተለያዩ የአካል እንቅስቃሴዎችና ንጽሕና ብቻ ናቸው። ለተወለደው ሕፃን በወሩ ጆሮ ሊቀጥሉለት፥ በሁለት ወሩ የእግር ጣቶች ሊያስተክሉለት ወላጆቹ ወደ ሐኪም ቢወስዱት ኖሮ ነገሩ እንግዳ ይሆን ነበር።

ጳውሎስ ሲጽፍ «በመንፈስ ጆምራችኋል፤ ምንም ተጨማሪ ነገር አያስፈልግም፤ በመንፈስ ብትመላለሱ በጌታ ታድጋላችሁ» ይላል።

ከእግዚአብሔር አብ ዘንድ ተአምራት ተለማምደዋል (3፡5)። በዚህ ጥቅስ በውስጠ ታዋቂነት የሚገኘው «እርሱ» የሚለው ቃል መንፈስን የሚሰጥና በእነርሱ ዘንድ «ተአምራትን የሚያደርግ» እግዚአብሔር አብ ነው። አማኙ ክርስቶስን አምኖ በተለወጠበት ጊዜ ወደ እርሱ የመጣው ያው መንፈስ ቅዱስ መላው አካል ይገነባ ዘንድ በእርሱ ውስጥና በእርሱ በኩል መሥራቱን ይቀጥላል (ቆላ. 2፡19፤ ኤፌ. 4፡16)። እግዚአብሔር አብ መንፈስን በኃይልና በበረከት ይሞላዋል፤ ይህም የሚሆነው በእምነት እንጂ በሕግ ሥራዎች አይደለም። «በእናንተ ዘንድ» የሚለው ቃል «በእናንተ ውስጥ» ተብሎ ሊተረጎምም ይችላል። ስለዚህ እነዚህ ተአምራት በክርስቲያኖች ሕይወት ውስጥ ያሉትን አስደናቂ ለውጦችና በቤተ ክርስቲያን ጎብረት ውስጥ የሚፈጸሙትን ምልክቶችና ድንቆች ሁሉ ያጠቃልላሉ።

አንድ የክርስቲያንን ሃይማኖት በጥርጣሬ ይመለከት የነበረ ሰው በጣም ከባድ ሰካራም የነበረ አዲስ ክርስቲያንን «በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሚገኙ ተአምራት በእርግጥ ታምናለህን?» ብሎ ጠየቀው።

አማኙም መልሶ «በእርግጥ አምናለሁ» አለ።

ተጠራጣሪውም የፈዝ ሳቅ እየሳቀ «ኢየሱስ ውኃውን ወደ ወይን ጠጅ መለወጥ መቻሉን ታምናለህ ማለት ነውን?» ብሎ ጠየቀው።

«አዎን በሚገባ! በቤቴ እንኳ ለመጠጥ አባክን የነበረውን ገንዘብ ለምግብ ልብስና የቤት እቃዎችን ለመግዛት እንዲያስችለኝ ሲያደርግ ተመልክቼአለሁ» ብሎ መለሰለት።

2. መጽሐፍ ቅዱሳዊ የመከራከሪያ አሳብ (3፡6-14)

ጳውሎስ ከግላዊ ልምምድ ቀጥሎ ወደ እግዚአብሔር ቃል ነባራዊ ማረጋገጫ ይመለሳል። ተግባራዊ ልምምዳችንን በእግዚአብሔር ቃል እንመዝናለን እንጂ፥ የእግዚአብሔርን ቃል እውነት ከልምምዳችን አንጻር

በማየት ውሳኔ ልንሰጥበት አንችልም። ጳውሎስ በመጀመሪያው ክፍል ስድስት ጥያቄዎችን ጠይቆ ነበር። በዚህ ክፍል ደግሞ ደህንነት በክርስቶስ በማመን እንጂ በሕግ ሥራዎች እንዳይደለ ለማረጋገጥ ስድስት የብሉይ ኪዳን ጥቅሶችን ያቀርባል። የይሁዲነት አቀንቃኞች አማኞችን ወደ ሕግ ሥራ መልሰው ለመውሰድ ፈልገው ስለ ነበር ጳውሎስ ሕግን ይጠቅሳል። በሃይማኖታቸው ውስጥ የአብርሃምን ስፍራ አጉልተው ስለ ነበር ጳውሎስ አብርሃምን የእርሱ አንድ ምስክር አድርጎ ያቀርበዋል።

(1) አብርሃም የዳነው በእምነት ነበር (3፡6-7)። የእግዚአብሔር ጽድቅ ለአብርሃም የተቆጠረለት በእግዚአብሔር የተሰሩ ቃሎች በማመኑ ብቻ እንደ ነበር ሙሴን በመጥቀስ ይጀምራል (ዘፍ. 15፡6)። በገላትያ 3፡6 እና በዘፍ. 15፡6 የሚገኘው «ተቆጠረለት» በሮሜ 4፡11፥ 22-25 «ይቆጠሩ» ና «ይቆጠርልን» ከሚሉት ጋር አንድ ናቸው። የግሪኩ ቃል ትርጉም «በአንድ ሰው የሂሳብ መዝገብ ውስጥ ማስቀመጥ» የሚል ግንዛቤን ይሰጣል። አንድ ኃጢአተኛ በክርስቶስ በሚያምንበት ወቅት የእግዚአብሔር ጽድቅ በእርሱ መዝገብ ላይ ይመዘገብለታል። ከዚህም በላይ ያለፈው ኃጢአቱ ሁሉ አይታሰብበትም። (ሮሜ 4፡1-8)። ይህ ማለት መዝገቡ በእግዚአብሔር ፊት ሁልጊዜ ንጹሕ ስለ ሆነ አማኝ ባለፈው ኃጢአቱ ጨርሶ አይፈረድበትም ማለት ነው።

የአይሁድ ሕዝብ ከአብርሃም ጋር ስላላቸው ግንኙነት ከፍተኛ ትምክህት ነበራቸው። ችግሩ ይህን ግንኙነት የዘለዓለም ደኅንነት ዋስትና አድርገው ማሰባቸው ነበር። መጥምቁ ዮሐንስ፥ በሥጋ ከአብርሃም ዘር መሆናቸው የመንፈሳዊ ሕይወት ዋስትና እንደማይሆናቸው አስጠንቅቆአቸው ነበር (ማቴ. 3፡9)። ኢየሱስ፥ በሥጋ «የአብርሃም ዘር» በመሆንና በመንፈስ «የአብርሃም ልጅ» በመሆን መካከል ግልጽ ልዩነት መኖሩን አስቀምጦአል (ዮሐ. 8፡33-47)። ዛሬም አንዳንድ ሰዎች ደኅንነት በውርስ እንደሚተላለፍ ያስባሉ። አንድ ሰው አባትና እናቱ እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሰዎች ከሆኑ እርሱም ይድናል ብለው ያስባሉ። ይህ ግን እውነት አይደለም። ከዚህ ቀደም ብዙ ጊዜ እንደ ተባለው «እግዚአብሔር የሁለተኛ ትውልድ ክርስቲያኖች የሉትም»።

(2) ይህ ደኅንነት ለአሕዛብ ነው (ገላ. 3፡8-9)። በቁጥር 8 የምናገኘው «አሕዛብ» የሚለው በቀላሉ አይሁድ ያልሆኑ ሕዝቦች ማለት ነው። ጳውሎስ ከሙሴ መጽሐፍ (ዘፍ. 12፡3) የጠቀሰው ቃል

የሚያረጋግጠው እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር ከነበረው ከመጀመሪያው ግንኙነት ጀምሮ የደኅንነት የተስፋ ቃል የሰጠው ለአሕዛብ ሁሉ መሆኑን በመግለጽ ነው። እግዚአብሔር ከብዙ ምእተ ዓመታት በፊት «መልካሙን የምሥራች» ለአብርሃም ሰበከለት። ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች ያመጣላቸውም ይህንኑ የምሥራች ነበር። ይህም ኃጢአተኞች ሕግን በመጠበቅ ሳይሆን በእምነት ይጸድቃሉ የሚል ነው። በዚህ ሥፍራ የተሰጠው ገለጻ ምክንያታዊ ነው። አሕዛብን በእምነት ሊያድን እግዚአብሔር ተስፋን ከሰጠ፥ የይሁዲነት አቀንቃኞች አሕዛብ አማንያንን ወደ ሕግ ለመመለስ የሚያደርጉት ጥረት ስሕተት ነው ማለት ነው። እውነተኞቹ «የአብርሃም ልጆች» በሥጋ ዘሩ የሆኑት አይሁዳውያን አይደሉም፤ በኢየሱስ ክርስቶስ ያመኑ አይሁዳውያንና አሕዛብ እንጂ። «ከእምነት የሆኑ» (አማኞች) «ካመነዉ ከአብርሃም» ጋር የተባረኩ ናቸው።

ዘፍጥረት 12፡1-3 የተጻፈውን እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር የገባውን ታላቅ ቃል ኪዳን ስታነብ በርካታ የተለያዩ ተስፋዎች እንዳሉ ትገነዘባለህ። እነዚህ ተስፋዎች አንዳንዶቹ ግላዊ፥ አንዳንዶቹ ብሔራዊና ፖለቲካዊ፥ ሌሎች ደግሞ ዓለም አቀፋዊና መንፈሳዊ ናቸው። እግዚአብሔር የአብርሃምን ስም ታላቅ እንዳደረገው እርግጥ ነው። በአይሁዳውያን ብቻ ሳይሆን በክርስቲያኖች፥ በሙስሊሞችና በሌሎች ሁሉ ዘንድ ይከበራል። እግዚአብሔር በገባው ተስፋ ቃል መሠረት ዘሩን አበዛለት፤ አብርሃምን የባረኩ ሁሉ ተባርከዋል። የአብርሃምን ዘር በረገሙ ሁሉ ላይ ፍርድን አምጥቷል (በግብፅ፥ ባቢሎንና ሮም ላይ የደረሰውን ማቅረብ ይቻላል)። እግዚአብሔር በአብርሃምና በአይሁድ ሕዝብ በኩል የላከው ታላቁ በረከት ግን ከዘላለማዊ ደኅንነታችን ጋር የተያያዘ ነው። አሕዛብ በሙሉ በእርሱ የሚባረኩበት የተስፋው «ዘር» ኢየሱስ ክርስቶስ ነው (ገላ. 3፡16)።

(3) ይህ ደኅንነት በእምነት እንጂ በሕግ አይደለም (3፡10-12)። ሕግ የሚያመጣው መርገምን እንጂ በረከትን ስላይደለ ሕግን በመጠበቅ ደኅንነት ሊገኝ አይችልም። ይህንንም ለማረጋገጥ ጳውሎስ ከዘዳግም ይጠቅሳል (27፡26)። ሕግ መታዘዝን ይጠይቃል። ይህም አንድ እንኳ ሳይቀር ሕግጋትን በሙሉ መጠበቅ ማለት ነው። ሕግ ሰዎች ገብተው የፈለጉትን የሚመርጡበት «ሃይማኖታዊ ምግብ ቤት» አይደለም (ያዕ. 2፡10-11 ተመልከት)። ጳውሎስ በመቀጠል ከእንባቆም ይጠቅሳል፡-

«ጻድቅ በእምነት ይኖራል» (2፡4)። ይህ ዐረፍተ ነገር በጣም አስፈላጊ ስለ ነበር መንፈስ ቅዱስ በሦስት የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት በፊት በተጠቀሰው መንገድ እንዲያስረዱት አድርጎአቸዋል። የሮሜ መጽሐፍ «ጻድቅ» የሚለውን ቃል ሲያብራራው አንድ ኃጢአተኛ በእግዚአብሔር ፊት እንዴት እንደሚጸድቅ ይነግረናል (ሮሜ 1፡17 ተምልከት)። የገላትያ መጽሐፍ ጻድቅ ሰው እንዴት «እንደሚኖር» ሲናገር ዕብራውያን ደግሞ «በእምነት» የሚለውን ቃል ያብራራል (ዕብ. 10፡38)። ሕግ የሚገድልና ኃጢአተኛን በእግዚአብሔር ፊት ጥፋተኛ መሆኑን የሚያሳይ ስለ ሆነ ማንም ሰው «በሕግ» መኖር አይችልም (ሮሜ 3፡20፥ 7፡7-11)።

አንዳንድ ሰዎች ለሕጉ ለመታዘዝ እንኳ እምነትን ይጠይቃል በማለት ሊከራከሩ ይችሉ ይሆናል። ስለዚህ ጳውሎስ ዘሌዋውያንን በመጥቀስ እግዚአብሔር የሚፈልገው ሕግን ማድረግ እንጂ በሕግ ማመንን አይደለም ይላል (18፡5)። ሕግ «አድርግና በሕይወት ኑር» ሲል ጸጋ ግን «እመንና በሕይወት ኑር» ይላል። የጳውሎስ የራሱ ልምምድም ሆነ (ፊልጵ. 3፡1-10) የአጠቃላዩ የእስራኤል ሕዝብ ታሪክ (ሮሜ 10፡1-10) በእምነት የሚገኝ ጽድቅ እንጂ በሥራ የሚገኝ ጽድቅ ኃጢአተኞችን ሊያድን ጨርሶ እንደማይችል ያመለክታሉ።

የይሁዲነት አቀንቃኞች የፈለጉት የገላትያ ሰዎችን የሕግ ሥራዎች ወደ ሞላበት ሃይማኖት ለመምራት ማባበልን ሲሆን፥ የጳውሎስ ፍላጎት ግን በክርስቶስ በማመን ፍቅርና ሕይወት በሞላበት ኅብረት ሐሴት እንዲያደርጉ ነበር። ለአንድ ክርስቲያን፥ ለሕግና ለጽድቅ ሥራዎች ብሎ እምነትና ጸጋን መተው ማለት፥ ከጌታ ጋር ባለው እለታዊ ኅብረት የሚለማመደውን አስደናቂ ነገር ሁሉ ማጣት ማለት ነው። ሕግ ኃጢአተኛን «ጻድቅ ነህ» ሊለውም ሆነ (ገላ. 2፡16)፥ ጽድቅን ሊሰጠው አይችልም (2፡21)። ሕግ የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ ሊሰጥም ሆነ ለእግዚአብሔር ልጆች የሚገባውን መንፈሳዊ ርስት የማግኘት ዋስትና ሊያስገኝ አይችልም (3፡18)። ሕግ ሕይወትን ሊሰጥ አይችልም (3፡21)፤ ደግሞም ሕግ ነፃነትን ሊሰጥ አይችልም (4፡8-10)። ታዲያ ወደ ሕግ መመለስ ለምን አስፈለገ?

(4) ይህ ደኅንነት በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የሚገኝ ነው (3፡13-14)። እነዚህ ሁለት ቁጥሮች ጳውሎስ በዚህ ክፍል ያላቸውን ነገሮች በሙሉ ቁልጭ ባለ መንገድ አሳጥረው ያቀርባሉ። ሕግ ኃጢአተኞችን

ከመርገም በታች ያደርጋቸዋልን? እንግዲያስ ክርስቶስ ከዚያ መርገም ተቤዝቶናል። የአብርሃምን በረከት ትፈልጋለህን? ይህ በረከት በክርስቶስ በኩል የሚገኝ ነው። የአሕዛብ ወገን ብትሆንም እንኳ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ትፈልጋለህን? ይህ ስጦታ በክርስቶስ በኩል ለአሕዛብ ተሰጥቷልና የሚያስፈልግህ በክርስቶስ ማመን ብቻ ነው። ወደ ሙሴ የምንመለስበት አንዳችም ምክንያት የለንም።

ጳውሎስ እንደገና ከዘዳግም ጠቅሶ «በእንጨት ላይ የተሰቀለ በእግዚአብሔር ዘንድ የተረገመ ነውና» (21:23) ይላል። አይሁዶች ወንጀለኞችን በሞት የሚቀጡት በድንጋይ ወግረው በመግደል ነበር እንጂ በመስቀል አልነበረም። ከባድና ከፍተኛ የሕግ መተላለፍ ያደረገ ወንጀለኛ ሬሳ ግን ለሰው ሁሉ እንዲታይ ሆኖ በዛፍ ላይ ይሰቀል ነበር። የአይሁድ ሕዝብ ሬሳን የሚንከባከቡት በከፍተኛ ጥንቃቄ ስለ ነበር በዛፍ ላይ መሰቀል ታላቅ ውርደት ነበር። ሬሳው ሰዎች እንዲያዩት ለተወሰነ ጊዜ ከተሰቀለ በኋላ ይወርድና ይቀበር ነበር (ኢያሱ 8:29፤ 10:26፤ 2ኛ ሳሙ. 4:12)።

ጳውሎስ ከብሉይ በጠቀሰው ቃል «እንጨት» የሚለው ኢየሱስ ከተሰቀለበት መስቀል ጋር እንደሚያያዝ ግልጽ ነው (የሐዋ. 5:30፤ 1ኛ ጴጥ. 2:24)። የኢየሱስ አካል በመስቀል ላይ የዋለው በድንጋይ ተወግሮ ከተገደለ በኋላ አልነበረም፤ ነገር ግን በሕይወት እያለ በመስቀል ላይ ተቸንክሮ እንዲሞት ተደረገ። ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ በመሞት የሕግን መርገም ለእኛ ሲል ተሸከመ፤ ስለዚህም በክርስቶስ የሚያምኑ ሁሉ በሕግና በአስከፊው መርገም ሥር አይደሉም። በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ባለን እምነት የአብርሃም በረከት (በእምነት የሚገኝ ጽድቅና የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ) አሁን ለእኛ ተሰጥቶአል።

በቁ.13 ላይ የምንመለከተው «ዋጀን» የሚለው ቃል አንድን ባሪያ ነፃነቱን ለመስጠት መግዛትን የሚያመለክት ነው። አንድን ባሪያ ከመጀመሪያው ባለቤቱ ገዝቶ በባርነት ማቆየት ይቻላል፤ ክርስቶስ ያደረገው ግን እንደዚህ አይደለም። ደሙን በመስቀል ላይ በማፍሰስ ነፃ እንድንሆን ገዛን። የይሁዲነት አቀንቃኞች ክርስቲያኖችን ወደ ባርነት ሊመሩ ፈልገው ነበር። ክርስቶስ የሞተው ግን ነፃ ሊያወጣቸው ነው። ደህንነት ከአንድ የባርነት አይነት ወደ ሌላ ባርነት መለወጥ አይደለም። ደህንነት ከኃጢአትና ከሕግ ባርነት ነፃ መሆንና በክርስቶስ ወደሚገኘው የእግዚአብሔር ጸጋ ነፅነት መግባት ማለት ነው።

ይህም የሚከተለውን ጥያቄ ያስነሣል፡- «እነዚህ የይሁዲነት አቀንቃኞች የሕግ መንገድ ከጸጋ መንገድ የሚበልጥ አድረገው የገላትያ ክርስቲያኖችን ሊያሳምኑ የቻሉት እንዴት ነበር? ማንኛውም አማኝ ሆን ብሎ በነፃነት ምትክ ባርነትን የሚመርጠው ለምንድን ነው?» የዚህ ጥያቄ መልስ በከፊል የሚገኘው ጳውሎስ በቁጥር 1 «አዚም ያደረገባችሁ» ብሎ ከተጠቀመበት ቃል ሊሆን ይችላል። የቃሉ ትርጉም «በድግምት ኃይል አዚም ማድረግ፥ ማፍዘዝ» ማለት ነው። ክርስቲያኖችን በማፍዘዝ ከጸጋ ወደ ሕግ ዞር እንዲሉ ሊያደርጋቸው የሚችል በሕግ ውስጥ ምን አስደናቂ ነገር አለ?

በመጀመሪያ ሕግ ሥጋን ደስ የሚያሰኝ ነው። ሥጋ «ሃይማኖታዊ» መሆን፥ ለሕግጋት መታዘዝ፥ ቅዱሳት በዓላትን ማክበር፥ መጾምንም እንኳ ቢሆን ይወዳል (ገላ. 4፡10 ተመልከት)። ከመንፈስ ቅዱስ ምሪትንና ኃይልን እስካገኘን ለሕግጋት መታዘዝ፥ መጾም ወይም በክብር በዓል ቀን አምልኮ ማድረግ በራሳቸው አንዳችም ስህተት የለባቸውም። ሥጋ በሃይማኖታዊ ተግባራት፥ ማለትም በጸሎት ብዛት መጠን፥ በሚሰጠው ምጽዋት ብዛት፥ ወዘተ... መመካት ይወዳል (ሉቃስ 18፡9-14፤ ፊልጵ. 3፡1-10 ተመልከት)።

ሃይማኖታዊ ሕግ አክራሪነት ሰውን የሚያስደንቅበት ሌላው ባሕርዩ ለስሜቶች የሚሰጠው እርካታ ነው። እግዚአብሔርን «በመንፈስና በእውነት» (ዮሐ. 4፡24) በማምለክ ፋንታ የራስን ስሜቶች የሚያረካ የአምልኮ ሥርዓት ያበጃል። የሚመላለሰው በእምነት ሳይሆን በማየት፥ በመስማት፥ በመቅመስ፥ በማሽተትና በመዳሰስ ነው። በመንፈስ የሚመራ እውነተኛ አምልኮ አምስቱን የስሜት ሕዋሳትን የሚከድ አለመሆኑ እርግጥ ነው። ሌሎች አማኞችን እናያለን፤ መዝሙራትን እንሰማለን፤ እንዘምራለን፤ በጌታ እራት የምንወስደውን ሕብስትና ወይን እንቀምሳለን፤ እነዚህ ውጫዊ ሥርዓቶች እምነት ዘላለማዊ ነገሮችን የሚያይባቸው መስኮቶች ብቻ ናቸው እንጂ በራሳቸው ፍጻሜ አይደሉም።

በሃይማኖት ላይ የሚደገፉ ሰዎች ራሳቸውን የሚለኩትና የሚያወዳድሩት ከሌሎች ጋር ነው። የሕጋዊነት ሌላው የሚስብና የሚያስደንቅ ነገር ይህ ነው። እውነተኛ አማኝ ራሱን የሚያወዳድረው ከሌሎች ክርስቲያኖች ሳይሆን ከክርስቶስ ጋር ነው (ኤፌ. 4፡11-12)። በጸጋ በሚኖር ክርስቲያን መንፈሳዊ ጉዞ ለትዕቢት ስፍራ የለም። ሕግ

አከራሪዎች ግን ስለ ደረሱባቸው ግቦችና ወደ ራሳቸው እምነት ስላመጧቸው ሰዎች ይመካሉ (ገላ. 6፡13-14)።

አዎን በሕግ ዘንድ የሚሰብ አስደናቂ ነገር አለ። ነገር ግን ይህ ወደ ወጥመድ የሚመራ ማባበያ ብቻ ነው። አንድ አማኝ ይህን ማባበያ ከተቀበለ ራሱን በባርነት ወጥመድ ውስጥ ማስገባቱ ነው። እጅግ የሚበልጠውና የሚሻለው ነገር እግዚአብሔር በቃሉ የተናገረውን በትክክል መቀበልና በጸጋው ማረፍ ብቻ ነው። የዳንነው «በእምነት በሆነ ጸጋ» ስለሆነ «በእምነት በሆነ ጸጋ» መኖር አለብን። የበረከት መንገድ ይህ ነው፤ ሌላው መንገድ ግን የባርነት ነው።

ገላ. 3፡15-29

ወንድሞች ሆይ፥ እንደ ሰው ልማድ እላለሁ። የሰው እንኳ ቢሆን እርግጠኛውን ኪዳን ማንም አይንቅም ወይም አይጨምርበትም። ለአብርሃምና ለዘሩም የተስፋው ቃል ተነገረ። ስለ ብዙዎች እንደሚነገር፡- ለዘሮቹም አይልም፤ ስለ አንድ እንደሚነገር ግን፡- ለዘርህም ይላል፤ እርሱም ክርስቶስ ነው። ይህንም እላለሁ፤ ከአራት መቶ ሠላሳ ዓመት በኋላ የተሰጠው ሕግ አስቀድሞ በእግዚአብሔር የተረጋገጠውን ኪዳን የተስፋውን ቃል እስኪሽር ድረስ አያፈርስም። ርስቱ በሕግ ቢሆንስ እንግዲያስ በተስፋ ቃል አይሆንም፤ በተስፋ ቃል ግን እግዚአብሔር ለአብርሃም ሰጥቶአል።

እንግዲህ ሕግ ምንድር ነው? ተስፋው የተሰጠው ዘር እስኪመጣ ድረስ በመካከለኛው እጅ በመላእክት በኩል ስለ ሕግ መተላለፍ ተጨመረ። በመካከለኛውም ለአንድ ብቻ አይደለም እግዚአብሔር ግን አንድ ነው።

እንግዲህ ሕግ የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል የሚቃወም ነውን? አይደለም። ሕያው ሊያደርግ የሚቻለው ሕግ ተሰጥቶ ቢሆንስ በእውነት ጽድቅ ከሕግ በሆነ ነበር፤ ነገር ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ከማመን የሆነው የተስፋ ቃል ለሚያምኑ ይሰጥ ዘንድ መጽሐፍ ከኃጢአት በታች ሁሉን ዘግቶታል።

እምነትም ሳይመጣ ሊገለጥ ላለው እምነት ተዘግተን ከሕግ በታች እንጠበቅ ነበር። እንደዚህ በእምነት እንጸድቅ ዘንድ ሕግ ወደ ክርስቶስ የሚያመጣ ሞግዚታችን ሆኖአል፤ እምነት ግን መጥቶአልና ከእንግዲህ ወዲህ ከሞግዚት በታች አይደለንም። በእምነት በኩል ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁና፥ ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችኋልና። አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም፤ ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው የለም፤ ወንድም ሴትም የለም፤ ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና። እናንተም የክርስቶስ ከሆናችሁ እንክያስ የአብርሃም ዘር እንደ ተስፋውም ቃል ወራሾች ናችሁ።

- 6 -

የሕግ የማስተዋል ጥበብ

የይሁዲነት አቀንቃኞች ጳውሎስ ምንም ምላሽ ሊሰጥ ከማይችልበት ወጥመድ እንዳስገቡት አመኑ። ጳውሎስ እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ደኅንነት ያለው እቅድ ለሕግ ሥራዎች አንዳችም ሥፍራ እንደማይሰጠው ከብሉይ ኪዳን በመጥቀስ የማረጋገጥ ተግባሩን አጠናቆ ነበር። ይህ ከብሉይ ኪዳን ስድስት ጊዜ የመጥቀሱ ጉዳይ ግን ከባድ ችግር አስነሣ። የደኅንነት ጉዳይ ሕግን ጨርሶ የማያካትት ከሆነ በመጀመሪያ ደረጃ ሕግ ለምን ተሰጠ? ጳውሎስ ለሕግ ያለውን ዝቅተኛ ሥፍራ ለማሳየት ከሕግ ይጠቅሳል። ዳሩ ግን ሕጉ ያልተወገደ ከሆነ የጳውሎስ የመከራከሪያ አሳቦች ዋጋ የሌላቸው ይሆናሉ ማለት ነው። ምክንያቱም ጥቅሶቹ የተወሰዱት ከሕግ ነበርና ነው።

የእምነታችንን እውነተኛነት ምክንያታዊ በሆኑ ገለጻዎች ማቅረብ ይቻላል። ምንም እንኳ ማንም ሰው ሊገልጻቸው የማይችለው መለኮታዊ ምስጢራት ቢኖሩትም፥ ማንኛውም ሐቀኛ ሰው ሊረዳቸው የሚችል መለኮታዊ ምክንያቶችንም ያካተተ ነው። ጳውሎስ የአይሁድ እምነት መምህር ስለ ነበር ስለ ራሱ ለመከራከር ችሎታውም ብቃቱም ነበረው። በዚህ ክፍል በተስፋና በሕግ መካከል ያለውን ግንኙነት ለመገንዘብ የሚረዱ አራት ዐረፍተ ነገሮችን ያቀርባል።

1. ሕግ የተስፋውን ቃል መለወጥ አይችልም (3፡15-18)

በእነዚህ ቁጥሮች እግዚአብሔር በእርሱ በኩል የምድር አሕዛብ ሁሉ እንዲባረኩ ለአብርሃም የሰጠውን ተስፋ ለመግለጥ «ተስፋ» የሚለው ቃል ስምንት ጊዜ ተጠቅሷል (ዘፍ. 12፡1-3)። ይህ ተስፋ በእምነት መጽደቅንና የደኅንነት በረከቶችን ሁሉ ማግኘትን ያካትታል (ገላ. 3፡6-9)። በ2000 ዓ.ዓ. ለአብርሃም የተሰጠው ተስፋ (ዛሬም በክርስቶስ በኩል ለእኛ የተሰጠው) በ1450 ዓ.ዓ. አካባቢ ለሙሴ ከተሰጠው ሕግ ብዙ ምእተ ዓመታት ቀደም ብሎ የተሰጠ መሆኑ ግልጽ ነው። የይሁዲነት አቀንቃኞች አመለካከት የሕግ መሰጠት በመጀመሪያ የተሰጠውን ተስፋ ለውጦታል የሚል ነበር። ጳውሎስ የሚከራከረው ደግሞ አለወጠውም በማለት ነው።

በመጀመሪያ ደረጃ ሁለት የተለያዩ ወገኖች ያደረጉትን ስምምነት ከዓመታት በኋላ የመጣ ሌላ ሦስተኛ ወገን ሊለውጠው አይችልም። በቅድሚያ ያደረጉትን ስምምነት ሊለውጡ የሚችሉት ስምምነቱን ያደረጉት ሰዎች ናቸው። በስምምነቱ ላይ መጨመርም ሆነ ከስምምነቱ መቀነስ ሕገ ወጥነት ነው።

ኃጢአተኛ በሆኑ ሰዎች መካከል እንኳ ይህ እውነት ከሆነ ለቅዱሱ እግዚአብሔር ምን ያህል የበለጠ እውነት እንደሚሆን መገመት ይቻላል። አስታውስ! እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር ቃል ኪዳን አደረገ እንጂ አብርሃም ከእግዚአብሔር ጋር ቃል ኪዳን አላደረገም! እግዚአብሔር አብርሃም ማሟላት ያለበትን ምንም ቅድመ ሁኔታ አላስቀመጠም። እንዲያውም የቃል ኪዳን ስምምነቱ በሚደረግበት ጊዜ አብርሃም ተኝቶ ነበር (ዘፍ. 15 ተመልከት)። ቃል ኪዳኑ የጸጋ ቃል ኪዳን ነበር። እግዚአብሔር ለአብርሃም ቃል ኪዳን ገባለት እንጂ አብርሃም ለእግዚአብሔር ቃል ኪዳን አልገባም።

ጳውሎስ ግን በተጨማሪ ሌላ አስደናቂ እውነትን ይገልጻል። እግዚአብሔር ይህን ቃል ኪዳን ያደረገው ለአብርሃም ብቻ ሳይሆን ለክርስቶስም ጭምር ነበር። «. . . ለዘርህም ይላል እርሱም ክርስቶስ» (ገላ. 3፡16)።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ «ዘር» የሚናገረው ጽንሰ አሳብ በዘፍ. 3፡15 እንደ ተጠቀሰው ከሰው ውድቀት በኋላ የሚጀምር ነው። እግዚአብሔር በሰይጣን ዘርና (የዚህ ዓለም ልጆች፥ ዮሐ. 8፡33-44 ተመልከት) በሴቲቱ ዘር (የእግዚአብሔር ልጆችና በመጨረሻም የእግዚአብሔር ልጅ) መካከል ጠላትነት እንደሚኖር ተናገረ። መጽሐፍ ቅዱስ ይህን ጠላትነት ያሳያል። ለምሳሌ፡- በቃየልና በአቤል (1ኛ ዮሐ. 3፡10-12)፤ በእስራኤልና በአሕዛብ፤ በመጥምቁ ዮሐንስና በፈሪሳውያን፤ በኢየሱስና በፈሪሳውያን (ማቴ. 3፡7-9፥ ማቴ. 23፡29-33)፤ በእውነተኛ አማኝና በአስመሳይ አማኝ መካከል ያለውን ጠላትነት ማየት ይቻላል (ስለ እንክርዳድ የተሰጠውን ምሳሌ ተመልከት፥ ማቴ. 13፡24-30፥ 36-43)። ሰይጣን በብሉይ ኪዳን የነበረው ዓላማ የሴቲቱ ዘር (ክርስቶስ) ወደ ዓለም እንዳይመጣ መከላከል ነበር። ምክንያቱም የእግዚአብሔር ልጅ አንድ ቀን ራሱን እንደሚቀጠቅጠው ያውቅ ስለ ነበረ ነው።

ስናጠቃልለው እግዚአብሔር ይህን የተስፋ ቃል ኪዳን ያደረገው በክርስቶስ በኩል ከአብርሃም ጋር እንደ ነበር እንረዳለን። ስለዚህ በቃል ኪዳኑ ላይ ማንኛውንም ዓይነት ለውጥ ለማድረግ የሚችሉ እግዚአብሔር አብና እግዚአብሔር ወልድ ናቸው። ሙሴ ይህን ቃል ኪዳን መለወጥ አይችልም። ሊጨምርም ሆነ ሊቀንስ ጨርሶ አይችልም። የይሁዲነት አቀንቃኞች ግን በእግዚአብሔር ጸጋ ላይ ሊጨመር የሚቻል ነገር ያለ ይመስል በእግዚአብሔር ጸጋ ላይ ለመጨመር ፈለጉ፤ ከእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ኪዳን ላይ ደግሞ ቀነሱ። በመጀመሪያው የቃል ኪዳን ስምምነት ላይ ስላልነበሩ ይህን ለማድረግ መብት አልነበራቸውም።

በቁ. 17 ላይ የምንመለከተው 430 ዓመታት፥ ለመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች ለብዙ ዘመናት እንቆቅልሽ ሆኖባቸው ቆይቷል። አብርሃም ከተጠራበት ጊዜ አንሥቶ (ዘፍ. 12) ያዕቆብ ግብፅ እስከ ደረሰበት ወቅት ድረስ ያለው ጊዜ 215 ዓመታት ነው (ዘፍ. 46)። [ይህን የምናገኘው በሚከተለው ሁኔታ ነው፡- አብርሃም እግዚአብሔር ሲጠራው የ75 ዓመት ሰው ነበር፤ ይሰሐቅ ሲወለድ ደግሞ የ100 ዓመት ሰው ነበር (ዘፍ. 12፡4፥ 21፡5)። በእነዚህ ሁለት ጊዜያት መካከል ያለው ልዩነት 25 ዓመት ነው። ይሰሐቅ ያዕቆብ በሚወለድበት ጊዜ የ60 ዓመት ሰው ነበር (ዘፍ. 25፡26)፤ ያዕቆብ ደግሞ ወደ ግብፅ ሲሄድ የ130 ዓመት ሰው ነበር (ዘፍ. 47፡9)። ስለዚህ 25፡-60፡-130ለ 215 ዓመት ይመጣል።] ሙሴ ግን እስራኤላውያን በግብፅ መጻተኛ ሆነው የኖሩት ለ430 ዓመታት እንደ ነበረ ይነግረናል (ዘጸ. 12፡40)። ስለዚህ ከአብርሃም ጥሪ ጀምሮ ሕግ እስከ ተሰጠበት ጊዜ ድረስ ያሉት ዓመታት 645 እንጂ 430 አይደሉም። በዘፍ. 15፡13 እና የሐዋ. 7፡6 ደግሞ እስራኤላዊያን በግብፅ የቆዩባቸው ዓመታት 400 ዓመታት ያህል እንደ ሆኑ ተገልጾአል።

ለዚህ እንቆቅልሽ በርካታ መፍትሔዎች ቢሰጡም፥ ከሁሉ የላቀው አርኪ መልስ ግን የሚከተለው ነው፡- ጳውሎስ የቆጠረው ያዕቆብ ወደ ግብፅ የሄደበትና እግዚአብሔር ተገልጦ ቃል ኪዳኑን ካረጋገጠለት ጊዜ ጀምሮ ነው (ዘፍ. 46፡1-4)። ይህ 430 ዓመታት እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑን እንደገና ካጸናበት ጊዜ ጀምሮ ሕግ በሲና ተራራ እስከ ተሰጠበት ጊዜ ድረስ ያለው ነው።

ስለ ጊዜው ጉዳይ ከሚሰጠው መፍትሔዎች የምንመርጠው የትኛውም ቢሆን የቀረበው መሠረታዊ የመከራከሪያ አሳብ ግን ግልጽ ነው፡- ይህም

ከብዙ መቶ ዓመታት በኋላ የተሰጠው ሕግ አስቀድሞ በነበሩ ወገኖች የተደረገውን ቃል ኪዳን ለመለወጥ አይችልም የሚል ነው። እዚህ ላይ እንደ ሙሴ ሕግ ያሉ በኋላ የተሰጡ መገለጦች ቀደም ብለው ከተሰጡት ይልቅ ታላቅና የከበሩ ቢሆኑስ? የሚል ጥያቄ ሊነሣ ይችላል። ሆኖም ግን ጳውሎስ ለዚህም ቢሆን መልስ አለው።

2. ሕጉ ከተሰፋው ቃል አይበልጥም (3፡19-20)

ሕጉ በተሰጠበት ጊዜ የተፈጸመው ነገር የማይረሳና ጉልህ ነበር (ዘጸ. 19)። ነጎድጓዳዊ የመብረቅ ብልጭታ የታየበትና በዚህ ምክንያት ሕዝቡ በፍርሃት የተንቀጠቀጠበት ጊዜ ነበር። ሙሴ እንኳ በፍርሃት ሲንቀጠቀጥ ነበር (ዕብ. 12፡18-21)። ይህ ክስተት አብርሃም ቃል ኪዳኑን ከተቀበለበት ሁኔታ ጋር(ዘፍ. 15) ሲነጻጸር አስገራሚ ትዕይንት የታየበት ነበር። የይሁዲነት አቀንቃኞችም ይህ ስሜት የሚነካ ውጫዊ ድርጊት ደስ እንዳሰኛቸውና እንደነካቸው አያጠራጥርም። ጳውሎስ ግን ሕጉ ከቃል ኪዳኑ ተስፋ በሁለት መንገድ እንደሚያንስ ያመለክታል።

ሕጉ ጊዜያዊ ነበር (3፡19)። «...ተስፋው የተሰጠው ዘር እስኪመጣ ድረስ...ተጨመረ» ይላል። አሁን ጊዜያዊ የሆነው ሕግ ቋሚ ከሆነው ቃል ኪዳን ሊበልጥ እንደማይችል ግልጽ ነው። እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር የገባውን ቃል ኪዳን በምታነብበት ጊዜ አብርሃም እንዲያሟላ የተጠየቀው ቅድመ ሁኔታ መኖሩን አታይም። በቅድመ ሁኔታ ላይ የተመሠረተ አንዳችም ነገር አልነበረም። ቃል ኪዳኑ በጸጋ የተሰጠ ነበር። የሕግ በረከቶች ግን አንዳንድ ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላትን የሚጠይቁ ነበሩ። በተጨማሪም ሕጉ ማከተሚያ ነጥብ ነበረው። ይህም «ዘሩ (ክርስቶስ) እስኪመጣ ድረስ» ነበር። ሕግ በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ፍጻሜውን አግኝቶአል። ሕግ ከእኛ የሚጠይቀው ጽድቅ፥ ከእንግዲህ በመንፈስ ቅዱስ በኩል በእኛ ውስጥ ይሟላል (ሮሜ 7፡4፤ 8፡1-4)።

ሕግ መካከለኛ አገናኝን ይፈልግ ነበር (3፡19-20)። እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ ሕግን የሰጠው በመላእክት በኩል ሙሴን መካከለኛ በማድረግ ነበር። እስራኤላውያን «በመላእክት ሥነ-ሥርአት ሕግን» ተቀበሉ (የሐዋ. 7፡53)። ይህ ሕዝብ ሕጉን የተቀበለው በሦስተኛ አካል በኩል ነበር ማለት ነው። ሰንሰለቱ እግዚአብሔር ለመላእክቱ፥ መላእክት ደግሞ ለሙሴ ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር ቃል ኪዳንን ያደረገው

ያለምንም መካከለኛ አካል እርሱና አብርሃም በቀጥታ በሚገናኙበት መንገድ ነበር። እግዚአብሔር፥ ለአብርሃምና ለዘሩ የሚያደርገውን ሁሉ በቀጥታ ገለጠለት። መካከለኛ አስማሚ የሚያስፈልገው ስምምነቱ የሚደረገው በሁለት የተለያዩ አካላት መካከል ሲሆን ነው፤ የአብርሃምን ጉዳይ ስንመለከት ግን ይህን ቃል ኪዳን እግዚአብሔር ለአብርሃም ያደረገው እንጂ አብርሃም ለእግዚአብሔር የገባው ስላልነበር መካከለኛ አላስፈለገም። «እግዚአብሔር... አንድ ነው» (ገላ. 3:20)። ስለዚህ በመካከል የሚቆም ወይም የሚያስማማ አያስፈልግም።

የይሁዲነት አቀንቃኞች ሕግ በተሰጠበት ጊዜ በታየው ክብር፥ ነጎድጓድ፥ የመብረቅ ብልጭታ፥ መላእክትና ሌሎቹ ውጫዊ ነገሮች ተደንቀው ነበር። ጳውሎስ ግን ከውጫዊ ነገሮች ይልቅ አስፈላጊ የሆነውን ዋናውን ጉዳይ አሻግሮ ተመለከተ። ሕጉ ጊዜያዊ ነበር፤ መካከለኛ አገናኝም አስፈልጎት ነበር። የተሰፋው ቃል ኪዳን ግን ቋሚ ነበር፤ መካከለኛ አገናኝም አላስፈለገውም። ስለዚህ ቃል ኪዳኑ ከሕግ እጅግ የላቀ ነው ከማለት በቀር ምንም አማራጭ ሊኖር አይችልም።

3. ሕጉ የተሰፋን ቃል አይጻረርም (3:21-26)

የይሁዲነት አቀንቃኞች በቁጥር 21 ያለውን ጥያቄ «እንግዲህ ሕግ የእግዚአብሔርን የተሰፋ ቃል የሚቃወም ነውን?» በማለት ሲያስተጋቡ እንመለከታለን። እግዚአብሔር የራሱን አሳብ ይቃረናልን? ቀኝ እጁ የምታደርገውን ግራ እጁ አታውቅምን? ጳውሎስ ለዚህ ጥያቄ መልስ በሚሰጥበት ጊዜ ስለ እግዚአብሔር ዓላማዎችና መንገዶች ያለውን ጥልቅ አመለካከት ይገልጻል። የእግዚአብሔርን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ሕግ ከተሰፋው ቃል ጋር ይተባበራል አለ እንጂ ሕጉ የተሰፋ ቃሉን ይጻረራል አላለም። ሕግና ጸጋ እርስ በእርሳቸው የሚቃረኑ ቢመስሉም እንኳ በሚገባ ጠለቅ ብለን ስንመረምር ግን አንዱ ሌላውን እንደሚደግፍ እንገነዘባለን። እንጊዲህ ሕግ ለምን ተሰጠ?

(1) ሕግ የተሰጠው ሕይወትን ለማስገኘት አልነበረም (3:21)። የሙሴ ሕግ የአይሁድን ሕዝብ ሕይወት ይቆጣጠር እንደነበር እውነት ቢሆንም ለሕዝቡ መንፈሳዊ ሕይወት አልሰጠም፤ ሊሰጥም አይችልም ነበር(ገላ. 3:21፥ ከ2:21 ጋር መመሳከር አለበት)። ሕይወትና ጽድቅ በሕግ በኩል የሚገኙ ቢሆን ኖሮ ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ መሞት

አያስፈልገውም ነበር። ነገር ግን ኢየሱስ ሞቷልና፤ ስለዚህ ሕግ ለኃጢአተኞች ሕይወትና ጽድቅ ሊሰጥ ጨርሶ አይችልም ማለት ነው። እስራኤላውያንን ራስን ወደሚያጸድቅ ሃይማኖታዊ ሥነ-ምግባር የመራቸው «የሕግ አምልኮ» ነበር። ክርስቶስን እንዳይቀበሉ ያደረጋቸውም ይህ ነበር (ሮሜ 9፡30-10፡13)።

2 ሕግ የተሰጠው ኃጢአትን ለመግለጥ ነበር (3፡19፥ 22)

አንድን ኃጢአተኛ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ለማምጣት ሕግና ጸጋ ሲተባበሩ የምናየው እዚህ ላይ ነው። ሕግ ለአንድ ኃጢአተኛ ጥፋተኛ መሆኑን ሲያሳየው ጸጋ ደግሞ በክርስቶስ ሊያገኘው የሚችለውን ይቅርታ ያሳየዋል። «ሕግ ቅዱስ ነው፤ ትዕዛዚቱም ቅድስትና ጻድቅት በጎም ናት» (ሮሜ 7፡12)። እኛ ግን የረከስን ኃጢአተኞችና ክፉዎች ነን። ኃጢአተኛ የሚያደርገን ሕግ አይደለም፤ ኃጢአተኞች መሆናችንን ግን ይገልጥልናል (ሮሜ 3፡2 ተመልከት)። ሕጉ «እድፋም ፊታችንን» የሚያሳየን መስተዋት ነው (ያዕ. 1፡22-25)። ያደፈውን ፊታችንን ግን በመስተዋት አንታጠብም። በኢየሱስ ክርስቶስ ደም በኩል መንጻትን የሚሰጠን ግን ጸጋ ነው (1ኛ ዮሐ 1፡7)።

ሕጉን ትክክለኛና ተገቢ በሆነ ሁኔታ ልንጠቀምበት እንችላለን፤ በማይገባ መንገድም ልንጠቀምበት እንችላለን (1ኛ ጢሞ. 1፡8-11)። ትክክለኛውና ተገቢው መንገድ የሰዎችን ኃጢአት ሲያሳያቸውና አዳኝ ወደሆነው ጌታ ሲመራቸው ነው። የተሳሳተውና የማይገባው መንገድ ደግሞ ሕግን በመጠበቅ ደህንነትን ለማግኘት መሞከር ነው። ሰዎች «አሥርቱን ሕግጋት በመጠበቅ» ደህንነትን እንዳገኙ ሲናገሩ፥ ስለ እውነተኛው የሕግ ትርጉም ምንም የማያውቁ መሆናቸውን ነው የሚገልጡት። ሕግ አሕዛብም ሆኑ አይሁድ (ጠቅላላ የሰው ዘር) «ከኃጢአት በታች ሁሉን ዘግቶታል» (ገላ. 3፡22)። ሁሉም ኃጢአተኞች ስለ ሆኑ፥ ሁሉም በጸጋ ሊድኑ ይችላሉ። እግዚአብሔር አንድ እንጂ ሁለት የደህንነት መንገድ የለውም። ይኸውም በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ብቻ ነው።

3 ሕግ ለክርስቶስ መንገድ ለማዘጋጀት የተሰጠ ነበር (3፡23-26)

ጳውሎስ የሞግዚትን ሥራ እንደ ምሳሌ ያቀርባል፤ የሞግዚት ምንነት ለአብዛኛዎቹ አንባቢዎች እንግዳ ሊሆንባቸው አይችልም። በብዙ የግሪክና የሮም ቤተሰቦች ዘንድ በሚገባ የሠለጠነ ባሪያ ልጆችን ትምህርት ቤት በማድረስና በመመለስ እንዲሁም ከትምህርት ቤት ውጭ ባሉ ሰዓታት እነርሱን በመጠበቅ ያገለግል ነበር። አንዳንድ ጊዜ እነዚህን ልጆች ያስተምራቸዋል፤ ክፉ እንዳይደርስባቸው ይጠብቃቸዋል፤ የማይገባ ነገር እንዳያደርጉም ይከለክላቸዋል፤ አንዳንዴም ሊቀጣቸው እንኳ ይችላል። ጳውሎስ «ሞግዚት» የሚለው ይህንን ነው (3፡24)። ስለዚህ ይህ ቃል እንደ ዘመናዊው መምህር ዓይነት ትርጉም ሊሰጠው አይገባውም። የግሪኩ ቃል ትርጉም «ፔዳጎግ» የሚል ቃል የሚሰጥ ሲሆን የዚህ ቀጥተኛ ትርጉም «የልጅ መሪ» እንደ ማለት ነው።

ጳውሎስ ይህንን ምሳሌ በመጠቀም ስለ አይሁድና ስለ ሕጋቸው በርካታ ነገሮችን ይናገራል። በመጀመሪያ ደረጃ አይሁዶች በሕግ አደጉ እንጂ በሕግ አልተወለዱም ይላል። ባሪያው የልጆች ጠባቂና ሥርዓት አስያዥ እንጂ አባት አይደለም። ስለዚህ ሕግ የእስራኤልን ሕይወት ይቆጣጠራል እንጂ ለእስራኤል ሕይወትን አይሰጥም። የይሁዲነት አቀንቃኞች ሕግ ለሕይወትና ለጽድቅ አስፈላጊ ነው በማለት ቢያስተምሩም ጳውሎስ ግን ስሕተታቸውን እያጋለጠ ነው።

ጳውሎስ የሚያቀርበው ሌላው ሁለተኛ ነጥብ ከዚህም የላቀ ጠቃሚ ነው። የጠባቂው (የሞግዚቱ) ሥራ ልጁን ለብስለት(ለእድገት) ማዘጋጀት ሲሆን ልጁ የተወሰነ የእድገት ደረጃ ላይ ከደረሰ በኋላ ግን ሞግዚት አያስፈልገውም፤ ስለዚህ ሕግም የተሰፋው ዘር ኢየሱስ ክርስቶስ እስኪመጣ ድረስ የእስራኤልን ሕዝብ የሚያዘጋጅ ነበር። በእግዚአብሔር እቅድ ውስጥ የመጨረሻው ግብ የእርሱ መምጣት ነበር (ቁ. 22)፥ ነገር ግን «እምነት (ክርስቶስ) ሳይመጣ» (ቁ. 23) የእስራኤል ሕዝብ «በሕግ ታስሮ ነበር» (ቀጥተኛ ትርጉም ነው)።

እስራኤልን ከአሕዛብ የለየው ሕግ ነበር (ኤፌ. 2፡12-18)። የሕይወታቸውን የተለየ ገጽታ ሁሉ ይገዛ ነበር። በአይሁድ ሕዝብ የምእተ

ዓመታት ታሪክ ሕግ ለክርስቶስ መምጣት እያዘጋጃቸው ነበር። አዳኝ እንደሚያስፈልጋቸውም የሚያስገነዝባቸው ነበር። በሕግ ውስጥ የሚገኙት ጥላዎችና ተምሳሌቶች የመሢሑ አምሳያዎች ነበሩ (ሉቃስ 24፡27 ተመልከት)።

ለዚህ መልካም ምሳሌ የሚሆንልን በማቴዎስ 19፡16-22 የተጠቀሰው የወጣቱ ባለጠጋ ታሪክ ነው። ይህ ሰው ማንኛውም ሰው የሚያስፈልገው ነገር ሁሉ ቢኖረውም እርካታ ግን አልነበረውም። በሕይወቱ ዘመን ሁሉ ትእዛዛትን ለመጠበቅ ቢሞክርም አንድ የጎደለው ነገር እንዳለ ግን ይሰማው ነበር። ወደ ክርስቶስ ያመጡት ራሳቸው ሕግጋቱ ነበሩ። ኃጢአተኞች በደላቸውን እንዲገነዘቡ ማድረግ ከሕግ ዓላማዎች አንዱ ነው። በዚህ ሰው ታሪክ ውስጥ የሚያሳዝነው ነገር በሕግ መስተዋት ውስጥ ራሱን ሲመለከት የመጨረሻው ትዕዛዝ ማለትም («አትመኝ») የሚለውን አልፈጸመም ነበር። ስለዚህ ለተገለጸለት ነገር ታማኝ ባለመሆኑ የዘላለምን ሕይወት ሳያገኝ ተመለሰ።

ሕግ ዓላማውን ፈጽሟል፤ አዳኙ ስለ መጣ «ሞግዚት» ከእንግዲህ አያስፈልግም። መሢሑ በተገለጸበት ወቅት የእስራኤል ሕዝብ ሳይቀበሉት በመቅረታቸው አሳዛኝ ነው። ይህም በመሆኑ እግዚአብሔር በመጨረሻ ቤተ መቅደሱን መደምሰስና ሕዝቡን መበተን ነበረበት። ስለዚህም ዛሬ ለሃይማኖተኛው አይሁዳዊም ቢሆን አባቶቹ ሲያመልኩ በነበሩበት መንገድ እግዚአብሔርን ለማምለክ አይቻለውም። መሠዊያ፥ የክህነት አገልግሎት፥ መሥዋዕት፥ ቤተ መቅደስና ንጉሥ የለውም (ሆሴ. 3፡4)። በክርስቶስ ያመነ ማንኛውም ሰው ግን አይሁድ ሆነ አሕዛብ የእግዚአብሔር ልጅ የመሆንን መብት እንዲያገኝ እነዚህ ነገሮች ሁሉ በክርስቶስ ተፈጽመዋል።

ሕጉ የተሰፋ ቃሉን ሊለውጥ አይችልም፤ ደግሞም ከተሰፋ ቃሉ አይበልጥም። ነገር ግን ሕጉ የተሰፋ ቃሉ ተጻራሪ አይደለም፤ ሕግና ጸጋ በአንድነት ኃጢአተኞችን ወደ አዳኛቸው ለማምጣት የሚሠሩ ናቸው።

4. ሕግ የተሰፋው ቃል ሊያደርገው የሚችለውን ነገር ማድረግ አይችልም (3፡27-29)

በኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት የእስራኤል ሕዝብ ከልጅነት ወደ ጉልምስና ተሸጋገረ። ረጅሙ የዝግጅት ወቅት ተጠናቀቀ። ሕግ የተወሰነ ክብር ቢኖረውም፥ በክርስቶስ የሚገኘው የእግዚአብሔር የጸጋ ማዳን ግን

እጅግ የላቀ ክብር ነበረው። ሕግ ኃጢአትን መግለጥ ይችላል፤ እስከ ተወሰነ ደረጃ ቢሆንም ባሕርይንም መቆጣጠር ይችላል። ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስ ለኃጢአተኛ የሚያደርገውን ነገር ማድረግ ጨርሶ አይችልም።

በመጀመሪያ ደረጃ ሕግ ኃጢአተኛን ማጽደቅ አይችልም። እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- «ኃጢአተኛን አላጸድቅም» (ዘጸ. 23፡7)። ጳውሎስ ግን እግዚአብሔርን «ኃጢአተኛውን የሚያጸድቅ» ብሏል (ሮሜ 4፡5)። ንጉሥ ሰለሞን የሠራው ቤተ መቅደስ በሚመረቅበት ወቅት ባደረገው ጽሎት «በበደለኛውም ላይ ፍረድ፤ . . . ንጹሑንም አጽድቀው» አለ (1ኛ ነገሥት 8፡32)። በእግዚአብሔር የቅድስና ዓይን ስንመለከተው ይህ ትክክለኛና ተገቢ ጸሎት ነበር። ችግሩ ግን ጻድቅ የሆነ ማንም አለመኖሩ ነው። ኃጢአተኛ በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ የሚባለው በክርስቶስ በሚያምንበት ጊዜ ብቻ ነው።

በተጨማሪም ሕግ ሰውን ከእግዚአብሔር ይለያል እንጂ አንድ ሊያደርገው ጨርሶ አይችልም። እግዚአብሔር በሚገለጥበት በመገናኛው ድንኳን ዙሪያ አጥር ነበር። በቅድስትና በቅድስተ ቅዱሳን መካከል ደግሞ መጋረጃ ነበር።

በክርስቶስ ማመን ግን «ወደ ክርስቶስ ውስጥ» ያጠምቀናል (ገላ. 3፡27 ቀጥተኛ ትርጉም)። ይህ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት አማኙን የክርስቶስ ወገን ያደርገዋል፤ የአካሉ ክፍልም ያደርገዋል (1ኛ ቆሮ. 12፡12-14)። የውኃ ጥምቀት የዚህ የመንፈስ ቅዱስ ውስጣዊ ሥራ ውጫዊ ተምሳሌት ነው (የሐዋ. 10፡44-48 ተመልከት)።

«ክርስቶስን ለብሳችኋልና» (ገላ. 3፡27) የሚለው ሐረግ ልብስ መለወጥን የሚያመለክት ነው። አማኞች እድፋሙን የኃጢአት ቡትቶ አውልቀው ጥለው (ኢሳ. 64፡6)፥ በእምነት ከክርስቶስ ጋር ባላቸው አንድነት የጽድቅ መጎናጸፊያ ተቀብለዋል (ቆላ. 3፡8-15 ተመልከት)። ለገላትያ ሰዎች ግን «ልብስን የመቀየር» አሳብ ተጨማሪ ትርጉም ነበረው። አንድ ሮማዊ ሕጻን ከልጅነት ዕድሜው አልፎ ወደ ጉልምስና ሲደርስ የልጅነት ልብሱን አውልቆ ቶጋ የሚባለውን የአዋቂ ልብስ ይለብስ ነበር። በክርስቶስ ያመነ ግን ለእግዚአብሔር ሕፃን ልጅ ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔር ጎልማሳ ልጅ ጭምር ነው (ገላ. 3፡26 ተመልከት፤ በዚህ ስፍራ ሕፃን የሚለው ቃል የእግዚአብሔር ጎልማሳ ልጅ ተብሎ መተርጎም አለበት)።

አማኞቹ በእግዚአብሔር ፊት ያላቸው ስፍራ የነልማሳ ልጅ ሆኖ ሳለ፥ ታዲያ ሕየንነትን ወደሚያመለክተው ወደ ሕግ አሳብ ለምን ይመለሳሉ?

«ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና» (ገላ. 3፡28) የሚለው ምን ዓይነት አስደናቂ አባባል ነው! ሕግ በግለሰቦችና በሕዝቦች መካከል ብቻ ሳይሆን በተለያዩ የምግብ ዓይነቶችና እንስሳት መካከል እንኳ ልዩነት አድርጓል። ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ለመከፋፈል ሳይሆን አንድ ለማድረግ መጣ።

በገላትያ ጎብረተሰብ ውስጥ ባሪያዎች እንደ ዕቃ ይቆጠሩ ነበር፤ ሴቶችም ምንም ክብር አልነበራቸውም፤ አይሁዳውያን ደግሞ አሕዛብን ይንቋቸው ነበር፤ ስለሆነም ይህ ለገላትያ ክርስቲያኖች ደስ የማያሰኝ ዜና ነበር።

ፈሪሳዊያን በየቀኑ ጥዋት እንዲህ እያሉ ይጸልዩ ነበር፡- «እግዚአብሔር ሆይ! አይሁድ እንጂ አሕዛብ ስላልሆንኩ፥ ወንድ እንጂ ሴት ስላልሆንኩ፥ ነፃ ሰው እንጂ ባሪያ ስላልሆንኩ አመሰግንሃለሁ»። በክርስቶስ ግን እነዚህ ሁሉ ልዩነቶች ተወግደዋል።

ይህ ማለት ክርስቶስን በማመን በምንለወጥበት ጊዜ ብሔራችን፥ የፖለቲካ አቋማችን ወይም ጾታችን ይለወጣል ማለት አይደለም። ነገር ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን መንፈሳዊ ግንኙነት በተመለከተ እነዚህ ነገሮች ዋጋ አይኖራቸውም ማለት ነው። ሕግ ይህን ልዩነት ቢያጠናክረውም እግዚአብሔር ግን በጸጋው ለሰዎች ሁሉ ምህረትን ያደርግ ዘንድ፥ በእርሱ ፊት ሁሉም እኩል መሆናቸውን አወጀ (ሮሜ 11፡25-32)።

በመጨረሻ ሕግ የእግዚአብሔር ወራሾች ሊያደርገን ፈጽሞ እንደማይችል እናያለን (ገላ. 3፡29)። እግዚአብሔር የተስፋ ቃል የሰጠው ለአብርሃም ዘር ነበር። ያም ዘር ክርስቶስ ነው። (ዘር የሚለው ቃል በነጠላ ቁጥር መሆኑን ልብ በል 3፡16)። በእምነት «በክርስቶስ ውስጥ» ከሆንን በመንፈሳዊ አነጋገር እኛም የአብርሃም ዘሮች ነን ማለት ነው። ይህም ማለት እግዚአብሔር ለአብርሃም ተስፋ የሰጠው መንፈሳዊ በረከቶች ሁሉ ወራሾች ነን ማለት ነው። እንዲህም ስለ ተባለ በተለይ ለእስራኤል ተስፋ የተገቡለት ቁሳዊና ብሔራዊ በረከቶች በሙሉ ቅርተዋል ማለት አይደለም። ነገር ግን በዚህ ጊዜ ያለን ክርስቲያኖች ለመንፈሳዊ ብልጥግናችን ምክንያቱ

እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባቸው ተስፋዎች መሆናቸውን ለማሳየት ነው (ሮሜ 11፡13-36 ተመልከት)።

የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን በምናነብበት ጊዜ ይህ የገላትያ ክፍል እጅግ ዋጋ ያለው ሆኖ እናገኘዋለን። የብሉይ ኪዳን መንፈሳዊ ትምህርቶች ለአይሁዶች ብቻ የተሰጡ ሳይሆኑ፥ ለክርስቲያኖችም ከሕይወታቸው ጋር የሚያዛምዷቸው ትምህርቶች እንዳሉዋቸው እናያለን (ሮሜ 15፡4ና 1ኛ ቆሮ. 10፡11-12 ተመልከት)። ብሉይ ኪዳን የክርስቶስን መምጣት ቅድመ ዝግጅት ሲያመለክተን፥ በወንጌል ደግሞ እርሱን ራሱን ቀርቦ እናየዋለን። እንደዚሁም ከሐዋርያት ሥራ እስከ ራዕይ ያለው ክፍል ክርስቶስን የግል አድርጎ መቀበል በግልጽ የሚያመለክተን ነው።

ይህንን በክርስቶስ ያለህን ስፍራ በሚገባ በምትገነዘብበት ጊዜ ለክርስትና ሕይወትህ አዲስ አድናቆትና አመለካከት ይኖርሃል። ይህ ሁሉ የተገኘው በጸጋ እንጂ በሕግ አይደለም። አንተ በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ ጎልማሳ ልጅና ወራሽ ነህ። ታዲያ፥ በርስትህ እየተጠቀምህ ነውን? በሚቀጥለው ክፍል የጳውሎስ ዐቢይ ዓላማ ይህን ማብራራት ይሆናል።

ገላትያ 4፡ 1-18

ነገር ግን እላለሁ፥ ወራሹ ሕፃን ሆኖ ባለበት ዘመን ሁሉ፥ ምንም የሁሉ ጌታ ቢሆን ከቶ ከባሪያ አይለይም፤ ነገር ግን አባቱ እስከ ቀጠረለት ቀን ድረስ ከጠባቂዎችና ከመጋቢዎች በታች ነው። እንዲሁ እኛ ደግሞ ሕፃናት ሆነን ሳለን ከዓለም መጀመሪያ ትምህርት በታች ተገዝተን ባሪያዎች ነበርን፤ ነገር ግን የዘመኑ ፍፃሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ከሕግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ፤ እንደ ልጆች እንሆን ዘንድ፥ ከሕግ በታች ያሉትን ይዋጅ ዘንድ። ልጆችም ስለ ሆናችሁ እግዚአብሔር አባ አባት ብሎ የሚጮኽ የልጁን መንፈስ በልባችሁ ውስጥ ላከ። ስለዚህ ከእንግዲህ ወዲህ ልጅ ነህ እንጂ ባሪያ አይደለህም፤ ልጅም ከሆንህ ደግሞ በክርስቶስ የእግዚአብሔር ወራሽ ነህ።

ነገር ግን በዚያን ጊዜ እግዚአብሔርን ሳታውቁ በባሕርያቸው አማልክት ለማይሆኑ ባሪያዎች ሆናችሁ ተገዛችሁ፤ አሁን ግን እግዚአብሔርን ስታውቁ ይልቅስ በእግዚአብሔር ስትታወቁ እንደገና ወደ ደካማ ወደሚናቅም ወደ መጀመሪያ ትምህርት እንዴት ትመለሳላችሁ? እንደ ገና ባሪያዎች ሆናችሁ ዳግመኛ ለዚያ ልትገዙ ትወዳላችሁን? ቀንንና ወርን ዘመንንም ዓመትንም በጥንቃቄ ትጠብቃላችሁ። ምናልባት በከንቱ ለእናንተ ደክሜአለሁ ብዬ እፈራችኋለሁ።

ወንድሞች ሆይ፥ እኔ ደግሞ እንደ እናንተ ሆኜአለሁና፡- እንደ እኔ ሁኑ ብዬ እለምናችኋለሁ። አንዳችም አልበደላችሁኝም። በመጀመሪያ ወንጌልን በሰበክሁላችሁ ጊዜ ከሥጋ ድካም የተነሣ እንደ ነበረ ታውቃላችሁ፤ በሥጋዬም ፈተና የሆነባችሁን ነገር አልናቃችሁትምና አልተጸየፋችሁትም፤ ነገር ግን እንደ እግዚአብሔር መልአክ አዎን እንደ ክርስቶስ ኢየሱስ ተቀበላችሁኝ። እንግዲህ ደስ ማሰኘታችሁ ወዴት አለ? ቢቻልስ ዓይኖቻችሁን አውጥታችሁ በሰጣችሁኝ ብዬ እመሰክርላችኋለሁ። እንኪያስ እውነቱን ስለ ነገርኋችሁ ጠላት ሆንሁባችሁን? በብርቱ ይፈልጉአችኋል፥ ለመልካም አይደለም፤ ነገር ግን በብርቱ ትፈልጉአቸው ዘንድ በውጭ ሊያስቀሩአችሁ ይወዳሉ። ነገር ግን ከእናንተ ዘንድ በምኖርበት ጊዜ ብቻ ሳይሆን ሁልጊዜ በመልካም ነገር ተፈላጊ ብትሆኑ መልካም ነው።

- 7 -

ለማደግ ጊዜው አሁን ነው!

የሕግ አከራካሪነት አንዱ አሳዛኝ ገጽታ ደግሞ፥ ምንም እንኳ በውጫዊ መልኩ ሲታይ ሰውን ወደ መንፈሳዊ ብስለት የሚመራ ቢመስልም፥ ሐቁ ግን እንደገና ወደ መንፈሳዊ ልጅነት መምራቱ ነው። አብዛኛዎቹ አማኞች እንደሚመኙት ሁሉ የገላትያ ክርስቲያኖች ለማደግና በክርስቶስ ወደፊት ለመጓዝ ይፈልጉ ነበር። እድገታቸው ግን በተሳሳተ መንገድ ነበር። ይህ ልምምድ የተሻለ ክርስቲያን ለመሆን ብለው በተለያዩ የሕጋዊነት እንቅስቃሴዎች ከሚሳተፉ ሰዎች ልምምድ የተለየ አይደለም። የልባቸው ውስጣዊ ዓላማ ትክክል ቢሆንም ለማደግ የሚጠቀሙበት መንገድ ግን የተሳሳተ ነው።

ጳውሎስ በገላትያ ለነበሩና በእርሱ አገልግሎት ለተለወጡ ተወዳጅ አማኞች ሊያስተላልፈው የፈለገው እውነት ይህንኑ ነው። ሕግ የተሻሉ ክርስቲያኖች እንደሚያደርጋቸው እንዲያስቡ የይሁዲነት አቀንቃኞች አደንዝዘዋቸው ነበር። ሕግ አንዳንድ ነገሮች እንዲያደርጉና ያደረጉአቸውንም ነገሮች ውጫዊ ውጤቶች ለመመዘን ያስችላቸው ስለ ነበር አሮጌው ተፈጥሮአቸው በዚህ ተማርኮ ነበር። ድርጊታቸውን በሚመዝኑበትና የሥራ ክንውናቸውን በሚያዩበት ጊዜ ከመርካታቸው በተጨማሪ ጥቂትም ቢሆን ትምክህት እንደሚሰማቸው የተረጋገጠ ነው። እውነታው ሲታይ ወደ ኋላ እየተመለሱ ቢሆንም ለእነርሱ ግን ወደፊት እንደሚሄዱ ይመስላቸው ነበር።

እነዚህ ሰዎች የሚጓዙበትን አውሮፕላን የሚነዳው ነጂ የሚከተለውን ማስታወቂያ ሲናገር የሰሙትን ተጓዦች ይመስላሉ፡- «ተጓዦቻችን፥ አይሮፕላናችን አቅጣጫውን ስቷል፤ በዚህም ሁኔታ ያለአንዳች ዓላማ ስንጓዝ ከአንድ ሰዓት በላይ ሆኖናል። ይህ መጥፎ ዜና ቢሆንም መልካሙ ዜና ግን ጊዜያችንን በጥሩ ሁኔታ እያሳለፍን መሆናችን ነው።»

የገላትያ ሰዎች የክርስትና ሕይወትን ለመኖር ሕጋዊነት እንደማያስፈልጋቸው ለማሳመን ጳውሎስ ሦስት ነጥቦችን አቅርቦአል። የሚያስፈልጋቸው ሁሉ በኢየሱስ ክርስቶስ ውስጥ አላቸው።

1. የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባል የሆኑበትን መንገድ ይገልጽላቸዋል (4፡1-7)።

በክርስትና ሕይወታችን ካገኘናቸው በረከቶች አንዱ በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ እንደ ልጅ መሆናችን ነው (ገላ. 4፡5፥ ኤፌ. 1፡5)። ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብነት የገባነው አንድ ማደሪያና መጠለያ የሌለው ልጅ በአንድ ቤተሰብ ውስጥ እንዲኖር በሚደረግበት መንገድ አይደለም። የእግዚአብሔር ቤተሰብ የሆንነው ከእግዚአብሔር ዳግም በመወለድ ነው (ዮሐ. 3፡3)።

አዲስ ኪዳን ለዚህ ቃል የሚሰጠው «ጎልማሳ ሆነን እያለ የአንድ ቤተሰብ አባል መሆን» የሚል ነው። በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ስላለን ስፍራ የሚናገር ቃል ነው። የልጅነት መብት ሁሉ የተሰጠን ትላልቅ ልጆች ነን እንጂ ሕፃናት አይደለንም።

አብዛኛዎቹ የአዲስ ኪዳን ትርጉሞች በእግዚአብሔር ሕፃናት ልጆችና በእግዚአብሔር ጎልማሳ ልጆች መካከል ልዩነት መኖሩን ያለመግለጣቸው የሚያሳዝን ነው። በክርስቶስ በማመናችን ከእግዚአብሔር ቤተሰብ ለመወለዳችን እውነት ነው። በዚህ ሁኔታ በመወለዳችንም የእግዚአብሔር ጎልማሳ ልጆች ሆነን በዚያ ቤተሰብ ውስጥ የወራሽነት መብትና ሥልጣን አለን። አንድ ኃጢአተኛ በክርስቶስ አምኖ ሲድን ዕድገት የሚያስፈልገው «መንፈሳዊ ሕፃን» (1ኛ ጴጥ. 2፡2-3) ተደርጎ ነው የሚቆጠረው። ሆኖም ስለ ስልጣኑ ካሰብን ግን የአባቱን ሀብት በሙሉ መጠቀም የሚችልና የልጅነት መብቶች የተረጋገጡለት ጎልማሳ ልጅ ነው።

የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባል የምንሆነው በዳግም ልደት ሲሆን፥ በእግዚአብሔር ቤተሰብ አባልነታችን የምንደሰተው ግን እንደ ልጅ በመቆጠራችን ይሆናል። ስለዚህ በክርስቶስ ላለው መንፈሳዊ ብልጥግና ተጠቃሚ ለመሆን አንድን ክርስቲያን ምንም የሚያግደው ነገር አይኖርም። «ልጅም ከሆንህ ደግሞ በክርስቶስ የእግዚአብሔር ወራሽ ነህ» (ገላ. 4፡7)። ከዚህ በመቀጠል ጳውሎስ ወደ አንድ ቤተሰብ በጎልማሳነት እንደ ልጅ ስለ መቀላቀል ለአንባቢዎቹ ሦስት እውነታዎችን በመጥቀስ ያስታውሳቸዋል።

እነርሱም የሚከተሉት ናቸው፡- በፊት የባርነት ልጆች ነበርን (4፡1-3)። አባቱ ምንም ያህል ባለጸጋ ቢሆንም፥ ለአካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ የአባቱ ሀብት ተጠቃሚ ሊሆን አይችልም። በሮም ግዛት የነበሩ ባሪያዎች

ለሀብታም ጌቶቻቸው ልጆች እንክብካቤ ያደርጉ ነበር። የማንም ልጅ ይሁን በባርያው ቁጥጥር ሥር እስካለ ድረስ ሕፃን ነው። ሕፃኑ ልጅ ከሚጠብቀው አገልጋይ ብዙም የተሻለ ደረጃ የለውም። አገልጋዩን የሚያዘው የቤቱ ጌታ ነው፤ አገልጋዩ በተራው ደግሞ ሕፃኑን ያዘዋል።

በሕግ ዘመን የአይሁዶች መንፈሳዊ ሁኔታ ይህን ይመስላል። እንደምታስታውሰው ሕግ ሕዝቡን ሥርዓት የሚያስይዝና ለክርስቶስ መምጣት የሚያዘጋጅ «ሞግዚት» ነበር (ገላ. 3:23-25)። ስለዚህ የይሁዲነት አቀንቃኞች፥ የገላትያን ሰዎች ወደ ሕጋዊነት በሚመልሱበት ጊዜ ወደ ሃይማኖታዊ ባርነት ብቻ ሳይሆን ወደ መንፈሳዊ ሕፃንነትና ያለመብሰል እየመሯቸው ነበር።

ጳውሎስ አይሁዳውያንን «ከዓለም መጀመሪያ ትምህርት በታች» (4:13) ሆነው እንደ ትናንሽ ልጆች በባርነት ውስጥ እንደ ነበሩ ይናገራል። ይህም ማለት መሠረታዊ ትምህርት የሚረዱ ወይም እንደ አዲስ ፊደል ቆጣሪ አስተሳሰብ ጨቅላዎች ነበሩ። ስለዚህ እስራኤላውያን ለ15 ምእተ ዓመታት ለክርስቶስ መምጣት እንዲዘጋጁ መንፈሳዊ ፊደል በሚማሩበት የሕፃናት መጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ነበሩ። ከዚያ በኋላ «አልፋና ኦሜጋ» (ራዕይ 22:13) የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ይገለጥላቸዋል። ለሰው ልጅ የሚያስፈልገው መንፈሳዊ መገለጥ ሁሉ የተጠቃለለው በእርሱ ነው። የእግዚአብሔር የመጨረሻ ቃልም እርሱ ነው (ዕብ. 1:1-3)።

ስለዚህ ሕጋዊነት ወደ ኋላ ወደ ልጅነት መመለስ እንጂ ወደፊት ወደ ጉልምስናና ወደ ብስለት መጓዝ አይደለም። ሕግ በክርስቶስ ወደሚገኘው የመጨረሻ መገለጥ የሚደረግ ዝግጅት እንጂ የእግዚአብሔር የመጨረሻ መገለጥ አይደለም። እርግጥ አንድን ቋንቋ ለመረዳት መሠረት የሆኑትን ፊደሎቹን ማወቁ ወሳኝ ነው። ዳሩ ግን ከቤተ መጻሕፍት ውስጥ ገብቶ በየመደርደሪያው ላይ ያሉትን ትላልቅ ሥነ-ጽሑፎች በማንበብ ምትክ ፊደሎችን በመደጋገም የሚቆጥር ሰው ያልበሰለ አላዋቂ መሆኑን ያሳያል። በሕግ ሥር የነበሩ አይሁዳውያን በነጻነት ሐሴት የሚያደርጉ ጎልማሳ ልጆች ሳይሆኑ የባርነት ልጆች ነበሩ።

እግዚአብሔር ግን ከባርነት ዋጀን (4:4-5)። «የዘመኑ ፍጻሜ» (ቁ. 4) የሚለው አገላለጽ ዓለም በእግዚአብሔር ፈቃድና ጥበቃ ለአዳኙ መወለድ ተዘጋጅታ ስትጠብቅ የነበረችበትን ጊዜ ያመለክታል። ኢየሱስ በተወለደበት

ወቅት በሮም ግዛት ሥር የነበሩት ሕዝቦች የታላቁን ነፃ አውጪ መምጣት በታላቅ ናፍቆት ይጠባበቁ እንደ ነበር ታሪክ አዋቂዎች ይናገራሉ። የቀድሞዎቹ ሃይማኖቶች እየሞቱ ነበር፤ የጥንቶቹ ፍልስፍናዎች የሰዎችን ሕይወት ለመለወጥ የማይችሉ ባዶና ኃይል አልባ ሆነዋል፤ አዲስና እንግዳ ሃይማኖቶች አገሩን እያጥለቀለቁ ነበር። በሁሉም ስፍራ ሃይማኖታዊ ክስረትና መንፈሳዊ ረሃብ ነበር። በዚህ ሁሉ የሚታየው እግዚአብሔር ለልጁ መገለጥ ዓለምን እያዘጋጀ እንደ ነበረ ነው።

ከታሪካዊ አመለካከት አንጻር ስንመለከተው የሮም መንግሥት ራሱ እንኳ ለአዳኙ መወለድ ዓለምን በማዘጋጀት ረድቷል። ከተሞች እርስ በእርሳቸውና በመጨረሻም ከሮም ከተማ ጋር የሚያገናኙባቸው መንገዶች ተሠርቶላቸው ነበር። የሮም ሕግጋት የዜጎችን መብት ሲያስከብሩ ወታደሮቹ ደግሞ ሰላምን ያስጠብቁ ነበር። ከግሪካውያንና ሮማውያን ወራሪዎች የተነሣ የላቲንንና የግሪክ ቋንቋ በሮም ግዛት ሁሉ ታዋቂ ሆኑ። የክርስቶስ በቤተልሔም መወለድ በእግዚአብሔር እቅድ የተፈጸመ ድርጊት እንጂ አጋጣሚ አልነበረም። «የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ» ኢየሱስ መጣ። (ዳግም ተመልሶ የሚመጣውም በትክክለኛው ወቅት መሆኑን በዚህ አጋጣሚ ማስተዋል አለብን።)

ጳውሎስ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላካዊና ሰብዓዊ ባሕርያት እንዳሉት በጥንቃቄ ገልጿል (ቁ.4)። እንደ አምላክነቱ «ከአብ ወጥቶ» መጥቷል (ዮሐ. 16፡28)። ነገር ግን እንደ ሰውነቱ ደግሞ «ከሴት ተወልዷል»። በጥንቱ የተሰፋ ቃል አዳኙ «ከሴቲቱ ዘር» የሚገኝ እንደሚሆን ተገልጾ ነበር (ዘፍ. 3፡15)። ኢየሱስ ያንን የተሰፋ ቃል ፈጽሞታል (ኢሳ. 7፡14፤ ማቴ. 1፡18-25)።

ጳውሎስ የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ የመጣው ማን እንደሆነ፥ መቼ እንደ መጣና እንዴት እንደ መጣ ነግሮናል። አሁን ደግሞ ለምን እንደ መጣ ይገልጽልናል፡- «ከሕግ በታች ያሉትን ይዋጅ ዘንድ» (ገላ. 4፡5)። መዋጀት የሚለውን ቃል ከዚህ በፊት ተጠቅሞበታል (3፡13)። ትርጉሙም «ዋጋ በመክፈል ነፃ ማውጣት» ማለት ነው። አንድ ሰው በየትኛውም የሮም ከተማ ውስጥ ባሪያ በመግዛት የገዛውን ባሪያ ለራሱ በባርነት ሊያሳድረው ወይም ነፃ ሊያወጣው ይችል ነበር። (በሮም መንግሥት ውስጥ በጠቅላላ ወደ 60 ሚሊየን የሚደርሱ ባሮች ነበሩ።) ኢየሱስ የመጣው ነፃ ሊያወጣን ነው። ስለዚህ ወደ ሕግ ወደ ኋላ መመለስ ማለት ክርስቶስ በመስቀል ላይ የሠራውን ሥራ መና ማስቀረት ማለት ነው። ክርስቶስ የገዛን ልጆች እንጂ ባሪያዎች

ሊያደርገን አልነበረምና! አይሁዳዊያን በሕግ ሥር ያሉ ተራ ሕፃናት ሲሆኑ፥ አማኞች ግን በጸጋ በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ ጎልማሳዎች ናቸው።

እዚህ ነጥብ ላይ «የእግዚአብሔር ትናንሽ ልጆች(ሕፃናት)» በመሆንና «የእግዚአብሔር ጎልማሳ ልጆች» በመሆን መካከል ያለውን ንጽጽር በሠንጠረዥ ማየት የተሻለ ይሆናል።

ትንሽ ልጅ (ሕፃን)	ልጅ (ጎልማሳ)
በዳግም ልደት	በጉዲፈቻ (ከተወለደ በኋላ እንደ ልጅ የአንድ ቤተሰብ አባል መሆን)
ልጅነት ወደ ቤተሰቡ መግባት (መቀላቀል)	በቤተሰቡ መካከል በደስታ የሚኖር
በጠባቂ ሥር ያለ	የጎልማሳነት ነፃነት ያለው
ለመውረስ የማይችል	የአባቱ ወራሽ የሆነ

አሁን ልጆችም ወራሾችም ነን (4:6-7)። በዚህ አጋጣሚ ሦስቱ የሥላሴ አካላት በመንፈሳዊ ልምምዳችን ውስጥ ስላላቸው ድርሻ እናያለን። እግዚአብሔር አብ ልጁን ይሞትልን ዘንድ ላከልን። እግዚአብሔር ወልድ ደግሞ መንፈሱን በውስጣችን ይኖር ዘንድ ላከልን። በዚህ ስፍራ ለንጽጽር የቀረቡት አገልጋዮችና ልጆች እንጂ ሕፃናትና ጎልማሳ ልጆች አይደሉም። ምንም እንኳ ኮብላዩ ልጅ ከእርሱ የተወለደ ልጁ ቢሆንም አባቱን ከአገልጋዮቹ እንደ አንዱ አድርጎ እንዲቀበለው እንደ ጠየቀው ሁሉ የገላትያ ሰዎችም እግዚአብሔር እንደ ባርያ አድርጎ እንዲቆጥራቸው ፈለጉ (ሉቃስ 15:18-19)። ይህን ንጽጽር ቀለል ባለ መልኩ እንደሚከተለው ማየት ይቻላል። ለምሳሌ፦

ልጅ የአባቱ ዓይነት ባሕርይ ሲኖረው የአገልጋዩ ባሕርይ ግን የተለየ ይሆናል። እኛም በክርስቶስ በምናምንበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን ስለሚኖር «ከመለኮት ባሕርይ ተካፋዮች» ነን ማለት ነው (2 ጴጥ. 1:4)። ሕግ ግን ለአንድ ሰው የመለኮት ባሕርይ ሊሰጥ ፈጽሞ አይችልም። ሕግ ሊያደርግ የሚችለው ሰው መለኮታዊ ባሕርይ የጎደለውና ተስፋ ቢስ መሆኑን ማሳየት ብቻ ነው። ስለዚህ አማኝ ወደ ሕግ በሚመለስበት ጊዜ በውስጡ ያለውን መለኮታዊ ተፈጥሮ በመካድ አሮጌው ተፈጥሮ (ሥጋው) ሥራውን እንዲሠራ እድል እየሰጠ ነው ማለት ነው።

ልጅ አባት ሲኖረው አገልጋይ ግን የሚኖረው ጌታ ነው ያለው። ግንኛውም አገልጋይ አሳዳሪውን «አባዬ» ብሎ መጥራት አይችልም። አንድ ኃጢአተኛ በክርስቶስ በሚያምንበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ይቀበላል። የተቀበለው መንፈስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ ይነግረዋል (ሮሜ 8፡15-16)። አንድ ሕፃን ልጅ ማልቀሱ እንጂ ከአባቱ ጋር መነጋገሩ የተለመደ አይደለም። መንፈስ ወደ ልቡ በሚገባበት ጊዜ ይህ መንፈስ «አባ፥ አባት» ይላል(ገላ. 4፡6) በምላሹም አማኙ «አባ አባት» ብሎ ይጠራል (ሮሜ 8፡15)። አባ የሚለው የአራማይክ ቃል «አባቴ» የሚለውን የአማርኛ ትርጉም የሚሰጥ ነው። ይህ የሚያሳየው አንድ ልጅ ከአባቱ ጋር ያለውን ቅርበት ነው። የትኛውም አገልጋይ ከጌታው ጋር እንደዚህ አይነት ቅርበት አይኖረውም።

ልጅ የሚታዘዘው ከፍቅር የተነሣ ሲሆን አገልጋይ ግን ከፍርሃት የተነሣ ነው። አማኙ ለእግዚአብሔር ያለውን ፍቅር ለማነቃቃትና ለማሳደግ መንፈስ ቅዱስ በልቡ ውስጥ ይሠራል። «የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር...ነው» (ገላ. 5፡22) «በመንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን...ፈሰሰ» (ሮሜ 5፡5)። የይሁዲነት አቀንቃኞች የተሻለ ክርስቲያን የሚሆኑት ለሕግ ሲገዙ እንደ ሆነ ለገላትያ ሰዎች ነግረዋቸው ነበር፤ ሕግ ግን ለመታዘዝ የሚያስችለንን ኃይል ሊሰጠን ጨርሶ አይችልም። ይህን ማድረግ የሚችል ፍቅር ብቻ ነው። «ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ» (ዮሐ. 14፡15)።

ልጅ ባለጠጋ ሲሆን አገልጋይ ግን ድሃ ነው። «ልጆችም ወራሾችም ነን።» ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብ የተቀላቀልነው እንደ ጎልማሳ ልጅ ስለ ሆነ አሁኑኑ በርስታችን መጠቀም መጀመር እንችላለን። እግዚአብሔር የጸጋውን ባለጠግነት (ኤፌ. 1፡7፥ 2፡7)፥ የክብሩን ባለጠግነት፤ (ፊልጵ. 4፡19)፥ የመልካምነቱን ባለጠግነት (ሮሜ 2፡4)፥ የጥበቡን ባለጠግነት (ሮሜ 11፡33-36) አጎናጽፎናል። የእግዚአብሔር ባለጠግነቶች በሙሉ በክርስቶስ የሚገኙ ናቸው (ቆላ. 1፡19፤ 2፡3)።

ልጅ ለወደፊት የሚያስፈልገው ሁሉ አለው፤ አገልጋይ ግን የለውም። አንዳንድ መልካም ጌቶች ለባሮቻቸው በመጦሪያ ዕድሜያቸው የሚያስፈልጋቸውን ቢያደርጉላቸውም እንኳ ግዴታ ግን የለባቸውም። አባት ግን ለልጅ የሚያስፈልገውን ሁሉ ያዘጋጃል (2ኛ ቆሮ. 12፡14)።

በአንድ ጎኑ ካየነው ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብ እንደ ልጅ ሆነን የመግባታችን ጉዳይ ገና አልተጠናቀቀም፤ ምክንያቱም የክርስቶስን

መመለስና የሰውነታችንን መቤዠት ገና እየተጠባበቅን ስለ ሆነ ነው (ሮሜ 8፡23)። አንዳንድ ሊቃውንት ይህ ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብ የመቀላቀላችንን ሁለተኛ ደረጃ ሮማውያን ከቤተሰቡ ውጭ የሆነን ሰው የቤተሰቡ አካል አድርገው ለማቀላቀል ከሚያደርጉት ሥርዓት ጋር የሚመሳሰል እንደ ሆነ ይናገራሉ። በመጀመሪያ የሚቀበሉት በግል በሚደረግ ሥርዓት ሲሆን፥ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ በግልጽ በዳኞች ፊት ልጃቸውና የቤተሰባቸው አባል አድርገው እንደተቀበሉት ያውጃሉ።

ክርስቲያኖች በክርስቶስ የመዋጀትንና የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ የመሆንን የመጀመሪያውን እርምጃ ተለማምደናል። በክርስቶስ ዳግም ምጽአት የሚፈጸመውን የልጅነታችንን በግልጽ መታወጅና «እርሱን የምንመስልበትን» (1ኛ ዮሐ. 3፡1-3) ሁለተኛውን እርምጃ እየተጠባበቅን ነው። «ልጆችና ወራሾች» ነንና ከርስታችን የላቀው ክፍል ገና ሊመጣ ስለ ሆነ እንጠባበቃለን (1ኛ ጴጥ. 1፡1-5 ተመልከት)።

2. ወደ ኋላ ስለ መመለሳቸው ጳውሎስ ያቀረበው ቅሬታ (4፡8-11)

የገላትያ ሰዎች ከጸጋ ወደ ሕግ በመመለሳቸው ምን ሆኑ? በመጀመሪያ ነፃነትን በባርነት ለውጡ። ምንም የማያውቁ ኃጢአተኞች በነበሩበት ጊዜ ሐሰተኛ አማልክትን በማገልገል አሳዛኝ የሆነውን የአሕዛብ የባርነት ሕይወት ይለማመዱ ነበር። ከዚያ በኋላ ግን በክርስቶስ በማመን ከጥንቆላና ከአጋንንት ባርነት ነፃ ወጥተው ነበር። አሁን ደግሞ በክርስቶስ ያላቸውን ነፃነት ትተው ወደ ባርነት ተመለሱ። ከጸጋ ትምህርት ቤት በመውጣት በሕግ የሕፃናት መዋያ ተመዘገቡ። በጳውሎስ አገልግሎት እግዚአብሔር በውስጣቸው ያደረገውን መልካም ሥራ ሁሉ አጠፍ።

«ወደ ደካማ ወደሚናቅም» የሚለው ሐረግ ምን ያህል ወደ ኋላ እንደ ተመለሱ ያመለክታል። የወንጌልን ኃይል ለሕግ ደካማነት፥ የወንጌልን ብልጥግና ለሕግ ድህነት አሳልፈው እየሰጡ ነበር። ሕግ የሰውን ድካምና መንፈሳዊ ክስረት ይገልጻል እንጂ ማንንም ሰው ባለጸጋ ወይም ብርቱ አያደርግም። ጳውሎስ፥ ነፃነት ለባርነት፥ ኃይል ለድካም፥ ብልጥግና ለድህነት አልፎ እየተሰጠ መሆኑን ሲያይ ማዘኑ የሚገርም አይደለም።

የገላትያ ሰዎች ይህን ያደረጉት እንዴት ነበር? ይህን ያደረጉት የብሉይ ኪዳንን የሃይማኖት መመሪያ በመከተል «ቀንን፥ ወርንና ዘመንንም፥ ዓመትንም» (ቁ. 10) በጥንቃቄ ለይተው በማክበር ነበር።

ይህ ስለ ተባለ ግን ክርስቲያኖች በዓመት ውስጥ አንድ ቀን ለይተው የክርስቶስን ልደት ማክበራቸው ስህተት ነው ማለት ይሆን? ወይም መንፈስ ቅዱስ የወረደበትን ቀን፥ ወይም የበረከት መታሰቢያ የሆነውን የመከር ቀን ወዘተ... ማክበራቸው ኃጢአት ነውን?

እንደዚህ ማለት አይደለም። ይህን ጉዳይ የሚወስነው በዓሉን የምናከብርበት ውስጣዊ ስሜት ነው። የተለዩ የበዓል ቀናትን የምናከብረው እንደ ባሮች አንድ መንፈሳዊ ችሮታ እናገኛለን በሚል ተስፋ ከሆነ ኃጢአት ነው ማለት ነው። በምናከብረው በዓል በክርስቶስ ያለንን ነፃነት የምንገልጽና መንፈስ ቅዱስ በጸጋው እንዲጎበኘን ራሳችንን የምናዘጋጅ ከሆነ ግን በዓሉ መንፈሳዊ በረከት ሊሆነን ይችላል።

ክርስቲያኖች ሃይማኖታዊ ሥርዓትን ፈጻሚና አስፈጻሚ በመሆን ሕጎችን መደንገግ እንደሌለባቸው አዲስ ኪዳን ግልጽ ያደርገዋል (ሮሜ 14፡4-13)። የበዓል ቀናትን የሚያከብረውን ሰው ልናወድስ፥ የማያከብረውን ደግሞ ልናወግዝ ጨርሶ አይገባም። ነገር ግን አንድ ሰው ሃይማኖታዊ ሥርዓቶችን በመፈጸሙ ነፍሱ እንደምትድን ወይም ወዲያውኑ በጸጋ እንደሚያድግ ካሰበ በሕግ ተገዢነቱ በደለኛ ይሆናል።

በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት መካከል የተለያዩ ሥርዓቶች አሉ። ስለዚህ ከእግዚአብሔር ቃል ባሻገር በመሄድ ማወዳደር፥ መተቸትና መኮነን ተገቢ አይደለም። ሁላችንም ልንገነዘበው የሚገባን ሥጋን ደስ የሚያሰኝ የሕጋዊነት መንፈስ ወደ ኩራት እንደሚመራና ውጫዊው ገጽታም ለውስጣዊ ልምምዳችን ምትክ ሊሆን እንደሚችል ነው።

3. የእነርሱን ፍቅር አጥብቆ ይፈልጋል (4፡12-18)

ጳውሎስ መልካም መንፈሳዊ አባት ነበር፤ ግሣጼንና ፍቅርን ሚዛናዊ ማድረግ ይችልበታል። አማኞች ለእርሱ ያላቸውን ፍቅርና እርሱ ለአማኞች ያለውን ፍቅር በማስታወስ ከግሣጼ በመመለስ ፍቅርን ያሳያቸዋል። የገላትያ ሰዎች በአንድ ወቅት ለጳውሎስ ማንኛውንም ነገር ለመሠዋት ዝግጁ እስኪሆኑ ድረስ ፍቅራቸው ታላቅ ነበር። አሁን ግን እንደ ጠላታቸው ነው

የሚያዩት። የይሁዲነት አቀንቃኞች በመሀላቸው ገብተው ቀድሞ የነበራቸውን ፍቅር ሰልበውታል።

ጳውሎስ እንዲህ ተማሮ የሚናገረው ስለ የትኛው ድርጊታቸው እንደሆነ ግልጽ ባለመሆኑ ይበልጥ ቢያብራራው መልካም እንደ ነበር የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች ምኞታቸውን ይገልጻሉ። ጳውሎስ የገላትያን ሰዎች መጀመሪያ በጎበኘበት ጊዜ ሕመም ላይ ነበር። በምዕራፍ 1 ላይ እንደ ተመለከተው ጳውሎስ ይህን ደብዳቤ የጻፈው ለደቡብ ገላትያ ሰዎች ከሆነ፥ እንግዲያውስ በየሐዋ. 13-14 ስለተዘገበው ስለመጀመሪያው ሐዋርያዊ ጉዞው እየተናገረ ነው ማለት ነው። ጳውሎስ እነዚህን ከተሞች የመሠረተበት እቅድ አልነበረውም፤ ወደ እነዚህ ከተሞች እንዲሄድ ያደረገው በሰውነቱ ላይ ያደረው የሕመም ስሜት ነበር። ይህ ሕመም ምን እንደ ነበር በመላ ከመናገር በስተቀር ሌላ ምርጫ የለንም። እንዳንዶች ወባ ነበር ይላሉ። ሌሎች ደግሞ የዓይን ሕመም ነበር ይላሉ (ገላ. 4፡15 ተመልከት)። በሽታው ምንም ዓይነት ይሁን፥ የጳውሎስን የፊት ገጽታ አስከፊ አድርጎት ነበር። ዳሩ ግን የገላትያ ሰዎች መልኩን ሳይመለከቱ ስለ ተቀበሉት አመስግኖአቸው ነበር። እንደ እግዚአብሔር መልአክ አድርገው ነበር የተቀበሉት። ሰዎች የእግዚአብሔርን አገልጋዮች በውጫዊ አቀራረባቸው ሳይሆን ጌታን በመወከል የእርሱን መልእክት የሚያመጡ ናቸው ብለው ሲቀበሏቸው በጣም ደስ ያሰኛል።

ጳውሎስ የገላትያን ሰዎች ከዚህ ቀደም ለእርሱ የነበራቸው ፍቅር አሁን የት እንደ ገባ ይጠይቃቸዋል። በተጨማሪ «ወንጌልን ሰምታችሁ ክርስቶስን በተቀበላችሁ ጊዜ የተለማመዳችሁት ደስታና በረከት የት ደረሰ?» ይላቸዋል። በእርግጥ ጳውሎስ ምን ችግር እንደ ገጠማቸው ያውቅ ነበር። የይሁዲነት አቀንቃኞች መጥተው ልባቸውን ሰርቀዋቸው ነበር።

የሐሰተኛ አስተማሪዎች አንዱ ምልክት ሌሎች ሰዎች ወደ እምነት ያመጧቸውን ሰዎች ወደ ኢየሱስ ክርስቶስና እርሱን ወደ መምሰል ይበልጡን በማቅረብ ምትክ ወደ ራሳቸው እንዲመጡ ማድረጋቸው ነው። በመጀመሪያ ወደ ገላትያ የመጣውና ሰዎችን ወደ ክርስቶስ የመራው ጳውሎስ እንጂ የይሁዲነት አቀንቃኞች አልነበሩም። በአሁኑ ዘመን አንዳሉት መናፍቃን ሁሉ እነዚህም ሐሰተኛ አስተማሪዎች የጠፉ ኃጢአተኞችን ለክርስቶስ ከመማረክ ይልቅ በእውነት ጌታን የሚያገለግሉ ሰዎች ያፈሩአቸውን ፍሬዎች ይሰርቁ ነበር። ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች አፍቃሪና ወዳጃቸው እንደ ነበር

አረጋግጧል። ራሱን ከእነርሱ እንደ አንዱ በመቁጠር «...እኔ ደግሞ እንደ እናንተ ሆኜአለሁና» ይላል (ቁ. 12)። እነርሱ ግን ከጳውሎስ ተለይተው ሐሰተኛ እረኞችን ተከተሉ።

ጳውሎስ እውነቱን ሲነግራቸው የይሁዲነት አቀንቃኞች ግን ሐሰትን ነግረዋቸው ነበር። የጳውሎስ ፍላጎት ክርስቶስን ማክበር ነበር፤ የይሁዲነት አቀንቃኞች ግን ራሳቸውንና ወደ እምነት ያመጧቸውን ሰዎች ያከብሩ ነበር። «በብርቱ ይፈልጉአችኋል፤ ለመልካም አይደለም ነገር ግን በብርቱ ትፈልጉአቸው ዘንድ በውጭ ሊያስቀሩአችሁ ይወዳሉ» (ቁ. 17)።

እውነተኛ የእግዚአብሔር አገልጋይ ራሱን ከፍ ለማድረግ ወይም ሥራውን ለማሳደግ ሲል «ሰዎችን መጠቀሚያ» አያደርግም። ሰዎች ክርስቶስን በተሻለ ሁኔታ እንዲያውቁና እንዲያከብሩ በፍቅር ያገልግላቸዋል። እርሱ ብቻ ትክክል እንደ ሆነ ከሚያስብና ለእርሱ ብቻ ታማኝ እንድንሆንለት ከሚፈልግ አገልጋይ መጠንቀቅ ይኖርብናል። እንደዚህ ዓይነቱ ሰው እስከቻለ ድረስ ይጠቀምብንና ለሌላ ሰው ያስተላልፈናል። አወዳደቃችንም እጅግ የከፋና ጎጂ ይሆናል። የእውነተኛ መንፈሳዊ መሪ ተግባር ሰዎች ክርስቶስን እንዲያውቁና እንዲከተሉ ማድረግ እንጂ እርሱንና አገልግሎቱን ከፍ እንዲያደርጉ መሆን የለበትም።

«የወዳጅ ግቁሰል የታመነ ነው፤ የጠላት መሳም ግን የበዛ ነው» (ምሳሌ 27:6)። ጳውሎስ እውነቱን በመናገር ለገላትያ ሰዎች ያለውን ፍቅር አረጋግጦ ነበር፤ እነርሱ ግን አልተቀበሉትም። ይህ ወደ ባርነትና ወደ ሐዘን እንደሚመራቸው ባለማወቃቸው በይሁዲነት አቀንቃኞች «መሳም» ደስ እየተሰኙ ነበር። ክርስቶስ ልጆችና ወራሾች አድርጓቸው ሳለ እነርሱ ግን ፈጥነው ባሪያዎችና ለማኞች ሆነው ነበር።

የደህንነት ልምምዳቸውን ያላጡ ክርስቲያኖች ቢሆኑም እንኳ፥ የደህንነታቸውን ሐሴት ግን በማጣታቸው በምትኩ በሥራቸው ረክተው ነበር። የሚያሳዝነው ያጡትንና የጎደላቸውን ነገር አለማወቃቸው ነው። ለጸጋ ሕግን፥ ለመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ሃይማኖታዊ ተግባራትን በመተካት፥ የተሻሉ ክርስቲያኖች እንደ ሆኑ እያሰቡ ነበር።

የክርስትና ሕይወትህ እንቅስቃሴ ፊት ለፊት ወደ ነጻነት የሚገሰግስ ነው? ወይስ በባርነት ቀንበር ለመውደቅ ወደ ኋላ የሚንሸራተት ነው? ለዚህ ጥያቄ መልስ ከመስጠትህ በፊት በጥንቃቄ አስብ።

ገላትያ 4፡19-31

ልጆቼ ሆይ፥ ክርስቶስ በእናንተ እስኪሣል ድረስ ዳግመኛ ስለ እናንተ ምጥ ይዘኛል። ስለ እናንተ አመነታለሁና፤ አሁን በእናንተ ዘንድ ሆኜ ድምፄን ልለውጥ በወደድሁ።

እናንተ ከሕግ በታች ልትኖሩ የምትወዱ፥ ሕጉን አትሰሙምን? እስኪ ንገሩኝ። አንዱ ከባሪያይቱ አንዱም ከጨዋይቱ የሆኑ ሁለት ልጆች ለአብርሃም እንደ ነበሩት ተጽፎአልና። ነገር ግን የባሪያይቱ ልጅ እንደ ሥጋ ተወልዶአል፤ የጨዋይቱ ግን በተስፋው ቃል ተወልዶአል። ይህም ነገር ምሳሌ ነው፤ እነዚህ ሴቶች እንደ ሁለት ኪዳኖች ናቸውና። ከደብረ ሲና የሆነችው አንዲቱ ለባርነት ልጆችን ትወልዳለች፤ እርስዋም አጋር ናት። ይህችም አጋር በዓረብ ምድር ያለችው ደብረ ሲና ናት፤ አሁንም ያለችውን ኢየሩሳሌምን ትመስላለች፤ ከልጆችዋ ጋር በባርነት ናትና። ላይኛይቱ ኢየሩሳሌም ግን በነጻነት የምትኖር ናት፤ እርስዋም እናታችን ናት። አንቺ የማትወልጂ መካን፥ ደስ ይበልሽ፤ አንቺ አምጠሽ የማታውቂ፥ እልል በዪና ጩኺ፤ ባል ካላቱ ይልቅ የብቸኛይቱ ልጆች በዝተዋልና ተብሎ ተጽፎአል። እኛም ወንድሞች ሆይ፥ እንደ ይስሐቅ የተስፋ ቃል ልጆች ነን። ነገር ግን እንደ ሥጋ የተወለደው እንደ መንፈስ የተወለደውን በዚያን ጊዜ እንዳሳደደው ዛሬም እንዲሁ ነው። ነገር ግን መጽሐፍ ምን ይላል? የባሪያይቱ ልጅ ከጨዋይቱ ልጅ ጋር አይወርስምና ባሪያይቱን ከልጅዋ ጋር አውጣት። ስለዚህ ወንድሞች ሆይ፥ የጨዋይቱ ልጆች ነን እንጂ የባሪያይቱ አይደለንም።

- 8 -

ወላጅ እናትህን አግኝ

እኛ ወላጆች በዕድገት ደረጃችን ከገዛ ልጆቻችን ልቀን አንገኝም። እናቴ ሕፃናትን በተመለከተ እንደሚከተለው ትናገር እንደ ነበር አስታውሳለሁ፡- «ትናንሾች እያሉ ለቁጥጥር አስቸጋሪ ናቸው፤ በሚያድጉበት ጊዜ ግን ለቁጥጥር የማይቻሉ አሳዛኞች ይሆናሉ።»

ጳውሎስ በተምታታ መንፈሳዊ ሕይወት ውስጥ የነበሩትን የገላትያ አማኞችን ለመርዳት በሞከረ ጊዜ የተለማመደው ይህንን የመሰለ ስሜት ነበር። በመጀመሪያ ወንጌልን ይዞ ወደ እነርሱ በመጣ ጊዜ ወደ ጌታ ሲመለሱ ለማየት በመንፈሳዊ ምጥ ላይ ነበር። በእርግጥ ደህንነታቸውን ለማስገኘት ጌታ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ካሳለፈው ምጥ ጋር ሲወዳደር (ኢሳ.53፡11) የጳውሎስ ምጥ ምንም አልነበረም። አሁን ደግሞ የገላትያ ክርስቲያኖች ወደ ሕጋዊነትና «ወደ ዳግመኛ የጨቅላነት ልምምድ» በመውደቃቸው እንደገና ግግጥ ነበረበት። እኛ ወላጆች ልጆቻችን በእግዚአብሔር ፈቃድ የበሰሉ ሆነው ለማየት እንደምንጓጓ ሁሉ፥ ጳውሎስም በእነርሱ ውስጥ ክርስቶስ በሚገባ ተመሥርቶ ለማየት እጅግ ጓጉቶ ነበር።

የይሁዲነት አቀንቃኞች ለሕግ ጥብቅና ቆመው ስለ ነበር ጳውሎስ ይህንኑ ተቃውሟቸውን ለመቋቋምና ክርስቲያኖች በሕግ ሥር እንዳልሆኑ ለማሳየት ሕጉን ራሱን እንደማስረጃ ያቀርበዋል። እጅግ ታዋቂ ከሆነው ከእስማኤልና ከይስሐቅ ታሪክ በመነሣት (ዘፍ. 16፡21)፥ ክርስቲያን ከሙሴ ሕግ ጋር ስላለው ግንኙነት የሚያስረዱ መሠረታዊ እውነቶችን ከውስጡ ያቀርባል።

በዚህ ስፍራ የተገለጹት እውነቶች ገና ድሮ የተፈጸሙ ቢሆንም ጳውሎስ ግን ከበስተጀርባው ጥልቅ ትርጉም እንዳለው በማሰብ ትረካውን በተምሣሌታዊ መልክ አቀረበው። በእንግሊዝኛ ቋንቋ ከሁሉ የላቀ ታዋቂና ተምሣሌታዊ ታሪክ በጆን ቡንያን የተጻፈው «የመናኝ ጉዞ» የሚለው መጽሐፍ ነው። በዚህ መጽሐፍ ጆን ቡንያን፥ ክርስቲያን ከጥፋት ከተማ አምልጦ ወደ መንግሥተ ሰማያት የሚያደርገውን የጉዞ ልምምድ ይተርካል። መጽሐፉ በቅድሚያ በቀጥተኛ ትርጉም ቀጥሎም በታሪኩ ውስጥ ያሉት

ሰዎችና ተግባራት ስውር ትርጉሞችን በሚያስተላልፍበት ተምሣሌታዊ መልኩ ቀርቦአል።

ጳውሎስ በዚህ ክፍል ውስጥ ዘፍጥረትን በመጥቀስ መጠቀሙ በብሉይ ኪዳን የተፈጸሙ ድርጊቶች ሁሉ «ስውር ትርጉሞች» እንዳሏቸው አድርገን ለመቁጠር ምክንያት ሊሆነን አይችልም። በእንዲህ ዓይነቱ አቀራረብ ከተጠቀምን መጽሐፍ ቅዱስን ደስ ባለንና በወደድነው መልክ ማቅረብ ይቻላል። ብዙም የሐሰተኛ ትምህርቶች ከሚነሡበት መንገድ አንዱ ይህ ነው። ጳውሎስን ግን የዘፍጥረትን መጽሐፍ ታሪክ ስውር ትርጉም እንዲያስተውል መንፈስ ቅዱስ አስቻለው። ስለዚህ ብሉይ ኪዳንን ሁልጊዜ የምንተረጉመው በአዲስ ኪዳን ብርሃን አማካኝነት መሆን አለበት። አዲስ ኪዳን በሚፈቅድልን ስፍራ ደግሞ «የተሰወሩ ትርጉሞችን» መፈለግ እንችላለን። ይህ ካልሆነ ግን ለሁሉም ነገሮች መንፈሳዊ ትርጉም ከመስጠት ተቆጥበን የቅዱሳት መጽሐፍትን አባባሎች በቀጥተኛነታቸው መቀበል አለብን።

1. ታሪካዊ እውነታዎች (4፡19-23)

ታሪካዊ ክስተትን ለመረዳት ቀላሉ መንገድ የአብርሃምን ታሪክ ከዘፍ. 12-21 በተመዘገበው መንገድ መመልከት ነው። የአብርሃምን ዕድሜ የጥናታችን መነሻ በማድረግ ጳውሎስ ስለ ክርስቲያናዊ ነፃነት ለማስረዳት ያነሣቸውን ነጥቦች አለፍ አለፍ ብለን ለማየት እንሞክራለን።

በ75 ዓመቱ፡- አብርሃም ዘሩ እንደ ምድር አሸዋና ከዋክብት እንደሚበዛ ተስፋ ተሰጠውና ወደ ከነዓን እንዲሄድ በእግዚአብሔር ተጠራ (ዘፍ. 12፡1-9)። አብርሃምና ሚስቱ ሣራ ልጆች ቢፈልጉም እንኳ ሣራ መካን ነበረች። እግዚአብሔር ልጅን በመስጠት ተአምሩን ከማሳየቱ በፊት የአብርሃም ፍትወተ ሥጋና የሣራ ማኅፀን ምውት እስኪሆን ድረስ ጠበቀ (ሮሜ 4፡16-25)።

በ85 ዓመቱ፡- ሣራ የምትጠብቀው የተስፋ ልጅ በመዘግየቱ ትዕግሥቷ አለቀ። ስለዚህ አብርሃም አገልጋይዋ የሆነችውን አጋርን እንዲያገባና ከእርሷ ልጅን እንዲወልድ አሳብ አቀረበች። ይህ ተግባር በማኅበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያለው ቢሆንም የእግዚአብሔር ፈቃድ ግን አልነበረም። አብርሃም የሣራን አሳብ ተቀብሎ አጋርን አገባ (ዘፍ. 16፡1-3)።

በ86 ዓመቱ፡- አጋር ጸነሰች፤ ሣራ ደግሞ በዚህ ምክንያት ቅንዓት አደረባት። በሣራ ቤት ሁኔታዎች አስቸጋሪ እየሆኑ ስለ መጡ አጋር ተባረረች። እግዚአብሔር ግን በጉዳዩ ጣልቃ ገባና ወደ ቤቷ እንድትመለስ በማድረግ ለእርሷና ለልጇ እንክብካቤ እንደሚያደርግላት ተስፋ ሰጣት። አብርሃም የ86 ዓመት ሰው ሲሆን አጋር ወንድ ልጅ ወለደችለት፤ ስሙንም እስማኤል ብሎ ጠራው (ዘፍ. 16፡4-16)።

በ99 ዓመቱ፡- እግዚአብሔር አብርሃምን ከሣራ ልጅን እንደሚሰጠውና ስሙንም ይስሐቅ ብሎ እንደሚጠራው ነገረው። ቆይቶም ለሣራ ተገለጠላትና የተስፋ ቃሉን አጸናላት (ዘፍ. 17-18 ተመልከት)።

በ100 ዓመቱ፡- የተስፋው ልጅ ተወለደለት (ዘፍ. 21፡1-7)። በእግዚአብሔር እንደ ታዘዙት ይስሐቅ («ሳቅ») ብለው ሰየሙት። የይስሐቅ መወለድ በቤተሰቡ ውስጥ አዲስ ችግር ፈጠረ። እስማኤል ተቀናቃኝ አገኘ። እስማኤል የአብርሃም ብቸኛና ተወዳጅ ልጅ ሆኖ ለ14 ዓመታት ቆይቶ ነበር። ለዚህ ተቀናቃኝ የእስማኤል ምላሽ ምን ሊሆን ይችላል?

በ103 ዓመቱ፡- አይሁዳውያን የወለዱት ልጅ ሦስት ዓመት ሲሞላው ጡት እንዲተው የማድረግና ይህንንም አስመልክተው ከፍተኛ ግብዣ የማድረግ ልማድ አላቸው። በግብዣው ላይ እስማኤል በይስሐቅ ማፌዝና (ዘፍ. 21፡8-34) በቤትም ውስጥ ችግር መፍጠር ጀመረ። ለተፈጠረው ችግር የተገኘው መፍትሔ አንድ ብቻ ነበር። ይህም መፍትሔ ከፍተኛ ዋጋ የሚጠይቅ ነበር። ይህም አጋርና ልጇን ከቤት ማባረር ነበር። አብርሃም እጅግ እያዘነ ልጁን ከቤቱ አባረረ፤ ይህንንም እንዲያደርግ ያዘዘው ራሱ እግዚአብሔር ነበር (ዘፍ. 21፡9-14)።

ይህን ታሪክ እንዲሁ ላይ ላዩን ለተመለከተው ስለቤተሰብ ችግር የሚናገር ታሪክ ከመሆን የሚያልፍ አይመስልም። ጠልቀን ወደ ሥር ስንገባ ግን አስደናቂ መንፈሳዊ ኃይል ያለው ትርጉም አዝሎ እናገኛለን። አብርሃም፥ ሁለቱ ሚስቶቹና ሁለቱ ልጆቹ መንፈሳዊ እውነታን የሚወክሉ ናቸው፤ በመካከላቸው ያለው ግንኙነት እጅግ ጠቃሚ ነገሮችን ያስተምረናል።

2. መንፈሳዊ እውነታዎቹ (4፡24-29)

ጳውሎስ ከታሪኩ ባሻገር ያሉትን ትርጉሞች መግለጽ ይጀምራል። ምናልባት ከሁሉ በተሻለ መንገድ በሚከተለው ሁኔታ ከፋፍሎ ማስቀመጥ ይቻላል።

ብሉይ ኪዳን	አዲስ ኪዳን
ሕግ	ጸጋ
ባሪያይቱ አጋር	ሜዋዊቱ ሣራ
በሥጋ ፈቃዱ የተፀነሰው	በተአምር የተፀነሰው ይስሐቅ
እስማኤል በባርነት	ነፃይቱ ሰማያዊቷ ኢየሩሳሌም
ያለችው ምድራዊቷ	
ኢየሩሳሌም	

ጳውሎስ እስማኤልና ይስሐቅ ይባሉ ከነበሩት ሁለት ልጆች ይጀምርና (4፡22-23) እነዚህ ሁለት ልጆች የሁለቱ ልደቶቻችን ምሳሌ እንደ ሆኑ ይገልጻል። እነዚህ ሁለት ልደቶች ኃጢአተኛ ያደረገን የሥጋ ልደትና የእግዚአብሔር ልጆች ያደረገን መንፈሳዊ ልደት ናቸው። ይህንን ነገር እያሰብህ ዘፍ. 12፡1-2 ብታነብ ስለ ደህንነትህ አንዳንድ አስደናቂ መንፈሳዊ እውነቶችን ትረዳለህ።

ይስሐቅ በበርካታ ልዩ ሁኔታዎች የሚያልፉ አማኞችን ይገልጻል።

የተወለደው በእግዚአብሔር ኃይል ነበር። እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለሣራ ልጅ ከመስጠቱ በፊት ለ25 ዓመታት የቆየው አውቆ ነበር። ይስሐቅ የተወለደው «እንደመንፈስ ፈቃድ ገላ. 4፡29 እንደ ነበር ሁሉ ክርስቲያኖችም «ከመንፈስ የተወለዱ» ናቸው (ዮሐ. 3፡17)። ይስሐቅ ወደዚህ ምድር የመጣው እምነትን በሚወክለው በአብርሃምና ጸጋን በምትወክለው በሣራ በኩል ነበር። ስለዚህም ይስሐቅ እያንዳንዱ እውነተኛ ክርስቲያን እንደሚወለደው በ«ጸጋው በእምነት...» ተወለደ (ኤፌ. 2፡8-9)።

ሕፃኑ በልደቱ ለቤተሰቡ ደስታን አጎናፅፎአል፡- የስሙ ትርጉም «ሳቅ» የሚል ሲሆን በእድሜ ለገፉት ወላጆቹ በእርግጥ ታላቅ ደስታን እንዳመጣ የታወቀ ነው። ደህንነት፥ ለአማኙ ብቻ ሳይሆን በዙሪያው ላሉት ሁሉ ደስታን የሚያስገኝ ልምምድ ነው።

አደገኛ ጡትን ከመጥባት ተቋረጠ (ዘፍ. 21፡8)። ደህንነት ጅማሬ እንጂ ፍጻሜ አይደለም። ከተወለድን በኋላ ማደግ አለብን (1ኛ ጴጥ. 2፡2፤ 2ኛ ጴጥ. 3፡18)። ካደግን በኋላ ደግሞ ጡት ከመጥባት መቋረጥ ይከተላል።

«የልጅነትን ጠባይ» መሻር አለብን (1ኛ ቆሮ. 13፡11)። ዳሩ ግን ለእኛም ቢሆን የጨቅላ ክርስትና ወቅት «መጫወቻዎችን» መያዝ ቀላል ሲሆን፥ የበሰለ ክርስቲያን «መሣሪያዎችን» መያዝ ግን ይከብደናል። እንደዚሁ ሁሉ ልጅን ጡት ማስጣል ልጅን ደስተኛ የሚያደርግ አይደለም። ሆኖም ይህ ካልሆነ ደግሞ ሙሉ ሰው መሆን ፍጹም አይቻልም (እንዚህ ነጥብ ላይ መዝ. (131) አንብብ)።

ሕፃኑ ችግር ደርሶበት ነበር (ዘፍ. 21፡9)። አሮጌው ተፈጥሮአችን በእኛ ላይ ችግር እንደሚፈጥር ሁሉ እስማኤል (ሥጋ) በይስሐቅ ላይ ችግር ፈጥሮበት ነበር። (ጳውሎስ በገላ. 5፡16-26 ላይ ይህንን ጉዳይ በጥልቀት ያቀርበዋል።) አሮጌው ተፈጥሮአችን ራሳችንን ለክርስቶስ በመስጠት አዲስ ተፈጥሮን እስክንለብስ ድረስ አንዳችም ችግር እንደማይፈጥርብን ሁሉ፥ እስማኤል እስከ ይስሐቅ መወለድ ድረስ አንዳችም ችግር አልፈጠረም ነበር። በአብርሃም ቤት የተፈጠረው ውዝግብ ዛሬ ክርስቲያኖችን ከሚያጋጥመን መሠረታዊ ውዝግብ ጋር ተመሳሳይ ነው። በአጋርና በሣራ መካከል የነበረው ግጭት በሕግና በጸጋ መካከል ካለው ግጭት ጋር ተመሳሳይ ነው።

በእስማኤልና በይስሐቅ መካከል የነበረው ግጭት በሥጋና በመንፈስ መካከል ከሚደረገው ግጭት ጋር ይመሳሰላል። እነዚህን አራት ነጥቦች ልንለያያቸው እንደማንችል መገንዘብ በጣም አስፈላጊ ነው። የይሁዲነት አቀንቃኞች ሕግ አንድን አማኝ የበለጠ መንፈሳዊ ያደርገዋል ሲል ጳውሎስ ግን ሕግ በአማኝ ውስጥ የሥጋን ተቃውሞና የግጭት መንሥኤ የሚያመጣ ብቻ መሆኑን ግልጽ አደረገ (ሮሜ 7፡19 ተመልከት)። እስማኤልን ለመለወጥ ወይም ለመቆጣጠር ብቃት ያለው ሕግ አልነበረም። ለይስሐቅ ግን አንዳችም ሕግ አላስፈለገውም። «አሮጌ ተፈጥሮ ሕግን አያውቅም፤ አዲሱ ተፈጥሮ ደግሞ ሕግ አያስፈልገውም» የሚል ትክክለኛ አባባል አለ።

ጳውሎስ የሁለቱን ልጆች ጉዳይ ጠቃሚነት ከገለጸ በኋላ የአብርሃም ሁለቱን ሚስቶች ግለት የሣራና የአጋርን ሁኔታ መግለጽ ይቀጥላል። በሕግና በጸጋ መካከል ያለውን ተነጻጻሪነት በመግለጽ አማኝ በእግዚአብሔር ጸጋ በሚገኝ ፍቅር የተሞላ ነፃነት ያለው እንጂ በሕግ ሥር እንዳልሆነ ያረጋግጣል። ሕግ በክርስቲያን ላይ ኃይል እንደሌለው የሚያረጋግጡልንን እውነታዎች ከአጋር ሁኔታ ለመረዳት እንችላለን።

አጋር የአብርሃም ሁለተኛ ሚስት ነበረች። እግዚአብሔር ከሣራ እንጂ ከአጋር አልጀመረም።

እግዚአብሔር ከሰዎች ጋር ያለውን ግንኙነት ጉዳይ በተመለከተ የጀመረው በጸጋ ነው። እግዚአብሔር ለአዳምና ለሔዋን የሚያስፈልጋቸውን ነገር ሁሉ በዔደን የሰጠው በጸጋው ነበር። ኃጢአትን ካደረጉ በኋላ እንኳ ለጎፍረታቸው መሸፈኛ የሚሆናቸውን ቆዳ በጸጋው ሰጣቸው (ዘፍ. 3፡21)። የመዋጂያ መንገድ ይሆናቸው ዘንድ ሕግን አልሰጣቸውም። በዚህ ምትክ ያምኑበት ዘንድ በጸጋው የተመሠረተ ተስፋን ሰጣቸው፤ ይህም ድል ነሺና አዳኝ እንደሚልክላቸው ነው (ዘፍ. 3፡15)።

እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር ያለውን ግንኙነት በተመለከተ በመጀመሪያ የሠራው በጸጋ መሠረት እንጂ በሕግ አልነበረም። ከአብርሃም ጋር የገባው ቃል ኪዳን (ዘፍ. 15) ሙሉ በሙሉ በጸጋ ላይ የተመሠረተ ነበር፤ ምክንያቱም ቃል ኪዳኑ በሚመሠረትበት ጊዜ አብርሃም በፍጹም እንቅልፍ ውስጥ ነበር። እግዚአብሔር እስራኤልን ከግብፅ ባርነት ነፃ ያደረገው በጸጋ እንጂ በሕግ አልነበረም፤ ምክንያቱም ሕግ ገና አልተሰጠም ነበረና። ልክ የአብርሃም ሁለተኛ ሚስት እንደ ሆነችው አጋር ሁሉ ሕግ በነበረው ላይ «ተጨመረ» (ገላ. 3፡19)። አጋር አንድን ተግባር ለጥቂት ጊዜ ብቻ ፈጽማ ከመድረኩ እንደ ተሰወረች ሕግም ለተወሰነ ዓላማ አገልግሎት አበቃ (3፡24-25)።

አጋር ባሪያ ነበረች። በዚህ ክፍል ውስጥ አምስት ጊዜ ያህል አጋር «ባሪያ» ወይም «ባሪያይቱ» እየተባለች ተጠርታለች (ቁ. 22-23፥ 30-31)። ሣራ ጨዋ ሴት ስለ ነበረች ስፍራዋ የነፃነት ስፍራ ነበር፤ አጋር ግን አብርሃምን ብታገባ እንኳ ባሪያ ነበረች። በተመሳሳይ መንገድ ሕግ የተሰጠው እንደ አገልጋይ ነበር። እንግዲህ ሕግ ምንድር ነው? ተስፋው የተሰጠው ዘር እስኪመጣ ድረስ(3፡19) የሰዎችን ኃጢአት ለመግለጥ እንደ መስታወት ያገለግላል (ሮሜ 3፡20)። እኛን ወደ ክርስቶስ ለመምራት ያገለግላል (ገላ. 3፡23-25)። ሕግ ሞግዚት እንጂ እናት የሆነበት ጊዜ ግን ጨርሶ የለም።

አጋር የተስፋውን ልጅ እንድትወልድ አልተጠበቀባትም። አብርሃም ከአጋር ጋር የፈጸመው ጋብቻ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ ነበር። የአብርሃምና የሣራ ያለማመን ደካማነትና ትዕግሥት የማጣት ውጤት ነበር። አጋር ለማድረግ የሞከረችው ሣራ ልታደርግ የምትችለውን ነገር ብቻ ነበር፤ ነገር ግን አልተሳካላትም። ሕግ ሕይወትን (ገላ. 3፡21) ወይም ጽድቅን (2፡21) ወይም የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን (3፡2) ወይም መንፈሳዊ ርስትን

(3:18) ሊሰጥ አይችልም። የአብርሃም ወራሽ እንዲሆን የተወለደው ይስሐቅ ነበር (ዘፍ. 21:10)። እስማኤል ግን ይህን ርስት ሊካፈል አይችልም ነበር። ጳውሎስ ወደ ክርስቶስ ያመጣቸው አማኞች የበለጠ ክርስቶስን እንዲመስሉ በመንፈሳዊ ምጥ ውስጥ በነበረበት ጊዜ፥ የይሁዲነት አቀንቃኞች ግን አጋርን እንደገና እናት ለማድረግ እየሞከሩ ነበር። ምንም ዓይነት ሃይማኖት ወይም ሕጋዊነት ለሞተ ኃጢአተኛ ሕይወትን መስጠት አይችልም። ይህን ማድረግ የሚችለው በወንጌል አማካኝነት ክርስቶስ ብቻ ነው።

አጋር የወለደችው ሰው ባሪያ ነበር። እስማኤል «የሜዳ አህያን የሚመስል» ሰው ነበር (ዘፍ. 16:12)። ባሪያ ቢሆንም እንኳ እናቱን ጨምሮ ግንም ሊቆጣጠረው የሚችል ሰው አልነበረም። እንደ እስማኤል አሮጌው ተፈጥሮአችንም (ሥጋችን) ከእግዚአብሔር ጋር በጦርነት ላይ ነው። ሕግ ሊለውጠውም ሆነ ሊቆጣጠረው አይችልም። መንፈስና ሥጋ «እርስ በእርሳቸው ይቀዋወማሉ» (ገላ. 5:17)። ምንም ዓይነት ሃይማኖታዊ ተግባራት ይህን ሁኔታ ሊለውጡት አይችሉም። አጋርን (ሕግን) እናቱ እንድትሆን የሚመርጥ ሁሉ በባርነት ይወድቃል። (4:8-11፥ 22-25፤ 30-31፤ 5:1) ሣራን (ጸጋን) እናቱ እንድትሆን የሚመርጥ ሁሉ በክርስቶስ ባለው ነጻነት ሐሴት ያደርጋል። ልጆቹ ነጻ እንዲሆኑ እግዚአብሔር ይፈልጋል (5:1)።

አጋር ተባረረች። አጋር እንድትባረር ትእዛዙን የሰጠችው ሣራ ነበረች፡- «ይህችን ባሪያ ከነልጅዋ አሳድድ» (ዘፍ. 21:9-10)። እግዚአብሔርም ለዚህ ውሳኔ ድጋፍ ሰጥቶ ነበር። (ዘፍ. 21:12)። እስማኤል ለ17 ዓመታት በዚያ ቤት ቢቆይም በመጨረሻ መባረሩ ግድ ነበር። ቆይታው ዘላቂ አልነበረም። በዚያ ቤት ውስጥ አጋርና እስማኤል ከሣራና ከይስሐቅ ጋር ሊቆዩ አይችሉም ነበር። አንደኛው ጥንድ ቤቱን መልቀቅ ነበረበት።

ሕግና ጸጋ፥ ሥጋና መንፈስ ተቻችለው በአንድነት ሊቆዩ ጨርሶ የማይቻል ነገር ነው። አጋርና እስማኤል አንዳንድ ጊዜ እየመጡ ይህን ቤተሰብ እንዲጎበኙ እግዚአብሔር አልጠየቃቸውም። መለያየታቸው ለሁልጊዜ ነበር። በጳውሎስ ዘመንም ሆነ በዚህ ዘመን ያሉ የይሁዲነት አቀንቃኞች ግን ሣራና አጋርን፥ ይስሐቅና እስማኤልን ለማስታረቅ ይሞክራሉ። እንዲህ ዓይነቱ እርቅ ከእግዚአብሔር ቃል ተጻራሪ ነው። ሕግና

ጸጋን፥ እምነትና የሕግ ሥራዎችን፥ የእግዚአብሔርን የጽድቅ ስጦታና ሰው ጽድቅን ለማግኘት የሚያደርገውን ሙከራ መቀላቀል የማይቻል ነው።

አጋር ዳግመኛ አላገባችም። እግዚአብሔር ለየትኛውም ሕዝብ ቢሆን ሕግን እንደገና ፈጽሞ አልሰጠም፤ ይህ ለቤተ ክርስቲያንም ጭምር ግለት ነው። የይሁዲነት አቀንቃኞች በገላትያ ክርስቲያኖች ላይ የሕግን ቀንበር ለመጫን ያደረጉት ሙከራ የእግዚአብሔርን እቅድ መቃወም ነበር። በጳውሎስ ዘመን ቤተ ክርስቲያን «ከላይኛይቱ ኢየሩሳሌም» በሆነው በእግዚአብሔር ጸጋ የተሞላ የነፃነት አስተዳደር (ገላ. 4:26) ሐሴት ስታደርግ፥ የእስራኤል ሕዝብ ግን በሕግ ባርነት ሥር ነበሩ። የይሁዲነት አቀንቃኞች የሲና ተራራንና ሰግያዊቷ ጽዮንን ለማጋባት ፈለጉ (ዕብ. 12:22)። ይህን ማድረግ ግን ኢየሱስ በቀራኒዮ ተራራ ያደረገውን መካድ ነበር (ገላ. 2:21)። አጋር እንደገና እንድታገባ አልተፈቀደላትም።

በሰብአዊ አመለካከት አንጻር ስንመለከተው እግዚአብሔር ለአብርሃም እጅግ የሚወደውን ልጁን እስማኤልን እንዲያባርር ማዘዙ ጭካኔ ሊመስል ይችላል። ለተፈጠረው ችግር ብቸኛው መፍትሔ ግን ይህ ነበር። «በሚዳ አህያ» የተመሰለው ሰው ከተስፋው ልጅ ጋር ለመኖር ጨርሶ አይችልም። እዚህ ላይ እግዚአብሔር የሕግን እርግማን ተሸክሞ እኛን ነጻ እንዲያወጣ ልጁን ሊሰጠን የከፈለውን ዋጋ በጥልቁ ስሜት አስብ። የአብርሃም ልብ በሐዘን መሰበር ግለት የይስሐቅ ነጻ መውጣት ግለት ነበር። እግዚአብሔር ልጁን ሰጠን ግለት በክርስቶስ ያለውን ነጻነትም ሰጠን ግለት ነው።

3. ተግባራዊ በረከቶች (4:30-31)

ይስሐቅ የተስፋው ልጅ እንደ ነበረ ሁሉ እኛ ክርስቲያኖችም በጸጋ የተስፋው ልጆች ነን። በሚገ የተመሰለችው የጸጋ ቃል ኪዳን መንፈሳዊ እናታችን ናት። ሕግና አሮጌ ተፈጥሮ (አጋርና እስማኤል) ሊያሳድዱንና ወደ ባርነት ሊመልሱን ይፈልጋሉ። ይህን ችግር ማቃለል የምንችለው እንዴት ነው?

ልንለውጣቸው መሞከር እንችላለን። ሕግን ወይም አሮጌውን ተፈጥሮአችንን መለወጥ ስለማንችል ይህ ደግሞ ከንቱ ድካም ነው። «ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው»ና (ዮሐ. 3:6) ሁልጊዜም ሥጋ እንደ ሆነ ይቀራል በማለት መናገር እንችላለን። እግዚአብሔር እስማኤልንም ሆነ አጋርን

በግድም ሆነ በትምህርት ለመለወጥ አልሞከረም። እንደዚሁ ሁሉ አንተም ሆንህ እኔ አሮጌው ተፈጥሮአችንን መለወጥ አንችልም።

ከእነርሱ ጋር ተቻችለን ለመኖር እንሞክር ይሆናል። ዳሩ ግን ይህ ነገር በአብርሃም ቤት አልሠራምና፤ በእኛም ሕይወት ሊሠራ አይችልም። የገላትያ ሰዎች እንደዚህ ዓይነቱ ግቻቻል ተግባራዊ ለማድረግ ሞክረው ነበር። ቀስ በቀስ ግን ወደ ባርነት መራቸው እንጂ ምንም አላደረገላቸውም። በዚህ ዘመን ያሉ ሐሰተኛ አስተማሪዎች እንዲህ ይላሉ፦ «ክርስቶስን አትተው፤ በክርስቶስ ላይ ካለህ እምነት በተጨማሪ ግን ሕግን በመለማመድ ወደ ጠለቀ ክርስትና ሕይወት ግባ።» አጋርና እስማኤልን እንደገና ወደ ቤት እንዲመለሱ ብትጋብዛቸው እንደገና ወደ ባርነት የሚወስደውን መንገድ መረጥህ ማለት ነው። «እንደገና ወደ ደካማ ወደሚደነቅም ወደ መጀመሪያ ትምህርት እንዴት ትመለሳላችሁ?» (ገላ. 4፡9)።

ከእኛ አውጥተን ልንጥላቸው እንችላለን። ልናደርገው የሚገባው ይህንን ነው። ጳውሎስ ይህን ጉዳይ በመጀመሪያ ከእስራኤል ሕዝብ (ቁ. 25-27) ቀጥሎ ደግሞ ከእያንዳንዱ ክርስቲያን ሕይወት ጋር ያዛምደዋል። የእስራኤል ሕዝብ ለክርስቶስ መምጣት በሚያዘጋጀው በሕግ ባርነት ሥር ነበሩ። ይህ ግን ጊዜያዊ ነበር። አሁን ክርስቶስ ስለ መጣ ሕግ መወገድ ነበረበት። ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ይስሐቅ በእግዚአብሔር ተአምራዊ ኃይል የተወለደ የተስፋ ልጅ ነው። እርሱ ወደ ምድር ከመጣና ለሰዎች ሁሉ ከሞተ በኋላ ሕግ ስፍራውን መልቀቅ ነበረበት።

ጳውሎስ ኢሳ. 54፡1ን በመጥቀስ ቃሉን ከይስሐቅ መወለድ በፊት መካን ከነበረችው ከሣራና እንደገና ደግሞ ከቤተ ክርስቲያን (ገላ. 4፡27) ጋር ያዛምደዋል። ንጽጽሩን እንደሚከተለው ተመልከት፦

እስራኤል	ቤተ ክርስቲያን
ምድራዊ ኢየሩሳሌም	ሰማያዊቷ ኢየሩሳሌም
ባርነት	ነፃነት
ፍሬቢሱ ሕጋዊነት	ፍሬያማው ጸጋ

ሣራ መካን ነበረች፤ ስለዚህ አብርሃም አጋርን እንዲያገባ በማድረግ ፍሬያማ ለመሆን ሞከረች። ይህ ግን ያመጣው ውድቀትንና መከራን ብቻ ነበር። ሕግ ሕይወትን ወይም ፍሬያማነትን ሊሰጥ አይችልም። ሕጋዊነት

መካን ነው። ለመጀመሪያይቱ ቤተ ክርስቲያን ወደ ባርነት መመለስ ማለት የእግዚአብሔርን ቃል አለመታዘዝና መካን መሆን ማለት ነበር። የመጀመሪያይቱ ቤተ ክርስቲያን ጸጋን አጥብቃ በመያዟ በዓለም ዙሪያ ፍሬያማናቷን አስፋፋች።

ዛሬ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንና ክርስቲያኖች በግላቸው የገላትያ ሰዎች የሠሩትን ስህተት ሊደግሙት ይችላሉ። አጋርና እስማኤልን የማባረር ኃላፊነታቸውን ላይወጡ ይችላሉ። በክርስቲያኖች መካከል ከሚገኙ ዋና ዋና ችግሮች አንዱ ሕጋዊነት ነው። ሕጋዊነት መንፈሳዊ መመዘኛዎችን ማበጀት ያለመሆኑን ልናስታውስ ይገባል። ሕጋዊነት እነዚህን መመዘኛዎች ማምለክና እነርሱን በመጠበቃችን ምክንያት መንፈሳዊ እንደሆንን ማሰብ ማለት ነው። በእነዚህ መመዘኛዎች መሠረት በሌሎች አማኞች ላይ መፍረድ ማለት ነው። አንድ ሰው መንፈሳዊ ባይሆንም እንኳ ላያጨስ፥ ላይጠጣና ወደ ቲያትር ቤቶች ላይሄድ ይችላል። እንደዚሁም ፈሪሳውያን ከፍተኛ የሕይወት መመሪያ ቢኖራቸውም እንኳ ኢየሱስን ከመስቀል ወደ ኋላ አላሉም።

«መልካም የሆንን» እንዲመስለን ስለሚያደርግ አሮጌው ተፈጥሮአችን ሕጋዊነትን ይወደዋል። እስማኤል፥ እስማኤልነቱን ጠብቆ እስከቆየ ድረስ አንዳንድ መጥፎ ተግባራትን ላለመፈጸምም ሆነ ወይም አንዳንድ ሃይማኖታዊ ተግባራትን ለመፈጸም የሚከፍለው ዋጋ ጥቂት ነው። እስማኤል ይስሐቅ ከመወለዱ በፊት ለ17 ዓመታት በቤተሰቡ ውስጥ አንዳችም ችግር ሳይፈጥር ኖሮ ነበር፤ ይስሐቅ ከተወለደ በኋላ ግን ግጭቱ ተጀመረ። ሕጋዊነት የሚያስተናገደው እስማኤልን ነው። አንዳንድ ነገሮችን ባለማድረጉ ብቻ ራሱን መንፈሳዊ አድርጎ የሚቆጥር ክርስቲያን ራሱን ያታልላል። መንፈሳዊ ሕይወት ከአሉታዊ (አታድርግ) አልፎ ፍሬ የሞላበት አዎንታዊ (አድርግ) ገጽታ አለው።

የይሁዲነት አቀንቃኞች በጣም ግራኪ አቀራረብ እንዳላቸው አጠራጣሪ አይደለም። ከሃይማኖት ባለ ሥልጣኖች እውቅናን ያገኙ ናቸው (2ኛ ቆሮ. 3፡1)፤ መመዘኛቸውም ከፍተኛ ነበር። ለሚበሉትና ለሚጠጡት እንኳ ከፍተኛ ጥንቃቄ ያደርጉ ነበር። ሰዎችን ለራሳቸው በመግረክ ውጤታማ ነበሩ፤ ይህንንም ለሌሎች ለማስተዋወቅም ሆነ ስለ ማንነታቸው ማወጅ የሚወዱ ነበሩ (ገላ. 6፡12-14፤ 4፡17-18)። ለእያንዳንዱ የሕይወት ገጽታ የሚሆን መመዘኛ ስለ ነበራቸው፥ ለተከታዮቻቸው መንፈሳዊ የሆነውን ሰው መንፈሳዊ ካልሆነው ለመለየት የሚያስችል ደንብ አበጅተውላቸው

ክበር። ነገር ግን የይሁዲነት አቀንቃኞች ሕዝቡን የመሩት ወደ ነጻነትና ድል ሳይሆን ወደ ባርነትና ሽንፈት ነበር። ሕዝቡም ልዩነቱን አያውቁም ነበር።

ጳውሎስ በዚህ መልእክት የመጨረሻ ምዕራፍ ላይ ከሁሉም ይልቅ የሚብሰውን የሕጋዊነት አስከፊ ገጽታ ይጠቁማል። ይህም ለሥጋ ሥራ ዕድል ፈንታ መስጠቱ ነበር። አሮጌው ተፈጥሮ በሕግ ቁጥጥር ሥር ሊሆን አይችልም። ሁልጊዜም ያምፃልና ይህ በሚሆንበት ጊዜ የሚፈጸመውን ነገር ሁሉ ልብ በል! ሕጋዊነት የሞላባቸው የሃይማኖት ቡድኖች ብዙውን ጊዜ እርስ በእርሳቸው የሚዋጉትና የሚከፋፈሉት ለዚህ ነው («ነገር ግን እርስ በእርሳችሁ ብትነካከሱና ብትበላሉ...» ገላ. 5፡15)። ቡድኖቹ ብዙ ጊዜ ርካሽ በሆኑት የሥጋ ሥራዎች ተጠምደው የሚወድቁት ከዚህ የተነሣ ነው (5፡19-23)። እያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን የእነዚህ ችግሮች ተካፋይ ቢሆንም የሕጋዊነት መንፈስ ባለባቸው አካባቢዎች ግን ይበልጥ ገነው ይታያሉ። ስለዚህ አንተም አጋርና እስማኤል ከሣራና ከይስሐቅ ጋር እንዲኖሩ ስትጋብዝ ችግርን እየጋበዝክ መሆኑን እወቅ።

ክርስቲያን ከሕግ እርግማንና ቁጥጥር ነፃ ስለ ወጣ እግዚአብሔር ይመስገን። «ይህችን ባሪያ ከነልጅዋ አሳድድ።) ይህ እርምጃ አብርሃምን የከበደውን ያህል እኛንም ይከብደን ይሆናል። መደረግ ግን ያለበት ጉዳይ ነው። ሕግና ጸጋን ለመቀላቀል መሞከር የማይቻለውን መሞከር ማለት ነው። ውጤቱ የተሸነፈና ፍሬ የማያፈራ የክርስትና ሕይወት ነው የሚሆነው። በጸጋው ውስጥ በእምነት መኖር ግን ነጻና የተሟላ የክርስትና ሕይወትን ይሰጠናል።

ምስጢሩ ምንድን ነው? መንፈስ ቅዱስ ነው። ጳውሎስ «ተግባራዊ» በሆነው የመልእክቱ ማጠቃለያ ክፍል የሚያካፍለን ይህንን እውነት ነው። በዚህ መካከል እኔና አንተ እስማኤልና አጋር ወደ ሕይወታችን ተስበው እንዳይገቡ ልንጠነቀቅ ይገባል። ወደ ሕይወትችን ገብተው ከሆነም ልናስወጣቸው ይገባል።

ክፍል 3

የተግባራዊ ኑሮ ገለጻ ክፍል፡-

ጸጋና የክርስቲያን ሕይወት

ምዕራፍ 5-6

ገላትያ 5፡1-12

በነጻነት ልንኖር ክርስቶስ ነጻነት አወጣን፤ እንግዲህ ጸንታችሁ ቁሙ እንጂ እንደ ገናም በባርነት ቀንበር አትያዙ።

እነሆም እኔ ጳውሎስ እላችኋለሁ፡- ብትገረዙ ክርስቶስ ምንም አይጠቅማችሁም። ሕግንም ሁሉ እንዲፈጽም ግድ አለበት ብዬ ለሚገረዙት ሁሉ ለእያንዳንዶች ደግሜ እመሰክራለሁ። በሕግ ልትጸድቁ የምትፈልጉ ከክርስቶስ ተለይታችሁ ከጸጋው ወድቃችኋል። እኛ በመንፈስ ከእምነት የጽድቅን ተስፋ እንጠባበቃለንና። በክርስቶስ ኢየሱስ ሆኖ፥ በፍቅር የሚሠራ እምነት እንጂ መገረዝ ቢሆን ወይም አለመገረዝ አይጠቅምምና። በመልካም ትሮጡ ነበር፤ ለእውነት እንዳትታዘዙ ማን ከለከላችሁ? ይህ ማባበል ከሚጠራችሁ አልወጣም። ጥቂት እርሾ ሊጡን ሁሉ ያቦካል። የተለየ ነገር ከቶ እንዳታስቡ እኔ በጌታ ስለ እናንተ ታምኜአለሁ፤ የሚያናውጣችሁ ማንም ቢኖር ግን ፍርዱን ሊሸከም ነው። ነገር ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ እኔ ገና እስከ አሁን መገረዝን ብሰብክ እስከ አሁን ድረስ ለምን ያሳድዱኛል? እንኪያስ የመስቀል ዕንቅፋት ተወግዶአል። የሚያውኩአችሁ ይቆረጡ።

- 9 -

ቁም! ሌባ!

የይሁዲነት አቀንቃኞች እንዲህ ይሉ ነበር፡- «የጳውሎስ የጸጋ መሠረታዊ ትምህርት አደገኛ ነው፤ ሕግን በመተው ለልቅነት ስፍራ ይሰጣል። ለምን! ከሕጋችን ከራቅንና ከፍተኛ መመዘኛችንን ከተውን አብያተ ክርስቲያናቻችን ይበታተናሉ።»

በእግዚአብሔር ጸጋ ላይ መደገፍን የፈሩ የአንደኛው ምዕተ ዓመት የይሁዲነት አቀንቃኞች ብቻ አልነበሩም። በዘመናችንም በአብያተ ክርስቲያናቻችን ያሉ ሕጋዊያን በክርስቶስ ስላለን ነጻነት ማውራት ሃይማኖታዊ ሥርዓት አልበኝነት ያመጣል በማለት ያስጠነቅቃሉ። እነዚህ ሰዎች ጳውሎስ ስለ ጸጋ ያስተማረውን ትምህርት በተሳሳተ መንገድ ነው የሚረዱት። ጳውሎስ የዚህን መልእክት የመጨረሻ ክፍል (ገላ. 5-6) የጻፈው ይህን የተሳሳተ ግንዛቤ ለማስተካከል ነበር።

በአሁኑ ትምህርቱ ጳውሎስ የመከራከሪያ አሳብ ከማቅረብ ወደ ሕይወት ተዛምዶ፥ ከእምነት ትምህርት ወደ ተግባራዊ ጉዳይ ተሸጋግሮአል። በእምነት የሚኖር ክርስቲያን ዓመፀኛ ሊሆን አይችልም። ከዚህ በተጻራሪ ውጫዊ ሥርዓት ከሆነው ሰው ሠራሽ ሕግ እጅግ የላቀውን የእግዚአብሔርን ውስጣዊ ሥርዓት ይለማመዳል። በእግዚአብሔር ጸጋ የሚታመን፥ ለእግዚአብሔር መንፈስ የተሰጠ፥ ለሌሎች የሚኖርና እግዚአብሔርን ለማክበር የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ዓመፀኛ መሆን አይችልም። ሕግ አጥባቂው ግን በባርነት ስለሚኖር፥ በሥጋ ስለሚታመን፥ ለራሱ ብቻ ስለሚኖርና የእግዚአብሔርን ክብር ሳይሆን የሰውን ምስጋና ስለሚፈልግ ውሎ ቢያድርም ዓመፀኛ መሆኑ የግይቀር ነው።

ጳውሎስ በጸጋ ስለሚገኘው የክርስትና ነፃነት ያስተማረው መሠረታዊ የእምነት ትምህርት በፍጹም አደገኛ አልነበረም፤ አደገኛ ትምህርት ሕግ አክራሪነት ነው። ምክንያቱም ሕግ አክራሪነት የማይችለውን ለማድረግ ነው የሚሞክረው። አሮጌውን ተፈጥሮ ለውጦ ለእግዚአብሔር ሕግጋት እንዲታዘዝ ለማድረግ ይሞክራል። ሕግ አክራሪነት ውጤታማ የሚሆነው ለአጭር ጊዜ ነው። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሥጋ ማመፅ ይጀምራል። በመንፈስ

ቅዱስ ኃይል የሚታመን ራሱን የሰጠ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ሕግ አይቃወምም፤ ወይም በሕጉ ላይ አያምፅም፤ ይልቁንም ሕጉ በመንፈስ በኩል በሕይወቱ በሥራ ላይ ይውላል (ሮሜ 8፡1-4)። እነዚህን በግጠታለያዎቹ ምዕራፎች ላይ የሰፈሩትን አሳቦች ቅደም ተከተል መመልከት ቀላል ነው፡-

1. በክርስቶስ ነፃ ወጥቼአለሁ። ከእንግዲህ ወዲህ በሕግ ባርነት ሥር ልሆን አልችልም (ገላ. 5፡1-12)።
2. ሆኖም ሕይወቴን ከውስጥ ሆኖ የሚቆጣጠረኝ አንድ ረዳት ያስፈልገኛል። ይህ ረዳት መንፈስ ቅዱስ ነው (5፡13-26)።
3. በመንፈስ ቅዱስ ፍቅር ለራሴ ሳይሆን ለሌሎች የመኖር ፍላጎት አለኝ (6፡1-10)።
4. ይህ የነጻነት ሕይወት እጅግ መልካም በመሆኑ ለእግዚአብሔር ክብር ልኖረው እፈልጋለሁ፤ ምክንያቱም ይህን ለማድረግ ያስቻለኝ እርሱ ነው (6፡11-18)።

እስቲ ይህን የመሰለውን ሕይወት፥ በሕግና በአንዳንድ ሃይማኖታዊ መሪዎች ሥርዓት ሥር ለመኖር ከመረጠ ሰው ልምምድ ጋር አንደሚከተለው አወዳድር፡-

1. ለእነዚህ ሕጎች ከታዘዝኩ የበለጠ መንፈሳዊ ሰው እሆናለሁ። ይህን ሃይማኖታዊ መሪ እጅግ ስለማደንቀው ለእርሱ መመሪያ እገዛለሁ።
2. ለሕግ ለመታዘዝና ራሴን ለማሻሻል የሚሆን ብርታት እንዳለኝ አምናለሁ። የተነገረኝን በማድረጌም በተወሰነልኝ የሕይወት ብታት መመዘኛ ላይ እደርሳለሁ።
3. መሻሻል እያደረግሁ ነው። ከዚህ በፊት አደርጋቸው የነበሩትን አንዳንድ ነገሮች አሁን አላደርግም። ባለኝ መታዘዝና የሥነ-ሥርዓት ኑሮ ሌሎች ሰዎች ያመሰግኑኛል። ከሌሎች ጋር ባለኝ ጎብረት ከብዙዎች የተሻልሁ እንደ ሆንሁ ማየት እችላለሁ። በጣም መንፈሳዊ መሆን እንዴት አስደናቂ ነገር ነው።
4. ሌሎች ሰዎች እንደኔ ቢሆኑ ኑሮ እንዴት መልካም በሆነ ነበር። እኔ የእርሱ በመሆኔ እግዚአብሔር ዕድለኛ ነው። ሌሎች እንደ እኔ እንዲሆኑ ይህን ጉዳይ ለሌሎች የማካፈል ከፍተኛ ፍላጎት አለኝ። ቡድናችን እያደገ

ነው። ደግሞም እጅግ መልካም ምስክርነት አለው። ሌሎች ቡድኖች እንደ እኛ መንፈሳዊ ያለመሆናቸው በጣም የሚያሳዝን ነው።

ሕግ አክራሪነትን በየትኛውም መንገድ ብትመለከተው፥ አድብቶ የሚገባና ለጥፋት በምስጢር የሚሠራ አደገኛ ጠላት ነው። ጸጋን ለሕግ ብለህ በምትተውበት ጊዜ ሁሉ ያገኘኸውን ታጣለህ። ጳውሎስ በዚህ የመጀመሪያ ክፍል (5፡1-12) የሚገልጸው አማኝ ከእግዚአብሔር ጸጋ ወደሰው ሠራሽ ሕጎችና ደንቦች ሲመለስ ምን እንደሚያጣ ነው።

1. ባሪያ ትሆናለህ - አነጋገር ነፃነትህን ታጣለህ(5፡1)

ጳውሎስ ሕግ ምን እንደሚመስል ለመልእክቱ አንባቢዎች ለመግለጽ በሁለት ተምሳሌታዊ ግወዳደሪያዎች ከዚህ በፊት ተጠቅሟል፡- በሞግዚት ወይም በበላይ ጠባቂ (3፡24፤ 4፡12-25)፥ በሴት ባሪያ (4፡22-25)። አሁን ደግሞ ከባርነት ቀንበር ጋር ያወዳድረዋል። ጴጥሮስ ይህንኑ ተምሳሌት በታዋቂው የኢየሩሳሌም ጉባኤ ላይ እንደ ተጠቀመበት ታስታውሳለህ (የሐዋ. 15፡10 ተመልከት)።

የቀንበርን ምንነት መረዳት አስቸጋሪ አይደለም። ብዙ ጊዜ በሌላ ኃይል የመገዛት፥ የባርነት፥ የአገልግሎትና በቁጥጥር ሥር የመሆንን ጉዳይ ይወክላል። እንደዚሁም ለሌላ አካል በፈቃደኝነት የሚሰጥ አገልግሎትንና መገዛትን ያመለክታል። እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከግብፅ ባርነት ነፃ ባወጣ ጊዜ ቀንበር ሰብሮላቸው ነበር (ዘሌ. 26፡13)። አንድ ገበሬ በቀንበር የሚጠቀመው የሚያደርስባቸውን በሬዎች ለመምራትና ለመቆጣጠር እንዲያስችለው ነው። ምክንያቱም ነፃ ቢሆኑ ኖሮ በፈቃደኝነት አያገለግሉም ነበር።

በገላትያ የነበሩ አማኞች በክርስቶስ ባመኑ ጊዜ የኃጢአት ባርነት ቀንበር ተወግዶላቸው የክርስቶስን ቀንበር ተሸከሙ(ማቴ. 11፡28-30)። የሃይማኖት ቀንበር ጠንካራና ሸክሙም እጅግ ከባድ ነው። የክርስቶስ ቀንበር «ልዝብ» ሸክሙም «ቀሊል» ነው። ልዝብ የሚለው የአማርኛ ቃል የግሪክ ትርጉም «ደግ፥ ቸርነትና ጸጋ የተሞላ» ማለት ነው። የክርስቶስ ቀንበር ፈቃዱን እንድናደርግ ነጻ የሚያወጣን ሲሆን፥ የሕግ ቀንበር ግን ትእዛዛትን እንድንፈጽም ባሪያ ያደርገናል። ያልዳነ ሰው የኃጢአትን ቀንበር ይለብሳል (ሰቆ. ኤር. 1፡14)፤ ሃይማኖታዊ ሕግ አክራሪ የሆነው ሰው ደግሞ የባርነት

ቀንበር ይለብሳል (ገላ. 5፡ 1)። በእግዚአብሔር ጸጋ ላይ የሚደገፍ ክርስቲያን ግን የክርስቶስን የነጻነት ቀንበር ይለብሳል።

ከሕግ ባርነት ነጻ ያደረገን ክርስቶስ ነው። በመስቀል ላይ በመሞት ከሕግ እርግማን ነፃ አደረገን (ገላ. 3፡ 13)። አንድ ሰው በክርስቶስ ካመነ በኋላ ከጸጋ ሥር እንጂ (ሮሜ 6፡ 14) ከሕግ ቀንበር ባርነት ሥር አይደለም። ይህም ማለት እኛ ከሕግ ውጭ የሆንን ሥርዓተ አልበኞች ወይም ዓመፀኞች ነን ማለት አይደለም። የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመጠበቅ በእግዚአብሔር መንፈስ ውስጣዊ አመራር ስላለን ውጫዊ የሆነ የሕግ ኃይል አያስፈልገንም ማለት ነው (ሮሜ 8፡ 1-4)። ክርስቶስ የሞተው ነፃ ሊያወጠን እንጂ ባሪያ ሊያደርገን አይደለም። ወደ ሕግ መመለስ ማለት «አድርግና አታድርግ» በሚሉ ሕጎች ውስብስብ እንቆቅልሾች መታነቅና፥ መንፈሳዊ ጉልምስና ትተን ወደ «ዳግም ሕፃንነት» መመለስ፡ ማለት ነው።

ስለ ነፃነት ምንም ዓይነት ዋስትና የማይሰማቸው አንዳንድ ሰዎች መኖራቸው በጣም የሚያሳዝን ነው። የራሳቸውን ውሳኔ በነፃነት ከማድረግ ይልቅ፥ ለአንዳንድ መሪዎች ጨካኝና አምባ ገነን መመሪያ መታዘዝን ይመርጣሉ። በእግዚአብሔር ጸጋ አማካይነት ባገኙት ነጻነት እጅግ የሚፈሩ አማኞችም አሉ። ስለዚህ ሌሎች ለእነርሱ ውሳኔ እንዲያደርጉላቸው በመፈለግ በሕግ አክራሪነትና በአምባ ገነንነት በሚመራ ቡድን ሥር ይታቀፋሉ። ይህ ለአዋቂ ሰው የሕፃንን ሥራ የሚሠራ ሰውን ይመስላል። የክርስትና ነፃነት መንገድ የክርስቶስ የሙላት መንገድ ነው። ጳውሎስ የሚከተለውን ጥብቅ ማስጠንቀቂያ መስጠቱ የሚያስደንቅ አይደለም። «ጸንታችሁ ቁሙ፥ እንደገና በባርነት ቀንበር አትያዙ»።

2. ባለ ዕዳ ትሆናለህ - ሀብትህን ታጣለህ(5፡2-6)

ጳውሎስ ከጸጋ ወደ ሕግ የተመለሰ ክርስቲያን የሚደርስበትን ሦስት ኪሣራዎች ይገልጻል። «ክርስቶስ ምንም አይጠቅማችሁም» (ቁ. 2)፥ «ሕግንም ሁሉ እንዲፈጽም ግድ አለበት» (ቁ. 3)፥ «ከክርስቶስ ተለይታችሁ» (ቁ. 4)። ቀጥሎ ደግሞ በዚሁ በቁ.4 ወደምናገኘው አሳዛኝ ግጠቃለያ እንደርሳለን። «ከጸጋው ወድቃችኋልና።» ሕግ አክራሪነት የአማኝን ነጻነት የሚገፍ መሆኑ በጣም አሳዛኝ ነገር ነው። በተጨማሪ በክርስቶስ ያለውን መንፈሳዊ ብልጥግና ሁሉ ይገፋል። በሕግ ሥር የሚኖር አማኝ የከሰረ ባሪያ ይሆናል።

ደህንነትን ባልተቀበልንበት ወቅት ልንከፍለው የማንችለው የእግዚአብሔር ዕዳ እንደ ነበረን መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። ኢየሱስ በሁለቱ ተበዳሪዎች ታሪክ ይህንን ጉዳይ ግልጽ አድርጎታል (ሉቃስ 7፡36-50)። ሁለቱ ተበዳሪዎች ከአንድ አበዳሪ ገንዘብ ተበደሩ። የአንዱ ተበዳሪ ዕዳ ከሌላኛው አሥር ጊዜ የላቀ ነበር። እነዚህ ተበዳሪዎች መክፈል ስላቃታቸው አበዳሪው የሁለቱንም ዕዳ በታላቅ ችሮታው ተወላቸው። የሰው ልጅ ያለው የሥነ-ምግባር ብቃት ምንም ያህል ከፍተኛ ቢሆንም እንኳ የእግዚአብሔር ክብር ይጎድለዋል። አንድ ሰው ያለበት የኃጢአት ዕዳ ከሌላው ሰው ዕዳ አሥር ጊዜ ቢያንስ እንኳ መክፈል አይችልም። ስለዚህ በእግዚአብሔር የፍርድ መንበር ፊት ተራቁቶ ይታያል። ክርስቶስ በመስቀል ላይ በሠራው ሥራ፥ ዕዳቸው ምንም ያህል ከፍተኛ ቢሆንም እንኳ፥ እግዚአብሔር ለኃጢአተኞች በጸጋው ይቅርታ ለማድረግ ችሏል።

ስለዚህ በኢየሱስ ክርስቶስ ስናምን መንፈሳዊ ባለጠጋ እንሆናለን። ከእግዚአብሔር ጸጋ ባለጠግነት (ኤፌ. 1፡7)፥ ከክብሩ ባለጠግነት (ኤፌ. 1፡18፤ ፊልጲ. 4፡19)፥ ከጥበቡ ባለጠግነት (ሮሜ 11፡33)፥ «ፍለጋ ከሌለው የክርስቶስ ባለጠግነት» (ኤፌ. 3፡8) ተካፋዮች እንሆናለን። በክርስቶስ «የተሰወረ የጥበብና የእውቀት መዝገብ ሁሉ» አለን (ቆላ. 2፡3)። እንደዚሁም በእርሱ «ተሞልተናል» (ቆላ. 2፡10)። አንድ ሰው በክርስቶስ ውስጥ ከሆነ ጊዜ ጀምሮ እግዚአብሔር የሚፈልገው አይነት የክርስትና ኑሮ ለመኖር የሚያስፈልጉት ነገሮች ሁሉ አሉት።

የይሁዲነት አቀንቃኞች ግን «አንድ ነገር እንደ ጐደለን» እንድናምን ይፈልጋሉ። ይህም ለሕግ ከተገዛንና ሥነ-ሥርዓቶቹንም አክባሪ ከሆንን የበለጠ «መንፈሳዊነት እንደ ጐደለን» እንደምንሆን ነው። ጳውሎስ ግን ምንም ነገር መጨመር ስለማይቻል ሕግ አንዳችም ነገር እንደማይጨምርልን ግልጽ ያደርጋል። በዚህ ምትክ ሕግ እንደ ሌባ አድብቶ በመምጣት አንድ አማኝ በክርስቶስ ያለውን መንፈሳዊ ብልጽግና ይዘርፋል። ከክብድ ኪሣራም ላይ ስለሚጥለው ሊከፍለው ለማይችለው ዕዳ ተጠያቂ ያደርገዋል።

በጸጋ መኖር ማለት ለሚያስፈልገን ነገር ሁሉ በእግዚአብሔር ብልጽግና መታመን ማለት ነው። በሕግ መኖር ማለት ግን በራስ ብርታት፥ በሥጋ መታመንና ያለ እግዚአብሔር ችሮታ መኖር ማለት ነው። ጳውሎስ (ግርዘት በራሱ ምንም ልዩነት ባያመጣም እንኳ ቁ. 6፤ 6፡15) በዚህ ሁኔታ ግን ለግርዘት ሕግ መገዛት በክርስቶስ ያላቸውን ነፃነት ሁሉ ሊገፍ እንደሚችል

በማሳሰብ የገላትያ ሰዎችን ያስጠነቅቃቸዋል። በተጨማሪም ለአንዱ ሕግ መገዛት ሕግጋትን በሙሉ እንዲፈጽሙ ግዴታ ውስጥ የሚከት ነበር።

ሕግ አክራሪዎች ከሕግጋቱ አንዳችም ሳያስቀሩ በፍጹምነት መጠበቅ ስለማይችሉ ግብዝነታቸው እዚህ ላይ ይጋለጣል። በእነርሱ ዘንድ የብሉይ ኪዳን ሕግ ተፈጻሚነት የሚያገኘው፥ አንድ ደንበኛ ምግብ ቤት ውስጥ ያሉ የተለያዩ ምግቦችን ተመልክቶ የሚፈልገውን ከወሰደ በኋላ የቀሩትን ለመተው ባለው ምርጫ መልክ ነበር። ይህ ደግሞ ታማኝነት የጐደለው ምግባር ይሆናል። ለምሳሌ፡- በዚህ ዘመን ያለ ክርስቲያን የሞት መቅሠፍት የማለፍ (ፋሲካ) በዓልን ባያከብርም እንኳ፥ ሰንበትን ማክበር አለበት ማለት የእግዚአብሔርን ሕግ መንጣጠል ነው። ሕግጋትን ሁሉ የሰጠው አንዱ እግዚአብሔር ነው (ያዕ. 2፡9-11)። ከዚህ ቀደም ብሎ ጳውሎስ፥ ሕግጋትን በሙሉ አንዳችም ሳያስቀሩ በማይጠብቁ ሁሉ ላይ የሕግ መርገም በላያቸው ላይ እንዳለ በማረጋገጥ ሙሴን ጠቅሶ ነበር (ገላ. 3፡10፤ ዘዳ. 27፡26 ተመልከት)።

ይህን ለማብራራት ያህል እስቲ አንድ የመኪና አሽከርካሪ በከተማ ውስጥ እያሽከረከረ ሳለ አውቆም ይሁን ሳያውቅ ቀይ መብራት ጥሶ ሄደ እንበል። የትራፊክ ፖሊስ ይይዘውና የመንጃ ፈቃዱን ይጠይቀዋል። ወዲያውኑ ይህ ሾፌር ራሱን በመከላከል «እባክዎን ቀይ መብራት እንደ ጣስሁ አምናለሁ፤ ነገር ግን ማንንም ዘርፌ አላውቅም፤ በሕይወት ዘመኔ ሁሉ አመንዝሬ አላውቅም፤ ግብር አከፋፈልም ላይ አታልዬ አላውቅም» እያለ ቢለፈልፍ የትራፊክ ፖሊሱ ግን ፈገግ በማለት የክስ መጥሪያውን ይጽፍለታል። ምክንያቱም በብዙ ነገሮች ታዛዥ መሆን በአንድ ነገር እንኳ ያለመታዘዝን ጥፋት ሊያካክሰው ስለማይችል ነው። ጥፋተኛው ሰው እንዲቀጣ ታዛዥ የሆነው ሰው ደግሞ ጥበቃ እንዲያገኝ የሚያደርግ ያው አንድ ሕግ ነው። የሕግን የተወሰነ ክፍል እየተላለፉ የተቀሩትን ክፍሎች ደግሞ እየጠበቅሁ ነው ብሎ መመካት፥ ቅጣት የሚገባኝ ነኝ በማለት እንደማወጅ ነው የሚቆጠረው።

ጳውሎስ «ከጸጋው ወድቃችኋል» ሲል ምን ማለቱ እንደ ነበር አሁን በተሻለ ሁኔታ ልንረዳው እንችላለን (ገላ. 5፡4)። በዚህ አባባሉ የገላቲያ ሰዎች «ደህንነታቸውን አጥተዋል» ማለቱ እንዳልሆነ ግልጽ ነው። ምክንያቱም ጳውሎስ በዚህ መልእክት ውስጥ በአጠቃላይ ስለ ገላትያ ሰዎች ሲናገር ክርስቲያን መሆናቸውን በመቀበል ነበር። ቢያንስ ዘጠኝ ጊዜ ያህል

«ወንድሞች» እያለ ይጠራቸዋል። ደግሞም «እኛ» በሚለው «ተውላጠ ስም» ተጠቅሟል (4፡28፥31)። መልእክቱን የሚያነቡ ሰዎች አማኞች ባይሆኑ ኖሮ ጳውሎስ በእነዚህ አባባሎች ፈጽሞ አይጠቀምም ነበር። በተጨማሪም «ልጆችም ስለ ሆናችሁ እግዚአብሔር አባ አባት ብሎ የሚጮኽውን የልጁን መንፈስ በልባችሁ ውስጥ ላከ» (4፡6) ብሏል። ስለዚህ መልእክቱን የሚያነቡት ሰዎች ያልዳኑ ቢሆን ኖሮ ጳውሎስ እንደዚህ ለማለት ባልደፈረም ነበር።

በመሆኑም «ከጸጋው መውደቅ» ማለት ደህንነትን ማጣት ማለት ሳይሆን ከእግዚአብሔር ጸጋ ከልል ውጭ መውደቅ ማለት ነው። ጸጋና ሕግን መደባለቅ አትችልም። በሕግ ክልል ለመኖር ከወሰንህ በጸጋ ክልል መኖር አትችልም። በገላትያ የነበሩ ክርስቲያኖች ሐሰተኛ አስተማሪዎች አዚም አድርገውባቸው ነበርና (ገላትያ 3፡1)፤ በዚህ ምክንያት ለአውነት አይታዘዙም ነበር። ወደ ሌላ ወንጌል ዞር በማለት (1፡6-9) ወደ ቀድሞ ሃይማኖት የመጀመሪያ ነገሮች ተመልሰው ነበር (4፡9)። የዚህም ውጤት በባርነት ቀንበር መታነቃቸውና አሁን ባሉበት ሁኔታ «ከጸጋ ወድቀው» መገኘታቸው ነበር። የዚህ ውድቀት አሳዛኝነቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ሊያደርግላቸው የሚችለውን መልካም ነገሮች ሁሉ ከራሳቸው ላይ ገፍፈው መጣላቸው ነው።

ጳውሎስ ቀጥሎ ያቀረበው፥ አማኝ በጸጋ ክልል ውስጥ የሚኖረውን ሕይወት ነው (5፡5-6)። ይህ ክፍል ሁለቱን የሕይወት መንገዶች እንድናነጻጽር ይረዳናል። በጸጋ ስትኖር በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ትደገፋለህ። በሕግ ስትኖር ግን በራስህና በጥረትህ መደገፍህ ነው። እምነት ሕያው ሆኖ የሚሠራ እንጂ የሞተ አይደለም (ያዕ. 2፡14-26)። እምነት በመንፈስ ቅዱስ በኩል ስኬታማ ሊያደርግ የሚችለውን የሥጋ ጥረት ሊያደርገው አይችልም። እምነት የሚሠራው በፍቅር ነው። ይህ ፍቅር ለእግዚአብሔርና ለሌሎች ያለው ፍቅር ነው። ሥጋ ደግሞ ብዙ ጊዜ ስስታምነትንና ተቀናቃኝነትን እንጂ ፍቅርን ሊያመነጭ አይችልም (ገላ. 5፡15 ተመልከት)። ጳውሎስ የሕግ አክራሪነትን ሕይወት በውድቀት መስሎ ግቅረቡ የሚያስደንቅ አይሆንም።

አንድ አማኝ በእግዚአብሔር መንፈስ ላይ በመደገፍ በእምነት በሚራመድበት ጊዜ በእግዚአብሔር ጸጋ ክልል ውስጥ ስለሚኖር የሚያስፈልገውን ሁሉ ያገኛል። የእግዚአብሔርን ጸጋ ባለጸግነት

ይለማመዳል። ሁልጊዜ ወደፊት የሚጠብቀው ተስፋ ይኖረዋል (5፡5)። ይህም ኢየሱስ እንደ ራሱ ፍጹም ጻድቅ ሊያደርገን አንድ ቀን የመመለሱ ተስፋ ነው። ሕግ የፍጹም ጻድቅ የወደፊት ተስፋን አይሰጥም። ሕግ ለክርስቶስ የመጀመሪያ መምጣት መንገድ አዘጋጅቷል (3፡23-4፡7)። ለክርስቶስ ዳግም ምጽአት መንገድን ሊያዘጋጅ ግን አይችልም።

ስለዚህ ሕግ አከራሪነትን የሚመርጥ አማኝ መንፈሳዊ ነፃነቱንና ብልጽግናውን ከራሱ ላይ ይገፍፋል። እያወቀ ራሱን ከባርነት ቀንበር ሥርና ከኪሳራ ላይ ይጥላል።

3. እንደ ሯጭ - አቅጣጫህን ትስታለህ (5፡7-12)

ጳውሎስ ሯጮችን በምሳሌ የመጠቀም ልማድ ስላለው ብዙ ጊዜ በመልእክቶቹ ያነሣቸዋል። የመልእክቶቹ አንባቢዎች የነበሩት የገላትያ ሰዎች የኦሎምፒክ ጨዋታዎችንና ሌሎችንም የሩጫ እሽቅድምድሞችን የሚያካትቱ የግሪኮችን ውድድሮች ይመለከቱ ነበር። ጳውሎስ በእነዚህ ውድድሮች ተምሳሌነት የተጠቀመው ስለ ደህንነት ለመናገር እንዳልሆነ ልብ ማለት ያስፈልጋል። ለክርስቲያኖች ሁልጊዜም የሚናገረው የክርስትናን ሕይወት እንዴት መኖር እንዳለባቸው ነው። በግሪክ ውድድሮች ለመሳተፍ የመጀመሪያው ቅድመ ሁኔታ ዜግነት ነበር። እኛም በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን የሰማያዊቷ አገር (የመንግሥተ ሰማያት) ዜጋ ሆነናልና ሮጠን እናሸንፍ ዘንድ ጌታ ከውድድሩ አስገብቶናል። ይኸውም የምንሮጠው ሽልማትን ለማግኘት ነው ማለት ነው (ፊልጵ. 3፡12-21)። ስለዚህ የምንሮጠርው ደህንነትን ስላገኘንና በሕይወታችን የእግዚአእብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም (የሐዋ. 20፡24) ስለምንፈልግ እንጂ ደህንነትን ለማግኘት አይደለም።

«በመልካም ትሮጡ ነበር»። ጳውሎስ መጀመሪያ ወደ እነርሱ በመጣ ጊዜ የተቀበሉት «እንደ እግዚአብሔር መልአክ ነበር» (ገላ. 4፡14)። ቃሉን በመቀበልና ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በማመን መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው ነበር። ሁሉም ሰው የሚያየው ጥልቅ የሆነ ደስታ ይታይባቸው ነበር። ከጳውሎስ ላለመለየትና ማንኛውንም መሥዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ ነበሩ (4፡15)። አሁን ግን ጠላታቸው መስሎ ታያቸው። ለዚህ ምክንያቱ ምን ይሆን?

የቁጥር 7 ቀጥተኛ ትርጉም ለዚህ ጥያቄ መልስ ይሰጠናል። «በመልካም ትሮጡ ነበር፤ ለእውነት እንዳትታዘዙ ማን ከለከላችሁ?» በሩጫ ውድድር ውስጥ እያንዳንዱ ሯጭ የሚሮጥበት ጠባብ መንገድ በመስመር ተለይቶ ይሰጠዋል። አንዳንድ ሯጮች ተፎካካሪዎቻቸውን ከውድድር ለማስወጣት መስመሩን እንዲለቁ ለማድረግ መሰናክል ይፈጥሩባቸው ነበር። የይሁዲነት አቀንቃኞችም በገላትያ ሰዎች ላይ ያደረጉት መፈታተን ከዚህ ተለይቶ የሚታይ አልነበረም። የውድድር መስመራቸውን በማቋረጥ አቅጣጫቸውን እንዲለውጡ አስገደዷቸውና ከዋናው መንፈሳዊ መንገድ ለቀው በሌላ መንገድ እንዲሄዱ አደረጓቸው። ይህን ያደረገው እግዚአብሔር አልነበረም፤ ምክንያቱም እርሱ የጠራቸው በተሰመረላቸው «የጸጋ» መስመር እንዲሮጡ ነበር።

የጳውሎስ ገለጻ ከሩጫ ውድድር ወደ ምግብ ማብሰል ምሳሌነት ይሸጋገራል፤ በዚህ ስፍራ ስለ እርሾ ይናገራል። በብሉይ ኪዳን እርሾ የክፉት ምሳሌ ነው። ለምሳሌ፦ የሞት መቅሠፍት ባለፈበት ወቅት የፋሲካ በዓል ሲከበር እርሾ እንዲኖር አልተፈቀደም ነበር (ዘጸ. 12፡15-19፤ 13፡7)። ለአንዳንድ የተለዩ ሁኔታዎች ካልሆነ በስተቀር ከመሥዋዕቱ ጋር እርሾ እንዳይደባልቁ ታግደው ነበር (ዘጸ. 34፡25)። ኢየሱስ እርሾን የኃጢአት ተምሳሌት አድርጎ በመጠቀም «ከፈሪሳውያን እርሾ ተጠበቁ» በማለት አስጠንቅቋል (ማቴ. 16፡6-12)። ጳውሎስ ደግሞ በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የነበረውን ኃጢአት ለመግለጥ እርሾን በተምሳሌነት ጠቅሶአል (1ኛ ቆሮ. 5)።

እርሾ ጥሩ የኃጢአት ተምሳሌት ነው። ትንሽ ቢሆንም እንኳ ቀስ በቀስ ሁሉን ይበክላል። የይሁዲነት አቀንቃኞች ሐሰተኛ ትምህርት ወደ ገላትያ ቤተ ክርስቲያን የገባው በትንሹ ነበር፤ ብዙ ሳይቆይ ግን «እርሾው» ሁሉንም ለመበከልና ለመቆጣጠር ቻለ።

የሕግ አክራሪነት መንፈስ በቤተ ክርስቲያን ላይ የበላይነት የሚይዘው በድንገት አይደለም። እንደ እርሾ በምስጢር ይገባና ያድጋል፤ ብዙ ሳይቆይ አጠቃላይ ጉባኤውን ይመርዛል። ብዙ ጊዜ ሕግ አክራሪነትን እንዲነሣሣ የሚያደርጉት ውስጣዊ ምክንያቶች መልካም ናቸው፦ (ለምሳሌ «ከዚህ የተሻለ መንፈሳዊ ቤተ ክርስቲያን እንፈልጋለን»)። የሚጠቀምባቸው ዘዴዎች ግን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደሉም።

በአንድ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መመዘኛዎች መኖራቸው ስህተት አይደለም። ሆኖም እነዚህ መመዘኛዎች ማንኛውንም ሰው መንፈሳዊ ያደርጋሉ ብለን ልናስብ ግን አይገባም። ወይም መመዘኛዎችን ማሟላት የመንፈሳዊነት ማስረጃ ነው ብለን ልንቀበለው አይገባም። እርሾው ሲያድግ በቀላሉ ነው። ብዙ ሳይቆይ ስለ መንፈሳዊነታችን መመካት እንጀምራለን (በ1ኛ ቆሮ. 5:2 ጳውሎስ እዚህ ላይ ያስቀመጠው «ማበጥ» ወይም መወጠር የሚል ቃል ነው)። እርሾ የሚያደርገው ይህንኑ ነው። «ያሳብጣል ወይም ይነፋል።» የሌሎች ሰዎችን መንፈሳዊ አለመሆን መተቸት እንጀምራለን። ይህ በእርግጥ ሥጋን ብቻ የሚመግብና መንፈስን የሚያሳዝን ነው። እግዚአብሔርን የምናከብር እየመሰለን በራሳችን መንገድ መሄዳችን ነው።

እያንዳንዱ ክርስቲያን የሕግ አክራሪነትን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ማቆጥቆጥ የመከታተል ኃላፊነት አለበት። እንደ እርሾ ያነሰው ነገር ያድግና በክርስቲያናዊ ጎብረት ውስጥ ትልቅ ችግር ያስከትላል። ጳውሎስ ሐሰተኛ አስተማሪዎችን በሚያወግዝበት ጊዜ ኃይለኛ መራራ ቃል መጠቀሙ የሚያስደንቅ አይደለም። «ነገር ግን ወንድሞች ሆይ፥ እኔ ገና መገረዝን ብሰብክ እስካሁን ድረስ ለምን ያሳድዱኛል? እንኪያስ የመስቀል እንቅፋት ተወግዷል። የሚያውኳችሁ ይቆረጡ» (ገላ. 5:11-12)።

ከክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ወዲህ ግርዘት ምንም አይነት መንፈሳዊ ዋጋ የሌለው ውጫዊ ተግባር ብቻ ነው። ጳውሎስ ሐሰተኛ አስተማሪዎች በራሳቸው ላይ ቀዶ ጥገና ሊያካሂዱ ወይም ራሳቸውን ቢሰልቡ ይሻላቸው ነበር ይላል። ይህን የተመኘው ተጨማሪ «የባርነት ልጆች» ማፍራት እንዳይችሉ ነበር።

በእግዚአብሔር ጸጋ ክልል የሚኖር አማኝ ነፃ፥ ባለጸጋና ወደ ሽልማት ሙላት በሚያደርሰው ጠባብ መንገድ ላይ የሚጓዝ ነው። ጸጋን ለሕግ የተወ አማኝ ግን ባሪያ፥ ድሃና በትክክለኛው መንገድ ወጥቶ ባልተፈቀደ መንገድ የሚጓዝ ነው። በአጭሩ ተሸናፊ ነው። አሸናፊ የመሆኚያ ብቸኛው መንገድ ሕግና ጸጋን የሚያደባልቁ የሐሰተኛ አስተማሪዎችን የትምህርት «እርሾ ማስወገድ ነው»። ራስን ለመንፈስ ቅዱስ መስጠት ነው።

የእግዚአብሔር ጸጋ በሕይወት ለሚያስፈልጉን ነገሮች ሁሉ ብቁ ነው። በጸጋው ድነናልና (ኤፌ. 2:8-10)፤ በጸጋ እናገለግላለን (1ኛ ቆሮ. 15:9-10)። ጸጋ በመከራ እንድንጸና ያስችለናል (2ኛ ቆሮ. 12:2)። ድል

ነሺ ወታደሮች እንድንሆን የሚያጠነክረን ጸጋ ነው (2ኛ ጢሞ. 2፡1)። አምላካችን የጸጋ ሁሉ አምላክ ነው (1ኛ ጴጥ. 5፡10)። ወደ ጸጋው ዙፋን በመቅረብ ለሚያስፈልገን ነገር ሁሉ ጸጋን ማግኘት እንችላለን (ዕብ. 4፡16)። «የጸጋው ቃል» (የሐዋ. 20፡32) የሆነውን መጽሐፍ ቅዱስን በምናነብበት ጊዜ፥ የጸጋው መንፈስ (ዕብ. 10፡29) በክርስቶስ ምን ያህል ባለጠጎች እንደ ሆንን ይገልጽልናል።

«እኛ ሁላችን ከሙላቱ ተቀብለን በጸጋ ላይ ጸጋ ተሰጥቶናል» (ዮሐ. 1፡16)።

የቱን ያህል ባለጠጎች ነን!!

ገላትያ 5፡13-26

ወንድሞች ሆይ፥ እናንተ ለአርነት ተጠርታችኋል፤ ብቻ አርነታችሁ ለሥጋ ምክንያትን አይስጥ፥ ነገር ግን በፍቅር እርስ በእርሳችሁ እንደ ባሪያዎች ሁኑ። ሕግ ሁሉ በአንድ ቃል ይፈጸማልና፥ እርሱም፦ ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ የሚል ነው። ነገር ግን እርስ በርሳችሁ ብትነካከሱና ብትበላሉ እርስ በርሳችሁ እንዳትጠፋፉ ተጠንቀቁ።

ነገር ግን እላለሁ፥ በመንፈስ ተመላለሱ፥ የሥጋንም ምኞት ከቶ አትፈጽሙ። ሥጋ በመንፈስ ላይ መንፈስም በሥጋ ላይ ይመኛልና፥ እነዚህም እርስ በርሳቸው ይቀዋወማሉ፤ ስለዚህም የምትወዱትን ልታደርጉ አትችሉም። በመንፈስ ብትመሩ ግን ከሕግ በታች አይደላችሁም። የሥጋ ሥራም የተገለጠ ነው እርሱም ዝሙት፥ ርኩሰት፥ መዳራት፥ ጣዖትን ማምለክ፥ ምዋርት፥ ጥል፥ ክርክር፥ ቅንዓት፥ ቁጣ፥ አድመኛነት፥ መለያየት፥ መናፍቅነት፥ ምቀኝነት፥ መግደል፥ ስካር፥ ዘፋኝነት፥ ይህንም የሚመስል ነው። አስቀድሜም እንዳልሁ፥ እንደዚህ ያሉትን የሚያደርጉ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም። የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግሥት፥ ቸርነት፥ በጎነት፥ እምነት፥ የውሃት፥ ራስን መግዛት ነው። እንደዚህ ያሉትን የሚከለክል ሕግ የለም። የክርስቶስ ኢየሱስም የሆኑቱ ሥጋን ከክፉ መሻቱና ከምኞቱ ጋር ሰቀሉ።

በመንፈስ ብንኖር በመንፈስ ደግሞ እንመላለስ። እርስ በርሳችን እየተነሣሣንና እየተቀናናን በከንቱ እንመካ።

- 10 -

አምስተኛው ነፃነት

ፕሬዝዳንት ፍራንክሊን ዲ ሩዝቬልት፥ ጥር 6 ቀን 1941 ዓ.ም. ለምክር ቤቱ ባደረጉት ጠቃሚ ንግግር ላይ ከጦርነቱ ፍጻሜ በኋላ እንዲኖር ስለሚመኙት ዓለም የነበራቸውን ራእይ ሲያካፍሉ፥ ሰዎች ሁሉ ሊለማመዷቸውና ሐሴት ሊያደርጉባቸው ስለሚገባ አራት መሠረታዊ ነፃነቶች ተናግረው ነበር። እነዚህም፥ የንግግር ነፃነት፥ የአምልኮ ነፃነት፥ የመሠረታዊ ፍላጎት ነፃነትና ከፍርሃት ነፃ መሆን ናቸው። እነዚህ ነፃነቶች በ1941 ዓ.ም. ከነበሩበት ሁኔታ ይልቅ አሁን በተሻለና በላቀ ደረጃ ተግባራዊ ሆነዋል። ዓላማችን ግን ሌላ አምስተኛ ነጻነትን ትፈልጋለች። ሰው ከራሱና ከጨካኙ የኃጢአት ተፈጥሮው ቀንበር ነጻ መሆን ያስፈልገዋል።

ሕግ አክራሪዎች ከሕጎችና ከማስጠንቀቂያዎች ሥር ላሉ ችግሮች መፍትሔ እንዳላቸው ይናገራሉ። ጳውሎስ ግን ማንኛውም ሕግ የሰውን መሠረታዊ የኃጢአት ተፈጥሮ መለወጥ እንደማይችል ይገልጻል። ለውጥ የሚያመጣው ከውጭ ያለ ሕግ ሳይሆን ከውስጥ ያለ ፍቅር ነው። ከውስጣችን የሚመነጭ ሌላ ኃይል ያስፈልገናል። ይህ ኃይል የሚመጣው ከእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ነው።

መንፈስ ቅዱስ በገላትያ መጽሐፍ ቢያንስ 14 ጊዜ ያህል ተጠቅሷል። በክርስቶስ ስናምን መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን ለማደር ይመጣል (3:2)። እንደ ይስሐቅ ሁሉ የተወለድነው በመንፈስ ነው (4:29)። ለደኅንነታችን ዋስትና የሚሰጠን በውስጣችን ያለው መንፈስ ሲሆን (4:6) ለክርስቶስ እንድንኖርና እርሱን እንድናከብር የሚያስችለን መንፈስ ቅዱስ ነው። መንፈስ ቅዱስ የመለኮታዊ ኃይል ተጽዕኖ ብቻ ሳይሆን እንደ አብና ወልድ መለኮታዊ አካል ነው። እግዚአብሔር አብ ያቀደልህንና እግዚአብሔር ወልድ በመስቀል ላይ ያደረገልህን፥ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ደግሞ በግል ሕይወትህ ውስጥ ተግባራዊ ያደርግልሃል።

ከገላትያ መጽሐፍ የመዝጊያ ክፍል ውስጥ እጅግ አስፈላጊ የሆነው አንቀጽ ይህ ነው። ምክንያቱም ጳውሎስ አንድ አማኝ በክርስቶስ ባገኘው

ነፃነት ሐሴት እንዲያደርግ መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠውን ሦስት አገልግሎቶች የገለጸው በዚህ ክፍል ነው።

1. መንፈስ ቅዱስ የፍቅርን ሕግ እንድንፈጽም ያስችለናል (5፡13-15)

የእኛ ዝንባሌ በያዝናቸው ጉዳዮች ላይ በአንድ አቅጣጫ ርቆ መሄድ ነው። አንዳንድ አማኝ ነፃነትን በተሳሳተ መልኩ ስለሚረዳው የፈለገውን ሁሉ ማድረግ እንደሚችል ያስባል። ሌላው አማኝ ደግሞ ይህንን ስህተት በመመልከት በሰዎች ሁሉ ላይ ሕጎችን ይጭናል፤ እንዲፈጽሙአቸውም ያስገድዳል። እውነተኛው ክርስቲያናዊ ነፃነት የሚገኘው እንደ ልብ በመኖርና በሕግ አክራሪነት መካከል ባለው ሚዛናዊ በሆነ ነጥብ ላይ ነው።

ስለዚህ ጳውሎስ ጥሪያችንን በመግለጽ ይጀምራል። የተጠራነው ወደ ነጻነት ነው። ክርስቲያን በቅድሚያ የእግዚአብሔርን ይቅር ባይነት ስለ ተለማመደ በኃጢአት ተጠያቂ ከመሆን ፍጹም ነፃ ነው። እንደዚሁም ክርስቶስ በመስቀል ላይ ስለ ሞተለት ከኃጢአት ቅጣት ነፃ ነው። ኃጢአት በዕለታዊ ሕይወቱ ከነበረው ኃይል በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ነፃ ሆኗል። ደግሞም ሕግ ከሚጠይቃቸው ጉዳዮችና ከማስፈራሪያዎቹ ሁሉ ነፃ ነው። ክርስቶስ የሕግን መርገም በመሸከሙ የሕግን ጨካኝ አገዛዝ ለአንዴና ለመጨረሻ አስወግዷል። የተጠራነው «በክርስቶስ ጸጋ» ስለ ሆነ ነፃነትን አግኝተናል (ገላ. 1፡6)። ጸጋና ነፃነት በአንድነት የሚሄዱ ጉዳዮች ናቸው።

ጳውሎስ ጥሪያችንን በሚገባ ካስረዳ በኋላ «አርነታችሁ ለሥጋ ምክንያት እንዳይሰጥ ተጠንቀቁ!» በማለት ያሳስባል።

የእግዚአብሔር ጸጋ እውነተኛ ትርጉም ያልገባቸው ሰዎች ሁሉ ፍርሃት ይህ መሆኑ የተረጋገጠ ነው። «ሕግጋትንና ደንቦችን ከተውን ሥርዓተ አልበኝነትንና ዐመፅን እንፈጥራለን» ይላሉ።

እንደዚህ አይነቱ አደጋ መኖሩ እርግጥ ነው። ምክንያቱ ግን የእግዚአብሔር ጸጋ ብቃት ስላጣ ሳይሆን ሰው ከእግዚአብሔር ጸጋ በመጉደሉ ሰው (ዕብ. 12፡15)። «እውነተኛ የእግዚአብሔር ጸጋ» ተብሎ የሚጠቀስ ነገር ካለ (1ኛ ጴጥ. 5፡12) ሐሰተኛ የሚባል የእግዚአብሔር ጸጋ ደግሞ አለ ማለት ነው። «የአምላክን ጸጋ በሴሰኝነት» ለመለወጥ የልቅነት ፈቃድ አድርገው (ይሁዳ 4) የሚጠቀሙበት ሐሰተኛ አስተማሪዎች አሉ።

ስለዚህ የጳውሎስ ማስጠንቀቂያ ዋጋ ያለው ነው። የክርስቲያን ነጻነት ኃጢአትን የማድረጊያ ፈቃድ ሳይሆን ሌሎችን ለማገልገል የሚያስችል ዕድል ነው።

ይህ ወደ አንድ ትእዛዝ ይመራናል፡- «በፍቅር እርስ በእርሳችሁ እንደ ባሪያዎች ሁኑ» (ገላ. 5፡13)። ቁልፍ ቃሉ ፍቅር መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን ቀመሩ የሚከተለውን ይመስላል፡-

ነፃነት + ፍቅር = ለሌሎች አገልግሎቶች ማበርከት

ነፃነት — ፍቅር = የልቅነት ፈቃድ (የኃጢአት ባርነት)

ካርል የተባለ ሰው ወደ ኩሽና እየገባ ለሚስቱ እንዲህ አላት፡- «በዚህ ሳምንት ተጨማሪ የእረፍት ቀን አለኝ። በዚህ ቀን የዶንን ቢስኪሌት ለማስተካከልና ላሪን ሲያወራው ወደ ነበረው ሙዚየም ይዤ በመሄድ ለማሳለፍ አስቤአለሁ።»

ሚስቱ ግን «አንድ ቢስክሌት ማስተካከልና ወደሙዚየም መሄድ የእረፍት ቀንን በደስታ የማሳለፊያ መንገድ አይመስለኝም» አለችው።

ካርል መልሶ «ልጆቹን ለሚውድ ሰው ይህ እጅግ ደስ የሚያሰኝ ነው» አላት።

ስለ ፍቅር ያለው አስደናቂ ነገር፥ እግዚአብሔር እስካሁን የሰጣቸውን ሕግጋት በሙሉ የሚያካትት መሆኑ ነው። «ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ» የሚለው ቃል በሰዎች ጎብረት ውስጥ የሚኖረውን ማንኛውንም ችግር ያቃልለዋል (ሮሜ 13፡8-14 ተመልከት)። ለክርስቶስ ካለህ ፍቅር የተነሣ ሰዎችን የምትወድ ከሆነ አትሰርቃቸውም፤ ስለ እነርሱ ሐሰተኛ ነገር አትናገርም፤ አትቀናባቸውም ወይም በምንም መንገድ የሚገዳቸውን ነገር አታደርግም። እግዚአብሔር ሕግንና ሕግ የሚያስከትላቸውን ማስፈራሪያዎች ሁሉ የተካው ከልብ በሚመነጭ ፍቅር ነው።

ልጆቻችን ትናንሾች በነበሩ ጊዜ የምንኖረው ተሽከርካሪዎች በሚበዙበት አውራ ጎዳና አጠገብ ነበር። ወደ መንገዱ አጠገብ ከደረሱ እንደምንቀጣቸው ያውቁ ነበር። እያደጉ በሄዱ ቁጥር ደግሞ መታዘዝ ሽልማትን እንደሚያስገኝ ተማሩ። ስለዚህ መታዘዝ ከቅጣት ለማምለጥ ብቻ ሳይሆን ደስታን ለማግኘት ጭምር እንደሚያስችል ተረዱ። ዛሬ የምንኖረው በጣም ሥራ የሚበዛባትና አደገኛ በሆነች ከተማ ነው። ከልጆቻችን አንዳንዶቹ መኪና ያሽከረክራሉ። ሆኖም አደጋ ላይ እንዳይወድቁ ልናባብላቸውም ሆነ ልናስፈራራቸው

አያስፈልገንም። ሕይወታቸውን የሚቀጣጠር በፍቅር ላይ የተገነባ ሥነ ሥርዓት ስላላቸው፥ ሆነ ብለው ራሳቸውንም ሆነ ወላጆቻቸውን ወይም ሌሎችን የሚጎዳ ተግባር አያደርጉም። ፍቅር ሕግን ተክቷል።

ጉዳዩን በከፍተኛ ደረጃ ስናየው በውስጣችን ያለው መንፈስ ቅዱስ የሚያስፈልገንን ፍቅር ይሰጠናል (ሮሜ 5፡5፤ ገላ. 5፡6፥22)። የገላትያ አማኞች ይህ አይነቱ ፍቅር ተለይቷቸው እርስ በርሳቸው «ሲነካከሱና ሲበላሉ» ስለ ነበር የመጠፋፋት አደጋ ላይ ነበሩ (ገላ. 5፡15)። በዚህ ቦታ በተምሳሌነት የቀረበው እርስ በርሳቸው የሚጠቃቁ አውሬዎች ሁኔታ ነበር። ይህ ራሱ ሕግ ሰዎች በአንድነት ተስማምተው እንዲሄዱ የማድረግ አቅም እንደሌለው ማረጋገጫ ነው። አንዲት ቤተ ክርስቲያን ምንም ያህል ሕግጋትንና መመዘኛዎችን ብታበጅ እነዚህ ነገሮች የመንፈሳዊነት ዋስትና አይደሉም። የእግዚአብሔር ቅዱስ መንፈስ ልባችንን በፍቅር እንዲሞላ ካልፈቀድን በስተቀር ስስታምነትና ባላንጣነት በመካከላችን ይነግሣል። በገላትያ አብያተ ክርስቲያናት የነበሩ አክራሪዎችም ሆኑ ሥርዓት አልበኞች የክርስቲያኖችን ጎብረት እያጠፉና እያበላሹ ነበር።

መንፈስ ቅዱስ የሚሠራው በባዶ ሜዳ አይደለም። በክርስቶስ እኛን ያንጽና ይገነባ ዘንድ በእግዚአብሔር ቃል፥ በጸሎት፥ በአምልኮና በአማኞች ጎብረት ይጠቀማል። በየዕለቱ የእግዚአብሔርን ቃል ለማንበብና ለጸሎት በቂ ጊዜ የሚመድብና ለመንፈስ ቅዱስ ሥራ ራሱን የሚሰጥ አማኝ በነጻነቱ ሐሴት በማድረግ ቤተ ክርስቲያንን ለመገንባት ታላቅ አስተዋጽኦ ያደርጋል። ጳውሎስ በጸጋ የመንፈሳዊ አገልግሎትና በሕግ የሥጋ አገልግሎት መካከል ስላለው ልዩነት የሰጠውን መግለጫ ከ2ኛ ቆሮ. 3 ላይ አንብብ።

2. መንፈስ ቅዱስ ሥጋን እንድናሸንፍ ያደርገናል (5፡16-21፥24)

አንዱ በሌላው ላይ ያለው ተቃውሞ (አምባጓሮ) (5፡16-17)፡- ይስሐቅና እስማኤል በአንድነት መኖር እንዳልቻሉ ሁሉ መንፈስና ሥጋ (አሮጌ ተፈጥሮ) እርስ በርሳቸው በተቃውሞና በጦርነት ላይ ናቸው። ጳውሎስ «ሥጋ» ሲል ውጫዊ አካላችንን ማለቱ እንዳይደለ የተረጋገጠ ነው። የሰው አካል ኃጢአተኛ አይደለም። ክፉ ወይም በጎ ሊደረግበት የሚችል መካከለኛ ነው። አካላችንን የሚቆጣጠረው መንፈስ ቅዱስ ከሆነ በመንፈስ እንመላለሳለን። አካላችንን የሚቆጣጠረው ግን ሥጋ ከሆነ በሥጋ ምኞትና

ፍላጎት እንመላለሳለን። በመንፈስና በሥጋ መካከል ያለው ተቃውሞ ምክንያት መንፈስና ሥጋ የተለያዩ ፍላጎቶች ያላቸው መሆናቸው ነው።

እነዚህ ተቃራኒ ፍላጎቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተለያዩ መንገዶች ተገልጸዋል። ለምሳሌ፡- በግ ቆሻሻ ነገሮችን የማይወድ ንጹህ እንስሳ ሲሆን፥ አሳማ ግን ከታጠበች በኋላ ወደ ጭቃ የምትመለስ ንጽሕናን የማትወድ ናት (2ኛ ጴጥ. 2፡19-22)። ዝናቡ መዝነቡን አቁሞ መርከቡ በሚገባ ተደላድሎ ከቆመ በኋላ ኖህ አንድ ቁራ ሰድዶ ነበር፤ ቁራው ግን አልተመለሰም (ዘፍ. 8፡6-7)። ቁራ ሥጋ በል እንደ መሆኑ በቂ ምግብ በማግኘቱ በዚያው ቀረ። ኖህ ከንጹሕ አእዋፍ አንዷ የሆነችውን እርግብን በለቀቀ ጊዜ ግን ተመልሳ መጣች (ዘፍ. 8፡8-12)። ለመጨረሻ በለቀቃት ጊዜ ግን አልተመለሰችም። ይህ ማለት ልታርፍበት የምትችልበት ደረቅ መሬት አገኘች ማለት ነበር። ስለዚህ ውኃው ቀንሶ ነበር።

አሮጌው ተፈጥሮአችን ሁልጊዜ ንጹሕ ያልሆነን ነገር ለምግብነት በሚፈልጉት አሳማና ቁራ ይመሰላል። አዲሱ ተፈጥሮአችን ደግሞ ንጹህና ቅዱስ የሆኑትን ነገሮች አጥብቀው እንደሚፈልጉት ርግብና በግ አይነት ነው። ስለዚህ በአማኙ ሕይወት ውስጥ ትግል ቢካሄድ ምንም አያስደንቅም። የማያምነው ሰው ግን መንፈስ ቅዱስ ስለሌለው (ሮሜ 8፡9) ስለዚህ ጦርነት የሚያውቀው አንዳችም ነገር አይኖርም። እስማኤል፥ ይስሐቅ እስከሚወለድ ድረስ አንዳችም ችግር አልፈጠረም ነበር።

ክርስቲያን ሥጋን ድል መንሣት የሚችለው ውሳኔ ስላደረገ ብቻ እንዳይደለ ልብ በል። «እነዚህም እርስ በርሳቸው ይቀዋወማሉ። ስለዚህም የምትወዱትን ልታደርጉ አትችሉም» (ገላ. 5፡17)። ጳውሎስ በሮሜ መጽሐፍ ውስጥ የሚናገረው ይህንኑ ችግር ነበር። «የማደርገውን አላውቅምና፤ የምጠላውን ያን አደርጋለሁና ዳሩ ግን የምወደውን እርሱን አላደርገውም።...የማልወደውን ክፉ ነገር አደርጋለሁና ዳሩ ግን የምወደውን በጎ ነገር አላደርገውም» (ሮሜ 7፡15፥19)። ጳውሎስ ድል መኖሩን አልካደም። በእነዚህ ጥቅሶች ያስተላለፈው መልእክት ይህንን ድል በራሳችን ብርታትና ፈቃድ ልናገኘው ያለመቻላችንን ነው።

ድሉ (5፡18)፡- የችግሩ መፍትሄ ፈቃዳችንን ከሥጋችን ፍላጎት ጋር ማዋጋት ሳይሆን ፈቃዳችንን ለመንፈስ ቅዱስ ማስገዛት ነው። የዚህ ቁጥር ቀጥተኛ ትርጉም «በፈቃዳችሁ በመንፈስ ቅዱስ ብትመሩ ከሕግ በታች አይደላችሁም» የሚል ነው። መንፈስ ቅዱስ በፍቅር እንድንታዘዘው

የእግዚአብሔርን ሕግ በልባችን ላይ ይጽፋል። (ዕብ. 10፡14-17፤ 2ኛ ቆሮ. 3 ተመልከት)። «አምላኬ ሆይ ፈቃድህን ለማድረግ ወደድሁ፤ ሕግህም በልቤ ውስጥ ነው» (መዝ. (40)፡8)። በመንፈስ ቅዱስ መመራትና «በመንፈስ መመላለስ» ለሥጋ ፈቃድ ራስን የመስጠት ተቃራኒ ነው።

መስቀሉ (5፡19-21፥24)፡- ጳውሎስ እጅግ መጥፎ የሆኑትን አንዳንድ የሥጋ ሥራዎች ይዘረዝራል። (በማር. 7፡20-23፤ ሮሜ 1፡29-32፤ 1ኛ ጢሞ. 1፡9-10፥ 2ኛ ጢሞ. 3፡2-5 ተመሳሳይ መዘርዝሮችን ታገኛለህ።) ሥጋ ኃጢአትን ማመንጨት እንጂ የእግዚአብሔርን ጽድቅ በፍጹም ሊያፈራ አይችልም። «የሰው ልብ ከሁሉ ይልቅ ተንኰለኛ እጅግም ክፉ ነው» (ኤር. 17፡9)። በገላትያ መጽሐፍ ውስጥ የተሰጠው መዘርዝር በሦስት ዋና ክፍሎች ሊከፈል ይችላል።

(1) የፍትወት ኃጢአቶች (5፡19፥21)

ማመንዘር ባገቡ ሰዎች መካከል የሚደረግ ሕጋዊ ያልሆነ ወሲብ ሲሆን ዝሙት ግን ባላገቡ ሰዎች መካከል የሚደረግ ወሲብ ነው። ርኩሰት፥ አንድን ሰው እንዲረክስ የሚያደርገው የልብና የአእምሮ እድፈት ነው። ለርኩስ ሰው ሁሉም ነገር የሚታየው ቆሻሻ መስሎ ነው (ቲቶ 1፡15 ተመልከት)። መዳራት በሥነ ምግባር ዝቅተኛነት የተነሣ ዝሙት ማብዛት ሲሆን ምንም ዓይነት ኀፍረት የማያሳይ ልቅ ፍላጎት ነው። እነዚህ ኃጢአቶች በሙሉ በሮም መንግሥት ግዛት ውስጥ ከቁጥጥር ውጭ እንደ ነበሩ የታወቀ ነው። ስካርና ዘፋኝነት ማብራሪያ የሚያስፈልጋቸው አይደሉም።

(2) የጣዖት አምልኮ ኃጢአቶች (5፡20)

ጣዖትን ማምለክ ከላይ እንደ ተገለጹት ኃጢአቶች ዛሬም ከእኛ ጋር አለ። ጣዖትን ማምለክ በቀላል አባባል አንዳንድ ነገሮችን ከእግዚአብሔርና ከሰው ማስቀደም ነው። እግዚአብሔርን ማምለክ፥ ሰዎችን መውደድና በነገሮች መጠቀም ኃላፊነታችን ነው። እኛ ግን ብዙ ጊዜ ሰዎችን እንጠቀምባቸዋለን፤ ራሳችንን እንወዳለን፤ ነገሮችን እናመልካቸዋልን። እግዚአብሔርን ሙሉ በሙሉ ከጉዳያችን እናስወጣዋለን። ኢየሱስ የምናመልከውን እንደምናገለግል ተናግሯል (ማቴ. 4፡10)። ክርስቶስን ከማገልገል ይልቅ ለመኪናው፥ ለቤቱ፥ ወይም ለጀልባው ቅድሚያ የሚሰጥ ክርስቲያን ጣዖትን ወደማምለክ አደጋ ላይ ይገኛል (ቆላ. 3፡5)።ፉርማኪያ ከሚለው የግሪክ ቃል የተገኘው ጥንቆላ ወይም ምዋርት የሚለው ቃል

«መድሃኒቶችን መጠቀም» ማለት ነው። ፋርማሲ የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል የተገኘውም ከዚህ ነው። በጳውሎስ ዘመን የነበሩ ምዋርተኞች ክፉ የሆነ ተግባራቸውን ለመፈጸም ብዙ ጊዜ የሚጠቀሙት በመድኃኒቶች ነበር። በእርግጥ ጥንቆላ ወይም ምዋርት እንደ ሌሎች የአስማት ተግባራት ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተከለከለ መሆኑ ተገልጿል (ዘዳ. 18:9-22)።

(3) ማኅበረሰባዊ ኃጢአቶች (5:20-21)

ጥላቻ «ጠላትነት» ሌሎችን የማንቋሸሽና የመናቅ የአእምሮ ዝንባሌ ነው። ይህ ዝንባሌ የጠላትነት ተግባራዊ መግለጫ ወደሆነው ልዩነትና ሁከት ያመራል። ቅንዓት ቀናተኛነት ወይም ባላንጣነት ነው። ክርስቲያኖች እርስ በርስ ሲፎካከሩና በሌሎች ፊት አንዱ ሌላውን መጥፎ አድርጎ ሲያቀርብ ማየት እንዴት የሚያሳዝን ነው! ቁጣ የስሜት መግንፈልን የሚያሳይ ሲሆን፥ አድመኛነት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መከፋፈልን የሚፈጥር፥ ለራስ ብቻ የመስገብገብን ፍላጎት ያንጸባርቃል።

መለያየትና መናፍቅነት ተወራራሽ ቃሎች ናቸው። የመጀመሪያው የመከፋፈል አሳብ ያለው ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በድርጅታዊ መንፈስ የሚፈጠር የቡድን አሠራርን ያንጸባርቃል። ስለዚህ መከፋፈልና መለያየት የሚሉት ቃሎች የተሻሉ ትርጉሞች ናቸው። እነዚህ ሁለቱም ባሕሪያት ጌታን ሳይሆን እነርሱን እንድንከተላቸው አጥብቀው የሚጎተጉቱና ራሳቸውን የሚያስተዋውቁ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ተግባር ውጤቶች ናቸው። (መናፍቅነት ተብሎ የተተረጎመው ሄሪሲ የሚለው የግሪክ ቃል ምርጫን ማድረግ ማለት ነው።) ምቀኝነት የሚለው ቃል ቂም መያዝን የሚያመለክት ሲሆን የሌላን ሰው ንብረት በጥብቅ መፈለግ ማለት ነው (ምሳ. 14:30)። መግደልና ስካር ተጨማሪ ማብራሪያ አያስፈልጋቸውም።

እነዚህን ኃጢአቶች የሚለማመድ ሰው የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርስም። ጳውሎስ የሚናገረው ስለ ኃጢአት ተግባር ሳይሆን ስለ ኃጢአት ልማድ ነው። በእግዚአብሔር ቃል ላይ ያልተመሠረተ ሐሰተኛ የደህንነት ዋስትና አለ። አማኝ ከጸጋ እንጂ ከሕግ በታች ያለመሆኑ እውነታ ኃጢአት ለመሥራት ምክንያት ሊሆን የሚችል አይደለም (ሮሜ 6:15)። ይልቁኑ ጌታን በመታዘዝ መኖር ለራስ ብርታት መጨመር ነው።

እንደነዚህ አይነት አስቸጋሪ ኃጢአቶች የማስገኘት ችሎታ ያለው አሮጌው የኃጢአት ተፈጥሮ አንድ አማኝ እንዴት ሊቋቋመው ይገባል? ሕግ

አሮጌውን ተፈጥሮ ሊለውጥ ወይም ሊቆጣጠር አይችልም። አሮጌው ተፈጥሮ መሰቀል አለበት! (ገላ. 5:24)። ጳውሎስ አማኝ ክርስቶስን በሞቱ፥ በመቀበሩና በመነሣቱ እንደሚመስለው ይገልጻል(ሮሜ 6)። ክርስቶስ ለእኔ ሞቷል፤ እኔ ደግሞ ከእርሱ ጋር ሞቼአለሁ። ክርስቶስ ለእኔ የሞተው የኃጢአቴን ቅጣት ሊያስወግድልኝ ነው፤ እኔ ግን ከክርስቶስ ጋር የሞትሁ የኃጢአትን ኃይል ለመስበር ነው።

ጳውሎስ ይህንን ጉዳይ በገላትያ 2:19-20 ቀደም ብሎ የገለጸው ሲሆን በ6:14 ደግሞ እንደገና ያነሣዋል። የሚነግረን ራሳችንን ከመስቀል ላይ በመቸንከር እንድንሰቅል አይደለም፤ ምክንያቱም ይህ የማይቻል ነው። (አንድ ሰው በራሱ ላይ ሊፈጽማቸው ከማይችላቸው የሞት ተግባራት አንዱ መስቀል ነው።) ጳውሎስ የሚነግረን የሥጋ መሰቀል አንድ ጊዜ ያለቀና የተፈጸመ ጉዳይ መሆኑን ነው። የእኛ ኃላፊነት ይህን አምኖ መራመድ ነው። (በሮሜ 6 ላይ ጳውሎስ ይህንን መቍጠር ይለዋል። ይህንኑ እውነት በቆላ. 3:5-25 ቀርቦ ትመለከታለህ)።

እኔና አንተ የመንፈስ እንጂ የሥጋ ባለዕዳ አይደለንም (ሮሜ 8:12-14)። እግዚአብሔር ስለ አሮጌው ተፈጥሮ የሚለውን ነገር መቀበል አለብን እንጂ ያልሆነውን ነው ብለን ማመን የለብንም። ማንኛውንም ምኞቱን እንዲፈጽም ደስ የሚያሰኘውን ሁሉ በመመገብ ለሥጋ ማሰብ፥ መጨነቅ የለብንም (ሮሜ 13:14)። በሥጋ ምንም በጎ ነገር የለም (ሮሜ 7:18)። ስለዚህ በሥጋ መታመን የለብንም (ፊልጵ. 3:3)። ሥጋ ለእግዚአብሔር ሕግ ሊገዛ (ሮሜ 8:7)፥ እግዚአብሔርን ደስ ሊያሰኝ (ሮሜ 8:8) አይችልም። ሥጋ በሰውነታችን የሚሠራውን ሥራ ልንገድል የምንችለው በመንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው (ሮሜ 8:13)። መንፈስ ቅዱስ የሕይወት መንፈስ ብቻ አይደለም (ሮሜ 8:2፤ ገላ. 5:25)፤ የሞት መንፈስም ነው። ራሳችንን ለኃጢአት እንደ ሞትን አድርገን እንድንቆጥር ይረዳናል።

እስካሁን የእግዚአብሔርን መንፈስ ሁለት አገልግሎቶች ተመልክተናል። እነዚህም የፍቅርን ሕግ እንድናሟላና ሥጋን እንድናሸንፍ ማስቻል ናቸው። መንፈስ ቅዱስ ሦስተኛ አገልግሎትም አለው።

3. መንፈስ ቅዱስ ፍሬ እንድናፈራ ያስችለናል (5፡22-23፥ 25-26)

ሥጋን በግሽንፍ ክፉ ነገርን ያለመፈጸም አንድ ነገር ሲሆን መልካም ነገርን ግድረግ ግን ጨርሶ የተለየ ነገር ነው። አንድ ሕግ አክራሪ ሰው በዝሙት ወይም በነፍሰ ገዳይነት ተጠያቂ ላይሆን ይችላል (ማቴ. 5፡21-32 ተመልከት)። ነገር ግን እጅግ ውብ የሆኑትን የመንፈስ ቅዱስ ጸጋዎች በሕይወቱ ግየት ይቻላልን? አሉታዊ የሆኑ በጎ ነገሮች በአንድ ሰው ሕይወት ውስጥ መኖራቸው በቂ አይደለም፤ አዎንታዊ ብቃቶችም ሊኖሩት ይገባል።

በሥራና በፍሬ መካከል ያለውን ንጽጽር መመልከት አስፈላጊ ነው። በአንድ ፋብሪካ ውስጥ ያለው ማሽን በመሥራቱ የፋብሪካ ውጤቶችን ያስገኛል እንጂ አንዲት የፍሬ ዘለላ እንኳን ግምረት ጨርሶ አይችልም። ፍሬ ሕይወት ካለው ነገር ሊያድግ የሚገባው ነው። ይህም ከአግኙ አንጻር ሲታይ የመንፈስ ሕይወት ነው (ገላ. 5፡25)። «ሥራዎችን» ስናስብ ጥረትን፥ ድካምን፥ ውጥረትንና ልፋትን እናስባለን። «ፍሬን» በምናስብበት ጊዜ ደግም ውበትን፥ ጸጥታንና የሕይወትን መገለጥ እናስባለን። ሥጋ የሚያመርተው «የሞቱ ሥራዎችን» ሲሆን (ዕብ. 9፡14) መንፈስ ግን ሕያው ፍሬን ያፈራል። ይህ ፍሬ በውስጡ የበለጠ ፍሬን የሚሰጥ ዘር አለው (ዘፍ. 1፡11)። ፍቅር የበለጠና የተሻለ ፍቅርን ይሰጣል፤ ደስታ ደግሞ የበለጠ ደስታን ያመጣል። የኢየሱስ ትኩረት «ፍሬ የሚያፈራ... አብዝቶ እንዲያፈራ... ደግሞም ብዙ ፍሬ እንዲያፈራ» ነው (ዮሐ. 15፡2፥5)። ምክንያቱም እግዚአብሔርን የምናከብርበት መንገድ ይህ ነው። አሮጌው ተፈጥሮ ፍሬን ማፍራት አይችልም፤ ፍሬን ማፍራት የሚችለው አዲሱ ተፈጥሮ ብቻ ነው።

አዲስ ኪዳን ስለ በርካታ የተለያዩ ፍሬዎች ይነግረናል፤ ከእነዚህም ሰዎችን ለክርስቶስ መግረክ (ሮሜ 1፡13)፥ ቅዱስ አኗኗር (ሮሜ 6፡22)፥ ለእግዚአብሔር ስጦታዎችን ማቅረብ (ሮሜ 15፡26-28)፥ መልካም ሥራዎች (ቆላ. 1፡10)፥ ምስጋና (ዕብ. 13፡15)። በዚህ ክፍል የተዘረዘረው «የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ» ከባሕርይ ጋር የተያያዘ ነው (ገላ. 5፡22-23)። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ በሆነው በደኅንነትና (የሐዋ. 2፡38፤ 11፡17) ከአገልግሎት ጋር በተያያዙ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች

(1ኛ ቆሮ. 12)፥ ከክርስቲያን ባሕርይ ጋር ከተያያዙ የመንፈስ ጸጋዎች ግልጽ ልዩነት መኖሩን መረዳት በጣም አስፈላጊ ነው። አንዳንድ ክርስቲያኖች በስጦታዎቹ ላይ ከሚገባ በላይ በማተኮር የመንፈስን ጸጋዎች ናቅ አድርገው ወይም ቸል ብለው መመልከታቸው የሚያሳዝን ነው። ችሎታዎችን ከማሳየት ይልቅ እውነተኛውን የክርስቲያን ባሕርይ መገንባት መቅደም ያለበት ጉዳይ ነው።

እግዚአብሔር በሕይወታችን የሚፈልጋቸው ባሕርያት በዘጠኙ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች ውስጥ ይታያሉ። ጳውሎስ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬን ገለጻ ከፍቅር ይጀምራል፤ ምክንያቱም የቀሩት ፍሬዎች በሙሉ ከፍቅር የሚወጡ ናቸው። የቀሩትን ስምንት ፍሬዎች በቆሮንቶስ ውስጥ ከሚገኙ የፍቅር ባሕርያት ጋር አወዳድር (1ኛ ቆሮ. 13፡4-8 ተመልከት)። በዚህ ክፍል ፍቅርን ለመግለጽ አገልግሎት ላይ የዋለው የግሪክ ቃል «አጋፔ» የሚል ሲሆን ትርጉሙ መለኮታዊ ፍቅር ማለት ነው። (ትርጉሙ «ስሜታዊ ፍቅር የሆነው» «ኤሮስ» የሚለው የግሪኩ ቃል ግን በአዲስ ኪዳን ጨርሶ ጥቅም ላይ አልዋለም።) ይህ መለኮታዊ ፍቅር እግዚአብሔር ለእኛ የሰጠው ስጦታ ሲሆን (ሮሜ 5፡5) ልናሳድገውና ይበዛልን ዘንድ ልንጸልይ ይገባል (ፊልጵ. 1፡9)።

አንድ ሰው በፍቅር ክልል ውስጥ በሚኖርበት ጊዜ፥ ሰውጫዊ ሁኔታዎች ላለመናወጥ ብቃት ያለውን ውስጣዊ ሰላምና ደስታ ይለማመዳል። (ጳውሎስ በፊልጵ. 4፡10-20 የጻፈው ልምምድ እንዲህ እይነት ጉዳይ ነው።) ይህ «የተቀደሰ በጎ አሳብ» በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ እንኳ እንዲጓዝ አስችሎታል። ፍቅርና ደስታ በአንድነት ሰላምን ይፈጥራሉ። ይህም «አእምሮን ሁሉ የሚያልፍ የእግዚአብሔር ሰላም ነው (ፊልጵ. 4፡7)። እነዚህ የመጀመሪያዎቹ ሦስቱ የሕይወት ብቃቶች ክርስቲያናዊው ሕይወት ወደ አምላኩ ለመቃረብ እያዘነበለ ለመሆኑ ማስረጃዎች ናቸው።

የሚቀጥሉት ሦስቱ ደግሞ የክርስቲያናዊውን ሕይወት ሰብአዊ ዝንባሌ ገጽታ የሚያሳዩ ናቸው። እነዚህም ትዕግሥት (አንድን ዓላማ ሳይሰለቹና ሳያቋርጡ በብርታት ከግቡ ማድረስ)፥ ቸርነት (የውሃት) እና በጎነት (በተግባር የተገለጠ ፍቅር) ናቸው። ትዕግሥት ያለው ክርስቲያን በቀልን አያደርግም ወይም በሚቃወሙት ላይ ክፉ ነገር እንዲመጣ አይመኝም። እጅግ እንዲቀየም በሚያደርገው ነገር ውስጥ እንኳ ደግና የዋህ ይሆናል። ሌሎች ክፉ በዘሩበት ቦታ ሁሉ በጎነትን ይዘራል። የሰው ተፈጥሮ በራሱ ይህንን

ሊያደርግ ፈጽሞ አይችልም። ይህን ማድረግ የሚችለው መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው።

።ወደ የሚጨረሻዎቹ ጽዕቱ ብቃቶች ደግሞ በግል ራሱን የሚመለከቱ ናቸው፤ እሾሆች (ችግሮችንና ሊደገፉበት የሚችሉት አደገኛ ሰው መሆን)፥ የውሃት (ኃይልንና ሥልጣንን በትክክለኛ መንገድ መጠቀም፥ ከቁጥጥር ሥር ያዋለ ኃይል)ና ራሰን መግዛት ናቸው። የውሃትነቱ ይካሜነት አይደለም። ሊየሱስ ያንኑ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝ» አለ (ማቴ. 11፡28)። ሙሴም እጅግ የዋህ ሰው ነበር (ዘኁ. 12፡3)። ይሁን እንጂ ግንም ግን ደካማ ሊሉት አይችልም። የዋህ ክርስቲያን ወለዋይ ወይም ሐሳብ ግትር አይደለም። ዮበብ ግለት እውቀትን በትክክለኛ መንገድ መጠቀም ማለት እንደ ሆነ ሁሉ የውሃትም ማለት ሥልጣንና ኃይልን በትክክለኛ መንገድ መጠቀም ማለት ነው።

ሰርጌው ተፈጥሮ ከመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች አንዳንዶቹን ሊያስመስል ይችላል፤ ሆኖም ግን የመንፈስ ፍሬዎችን ሊያፈራ ፈጽሞ አይችልም። አንዱ ልዩነቷ የሚከተለው ነው፤ በአንድ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ መንፈስ ፍሬን በሚያፈራበት ጊዜ እግዚአብሔር ክብርን ሲያገኝ ክርስቲያኑ ግን ስለ ጥረቷ ያገኘው ጥቅም አይታወቀውም። ሥጋ በተግባር በሚገለጥበት ጊዜ ግን ገዐሰዜ ቦዊ ስዜ ሩሱ ይታበያል። ሌሎች ሲያመሰግኑት ደስ ይለዋል። የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ሊሰው ጮስጋ ሳይሆን ለእግዚአብሔር ክብር ይሆን ዘንድ ያበለጥ ክርስቶስን እንድንመስል ግድረግነው።

ሚሀፍራን ክቲኩታ ግሳይሚ ሕጅግ ኤስፈሊጊ ነው። ጳውሎስ ፍሬው ለማደግ ይሾል ዘንድ ሪዬሱ የአካባቢ ሁኔታ እንደሚያስፈልገው አስገንዝቧል (ቆላ. 2፡6-7)። ሙሉ በሙሉ ሞኖ የአካባቢ አየር ሁኔታ ግደግ እንደማይሾል ሁሉ፥ የመንፈስ ፍሬም በእያንዳንዱ ሰው ሕይወት ወይም በአያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሊሰኖር አይችልም።

ጋጽ ዋሲሲ የሚለድ፱ቋ ሥንፈስና ቃሉ ተስረፍ፱ፈው ባሉበት ነው። «በመንፈስ ተሞላ» (ቁ. 18) ማለት «የመንፈስን ኦርምጃ ተከትሎ ዚሱን ቋሚ ከሚመንፈስ ቃለ ሞቅደም ወደ ኃላም አለመቅረት ማለት ነው። ዩሀ ፆሌንሚኖናስን፥ ዲሉቲን፥ ኦምልኩን፥ ምስጋናንና ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር ያለ ኅብረትን የሚጠይቅ ነው። የቃሉ ዘር ሥር ሰዶ ፍሬን ይሰጥ ዘንዴ በቤቴ ሥለሆነ ሥንቀልን» ሁሉ ይጨምራል። የደሀዲትቱ አቀንቃኞች ለምስጋናና «ከንቱ ለሆነ ክብር» የሚንጉ ነበሩ። ይህም ወደ

ውድድርና መከፋፈል መራ። በዚህ አይነት ሁኔታ ውስጥ ፍሬ ሊያድግ ጨርሶ አይችልም።

ይህ ፍሬ የተመረተው ለውበቱና ለአይታ ማራኪነቱ ሳይሆን እንዲበላ ነው። በዙሪያችን ያሉ ሰዎች የፍቅር፥ የደስታ፥ የሰላምና የቀሩት የመንፈስ ጸጋዎች ረሃብተኞች ናቸው። እነዚህን ነገሮች በሕይወታችን ሲያዩ ክእነርሱ ሕይወት የሚጎድል ነገር እንዳለ ይረዳሉ። ፍሬ የምናፈራው እኛው እንድንጠቀምበት ሳይሆን ሌሎች እንዲመገቡትና እርዳታን እንዲያገኙ ነው። በዚህም እግዚአብሔር እንዲከበር ነው። ምናልባትም ሥጋ በሕይወታችን ምስጋናን የሚያስገኙ «ውጤቶችን» ሊያመጣልን ይችላል። ነገር ግን ለእግዚአብሔር ክብርን ሊያመጣ የሚችል ፍሬን ሊያፈራ አይችልም። ይህ ትዕግሥትን፥ በመንፈስ መኖርን፥ በብርሃን መራመድን፥ የእግዚአብሔርን ቃል ዝርና ክርስቶስን የማክበር እውነተኛ ፍላጎትን ይጠይቃል።

በአጭሩ ለዚህ ሁሉ ምስጢሩ መንፈስ ቅዱስ ነው። ከኃጢአትና ከራስ ነጻ መውጣት የሆነውን «እምስተኛውን ነፃነት» ሊሰጠን የሚችል እርሱ ብቻ ነው። የፍቅርን ሕግ እንድንፈጽም፥ ሥጋን እንድናሸንፍና ፍሬ እንድናፈራ ያስችለናል።

ታዲያ ራስህን ለእርሱ በመስጠት እንዲሠራ ተፈቅድለታለህን?

ገላትያ 6፡1-10

ወንድሞች ሆይ፥ ሰው በማናቸውም በደል ስንኳ ቢገኝ፥ መንፈሳዊያን የሆናችሁ እናንተ እንደዚህ ያለውን ሰው በየውሃት መንፈስ አቅኑት፤ አንተ ደግሞ እንዳትፈተን ራስህን ጠብቅ። ከእናንተ እያንዳንዱ የአንዱን ሸክም ይሸከም እንዲሁም የክርስቶስን ሕግ ፈጽሙ። አንዱ ምንም ሳይሆን ምንም የሆነ ቢመስለው ራሱን ያታልላልና። ነገር ግን እያንዳንዱ የገዛ ራሱን ሥራ ይፈትን፥ ከዚያም በኋላ ስለ ሌላው ሰው ያልሆነ ስለ ራሱ ብቻ የሚመካበትን ያገኛል፤ እያንዳንዱ የገዛ ራሱን ሸክም ሊሸከም ነውና።

ነገር ግን ቃሉን የሚማር ከሚያስተምረው ጋር መልካምን ነገር ሁሉ ይከፋፈል።

አትሳቱ፤ እግዚአብሔር አይዘበትበትም። ሰው የሚዘራውን ሁሉ ያንኑ ደግሞ ያጭዳልና፤ በገዛ ሥጋው የሚዘራ ከሥጋ መበስበስን ያጭዳልና፥ በመንፈስ ግን የሚዘራው ከመንፈስ የዘላለምን ሕይወት ያጭዳል። ባንዝልም በጊዜው እናጭዳለንና መልካም ሥራን ለመሥራት አንታክት። እንግዲያስ ጊዜ ካገኘን ዘንድ ለሰው ሁሉ ይልቁንም ለሃይማኖት ቤተ ሰዎች መልካም እናድርግ።

- 11 -

የፍቅር ነፃነት

«ሳልቬሽን አርሚ» የሚባለው ድርጅት መሥራች ጄኔራል ዊሊያም ቡዝ፥ በአንድ ዓለም አቀፍ ጉባኤ ላይ በሕመም ምክንያት ለመገኘት ባለመቻላቸው ስለ ላኩት መልእክት ብዙ ጊዜ የሚነገር አንድ ታሪክ አለ። ይኸውም ለጉባኤው ተወካዮች በስልክ ያስተላለፉት መልእክት ነው። መልእክቱ «ሌሎችን» የሚል አንድ ቃል ብቻ ነበር።

«ፒናትስ» በተሰኘ በአንድ የኩምክና ፊልም ውስጥ ሉሲ የተባለች ሴት ቻርሊ ብራውን የተባለውን ሰው «እዚህ ምድር ላይ ያለነው ለምንድን ነው?» ብላ ትጠይቀዋለች። እርሱም «ሌሎችን ለማስደሰት ነው» ብሎ ይመልስላታል። እርሷም ስለ መልሱ ለጥቂት ጊዜ ያህል ካሰበች በኋላ «ለካስ ሌሎቹስ በዚህ ምድር ያሉት ለምንድን ነው?» ብላ ደግማ ትጠይቀዋለች።

በክርስቲያን የቃላት ዝርዝር ውስጥ ቁልፍ ከሆኑ ሐረጎች አንዱ «እርስ በርሳችሁ» የሚለው ነው። «እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ» የሚለውን ትእዛዝ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ብቻ ከአሥራ ሁለት ጊዜያት በላይ ተጠቅሶ እናገኘዋለን። «እያንዳንዱ ስለ ሌላው ይጸልይ» (ያዕ. 5፡16)፥ «እርስ በእርሳችሁ ተመካከሩ» (1ኛ ተሰ. 5፡11)፥ «እርስ በርሳችሁ ተከባበሩ» (ሮሜ 12፡10)፥ «እርስ በርሳችሁ እንግድነት ተቀባበሉ» (1ኛ ጴጥ. 4፡19) የሚሉት ከሌሎች በርካታ ተመሳሳይ ምክሮች ጥቂቶቹ ናቸው።

በዚህ በምንመለከተው ክፍል ደግሞ ጳውሎስ «አንዱ የሌላውን ሸክም ይሸከም» የሚል ሐረግ ይጨምራል (ገላ. 6፡2)። በመንፈስ ቅዱስ የሚመራ ክርስቲያን ሌሎች ወገኖችን እንዴት ሊያገለግላቸው እንደሚገባ በጥብቅ ያሳስበዋል። በዚህ ክፍል ውስጥ ጳውሎስ ከሌሎች ጋር ልንካፈለው ስለሚገባ ሁለት እጅግ ጠቃሚ አገልግሎቶች ይገልጽልናል።

1. ሸክም መሸከም (6፡1-5)

ሕግ አክራሪዎች ሸክም የመሸከም ፍላጎት የላቸውም። በዚህ ምትክ በሌሎች ላይ ሸክምን ይጭናሉ (የሐዋ. 15፡10)። ኢየሱስ በኖረበት ዘመን የነበሩት ፈሪሳውያን አንዱ ኃጢአት ይህ ነበር። «ከባድና አስቸጋሪ ሸክም

ተብትበው በሰው ትከሻ ይጭናሉ፤ እነርሱ ግን በጣታቸው ስንኳ ሊነኩት አይወዱም» (ማቴ. 23፡4)። ሕግ አክራሪዎች ሁልጊዜ ከራሳቸው ይልቅ በሌሎች ላይ ይጠነክራሉ። በመንፈስ የሚመራ ክርስቲያን ግን ሌሎችን መርዳት እንዲችል ከሌሎች ይልቅ የበለጠ መሥዋዕት ለመክፈል ፈቃደኛ ነው።

ጳውሎስ በድንገት ተሰናክሎ በኃጢአት ውስጥ የወደቀን አንድ ሰው ተምሳሌታዊ ታሪክ ያቀርባል። «ቢወድቅ» የሚለው ቃል ዱብ ዕዳን የሚያመለክት ስለ ሆነ አውቆ አለመታዘዝ አይደለም። ጳውሎስ ይህን መግለጫ የተጠቀመው ለምንድን ነው? ምክንያቱም የሕግ አክራሪዎችን ክፋት ለመግለጽ ኃጢአት በሠሩ ሰዎች ላይ የሚወስዱትን የከፋ እርምጃ ከግጋለጥ የበለጠ ሌላ ግስረጃ ባለመኖሩ ነው። እዚህ ላይ አንዲት አመንዝራ ሴትን ይፈርድባት ዘንድ ወደ ኢየሱስ እየጎተቱ ፈሪሳውያን እንዳመጧት አስታውስ (ዮሐ. 8)፤ ወይም አሕዛብን ወደ ቤተ መቅደስ በማስገባቱ ቤተ መቅደሱን አርክሰሃል ብሎ ጳውሎስን ለመግደል ብጥብጥ ያስነሣውን የአድማ ቡድን አስታውስ (የሐዋ. 21፡27-40)። (ሕግ አክራሪዎች የሚፈልጉት እውነትንና ማስረጃን ሳይሆን ጥርጣሬንና አሉባልታን ነው። የቀረውን የሚያደርገው ተመጻዳቂው ግምታዊ አስተሳሰባቸው ነው።) ስለዚህ በዚህ አንቀጽ ውስጥ ጳውሎስ የሚያነጻጽረው አንድ የተሳሳተ ወንድምን መንፈሳዊ ሰውና ሕግ አክራሪ ሰው እንዴት እንደሚያስተናግዱት ነው።

(1) የአላማ ንጽጽር፡- መንፈሳዊው ሰው ይህንን የተሳሳተ ወንድም በፍቅር ሊያቀናው ሲጥር፥ ሕግ አክራሪዎች ግን ይበልጥ ይጎዱታል። «ማቅናት(ማደስ)» የሚለው ቃል ትርጉም «መረብን መጠገን ወይም የተሰበረ አጥንት መጠገን» እንደ ማለት ነው። ከዚህ በፊት የአጥንት ስብራት ገጥሞህ ከሆነ የተሰበረ አጥንትን መጠገን ምን ያህል ሕመም እንዳለበት ታውቃለህ። ኃጢአትን ያደረገ አማኝ በአውነት ውስጥ የተሰበረ አጥንት እንዳለበት ነውና መጠገን ያስፈልገዋል። በመንፈስ ቅዱስ የሚመራና በጸጋ ነጻነት የሚኖር አማኝ የተሳሳተውን ወንድም ለመመለስ ይጥራል፤ ምክንያቱም «የመንፈስ ፍሬ ፍቅር» ነውና (ገላ. 5፡22)። በፍቅር አንዱ ሌላውን ያገልግል (5፡13)። ኢየሱስ የኃጢአተኞች ሐኪም ለመሆን በፈለገ ጊዜ በፈሪሳውያን ከፍተኛ ነቀፋ ደርሶበት ነበር (ማር. 2፡13-17)። ስለዚህ በዚህም ዘመን መንፈሳዊ አማኝ በሕግ አክራሪዎች ነቀፋ ይደርስበታል።

ሕግ አክራሪ ሰው የተሳሳተውን ወንድም ከማቅናት ይልቅ ይኰንነዋል። የዚህን ወንድም ስህተት በማጉላት የራሱን መልካምነት ለማሳየት ይጠቀምበታል። ኢየሱስ ስለ ፈሪሳዊውና ቀራጩ ሰው በተናገረው ምሳሌ ፈሪሳዊው ያደረገው ይህን ነበር (ሉቃስ 18፡9-14)። «ፍቅር የኃጢአትን ብዛት ትሸፍናለች» (1ኛ ጴጥ. 4፡8)። አንድ ወንድም በሚወድቅበት ጊዜ ሕግ አክራሪ የሆነ ሰው ደስ ይሰኛል። ብዙ ጊዜም በወሬ ያዛምተዋል። ምክንያቱም ስለ ራሱ መልካምነትና የእርሱም ቡድን የተሳሳተው ሰው ከሚገኝበት ቡድን ምን ያህል የተሻለ እንደ ሆነ በትምክህት ለመናገር የሚችለው ይህን በመሰለው አጋጣሚ በመሆኑ ነው።

ጳውሎስ የተግሣጽን ቃል የተናገረው ለዚህ ነበር። «እርስ በርሳችን እየተነሣሣንና እየተቀናናን በከንቱ አንመካ» (ገላ. 5፡26)። መነሣሣት ማለት ፍልሚያ ማድረግ፥ መወዳደር ማለት ነው። በመንፈስ የሚመላለስ ክርስቲያን ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር አይወዳደርም ወይም «የራሱን ያህል መልካም እንዲሆኑ» አይጎተጉታቸውም። ሕግ አክራሪ ሰው የሚኖረው ግን በውድድርና ራሱን ከሌሎች በማነጻጸር ነው። ሌሎች ወንድሞች መጥፎ እንደ ሆኑ አድርጎ በማቅረብ የራሱን መልካምነት ለማሳየት ይሞክራል።

2. ዝንባሌን የተመለከተ ንጽጽር፡- በመንፈስ ቅዱስ የሚመራ አማኝ ጉዳዩን የሚያቀርበው በፍቅርና በየዋህነት መንፈስ ነው። ሕግ አክራሪዎች ግን የትምክህትና የመኰነን ዝንባሌ ይዘው ይቀርባሉ። ሕግ አክራሪ ሰዎች እንዲህ አይነቱን ኃጢአት ፈጽሞ ሊሠሩ እንደማይችሉ አድርገው ራሳቸውን ሰለሚቆጥሩ ዝንባሌያቸው መልካም አይደለም። በጸጋ የሚኖር አማኝ ግን ማንኛውም ሰው ከኃጢአት ነፃ የሚያደርግ ክትባት እንደ ሌለው ያውቃል። «እንደ ቆመ የሚመስለው እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ» (1ኛ ቆሮ. 10፡12)። የራሱን ድካም ስለሚገነዘብ ለሌሎች የትህትና ዝንባሌ አለው።

ነገር ግን ሁለተኛ ተነጻጻሪ ጉዳይ ደግሞ አለ። በልቡ የክርስቶስን ፍቅር ያውቃል። የክርስቶስ ሕግ «እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ» የሚል ነው (ዮሐ. 13፡34፤ 15፡12)። ጳውሎስ ከዚህ ቀደም ብሎ «የፍቅር ሕግን» ገልጦ ነበር (ገላ. 5፡13-15)። አሁን ደግሞ ከሕይወት ጋር ያዛምደዋል። «ርህሩህና ገር የሆነ የፍቅር እንክብካቤ» እንዲኖረን አጥብቆ ስለሚጠይቅ ጉዳዩ በቅርቡ የተገኘ ወይም ሥልጣኔ የወለደው አይደለም። አንድ ሐኪም የተሰበረ አጥንት በሚጠግንበት ጊዜ ርህራሄውንና ገርነቱን ቢያሳየን ምን

ያህል እናደንቀዋለን። እኛም የተሰበረ ሕይወትን ለመጠገን በምንፈልግበት ጊዜ የበለጠ «ርህራሄና ገርነት የሞላበትን የፍቅር እንክብካቤ» ማሳየት ይጠበቅብናል።

በማናቸውም በደል የተገኘን ሰው ለመርዳት መቅረብ ከፍተኛ ፍቅርንና ብርታትን የሚጠይቅ ነው። ኢየሱስ ይህንን ጉዳይ ለዓይን ከሚደረግ ቀዶ ሕክምና ጋር ያወዳድረዋል (ማቴ. 7፡1-5)። ግን ይህን ለማድረግ ብቃት ያለን ስንቶቻችን እንሆን?

ጳውሎስ፥ በዚህ ወቅት እርቅን የመመሥረት አስፈላጊነት በማስመልከት ጌታ ያስተማረው ትምህርት በአእምሮው ሳይኖር አይቀርም (ማቴ. 18፡15-35)። ወንድምህ ቢበድልህ በክርክር አሸናፊ ለመሆን ሳይሆን ወንድምህን ገንዘብህ ለማድረግ ወደ እርሱ ሄደህ በግልህ አነጋግረው። (በዚህ ስፍራ ጳውሎስ «አቅኑት» ብሎ የተጠቀመበት ቃል በ1ኛ ቆሮ. 9፡19-22 ያልዳነን ሰው ለክርስቶስ ስለ መማረክ ከተናገረው ቃል ጋር ተመሳሳይ ነው። የጠፉትን ለክርስቶስ መማረክ አስፈላጊ እንደ ሆነ ሁሉ፥ ደህንነት ያገኙትንም ማቅናት አስፈላጊ ነው።) በዚህ እርምጃ ወንድምህ ከሰማህ ጉዳዩ አለቀ ማለት ነው። ሊሰማህ ካልወደደ ግን አንድ ሁለት መንፈሳዊ ሰዎች ከአንተ ጋር እንዲሄዱና እንዲያነጋግሩት ጠይቅ። በዚህ ደረጃ አሻፈረኝ ካለ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ በሙሉ ሊያውቀውና የሥነ ሥርዓት እርምጃዎችን ሊወስድበት ግድ ነው። ነገር ግን ኢየሱስ በተጨማሪ የሚጠቁመው ጉዳይ የሥነ-ሥርዓት እርምጃዋ ስኬታማ እንዲሆን ቤተክርስቲያን ጸሎትንና (ማቴ. 18፡19-20)ና ይቅርታ ማድረግን (ማቴ. 18፡21-35) መለማመድ እንዳለባት ነው።

ሕግ አክራሪዎች ለእንደዚህ አይነቱ መንፈሳዊ «ነፍስን መማረክ» ጊዜ እንደሌላቸው እርግጥ ነው። ወንድሙ እንደ በደለ ሲሰማ ወደ እርሱ በመሄድ ፈንታ ይህን ደስ የማያሰኝ ወሬ ለሌሎች በማካፈል ወሬውን ያስፋፋል። (ለሽፋን ያህል ግን ስለ ጉዳዩ በተሻለ ሁኔታ ጠንክሮ ለመጸለይ ነው ይላል።) ያንንም ወንድም መንፈሳዊ አይደለም በማለት መኮነን ይጀምራል።

አስታውስ! እነዚህ ሕግ አክራሪዎች ራሳቸውን የተሻሉ አድርገው የሚያቀርቡት ወንድማቸውን መጥፎ አድርጎ በማሳየት ነው። ስለዚህ ጳውሎስ በዚህ ስፍራ ማስጠንቀቂያ ይጽፋል (ቁ. 3-4)። የይሁዲነት አቀንቃኞች ስለ ራሳቸው፥ ስለ ውጤታማነታቸውና ወደ ክርስቶስ ስላመጧቸው ሰዎች በትምክህት ስለሚያወሩ ጥፋተኞች ነበሩ (ገላ. 6፡12-14)። ይህንን ብዙ

ጊዜ የሚያደርጉት ራሳቸውን ከሌሎች ጋር በማወዳደር ነበር (2ኛ ቆሮ. 10፡11 ተመልከት)። እንዲህ ዓይነቱ ማወዳደሪያ ግን ኃጢአት የሞላበትና አሳሳች ነው። ከእኛ የባሰ መጥፎ የሆነ አንድን ሰው ማግኘትና ራሳችንን ከእርሱ ጋር በማወዳደር ከእርሱ ይልቅ የተሻልንና ጥሩ የሆንን መስሎ እንዲሰማን ማድረግ ቀላል ነው። የአንድ ወንድም ውድቀት ወይም ድካም እኛን ከእርሱ የተሻልን ሆኖ እንዲሰማን የሚያደርግ ቢሆንም እንኳ የዚያን ወንድም ውድቀት ወይም ድካም ሳንገልጥ እንድንኖር የሚያደርገን ክርስቲያናዊ ፍቅር ነው።

«እያንዳንዱ የገዛ ራሱን ሥራ» ሊፈትን (ገላ. 6፡4) የሚያስፈልገው በእግዚአብሔር ፊቃድ ብርሃን እንጂ በአንድ ሌላ ሰው ስኬታማነት ጥላ ወይም ከለላ አይደለም። «ነገር ግን እያንዳንዱ የገዛ ራሱን ሥራ ይፈትን፥ ከዚያ በኋላ ስለ ሌላው ሰው ያልሆነ ስለ ራሱ ብቻ የሚመካበትን ያገኛል። እያንዳንዱ የገዛ ራሱን ሸክም ሊሸከም ነውና» (ገላ. 6፡4-5)። በእግዚአብሔር ሥራ ውስጥ ከኃጢአትና ከሰይጣን ካልተወዳደርን በስተቀር ለውድድር ስፍራ የለም። «ከሁሉ የላቀ፥ ከሁሉ በተሻለ ፍጥነት የሚያድግ፥ እጅግ በጣም ትልቅ፥ መልካም የሚሉ ቃሎች ለክርስቲያናዊ አገልግሎት ጥቅም ላይ ውለው ስንመለከት ክብሩን የሚያገኘው ማን ይሁን ብለን እንጠይቃለን።

ይህ ማለት መረጃ መሰብሰብ ስሕተት ነው ማለት አይደለም። ቻርልስ ሃደን ስፐርጀን ብዙ ጊዜ እንዲህ ይል ነበር፤ «ሥነ አኃዛዊ መረጃን የሚነቅፉ ሰዎች ብዙ ጊዜ የሚዘግቡት ነገር የሌላቸው ናቸው።» እኛ መልካም ሆነን እንታይ ዘንድ ሌሎቹን ክፉ አድርገን ላለማሳየት ግን መጠንቀቅ አለብን። ልክ እንደ ራሳችን አድርገን በሌሎች ስኬታማነትና ባገኟቸው በረከቶች ሐሴት ልናደርገ ይገባናል (ሮሜ 12፡10)። የአካል አንዱ ክፍል የተባረከ ከሆነ አጠቃላይ አካሉ ይባረካልና።

በቁጥር 2 ና 5 ላይ ባሉ አሳቦች መካከል ግጭት የለም። ምክንያቱም፥ «ሸክም» ተብሎ ለተተረጎመው አሳብ አገልግሎት ላይ የዋሉት የግሪክ ሁለት ቃሎች የተለያዩ በመሆናቸው ነው። በቁ. 2 ላይ ያለው እጅግ ከባድ የሆነ ሸክም ሲሆን ቁ. 5 የሚገልጸው ግን «የአንድን ወታደር ትጥቅ» ነው። የሕይወትን ከባድ ሸክም በመሸከም አንዱ ሌላውን ሊረዳ ይገባል። እያንዳንዱ ሰው ለራሱ የሚሸከመው የግል የሕይወት ኃላፊነት ደግሞ አለ። «እያንዳንዱ ወታደር የራሱን ትጥቅ ይሸከም።» መኪናዬ ቢበላሽ በቅርብ

ያለ ወዳጄ ልጆቼን ወደ ትምህርት ቤት በማድረስ ሊረዳኝ ይችላል። እንደ አባት እኔ ብቻ ልወጣው የሚገባኝን ኃላፊነት የመወጣት ግዴታ ግን የለበትም። ልዩነቱ ይህ ነው። በቤቴ ውስጥ አባት የሚሆነ ሌላ ሰው ይመጣል ብዬ መጠበቅ የለብኝም። ይህ እኔ ብቻ የምሸከመው ሸክም (እና መብት) ነው።

2. በረከቶችን መከፋፈል (6:6-10)

በቤተ ክርስቲያን ቋንቋ የቃላት ዝርዝር ውስጥ ቁልፍ ከሆኑ ቃሎች «እርስ በእርሳችሁ» የሚለው አንዱ እንደ ሆነ ሁሉ ጎብረት የሚለውም ቃል እንዲሁ ቁልፍ ቃል ነው። በቁጥር 6 ላይ «መከፋፈል» ተብሎ ተተርጉሟል። ቤተ ክርስቲያን ከተቆረቆረችበት ጊዜ ጀምሮ የክርስቲያን ተግባር አንዱ መለያ «አንዱ ለሌላው ማካፈል» የሚል ነበር (የሐዋ. 2:41-47)። ይህን አሳብ የሚገልጠው ኮይኖኒያ የሚለው የግሪኩ ቃል በእንግሊዝኛውም ሆነ በአማርኛው ትርጉም በሃይማኖታዊ ጽሑፎች ውስጥ በየሰፍራው እናገኘዋለን። ትርጉሙ በቀላል አባባል «በጋራ መያዝ» ማለት ሲሆን፥ በክርስቶስ ያለንን የጋራ ጎብረት (ገላ. 2:9)፥ የጋራ እምነታችንን (ይሁዳ 3)፥ በክርስቶስ መከራ ተካፋይ መሆናችንን ሁሉ ይጨምራል (ፊልጵ. 3:10)። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ኮይኖኒያ የሚለው ቃል ብዙ ጊዜ የሚያመለክተው ቁሳዊ በረከቶችን ስለ መከፋፈል ነው (የሐዋ. 2:42፤ 2ኛ ቆሮ. 8:4፤ ዕብ. 13:16 [የግሪኩ ቅጂ])። በእነዚህም ቁጥሮች የምንመለከተው በጳውሎስ አእምሮ ውስጥ ያለውን ይህን አንገብጋቢ ነጥብ ነው።

ጳውሎስ መልካም ነገርን እንድንከፋፈል ከሚያዝ ከአንድ ሕግ ይጀምራል (ቁ. 6)። የቃሉ አስተማሪ የሆነ ሰው መንፈሳዊ ሀብትን የሚያካፍል ሲሆን ከእርሱ የሚማሩ ሰዎች ደግሞ ቁሳዊ ሀብታቸውን ማካፈል አለባቸው። (ጳውሎስ የአሕዛብ አብያተ ክርስቲያናት ለአይሁድ አማኞች እርዳታ ማድረግ እንዳለባቸው ሲገልጽ የተጠቀመበት አቀራረብ ይህ ነበር - ሮሜ 15:27።) በቁሳዊ ነገሮች የምናደርገው ሁሉ መንፈሳዊ ነገሮችን እንዴት እንደምንመዝን ማስረጃ እንደ ሆነ ልናስታውስ ይገባል። «መዝገብህ ባለበት ልብህ ደግሞ በዚያ ይሆናልና» (ማቴ. 6:21)።

ሐዋርያው ጳውሎስ ገንዘብ ላልዳነው ሰው የማሰናከያ ድንጋይ እንዳይሆን ይፈልግ ስለ ነበር ለራሱ መተዳደሪያ የሚሆነውን ሥራ ይሠራ

ነበር (1ኛ ቆሮ. 9 ተመልከት)። ሆኖም ግን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚያገለግሉ መንፈሳዊ መሪ በሕዝቡ ስጦታ መደገፍ እንዳለበት በተደጋጋሚ ያስተምር ነበር። ኢየሱስ «ለሠራተኛ ደመወዙ ይገባዋል» ብሎ እንደ ተናገረ (ሉቃስ 10፡7) ጳውሎስ የዚህን ዐረፍተ ነገር ስሜት አስተጋብቷል (1ኛ ቆሮ. 9፡11፣14)።

ከዚህ ትእዛዝ በስተ ጀርባ ያለውን መንፈሳዊ መመሪያ መገንዘብ ግን እጅግ አስፈላጊ ነው። እግዚአብሔር አማኞችን ለመጋቢዎችና ለአስተማሪዎች (ለወንጌላውያንም ፊልጵ. 4፡10-19) ቁሳዊ የሆኑ ፍላጎቶቻቸውን ለሚሟያ የሚሆን ነገር እንዲከፍሏቸው ከማዘዙም በተጨማሪ ስጦታንም የሚሰጡ ሰዎች ከፍተኛ በረከት እንደሚያገኙ ገልጿል (ገላ. 6፡7-8)። የመዝራትና የማጨድ መሠረታዊ ሕግ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሙሉ ይገኛል። እግዚአብሔር የዘራነውን እንድናጭድ ደንግጓል። ይህ ሕግ ባይኖር ኖሮ «የምክንያትና ውጤት» አጠቃላይ መመሪያ ውድቅ ይሆን ነበር። ስንዴ የዘራ ገበሬ ስንዴ ለማጨድ ይዘጋጃል። ይህ ባይሆን ኖሮ በዓለም ላይ ከፍተኛ ቀውስ ይፈጠር ነበር።

እግዚአብሔር የት እንደምንዘራ እንድንጠነቀቅ ነግሮናል። ጳውሎስ በዚህ ስፍራ ያተኮረበት መመሪያ ይህ ነው። ቁሳዊ ሀብታችን በሁለት የተለያዩ መሬቶች ላይ ሊዘራ እንደሚችል ዘር አድርጎ ይገልጸዋል። ሁለቱ የተለያዩ መሬቶች ሥጋና መንፈስ ናቸው። ቁሳዊ ንብረታችንን የሥጋውን ወይም የመንፈስን ተግባር ለመፈጸም ልንጠቀምበት እንችላለን። መዝራታችንን ከፈጸምን በኋላ ግን ምርቱን መለወጥ አንችልም።

ለሥጋ የተዘራ ገንዘብ ያለ አግባብ የመበልጸግንና የተገኘውን ብልጽግና ያለ አግባብ የመጠቀምን ውጤት ያመጣል (ገላ. 5፡19-21 ተመልከት)። ይህንንም ገንዘብ አንድ ጊዜ ካወጣነው በኋላ እንደገና መልስ ማግኘት አይቻልም። ለመንፈስ የተዘራ ገንዘብ ግን (ለምሳሌ ቃሉን ለሚያስተምሩ ብለን ማካፈል) ሕይወትን ያስገኛል። በዚያ ምርት ውስጥ እንደገና ሊዘራና ለሌላ ምርት ሊዘጋጅ የሚችል ዘር ያስገኛል። ይህም ዑደት እስከ ዘለዓለም ድረስ ይቀጥላላ። እያንዳንዱ አማኝ ቁሳዊ ሀብቱን እንደ ዘር ቢቆጥርና በሚገባ ቢዘራው በእግዚአብሔር ሥራ ውስጥ የገንዘብ እጥረት ሊኖር አይችልም። ብዙ ዘሮች የሚባክኑት በሥጋዊ ነገሮች ስለ ሆነ ለእግዚአብሔር ክብርን ሊያመጡ ያለመቻላቸውን መመልከቱ ያሳዝናል።

ይህንን መመሪያ ከሕይወታችን ጋር በማዛመድ ተግባራዊ የምናደርግበት ከዚህ የላቀ መንገድ መኖሩ አያጠራጥርም። ምክንያቱም የምናደርገው ነገር ሁሉ በሥጋ ወይም በመንፈስ ላይ የምናፈሰው መዋዕለ ነዋይ ሆኖ ስለሚቆጠር የዘራነውን ሁሉ ያንኑ ደግሞ እናጭዳለን። የምናጭደውም በዘራንበት መጠን ነው። «በጥቂት የሚዘራ በጥቂት ደግሞ ያጭዳል፥ በበረከት የሚዘራ በበረከት ደግሞ ያጭዳል» (2ኛ ቆሮ. 9፡6)። በመንፈስ የሚመላለስና በመንፈስ የሚዘራ አማኝ መንፈሳዊ ምርትን ያጭዳል። አዘራሩ በበረከት ከሆነ ምርቱም በዚህ ሕይወት እንኳ ባይሆን በሚመጣው ዘለዓለማዊ ሕይወት የተትረፈረፈ ይሆናል።

የጳውሎስ ጠላቶች የነበሩት የይሁዲነት አቀንቃኞች በመስጠትና በመቀበል ጉዳይ እንዲህ አይነት መንፈሳዊ ዝንባሌ አልነበራቸውም። ጳውሎስ ለኦሮው ሲል በሥራ መጠመዱና ላቡን ማፍሰሱ ለቤተ ክርስቲያን ሸክም ላለመሆን ነበር። ሐሰተኛ አስተማሪዎች ግን አብያተ ክርስቲያናትን የራሳቸውን እቅድ ለማስፈጸምና ሳጥናቸውን ለመሙላት ተጠቅመውባቸዋል። በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የተፈጸመውና ጳውሎስን የሚከተለውን መልእክት ይጽፍ ዘንድ ያደረገው ይህ ዓይነቱ አድራጎት ነበር። «ማንም ባሪያዎች ቢያደርጋችሁ ማንም ቢበላችሁ፥ ማንም ቢቀማችሁ፥ ማንም ቢኮራባችሁ፥ ማንም ፊታችሁን በጥፊ ቢመታችሁ ትታገሣላችሁና» (2ኛ ቆሮ. 11፡20)

ሥርዓት የለሽ የሆነውና የገዛ ጥቅሙን የሚያስፋፋው ሰው ሲከበርና የሚፈልገውን ነገር ሁሉ ሲያገኝ፥ ታላቅ መስዋዕትነትን በመክፈል በፈሪሃ እግዚአብሔር የሚሠራ መጋቢ ሲሰደድና ተገፍቶ ሲወጣ ያየነው ምን ያህል አየተናል? ሥጋዊ ለሆነው አማኝ «መንፈሳዊ አምባገነንነትን የሚያራምደውና የሕግ አክራሪነቱ የታወቀው መጋቢ አመራር ያረካዋል። ምክንያቱም በዚህ ሰው አመራር ሥር ዋስትና ያለው፥ ስኬታማና መንፈሳዊ ሰው የሆነ ስለሚመስለው ነው። ሥጋዊ አማኝ ሊፈጽመው የፈለገው ተግባር የበለጠ ውጤታማ እንዲሆን ያለውን ሁሉ ለማካፈል ወደ ኋላ ባይልም ዳሩ ግን የዘራው ለሥጋው እንጂ ለመንፈስ ያለመሆኑን ውሎ አድሮ ይገነዘባል።

ጳውሎስ ትእዛዙንና (ገላ. 6፡6) በትእዛዙ ሥር ያለውን መመሪያ (ቁ. 7ና 8) ከሰጠ በኋላ ቀጥሎ አንድ ተስፋን ይሰጠናል (ቁ. 9)፤ «ባንዝልም በጊዜው እናጭዳለንና።» ከዚህ ተስፋ በስተጀርባ አንድ አደጋ አለ፤ ይህ

አደጋ በጌታ ሥራ ውስጥ ድካምን ማሳየትና በመጨረሻም ጉልበት አጥቶና ራስን ስቶ አገልግሎትን ማቆም ነው።

የመንፈሳዊ ጉልበት ማጣትና መሳት አንዳንድ ጊዜ ምክንያቱ ለጌታ ሙሉ ለሙሉ ያለመሰጠት ነው። «በሥራ፥ በድካምና በትዕግሥት» አንጻር የተመሰገኑትን ሁለት አብያተ ክርስቲያናት በንጽጽር መመልከት ጠቃሚ ነው (1ኛ ተሰ. 1:3፤ ራእይ 2:2)። በኤፌሶን የነበረችዋ ቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያ ፍቅሯን ትታ ወደ ኋላ ተመልሳ ነበር (ራእይ 2:4-5)። ለምን? መልሱ ለተሰሎንቄ ቤተ ክርስቲያን በተነገረው በጎ ምስክርነት ተሰጥቷል፥ ይህም «የእምነታችሁን ሥራ፥ የፍቅራችሁን ድካም፥ የተስፋችሁን መጽናት» ነው። ዋናዎቹ ተፈላጊ ባሕሪያት ሥራ፥ ድካምና ትዕግሥት ብቻ ሳይሆኑ ተገቢ የሆነ ውስጣዊ መነሣሣት ያለበት «እምነት፥ ፍቅርና ተስፋ» ናቸው። ለጌታ እየሠራን መንፈሳዊ የሆነው የውስጥ መነሣሣታችን እንዲሞት ማድረግ እንዴት ቀላል ነው። ሚልክያስ እንደ ተነበየባቸው የእስራኤል ካህናት ጌታን እያገለገልን «ይህ ድካም ነው» በማለት እናጉረመርማለን (ሚል. 1:13)።

አንዳንድ ጊዜ ለጌታ ሥራ ታክተን አቅም በማጣት የምንስተው ባለመጸለያችን ነው። «ሳይታክቱም ዘወትር ሊጸልዩ እንዲገባቸው...ነገራቸው» (ሉቃስ 18:1)። ጸሎት ለመንፈሳዊ ሕይወት ያለው አስፈላጊነት አየር ለሥጋዊ አካላችን የሚያስፈልገውን ያህል ነው። መተንፈስ ብናቆም ራሳችንን ስተን እንወድቃለን። በምግብ እጦት ደግሞ መድከምና ተዝለፍልፎ መውደቅ ይቻላል። «ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም» (ማቴ. 4:4)። በሚገባ ሳንመገብና እረፍት ሳናደርግ ለመኖር ብንሞክር አሁንም ራሳችንን ስተን እንወድቃለን። ለእያንዳንዱ ቀን የሚያስፈልገንን ብርታት ለማግኘት «እግዚአብሔርን በመተማመን መጠበቅ» (ኢሳ. 40:28-31) እጅግ አስፈላጊ ነው።

ጳውሎስ «በጊዜው እናጭዳለንና» በማለት የሚሰጠን ተስፋ ግን ተግተን እንድንቀጥል ይረዳናል። አንድ የተዘራ ዘር ወዲያውኑ ፍሬ እንደማይሰጥ ግልጽ ነው። ለተፈጥሮ ጊዜ እንዳለው ሁሉ ለነፍስም ጊዜ አለው። ስለዚህ ዘሩ ሥር እንዲያወጣና ፍሬ እንዲሰጥ ጊዜ ልንሰጠው ያስፈልጋል። አራሹ አጫጁን ሲያገኘው እንዴት ይደሰታል (አሞጽ 9:13)። አንድ ቀን

ለማጨድ እንድንችል በየዕለቱ ልንዘራ ይገባናል (መዝ. (126)፡5-6)። ሆኖም የመከሩ ጌታ ባለቤቱ እንጂ አራሾቹ እንዳልሆኑ ማስታወስ አለብን።

በረከቶችን መከፋፈል ቃሉን ከማስተማርና ቁሳዊ ነገሮቻችን ከመስጠት ሁሉ የላቀ ነገር ነው። ይህ «ለሰው ሁሉ» መልካም ማድረግን ይጨምራል (ገላ. 6፡10)። በዚህ ዓለም ላይ ክፉ የሚያደርጉ ሰዎች አሉ (መዝ. (34)፡16)። ለመልካም እንኳ ክፉ የሚመልሱ ሰዎች አሉ (መዝ. (35)፡12)። በዓለም ላይ የሚኖሩ አብዛኛዎቹ ሰዎች ለበጎ በጎን ለክፉ ክፉን ይመልሳሉ። (1ኛ ተሰ. 5፡15፤ ሉቃስ 6፡32-35 ተመልከት)። ክርስቲያን ግን ለክፉ እንኳ በጎን መመለስ ይጠበቅበታል (ሮሜ 12፡18-21)። ይህንንም በክርስቲያናዊ ፍቅር አንጻር ልናደርገው ይገባል። የክርስቲያን መልካም ሥራዎች ለጌታ የሚሠዋቸው መንፈሳዊ መሥዋዕቶች ናቸው (ዕብ. 13፡16)።

«ለሰው ሁሉ መልካም» ልናደርግ ይገባል። ብርሃናችን እንዲበራና በሰማይ ያለው አባታችን እንዲከበር የምናደርገው በዚህ ዓይነት ነው (ማቴ. 5፡16)። ለማያምኑ ሰዎች የምንመሰክረው በቃላቶች ብቻ ሳይሆን በሥራዎችም ጭምር ነው። ሥራዎቻችን የቃል ምስክርነታችንን መንገድ የቀና ያደርጉታል። የተሰሚነት ሥልጣን እንዲኖረን ያደርጋሉ። ይህ ማለት ደግሞ የምንሠራው ሁሉ «ይህ ሰው የእኔ እርዳታ ማግኘት ይገባዋልን?» ብለን በመጠየቅ መሆን የለበትም። እኛስ እግዚአብሔር በክርስቶስ ያደረገልን ነገር የሚገባን ነውን? ራሱን ለመከላከል እንደ ሞከረው የሕግ ሰው «ባልንጀራዬ ማን ነው?» ብለን ክርክር የምንከፍትበትም ጉዳይ አይደለም (ሉቃስ 10፡25-37)። ኢየሱስ ይህን ለመሰለው ጉዳይ የምናቀርበው ጥያቄ «ባልንጀራዬ ማን ነው?» የሚል ሳይሆን «ለማን ባልንጀራ መሆን እችላለሁ?» የሚል መሆን እንዳለበት ግልጽ አድርጎልናል።

ለሰው ሁሉ መልካም በምናደርግበት ጊዜ «ለሃይማኖት ቤተሰዎች»፥ ለአማኞች ጎብረት ቅድሚያ መስጠት አለብን። ይህ ማለት ደግሞ አንዲት አጥቢያ ቤተክርስቲያን ከአካባቢዋ ትለይ ወይም አባሎችዋ ሌሎችን ለመርዳት አንዳችም ነገር አያድርጉ ማለት አይደለም። ይልቁኑ ሚዛናዊ የመሆን ጉዳይ የሚጠይቅ ነው። በጳውሎስ ዘመን የነበሩ አማኞች በውጭ ካሉ ይልቅ በርካታ ነገሮች የሚያስፈልጋቸው ነበሩ። ምክንያቱም ብዙዎቹ አማኞች ለእምነታቸው መከራን እየተቀበሉ ነበር (ዕብ. 10፡32-34

ተመልከት)። በተጨማሪ ሰው በጎረቤቱ ላሉ ሰዎች ከማሰቡ በፊት ለራሱ ቤተሰብ ሁልጊዜ ማሰብ አለበት (1ኛ ጢሞ. 5፡8)።

ሆኖም ግን ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር ያለንን የምንከፋፈለው፥ ሁላችንም ከችግር ለማትላቀቀዋ ለዚህች ዓለም ማካፈል እንችል ዘንድ ነው። በሃይማኖት ቤተሰብ ውስጥ የሚገኝ ክርስቲያን ለማስተላለፍ እንዲችል የሚቀበል ሰው ነው። እርስ በርሳችን በፍቅር ስንገዛ ለሰዎች ሁሉ በፍቅር እንትረፈረፉለን (1ኛ ተሰ. 3፡12)።

መሆንም ያለበት እንደዚህ ነው።

ገላትያ 6፡11-18

እንዴት ባሉ ታላላቆች ፊደላት በእጄ እንደ ጻፍሁላችሁ እዩ። በሥጋ መልካም ሆነው ሊታዩ የሚወዱ ሁሉ እንድትገረዙ ግድ አሉአችሁ፥ ነገር ግን ስለ ክርስቶስ መስቀል እንዳይሰደዱ ብቻ ነው። በሥጋችሁ እንዲመኩ ልትገረዙ ይወዳሉ እንጂ የተገረዙት ራሳቸው እንኳ ሕግን አይጠብቁም። ነገር ግን ዓለም ለእኔ የተሰቀለበት እኔም ለዓለም የተሰቀልሁበት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክህት ከእኔ ይራቅ። በክርስቶስ ኢየሱስ አዲስ ፍጥረት መሆን ይጠቅማል እንጂ መገረዝ ቢሆን ወይም አለመገረዝ አይጠቅምምና። በዚህም ሥርዓት በሚመላለሱ ሁሉ ላይ በእስራኤልም ላይ ሰላምና ምሕረት ይሁን።

እኔ የኢየሱስን ማኅተም በሥጋዬ ተሸክሜአለሁና ከእንግዲህ ወዲህ አንድ ስንኳ አያድክመኝ።

ወንድሞች ሆይ፥ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከመንፈሳችሁ ጋር ይሁን። አሜን።

- 12 -

የነፃነት መለያዎች

ጳውሎስ አንድን መልእክት በቃል እየተናገረ ጸሐፊ እንዲጽፍለት ካደረገ በኋላ ብዕሩን ወስዶ የራሱን የስንብት ቃል መጻፍ ልማዱ ነበር። እንደ ፊርማ የሆነች የማጠቃለያ ዐረፍተ ነገሩ «የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከእናንተ ጋር ይሁን» የምትል ነበረች (1ኛ ተሰ. 5፡28፤ 2ኛ ተሰ. 3፡17-18 ተመልከት)። በዚህ መልእክት ላይ ግን የገላትያ ሰዎች የመልእክቱን አሳብ እንዲያገኙት ለማድረግ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት የማጠቃለያ አንቀጹን በሙሉ በገዛ እጁ ነው የጻፈው። «እንዴት ባሉ ታላላቆች ፊደላት በእጄ እንደ ጻፍሁላችሁ እዩ።»

ጳውሎስ ይህን አንቀጽ የጻፈው ለምን ነበር? ደግሞስ ትላልቅ ፊደላትን የተጠቀመው ለምን ነበር? መንፈስ ቅዱስ እነዚህን የማጠቃለያ ቃሎች እንዲጽፍ የመራው በሕግ አክራሪዎችና በመንፈስ ቅዱስ በሚመሩ ክርስቲያኖች መካከል አንድ የመጨረሻ ንጽጽር በማድረግ፥ በመንፈስ የሚመራ አማኝ የሚኖረው ለሰው ምስጋና ሳይሆን ለእግዚአብሔር ክብር እንደ ሆነ ለማሳየት ነበር። በትላልቅ ፊደላት የጻፈው ደግሞ «አያምልጣችሁ» የሚል አትኩሮት ለመስጠት ነበር።

አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቆች የጳውሎስ የሥጋ መውጊያ የአይን ሕመም ችግር እንደ ነበረ ያምናሉ። (2ኛ ቆሮ. 12፡1-10፤ ገላ. 4፡14-15)። ይህ ግለት የጻፈውን ተመልሶ ለማንበብ እንዲችል በትላልቅ ፊደላት መጻፍ ነበረበት ግለት ይሆናል። ይህ ነገር እውነት ቢሆንም ባይሆንም ጳውሎስ ግን ይህን መልእክት በተለየ መንገድ መደምደሙ አንድ ጠቃሚ የሆነ የተለየ ነገር እንዳለው ለማስተላለፍ ማቀዱን ግልጽ ያደርገዋል። የዐይን ችግር ከነበረበት፥ ይህን ማጠቃለያ አንቀጽ በገዛ እጁ ለመጻፍ ፈቃደኛ መሆኑ የአንባቢያኑን ልብ ለመሳብ ሲል ያደረገው ለመሆኑ የተረጋገጠ ነው።

በሕግ ሥር የሚኖር አማኝና በጸጋ ሥር የሚኖር አማኝ በከፍተኛ ሁኔታ እርስ በርሳቸው እንደሚቃረኑ አሳይቶአቸዋል። የቅራኔው መንስዔ «የተለያዩ መሠረታዊ የእምነት ትምህርቶች ጉዳይ» ሳይሆን ሁለት የተለያዩ የሕይወት መንገዶች ጉዳይ ነው። ከባርነት ወይም ከነፃነት (ገላ. 5፡1-12)፥ ከሥጋ

ወይም ከመንፈስ (5፡13-26)፥ ለራስ ወይም ለሌሎች ከመኖር (6፡1-10) መምረጥ ነበረባቸው።

አሁን አራተኛውን ማነጻጸሪያ ያቀርባል፤ ይህም ከሰው ምስጋና ለማግኘት ወይም ለእግዚአብሔር ክብር ሲሉ መኖርን ነው (ገላ. 6፡11-18)። ለዚህም መነሻ ነጥቡ ውስጣዊ ዓላማን በማስመልከት ነው። በዚህ ዘመን ባሉ አብያተ ክርስቲያናት የምናገኛቸውን አገልጋዮች ውስጣዊ ዓላማ የመመርመርን ያህል እጅግ አስፈላጊ የሆነ ጉዳይ የለም። ሁላችንም ብንሆን ምን እያደረግን እንዳለን እናውቃለን፤ ነገር ግን ለምን እንደምናደርገው እናውቅ ይሆን? መልካም ሥራ በመጥፎ ውስጣዊ ዓላማ ይመረዛል።

ጳውሎስ ይህን ጥንቃቄ የሚያስፈልገውን ጉዳይ አስገራሚ በሆነ መንገድ ያቀርበዋል። ሕግ አክራሪ ሰዎች የገላትያ አማኞችን ለግርዘት ሥርዓት እንዲገዙ ለማድረግ ፈልገው ነበር። ስለዚህ ጳውሎስ ይህን ጉዳይ በመውሰድ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ከሠራው ሥራና ከራሱ አገልግሎት ጋር ያያይዘዋል። በዚህ አንቀጽ ውስጥ ጳውሎስ፥ ሦስት ሰዎችን ለይቶ ያቀርባል። እነርሱም ሕግ አክራሪ የሆነ ሰው (6፡12-13)፥ ኢየሱስ ክርስቶስና (6፡14-16) ሐዋርያው ጳውሎስ ራሱ (6፡17-18) ናቸው።

1. ሕግ አክራሪ ሰው (6፡12-13)

ጳውሎስ ስለ ሕግ አክራሪ ሰው የሚናገረው አንዳችም በጎ ነገር የለውም። ይህን ሰውና መሰሎቹን በአራት የተለያዩ መንገዶች ይገልጻል።

በመጀመሪያ ፎካሪዎች ናቸው (6፡12-13)፡- ዋና ዓላማቸው ሰዎችን ለክርስቶስ መማረክ ወይም አማኞች በጸጋ እንዲጸኑ መርዳት እንኳ አይደለም። ዋና ዓላማቸው ብዙ ሰዎችን በትምህርታቸው መለወጥና ስለዚሁ ስላደረጉት ነገር መፎከር ነበር። በውስጣቸው አንዳችም መልካም ነገር ባይኖራቸው እንኳ «በውጫዊ ገጽታቸው መልካም ሆነው ሊታዩ» ይፈልጉ ነበር። ተግባራቸው ሁሉ ለቤተ ክርስቲያን ጥቅም ወይም ለእግዚአብሔር ክብር ሳይሆን ለራሳቸው ክብር ነበር።

ሰዎችን ለክርስቶስ መማረክ ወይም የእግዚአብሔር ሥራ ሲያድግና ሲጨምር ማየት ስህተት እንዳልሆነ ግልጽ ቢሆንም፥ እነዚህን ነገሮች ለሰው ክብር ማስገኛ እንዲሆኑ መፈለግ ግን በማያሻማ ሁኔታ ስህተት ነው። ሰዎችን በመንፈሳዊ አገልግሎታችን ላይ በብዛት ተካፋይ እንዲሆኑ የምንፈልገው

ለቁጥራቸው ማደግ ስንል ሳይሆን ሰዎች ዋጋ ስላላቸው ነው። ሰዎችን ለግላችን የስግብግብነት እቅድ ማሟያና ለክብር ማስገኛ ስንል ልንጠቀምባቸው አይገባም።

የበርካታ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት መጽሔቶችንና ጋዜጦች አገኛለሁ። ሆኖም በአንዱ መጽሔት ላይ የቤተ ክርስቲያኒቱ መጋቢ የሆነው ሰው ሌሎች ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን በስም በመጥቀስ ከእነዚህ ሁሉ የእርሱ ቤተ ክርስቲያን ምን ያህል የተሻለ እንደ ሆነ ለማሳየት የጻፋቸውን ነገሮች ሳይ ደነገጥሁኝ። የሚገርመው ደግሞ ከጠቀሳቸው አብያተ ክርስቲያናት አንዳንዶቹ የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት እንኳ አልነበሩም። ስለዚህ ሌሎች ይህንን ትምክህት የሞላበትን ጽሑፍ ሲያነቡ ስለ ክርስቶስና ስለ ወንጌል ምን ሊያስቡ እንደሚችሉ በማሰብ አዘንሁኝ። ይህ አንድ መጋቢ ቤተ ክርስቲያናቸውን በመኩነኑ ብቻ ለአባላቱ ዳግመኛ ስለ ክርስቶስ መመስከር እጅግ እንደሚከብድ አያጠራጥርም።

ሁለተኛ፥ አለመግባባትን ለማስወገድ እውነትን እንኳ በሐሰት የሚለውጡ ናቸው (6፡12)። ግርዘትንና ከዚህ ሥርዓት ጋር የሚሄዱትን ነገሮች ሁሉ የሚሰብኩትና የሚለማመዱት ለምን ነበር? ስደት እንዳይደርስባቸው በመፍራት ነበር። ጳውሎስ ከጽድቅ ሥራዎች ተለይቶ ያለውን የእግዚአብሔር ጸጋና ደህንነት በመስበኩ ተሰደደ (ገላ. 5፡11)። የይሁዲነት አቀንቃኞች በአንድ በኩል ክርስቲያኖችን ክርስቲያኖች እንደ ሆኑ እንዲያስቡ ሲያደርጉ፥ በሌላ በኩል ደግሞ ለሙሴ ሕግ ተከታዮች ሕግን እንደሚታዘዙ እንዲያስቡ ለማድረግ ይሞክሩ ነበር። ስለዚህ ከክርስቶስ መስቀል ወገን በመቆጠርና ይህም በሕግ ላይ በሚያመጣው ከፍተኛ ጠንቅ ሳቢያ ከሕግ አክራሪዎች ሊደርስባቸው ከሚችለው ስደት አመለጡ።

እኛ ግን ዛሬ ለመስቀሉ (ለክርስቶስ የመስቀል ሞት) ልዩ ፍቅርና አክብሮት አለን። ከዚህም የተነሣ በአንገታችን ወይም በደረታችን ላይ የመስቀል ቅርፅ እናንጠለጥላለን። ለመጀመሪያው ምእተ ዓመት ዘመን ክርስቲያኖች ግን መስቀል ተወዳጅ የጌጥ ዕቃ ከመሆን ምትክ የመጨረሻ ዝቅተኛ ሞትና የውርደት ምልክት ነበር። አንድ ጨዋ የሮም ዜጋ ከሌሎች ጋር በሚወያይበት ወቅት በመሀሉ ስለ መስቀል አንሥቶ ያወራል ማለት ጨርሶ የማይታሰብ ነበር። በአጭሩ መሰቀል ተንቆ የመጣልና የጎፍረት ምልክት ነበር።

ጳውሎስ ክርስቶስን ባመነ ጊዜ ራሱን ከመስቀሉ ጎን በማሰለፍ የሚያስከትለውን ችግር ሁሉ ተቀብሏል። መስቀሉ ለአይሁድ የማሰናከያ አለት፥ ለአሕዛብ ደግሞ ሞኝነት ነበር (1ኛ ቆሮ. 18፡31)። ሕግ አክራሪዎች ከክርስቶስ የመስቀል ሞት ይልቅ በግርዘት ላይ በማተኰር በርካታ ሰዎችን ለመማረክ ችለው ነበር። የሃይማኖት ትምህርታቸው የመስቀሉን ጎፍረት የሚያስወግድ ስለ ነበር በቀላሉ ብዙ ተከታዮች አግኝተው ነበር።

ሦስተኛ፥ ሰዎችን በማግባባት ዘዴ የሚማርኩ ነበሩ (6፡12)። «ግድ አሉአችሁ» የሚለው ቃል ጠንካራ የሆነ የማሳመኛ ክርክርንና ማስገደድንም እንኳ የሚጨምር ነው። ይህ ቃል በገላትያ 2፡14 ላይ «ግድ አልሃቸው» ተብሎ ተተርጉሟል። ሆኖም ግን አገባቡ አንድን ሰው ከፈቃዱ ውጭ በማስገደድ አንድን ነገር ማስፈጸም ለማለት አልነበረም። የይሁዲነት አቀንቃኞች በማግባቢያ ዘዴዎቻቸው ለማሳመን የሚጥሩ ሰዎች ነበሩ። ሕግ አክራሪነት የሕይወት መንገዳቸው እንደ ሆነ ለማሳመን የገላትያን ሰዎች ከማር በለሰለሰ አንደበታቸው ያግባቡአቸው ነበር። ጳውሎስ ግን ቃሉን በተናገረባቸው ስፍራዎች ሁሉ በእውነትና በታማኝነት ይናገር ነበር። በንግግር ችሎታውም ሆነ ወይም በተለያዩ የማሳመኛ ዘዴዎች አልተጠቀመም። (ጳውሎስ ለሚያደምጡት ሰዎች ቃሉን እንዴት ያቀርብ እንደ ነበር ከ1ኛ ቆሮ. 2፡1-5፤ 2ኛ ቆሮ. 4፡1-5 ተመልከት። ጳውሎስ መልእክተኛ ወይም አምባሳደር እንጂ የፖለቲካ ሰው አልነበረም።)

አራተኛ፥ ግብዞች ነበሩ (6፡13)። «ለሕግ እንድትገዙ የሚፈልጉ ቢሆንም እንኳ እነርሱ ለሕግ አይገዙም።» ሕግ አክራሪያን ኢየሱስ «እየተናገሩ አያደርጉትምና» ብሎ ከተናገረላቸው ፈሪሳውያን ተለይተው የሚታዩ አይደሉም (ማቴ. 23፡3)። የጳውሎስ አሳብ የይሁዲነት አቀንቃኞች ሕግን መጠበቅ አለባቸው ማለት እንዳልሆነ ግልጥ ነው። ምክንያቱም ሕግን መጠበቅ አይቻልም፤ ደግሞም አያስፈልግም። ይልቁኑ ጳውሎስ ታማኝ ስላለመሆናቸው ኮነናቸው። ደግሞም ግብዞች ነበሩና ቢችሉም እንኳ ሕግን የመጠበቅ ፍላጎት አልነበራቸውም። ለሕግ የነበራቸው ክብር ብዙዎችን ለስውር ዓላማቸው ለመማረክ በሽፋንነት ለመጠቀሚያ ብቻ ነበር። በአባላቶቻቸው ቁጥር አንጻር ከፍ ያለ አኃዛዊ ዘገባን በማቅረብ የላቀ ክብርን ለማግኘት ይፈልጉ ነበር።

አዎን! ሕግ አክራሪ የሆነ ሰው መለያ ምልክት ያለው ነው። ስለዚህ ማንነቱን እንዳወቅህ ከእርሱ ራቅ!

2. ኢየሱስ ክርስቶስ (6፡14-16)

ጳውሎስ መልእክቶቹ ስለ መስቀሉ ደግሞ ደጋግሞ ያነሣል (2፡20-21፤ 3፡13፤ 4፡5፤ 5፡11፥ 24፤ 6፡12) «ጽድቅስ በሕግ በኩል ከሆነ እንኪያስ ክርስቶስ በከንቱ ሞተ» (2፡21)። ክርስቶስን «የተለየ ሰው» ያደረገው የቀራኒዮ ቁስሎቹ ናቸው። ምክንያቱም በእርሱ ለሚያምኑ ቁስሎቹ ነፃነት ማለት ናቸው። የይሁዲነት አቀንቃኞች በግርዘት ይመኩ ነበር። ጳውሎስ ግን በመስቀል ላይ በሞተውና ከሞት በተነሣው አዳኝ ይመካ ነበር። ለመስቀሉም ልዩ ፍቅርና አክብሮት ነበረው። ይህ ማለት በመስቀሉ ላይ ለተፈጸመው ሞካኔና ሥቃይ ማለት አይደለም። እርሱ ግን መስቀሉን የተመለከተው ወንጀለኞች እንደሚሞቱበት ተራ እንጨት አድርጎ አይደለም። የክርስቶስ መስቀል ትምክህቱ ነበር። ለመሆኑ ጳውሎስ በመስቀሉ የተመካው ለምን ይሆን?

በመጀመሪያ፥ የመስቀሉን ስብእና ያውቅ ስለ ነበር ነው። በገላትያ መልእክት ብቻ ኢየሱስ ክርስቶስ ቢያንስ 45 ጊዜ ያህል ተጠቅሷል። ይህ ማለት ከመጽሐፉ ቁጥሮች አንድ ሦስተኛው እጅ ስለ ኢየሱስ ይናገራሉ ማለት ነው። ጳውሎስ በኢየሱስ ክርስቶስ ስብእና ፍጹም ተማርኮ ነበር። መስቀሉን ትምክህቱ ያደረገለትም ክርስቶስ ነበር። አይሁዳዊ መምህር ሆኖ ባገለገለባቸው የመጀመሪያ ዓመታት ጳውሎስ ክብርን ሊያገኝባቸው የሚችላቸው በርካታ ሁኔታዎች ነበሩ (ገላ. 1፡13-14፤ ፊልጵ. 3፡1-10)። ክርስቶስን ካመነ በኋላ ግን የነበረውን ክብር እንደ መናኛ ነገር ቆጠረው። ሕግ አክራሪዎች ግን በክርስቶስ ስለማይመኩ በመስቀሉም አይመኩም ነበር። ክብርን የሚሰጡት ለሙሴና ለራሳቸው ነበር። የመስቀሉን ሰው በእርግጥ አላወቁትም ነበር።

ሁለተኛ፥ የመስቀሉን ኃይል ያውቅ ስለ ነበር ነው። በመሠረቱ የተማረ የአይሁድ መምህር ለነበረው ለሳኦል፥ በተለይም በመስቀሉ ላይ የተፈጸመን መሥዋእትነት ሃይማኖታዊ ክብደት ይኖረዋል ብሎ መቀበል ጨርሶም የማይታሰብ በሆነ ነበር። መሢሑ ይመጣል ለሚለው ትንቢት ምንም ጥርጣሬ አልነበረውም። ዳሩ ግን የሚመጣው ለመሞት ነው ብሎ ለመገመት፥ ለዚያውም በተረገመ የመስቀል ሞት ይሆናል ብሎ በማሰብ በሳኦል የሥነ መለኮት ትምህርት ውስጥ ስፍራ አልነበረውም። በዚያን ዘመን መስቀል የደካማነትና የጎፍረት የመጨረሻ ምሳሌ ነበር። ሆኖም የጠርሴሱ ሳኦል የመስቀሉ ኃይል ከነካው በኋላ ሐዋርያው ጳውሎስ ሆነ። መስቀሉ የማሰናከያ

አለት መሆኑ ቀረና «ክርስቶስ ለኃጢአታችን ሞተ» ለሚለው መልእክቱ የግዕዘን ድንጋይ ሆነ።

ለጳውሎስ መስቀሉ ማለት ከእኔነት (ገላ. 2፡20)፥ ከሥጋ (5፡24)ና ከዓለም (6፡14) ነፃ መውጣት ማለት ነው። በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ የእግዚአብሔር ኃይል ለአማኞች ነፃነትና ድልን ለማጎናጸፍ ቻለ። አሁን ሕያው ሆነን የምንኖረው እኛ አይደለንም። በእኛ ውስጥ የሚኖረው፥ በእኛም በኩል የሚሠራው ክርስቶስ ነው። ራሳችንን ለእርሱ በሰጠን መጠን በዓለምና በሥጋ ላይ ድል እንቀዳጃለን። ለሰው ልጅ በእኔነት፥ በሥጋና በሕግ ላይ ድል የሚሰጥ ኃይል በሕግ ውስጥ እንደሌለ ግልጽ ነው። ከዚህ በተቃራኒ ሕግ የሰውን የእኔነት ስሜት የሚቀሰቅስ (እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት አንድ ነገር ማድረግ እችላለሁ» እና ሥጋ እንዲሠራ የሚያበረታታ ነው። ዓለም መስቀሉን እስካልተከተለች ድረስ «ሃይማኖተኛ» ብንሆን ባንሆን ግድ የላትም። እንዲያውም ዓለም ከኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል የተለየ ሃይማኖትን ታበረታታለች። ስለዚህ ሕግ አክራሪ የሆኑ ሰዎች ራስ ወዳድነትን ከፍ ያደርጋሉ፤ ሥጋን ያቆላምጣሉ፤ ዓለምን ደግሞ ያስደስታሉ። እውነተኛ ክርስቲያን ግን ሦስቱንም ይንቃል።

ሦስተኛ፥ የመስቀሉን ዓላማ ያውቅ ስለ ነበር ነው። ይህም አዲስ «የእግዚአብሔር ሕዝብን» ወደ ዓለም ለማምጣት ነው። ለብዙ ምእተ ዓመታት የእስራኤል ሕዝብ የእግዚአብሔር ሕዝብ ነበሩ። ሕግ ደግሞ የሕይወት መንገዳቸው ነበር። እነዚህ ሁሉ የኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት መሰናዶዎች ነበሩ (ገላ. 4፡1-7)። አሁን ግን ክርስቶስ መጥቶ ታላቁን የመዋጀት ሥራ አጠናቋል። በዚህም እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ ወደ ጎን ትቶ «አዲስ ፍጥረት»እና «የእግዚአብሔር እስራኤል» የሆነውን አዲስ ሕዝብ ወደ ዓለም አምጥቷል። ይህ ማለት እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር ያለውን ጉዳይ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ አጠናቋል ማለት አይደለም። እግዚአብሔር ዛሬ ከአሕዛብም ከአይሁድም «ለስሙ የሚሆንን ወገን» (የሐ. 15፡14) እየጠራ እያወጣ ነው። በክርስቶስ ዘንድ የዘርና የብሔር ልዩነት የለም (ገላ. 3፡27-29)። ጳውሎስ (በሮሜ 11) በግልጽ የሚያስተምረን እግዚአብሔር ለአይሁድ ሕዝብ የወደፊት እቅድ እንዳለው ነው።

የመስቀል አንዱ ዓላማ አዲስ ፍጥረት ማስገኘት ነው (ገላ. 6፡15)። «አዲሷም ፍጥረት» የምትባለው የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያን

ናት። «አሮጌው ሰው» በአዳም የሚመራ ፍጻሜው ውድቀት ነው። አዲሱ ፍጥረት ግን በክርስቶስ የሚመራና ስኬታማ የሚሆን ነው።

ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች ስለ ሁለቱ አዳሞች (ሮሜ 5፡12-21) መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ገልጾላቸዋል። የመጀመሪያው አዳም እግዚአብሔርን ባለመታዘዝ ወደ ዓለም ኃጢአት፥ ሞትና ፍርድን አመጣ። የመጨረሻው አዳም (1ኛ ቆሮ. 15፡45) እግዚአብሔርን በመታዘዝ ሕይወትን፥ ጽድቅንና ደኅንነትን አመጣ። አዳም አንድ ኃጢአት ሠራና ፍጥረትን ሁሉ ወደ ፍርድ አስገባ። ክርስቶስ በመስቀል ላይ በመሞት ፍጹም መታዘዝን በማሳየቱ የዓለም ሁሉ ኃጢአት ዋጋ ተከፈለ። በአዳም ኃጢአት ምክንያት ሞት በዓለም ላይ ነገሠ። በክርስቶስ ድል ምክንያት በክርስቶስ በኩል «በሕይወት መንገሥ» እንችላለን (ሮሜ 5፡17)። በሌላ አነጋገር ለመግለጽ አማኝ «የአዲስ ፍጥረት» አካል ነው። ይህ አዲስ ፍጥረት «የአሮጌው ተፈጥሮ» ውሱንነትና ጉድለት አንዳችም ነገር የማይታይበት «መንፈሳዊ ፍጥረት» ነው (2ኛ ቆሮ. 5፡17 ተመልከት)።

የመስቀሉ ሌላኛው ዓላማ «የእግዚአብሔር እስራኤል» የሆነውን (ገላ. 6፡16) አዲስ ሕዝብን መፍጠር ነው። በአዲስ ኪዳን ስለ ቤተክርስቲያን ከተጠቀሱት በርካታ ስሞች አንዱ ይህ ነው። ኢየሱስ ለአይሁድ መሪዎች እንዲህ አለ፡- «የእግዚአብሔር መንግሥት ከእናንተ ትወሰዳለች። ፍሬዋንም ለሚያደርግ ሕዝብ ትሰጣለች» (ማቴ. 21፡43)። ጴጥሮስም ያንን ሕዝብ እንዲህ በማለት ይገልጸዋል፡- «የተመረጠ ትውልድ፥ የንጉሥ ካህናት፥ ቅዱስ ሕዝብ፥ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ» (1ኛ ጴጥ. 2፡9)።

ቀደም ብለን እንደ ጠቀስነው ይህ ማለት በእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ ቤተ ክርስቲያን የእስራኤልን ሕዝብ በዘለዓለማዊነት ተክታለች ማለት አይደለም። ነገር ግን የእስራኤል ሕዝብ ከብዙ ምእተ ዓመታት በፊት ጀምሮ የእግዚአብሔር ሕዝብ እንደ ነበረ በዚህ ዘመን ደግሞ ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ሕዝብ ናት ማለት ነው።

ለይሁዲነት አቀንቃኞች ይህ ምን አይነት ግሣጼ ነው? ያ ሕግ በእስራኤል ሕዝብ ሊጠበቅ ያልተቻለ የነበረ ቢሆንም ቤተ ክርስቲያንን ወደ ብሉይ ኪዳን ሕግ ለመመለስ ፈልገው ነበር። ለእግዚአብሔር አዲስ ሕዝብ ለሆነው ለቤተ ክርስቲያን ስፍራ ለመስጠት የእስራኤል ሕዝብ ወደ ጎን ተተወ።

በዚህ ዘመን ያሉ አማኞች በሥጋ «የአብርሃም ልጆች» ላይሆኑ ይችላሉ። በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ባለ እምነት ግን (ገላ. 4:28-29) «የአብርሃም ዘሮች» ናቸው። ከሥጋዊ ግርዘት እጅግ የላቀውን ውስጣዊ የልብ ግርዘትን ተለማምደዋል (ፊልጵ. 3:3፤ ሮሜ 2:19፤ ቆላ. 2:1)። በዚህ ምክንያት መገረዝም ሆነ ያለመገረዝ ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚያስገኘው ምንም ውጤት የለም (ገላ. 6:15፤ 5:6 ተመልከት)።

3. ሐዋርያው ጳውሎስ (6:17-18) ጳውሎስ በግርዘት ምልክት የተመካበት አንድ ወቅት ነበር (ፊልጵ. 3:4-6)። በክርስቶስ ካመነ በኋላ ግን ሌላ ዓይነት ምልክት ያለበት ሰው ሆነ። አሁን ለኢየሱስ ክርስቶስ በሚሰጠው አገልግሎት በደረሰበት ጠባሳና በተቀበለው ሥቃይ ይመካል።

ከሕግ አክራሪዎች ጋር ያለው ተነጻጻሪነት ግልጽ ነው። «የይሁዲነት አቀንቃኞች ምልክት ሊያደርጉብንና ስለዚያም ሊመኩ ይፈልጋሉ። እኔ ግን የኢየሱስን ማኅተም ለክብሩ በሥጋዬ ተሸክሜአለሁና።» ይህ እንዴት የሚቆጠቁጥ ተግሣጽ ነው! «እንደ እኔ ሃይማኖታዊ መሪዎቻችሁ ለክርስቶስ ክብር ሲሉ የደረሰባቸው ጠባሳ ካለ እስቲ ያሳዩን። ከዚያ በተረፈ ግን በከንቱ አያስቸግሩን!»

ጳውሎስ «አምስቱ የቀራንዮ የሥቃይ ቁስሎች በሥጋዬ ተሸክሜአለሁ» አላለም። ሆኖም በምትኩ ሕግ አክራሪዎች ያልተቀበሉትን መከራ ለክርስቶስ ሲል እንደ ተቀበለ ይገልጻል፤ ይህንንም የሚያረጋግጥበት በሥጋው ላይ ጠባሳ አለው። 2ኛ ቆሮንቶስ 11:18-33 ስታነብ ይህንን የጳውሎስ አሳብ ለመረዳት አንዳችም ችግር አያጋጥምህም። ጳውሎስ በብዙ ስፍራና በብዙ መንገድ ለክርስቶስ መከራን ተቀብሏል።

በጳውሎስ ዘመን የአረመኔን ጣዖትና አማልእክት የሚከተሉ ሰዎች የጣዖቶቻቸውን ወይም የአማልእክታቸውን ምልክት በሰውነታቸው ላይ ይነቀሱ ነበር። በአማልእክታቸው ስለሚመኩ ሌሎች ይህን እንዲያውቁ ይፈልጉ ነበር። በተመሳሳይ መንገድ ጳውሎስ የኢየሱስ ክርስቶስ መለያ ተሰጥቶት ነበር። ይህ መለያ ሊጠፋ የሚችል ጊዜያዊ መለያ አልነበረም። እስከ መቃብሩ ድረስ አብሮት የሚሄድ ቋሚ ምልክት ነበር። ይህን ምልክት የተቀበለው ደግሞ በቀላሉ አልነበረም። ለክርስቶስ የተለየ ሰው ይሆን ዘንድ በተደጋጋሚ መከራ መቀበል ነበረበት።

በዚያ ዘመን ባሪያዎችንም መንቀስ የተለመደ ነበር። የባሪያው ጌታ ማን እንደ ሆነ የሚለየውም በዚሁ ንቅሳት አማካይነት ነበር። እንደዚሁ መሆኑን ጳውሎስ የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ መሆኑን የማረጋገጥ መለያውን አድርጎ ነበር።

ኃጢአት የሰው ባሕርይ መለያ ምልክት ሊሆን ስለ መቻሉም በዚህ አጋጣሚ ማጤን ይኖርብናል። ኃጢአት በሰው አእምሮ፥ በሰው ሰብእና፥ በሰው አካል ላይ እንኳ ምልክት ማድረግ ይችላል። ኢየሱስ በሚመለስበት ጊዜ አብዛኛ ሰዎች በሚሸከሙት የኃጢአት ምልክቶች አይመኩም፤ ንስሐ መግባትም እነዚያን ምልክቶች አያስወግድም። ክርስቶስ ሲመለስ እነዚህ ለውጦች በሙሉ ተፈጻሚነት ስለሚያገኙ እግዚአብሔር ይመስገን!) ክርስቶስን መውደድ ለእርሱ መኖሪያ ለእርሱ ክብር በተለየ ምልክት መታወቅ እንዴት የላቀ ነገር ነው።

የአሁኑም ዘመን አማኞች ማስታወስ የሚገባቸው ለክርስቶስ መከራን የተቀበለው መሪ ሊያካፍላቸው የሚችለው ነገር ያለው ሰው መሆኑን ነው። በጳውሎስ ዘመን የነበሩ የይሁዲነት አቀንቃኞች መከራን ስለ መቀበል ምንም አያውቁም ነበር። ምናልባት የዚያው ሃይማኖት ቅርንጫፍ ቡድን አባል በመሆናቸው እጅግ መጠነኛ በሆነ መንገድ ስደት ገጥሟቸው ይሆናል። ይህ ግን የክርስቶስ መከራ ተካፋይ ከመሆን ጋር ጨርሶ አይገናኝም (ፊልጵ. 3፡10)።

በምቹ ምሽግ ውስጥ ነዋሪ ሆኖ ከዓለም፥ ከሥጋና ከዲያብሎስ ጋር ስለሚደረግ ትግል አንዳችም ነገር ከማያውቅና ለክርስቶስ መታዘዙን የሚያሳይ ምልክት ከሌለው የሃይማኖት መሪ ተጠንቀቅ። ጳውሎስ ቁጭ ብሎ ትእዛዝ የሚሰጥ አዋጊ መኰንን አልነበረም፤ ወደ ግንባር በመሄድና በኃጢአት ላይ ጦርነት ከፍቶ በመተናነቅ የራሱን ብዙ መከራ የተቀበለ ሰው ነበር።

ጳውሎስ ወደ መልእክቱ ፍጻሜ ሲቀርብ ልክ በጀመረበት መንገድ ያጠቃልላል። ጸጋ! «የሙሴን ሕግ» ሳይሆን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ጸጋ!

ሁሉም ነገር በዚህ ተጠቃልሏልና ተጨማሪ ነገር መናገሩ አይጠቅምም።